# የማቴዎስ ወንጌል

*አስተዋፅኦ*

I. ስለ መሲሑ የቀረበ መግቢያ (1፥1—4፥11)
   (ሀ) ኢየሱስ ከአይሁድ ወገን መሆኑን የሚያመለክት የትውልድ ሐረግ (1፥1-17)
   (ለ) የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና ወደ ግብፅ መሰደዱ (1፥18—2፥23)
   (ሐ) የመሲሑ መንገድ ጠራጊ ነቢይ (3፥1-12)
   (መ) የመሲሑ መጠመቅ (3፥13-17)
   (ሠ) የመሲሑ መፈተን (4፥1-11)

II. የኢየሱስ መሲሓዊ አገልግሎት በገሊላ ውስጥና በአካባቢዋ (4፥12—18፥35)
   (ሀ) በዕጣሬ መልክ የቀረበ የመጀመሪያው የገሊላ አገልግሎቱ ዐጭር ገለጻ (4፥12-25)
   (ለ) ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ደቀ መዝሙርነት የተደረገ ገለጻ (5፥1—7፥29)
   (ሐ) ትረካ 1፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ታላላቅ ሥራዎች (8፥1—9፥38)
   (መ) ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዐዋጅ የተደረገ ገለጻ (10፥1-42)
   (ሠ) ትረካ 2፤ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት (11፥1—12፥50)
   (ረ) ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር የተደረገ ገለጻ (13፥1-58)
   (ሰ) ትረካ 3፥ በእግዚአብሔር መንግሥት የተከሠተ ችግር (14፥1—17፥27)
   (ሸ) የእግዚአብሔር መንግሥት አባል ስለ መሆን የተደረገ ገለጻ (18፥1-35)

III. ኢየሱስ በገሊላ/በጳርያና በኢየሩሳሌም የፈጸመው መሲሓዊ አገልግሎት ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱ (19፥1—26፥46)
   (ሀ) ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጕዞ (19፥1—20፥34)
   (ለ) ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ያሳለፈው የመጨረሻ ሳምንት (21፥1—26፥46)
      1. በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱና ቤተ መቅደሱን ማንጻቱ (21፥1-22)
      2. ከአይሁድ ጋር የነበረው ክርክር (21፥23—22፥46)
      3. የአይሁድ ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን መወገዛቸው (23፥1-39)
      4. ስለ ወደ ፊቱ የእግዚአብሔር መንግሥት በደብረ ዘይት ተራራ የተደረገ ገለጻ (24፥1—25፥46)
      5. ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት የተደረገ ሤራ (26፥1-16)
      6. የጌታ እራት (26፥17-30)
      7. ጌቴሴማኒ (26፥31-46)

IV. ኢየሱስ መያዙ፣ መከራ መቀበሉና በመስቀል ላይ መሞቱ (26፥47—27፥66)
   (ሀ) መያዙ (26፥47-56)
   (ለ) መከራ መቀበሉ (26፥57—27፥26)
   (ሐ) መሰቀሉ (27፥27-56)
   (መ) መቀበሩ (27፥57-66)

V. ትንሣኤ (28፥1-20)
   (ሀ) ለሴቶች የተገለጠ ክቡር ትንሣኤ (28፥1-10)
   (ለ) ሐሰተኛ ምስክሮች (28፥11-15)
   (ሐ) የተነሣው ጌታ የሰጠው ተልእኮ (28፥16-20)

**ጸሐፊው፤** *ማቴዎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ኢየሱስ፣ መሲሓዊው ንጉሥ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ60ዎቹ ዓ.ም.*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይህ ወንጌል በመጀመሪያ የአዲስ ኪዳንና የ"ክርስቶስ ... የሕያው እግዚአብሔር ልጅ" (16፥16) መግቢያ ሆኖ በሚገባ ተቀምጦአል። በወንጌሉ ውስጥ ጸሓፊው ማን እንደ ሆነ ባይገለጽም፣ ሁሉም የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንድ ቃል በሰጡት ምስክርነት መሠረት (በግምት ከ130 ዓ.ም. ጀምሮ)፣ ይህ ወንጌል የተጻፈው ከዐሥራ ሁለቱ የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ በሆነው በማቴዎስ ነው።

የማርቆስ ወንጌል ለሮማውያን (የማርቆስ ወንጌል መግቢያ ይመ)፣ የሉቃስ ወንጌል ደግሞ ለቴዎፍሎስና ለአሕዛብ አማኞች እንደ ተጻፈ ሁሉ (የሉቃስ ወንጌል መግቢያ ይመ)፥ የማቴዎስ ወንጌልም ለአይሁድ አማኞች ተጽፎአል። የዚህ ወንጌል አይሁዳዊ ዳራ የሚከተሉትን ጨምሮ በብዙ መንገድ ይታያል፤ (1) ኢየሱስ ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው መሲሕ መሆኑን ለማረጋገጥ በብሉይ ኪዳን መገለጥ፣ ትስፋና ትንቢት ላይ በመደገፉ፤ (2) የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ አመጣጥ ከአብርሃም በመጀመሩ (1፥1-17)፤ (3) ኢየሱስ "የዳዊት ልጅ" መሆኑን በተደጋጋሚ ማወጁ (1፥1፤ 9፥27፤ 12፥23፤ 15፥22፤ 20፥30-31፤ 21፥9:15፤ 22፥41-45)፤ (4) ከአክብሮት የተነሣ አይሁድ የእግዚአብሔርን ስም በቀጥታ ለመጥራት ባለመፈለጋቸው፣ እነርሱ የሚመርጡትን ስያሜ ለምሳሌ፣ "መንግሥተ ሰማይ" ("የእግዚአብሔር መንግሥት ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ስም ነው") የሚለውን መጠሪያ ሐረግ በመጠቀሙ፤ (5) ከሌሎቹ ወንጌሎች በተለየ ሁኔታ ያለምንም ተጨማሪ ማብራሪያ የአይሁድን ልማድ በመጥቀሱ።

ይሁን እንጂ ይህ ወንጌል ሙሉ በሙሉ ለአይሁድ ብቻ የተጻፈ አይደለም። የማቴዎስ ወንጌል ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ መልእክት፣ የወንጌልን ሁሉን ዐቀፍ እይታ በታማኝነት በማሳየት፣ የተጻፈው በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን ነው (ለምሳሌ 2፥1-12፤ 8፥11-12፤ 13፥38፤ 21፥43፤ 28፥18-20)።

የማቴዎስ ወንጌል ከየት ቦታና መቼ እንደ ተጻፈ በትክክል አይታወቅም። ይሁን እንጂ ማቴዎስ ከ70 ዓ.ም. ቀደም ብሎ በፓለስቲን ወይም በሶርያዋ አንጾኪያ ሳለ፥ ይህን ወንጌል መጻፉን የሚያመለክቱ አሳማኝ የሆኑ በቂ ምክንያቶች አሉ። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የማቴዎስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌሎች ውስጥ በመጀመሪያ መጻፉን ያምናሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ የቀዳሚነቱን ስፍራ ለማርቆስ ወንጌል ያደርጋሉ።

### ዐላማ

ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው በሚከተለው ምክንያት ነው፤ (1) ስለ ኢየሱስ ሕይወት የዐይን ምስክርነቱን ለአንባቢዎቹ ለመስጠት፣ (2) ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነና የብሉይ ኪዳን ነቢያት አስቀድመው የተናገሩለት ለረዥም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው መሲሕ መሆኑን ለአንባቢዎቹ አስረግጦ ለመግለጽ፣ (3) የእግዚአብሔር መንግሥት ቀደም ብሎ ባልተገለጸበት መንገድ በክርስቶስና በሥራው አማካይነት እንደሚገለጽ ለማሳየት ነው። ማቴዎስ አንባቢዎቹ የሚከተሉትን ሁኔታዎች እንዲያስተውሉ አጥብቆ ይፈልጋል፤ (1) እስራኤል በአብዛኛው ኢየሱስንና መንግሥቱን ተቃውመዋል፤ እንደ ፖለቲካ መሪ ሳይሆን መንፈሳዊ መሲሕ ሆኖ በመምጣቱ ሊያምኑበት አለመፈለጋቸውን፣ (2) ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ በመሆን ሊፈርድና አሕዛብን ሊገዛ በክብር የሚመጣው በዘመኑ መጨረሻ ላይ ብቻ መሆኑን እንዲገነዘቡ።

### ቅኝት

ማቴዎስ ኢየሱስን የእስራኤል ትንቢታዊ ተስፋ ፍጻሜ መሆኑን በማመልከት አቅርቦታል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የብሉይ ኪዳንን ትንቢት በሚከተለው ሁኔታ ፈጽሞአል፦ በልደቱ (1፥22-23)፣ በተወለደበት ስፍራ (2፥5-6)፣ ከግብፅ በመመለሱ (2፥15)፣ ናዝሬትን መኖሪያው በማድረጉ (2፥23)፣ መሲሓዊ መንገድ ጠራጊ የተላከለት በመሆኑ (3፥1-3)፣ የይፋ አገልግሎቱን በጀመረበት ስፍራ (4፥14-16)፣ በፈውስ አገልግሎቱ (8፥17)፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ በፈጸመው ሥራ (12፥17-21)፣ በምሳሌዎች በማስተማሩ (13፥34-35)፣ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱ (21፥4-5) እና ዐልፎ በመሰጠቱ (26፥50)።

ከምዕራፍ 5 እስከ 25 ያለው ክፍል አምስት የኢየሱስን ዋና ዋና ገለጻዎችና በመሲሕነቱ የሠራቸውን አምስት ታላላቅ ሥራዎች መዝግቦ ይዞአል። አምስቱ ዋና ዋና ገለጻዎች የሚከተሉት ናቸው፦ (1) የተራራው ስብከት (ምዕ 5-7)፣ (2) የእግዚአብሔር መንግሥት ተጓዥ ዐዋጅ ነጋሪዎች ለሆኑት የተሰጠ መመሪያ (ምዕ 10)፣ (3) ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የተሰጡ ምሳሌዎች (ምዕ 13)፣ (4) የእውነተኛ ደቀ መዛሙርት ባሕርይ (ምዕ 18) እና (5) ስለ ዘመን ፍጻሜ በደብረ ዘይት ተራራ የተደረገ ንግግር (ምዕ 24—25)። በዚህ ወንጌል ውስጥ ያሉት አምስቱ ዋና ዋና ትረካዎች የሚከተሉት ናቸው፦ (1) ኢየሱስ

የእግዚአብሔርን መንግሥት እውንነት የሚመሰክሩ ታላላቅ ሥራዎችንና ታምራትን ማድረጉ (ምዕ 8-9)፣ (2) ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሀልዎት በይበልጥ ማሳየቱ (ምዕ 11—12)፣ (3) የእግዚአብሔርን መንግሥት ሲታወጅ የተለያዩ ችግሮችን ማስነሣቱ (ምዕ 14—17)፣ (4) ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መጓዙ፣ ከመሞቱ በፊት ያለውን የመጨረሻ ሳምንት በዚያ ማሳለፉ (19፥1—26፥46)፣ (5) ኢየሱስ መያዙ፣ መከራ መቀበሉ፣ በመስቀል ላይ መሞቱና ከሙታን መነሣቱ (26፥47—28፥20)። የዚህ ወንጌል የመጨረሻ ሦስት ጥቅሶች፣ የኢየሱስን "ታላቅ ተልእኮ" ይዘው ይገኛሉ።

## ልዩ ገጽታ

የማቴዎስ ወንጌልን ልዩ የሚያደርጉት ሰባት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች ወንጌሎች ይልቅ አይሁዳዊነትን በይበልጥ የሚያንጸባርቅ ወንጌል ነው፤ (2) የኢየሱስን ትምህርት እንዲሁም የፈውስና ነጻ የማውጣት አገልግሎቱን ሥርዐታዊ በሆነ መልክ የያዘ መጽሐፍ ነው። ይህ በሁለተኛው ምእተ ዓመት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን አዳዲስ አማኞችን ለማስተማር በከፍተኛ ደረጃ እንድትጠቀምበት አድርጎአል። (3) አምስቱ ዋና ዋና ገለጻዎች በወንጌሎቹ ውስጥ ካሉት የኢየሱስ ትምህርቶች መካከል በጣም ሰፊ የሆኑ ስብስብ ሐሳቦችን የያዙ ናቸው፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) በተለይም በገሊላ የነበረውን አገልግሎቱን (ለ) ስለ ሥነ ፍጻሜ የተጻፈውን። (4) ይህ ወንጌል ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በይበልጥና በተደጋጋሚ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ዙሪያ የታዩ ሁኔታዎች የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ መሆናቸውን ልዩ በሆነ መልክ አቅርቦአል። (5) መንግሥተ ሰማይን/ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይህ ወንጌል እንደ ሌሎቹ ወንጌሎች ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ጠቅሶታል። (6) የማቴዎስ ወንጌል በሚከተሉት ላይ አጽንዖት ያደርጋል፤ (ሀ) በእግዚአብሔር መንግሥት የጽድቅ መለኪያዎች ላይ (ምዕ 5—7)፣ (ለ) የእግዚአብሔር መንግሥት በኀጢአት፣ በበሽታ፣ በአጋንንት፣ በሞት ላይም እንኳ አሁን ባለው ኀይል፣ (ሐ) በዘመኑ መጨረሻ ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደፊት በሚቀዳጀው የመጨረሻ ድል ላይ። (7) ቤተ ክርስቲያን የወደፊት የክርስቶስ አካል መሆኗን አስቀድሞ የተናገረ ወይም የጠቀሰ ይህ ወንጌል ብቻ ነው (16፥18፤ 18፥17)።

## የማቴዎስ ወንጌልን ማንበብ

ሙሉውን አዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የማቴዎስ ወንጌል ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአርባ አራት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1 ❑ 2 ❑ 3 ❑ 4 ❑ 5፥1-20 ❑ 5፥21-48 ❑ 6፥1-18 ❑ 6፥19—7፥6 ❑ 7፥7-29
❑ 8፥1-27 ❑ 8፥28—9፥17 ❑ 9፥18-38 ❑ 10፥1-23 ❑ 10፥24-42 ❑ 11 ❑ 12፥1-21
❑ 12፥22-50 ❑ 13፥1-23 ❑ 13፥24-43 ❑ 13፥44—14፥12 ❑ 14፥13-36 ❑ 15፥1-28
❑ 15፥29—16፥12 ❑ 16፥13—17፥13 ❑ 17፥14—18፥14 ❑ 18፥15-35 ❑ 19፥1-15
❑ 19፥16—20፥16 ❑ 20፥17-34 ❑ 21፥1-32 ❑ 21፥33—22፥14 ❑ 22፥15-46 ❑ 23
❑ 24፥1-35 ❑ 24፥36-51 ❑ 25፥1-30 ❑ 25፥31-46 ❑ 26፥1-30 ❑ 26፥31-56
❑ 26፥57-75 ❑ 27፥1-26 ❑ 27፥26-44 ❑ 27፥45-66 ❑ 28

*ማስታወሻ*

## የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ

*1፥1-17 ተጓ ምብ — ሉቃ 3፥23-38*
*1፥3-6 ተጓ ምብ — ሩት 4፥18-22*
*1፥7-11 ተጓ ምብ — 1ዜና 3፥10-17*

1 የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ የሆነው
የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ
የሚከተለው ነው፤
2አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤
ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፤
ያዕቆብ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤
3ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስ ኤስሮምን ወለደ፤
ኤስሮምም አራምን ወለደ፤
4አራም አሚናዳብን ወለደ፤
አሚናዳብ ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶን ሰልሞንን ወለደ፤
5ሰልሞን ቦዔዝን ከረዓብ ወለደ፤
ቦዔዝ ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤
ኢዮቤድ እሴይን ወለደ፤
6እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።
ዳዊት የኦርዮ ሚስት ከነበረችው
ሰሎሞንን ወለደ፤
7ሰሎሞን ሮብዓምን ወለደ፤
ሮብዓም አቢያን ወለደ፤
አቢያም አሣፍን ወለደ፤
8አሣፍ ኢዮሣፍጥን ወለደ፤
ኢዮሣፍጥ ኢዮሆራምን ወለደ፤
ኢዮሆራም ዖዝያንን ወለደ፤
9ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ፤
ኢዮአታም አካዝን ወለደ፤
አካዝ ሕዝቅያስን ወለደ፤
10ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ፤
ምናሴ አሞንን ወለደ፤
አሞንም ኢዮስያስን ወለደ፤
11ኢዮስያስ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ፣
ኢኮንያንንና[ሀ] ወንድሞቹን ወለደ፤
12ከባቢሎን ምርኮ በኋላ፣
ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤
ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤
13ዘሩባቤል አብዩድን ወለደ፤
አብዩድ ኤልያቄምን ወለደ፤
ኤልያቄም አዛርን ወለደ፤
14አዛር ሳዶቅን ወለደ፤
ሳዶቅ አኪምን ወለደ፤
አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤
15ኤልዩድ አልዓዛርን ወለደ፤
አልዓዛር ማታንን ወለደ፤
ማታን ያዕቆብን ወለደ፤
16ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤
ዮሴፍም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት
የማርያም እጮኛ ነበር።
17እንግዲህ ከአብርሃም እስከ ዳዊት
ዐሥራ አራት ትውልድ፣ ከዳዊት እስከ
ባቢሎን ምርኮ ዐሥራ አራት ትውልድ፣
ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ[ለ] ልደት
ዐሥራ አራት ትውልድ ይሆናል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

18የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ታሪክ
እንዲህ ነው፤ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ
ታጭታ ሳይገናኙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ
ተገኘች። 19እጮኛዋ ዮሴፍ ጻድቅ ሰው ስለ
ነበርና ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት
ስላልፈለገ በስውር ሊተዋት ወሰነ።
20በዚህ ሐሳብ ሳለ፣ የእግዚአብሔር መልአክ

1፥1 ዘፍ22፥18፤ 2ሳሙ7፥12-16፤ ኢሳ9፥6:7፤ 11፥1፤ ኤር23፥5:6፤ ማቴ9፥27፤ ሉቃ1፥32:69፤ ገላ3፥16፤ ራእ22፥16
1፥2 ዘፍ21፥3:12፤ 25፥26፤ 29፥35፤ 49፥10
1፥3 ዘፍ38፥27-30
1፥5 ዕብ11፥31
1፥6 1ሳሙ16፥1፤ 17፥12፤ 2ሳሙ12፥24
1፥10 2ነገ20፥21
1፥11 2ነገ24፥14-16፤ ኤር27፥20፤ 40፥1፤ ዳን1፥1:2
1፥12 1ዜና3፥17:19፤ ዕዝ3፥2
1፥16 ማቴ27፥17፤ ሉቃ1፥27
1፥18 ሉቃ1፥35
1፥19 ዘዳ24፥1
1፥20 ማቴ27፥19፤ ሐሥ5፥19

[ሀ] 1፥11 ዮአኪን ማለት ነው፤ ቍ 12 ይመ
[ለ] 1፥17 ወይም መሲሕ «ክርስቶስ» (በግሪክ) እና «መሲሕ» (በእብራይስጥ) ሁለቱም «የተቀባ» የሚል ትርጉም አላቸው

**1፥1 የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ፤** የማቴዎስ ወንጌል በአይሁድ ልማድ መሠረት በአባት ዘር ማለትም በዮሴፍ ዘር በኩል የኢየሱስ ክርስቶስን የትውልድ ሐረግ ለማመልከት አባታዊ የትውልድ ሐረግን በመዘርዘር ይጀምራል (ቍ 16)። ዮሴፍ የኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋ አባቱ ባይሆንም (ቍ 20)፣ በሕግ መሠረት አባቱ ነበር። መሲሑ ከአብርሃምና (ዘፍ 12፥3፤ 22፥18፤ ገላ 3፥16) ከዳዊት ዘር (2ሳሙ 7፥12-19፤ ኤር 23፥5) እንደሚገኝ እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ ስለ ተናገረ፣ ኢየሱስ የመሲሑን የዘር ሐረግ የሚያሟላ መሆኑን ለአይሁድ ለማሳየት ሲል፤ ማቴዎስ ወደ ኋላ ተመልሶ የኢየሱስን ሕጋዊ የዘር ሐረግ ከእነዚህ ሁለት ሰዎች ዘር ጋር ያያይዘዋል።

**1፥1 ክርስቶስ፤** ክርስቶስ የሚለው የግሪክ ቃል «የተቀባ» ማለት ነው፤ ይህም ቃል በዕብራይስጥ «መሲሕ» ለሚለው ቃል አቻ ትርጉም ነው (ዳን 9፥25-26)። (1) ማቴዎስ ከመጀመሪያ ጀምሮ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተቀባ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ መሆኑን በአጽንዖት ተናግሮአል (ከኢሳ 61፥1፤ ከሉቃ 4፥18፤ ከዮሐ 3፥34፤ ከሐሥ 10፥38 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) ሰውቀትንና እውነትን ለማምጣት ነቢይ (ዘዳ 18፥15)፤ መሥዋዕትን ለማቅረብና በደልን ለማስወገድ ካህን (መዝ 110፥4፤ ዕብ 10፥10-14)፣ ለመግዛት እንዲሁም ለመምራትና የጽድቅን መንግሥት ለመመሥረት ንጉሥ ሆኖ (ዘካ 9፥9) ተቀብቶ ነበር።

**1፥1 የዳዊት ልጅ፤** (1) ከዳዊት ቤት የሆነውን የዮሴፍን የትውልድ ሐረግ በመጥቀስ፣ ኢየሱስ ሕጋዊ የዳዊት ዘር መሆኑን ማቴዎስ በእርግጠኝነት ይገልጻል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ቢጸነስም፤ ሕጋዊ የዳዊት ልጅ በመሆን የዮሴፍ ልጅ ተብሎ ተመዝግቦአል። (2) ሉቃስ ባቀረበው የትውልድ ሐረግ ደግሞ በማርያም (እርሷም ደግሞ ከዳዊት ዘር ነበረችና) ወገኖች ማለትም በወንዶቹ በኩል ያለው የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ተጠቅሶአል (ሉቃ 3፥23 እና የሚከተሉትን ቍጥሮች ይመ)። ከዚህም በላይ ሉቃስ ኢየሱስ የማርያም ደምና ሥጋ ማለትም ልጅ መሆኑንና ከዚህም የተነሣ ከእኛ እንደ አንዱ መሆኑን (ከሮሜ 1፥3 ጋር ያነጻጽሩ) በአጽንዖት ተናግሮአል። ስለዚህ የወንጌል ጸሐፊዎች ሁሉ ኢየሱስ የመሲሕነት ሕጋዊና ትውልዳዊ መብት ያለው መሆኑን አረጋግጠዋል።

**1፥16 የኢየሱስ ... የማርያም፤** የኢየሱስ ከድንግል መወለድ በትውልድ ሐረጉ ዝርዝር ውስጥ ተጠብቆአል። «ወለደ» የሚለው ቃል በስሞች ሁሉ ላይ እስከ ዮሴፍ ስም ድረስ ያለ መሆኑንና በኋላ ግን ሐሳቡ የተለወጠ መሆኑን ልብ ይበሉ። «ዮሴፍ ኢየሱስን ወለደ» ተብሎ አልተጻፈም፤ የተጻፈው ግን «ዮሴፍ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት የማርያም እጮኛ ነበር» ተብሎ ነው (ማቴ 1፥23 እና ማብ ይመ)።

በሕልም ተገለጠለት፤ እንዲህም አለው፤
"የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፤ እጮኛህን
ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፤
የፀነሰችው በመንፈስ ቅዱስ ነውና። [21]ወንድ
ሉቃ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየሱስ[a] ብለህ
1፥76- ትጠራዋለህ፤ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው
79 ያድናቸዋልና።"
[22]ጌታ በነቢዩ እንዲህ ሲል የተናገረው
ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ፤ [23]"እነሆ፤ ድንግል
ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤
ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤" ትርጓሜውም፣
"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው።
[24]ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃ፤ ከዚያም
የጌታ መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ
ቤቱ ወሰዳት።[m] [25]ይሁን እንጂ የበኵር
ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤
የተወለደውንም ሕፃን፣ "ኢየሱስ" ብሎ
ጠራው።

1፥21 መዝ130፥8፤ ሉቃ1፥31፤ 2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ ሐሥ5፥31፤ ሮሜ11፥14፤ ቲቶ2፥14
1፥22 ማቴ2፥15፡17፡23፤ 4፥14፤ 8፥17፤ 12፥17፤ 21፥4፤ 26፥54፡56፤ 27፥9፤ ሉቃ4፥21፤ 21፥22፤ 24፥44፤ ዮሐ13፥18፤ 19፥24፡28፡36
1፥23 ኢሳ7፥14፤ 8፥8፡10
1፥24 ሐሥ5፥19
1፥25 ቍ21፤ ሉቃ1፥31

## የጠቢባን ከምሥራቅ መምጣት

2 በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተ
ልሔም ይሁዳ ከተወለደ በኋላ ጠቢባን
ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጥ ተው፣
[2]"የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?

2፥1 ሉቃ1፥5፤ 2፥4-7 2፥2 ዘኍ24፥17፤ ኤር23፥5፤ ማቴ27፥11፤ ማር15፥2፤ ሉቃ23፥38፤ ዮሐ1፥49፤ 18፥33-37

*[a] 1፥21 ኢየሱስ በግሪኩ ሲሆን በዕብራይስጡ ኢያሱ ነው፤ ትርጕ ሙም እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው*

*[m] 1፥24 ወደ ቤቱ ወሰዳት የሚለው የግሪኩ ቃል ሚስቱ እንድትሆን ወሰዳት ይለዋል*

**1፥21 ኢየሱስ፤** ኢየሱስ የሚለው ቃል "የሹዋ" (ኢያሱ) ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል አቻ የግሪክ መጠሪያ ስም ሲሆን፣ ትርጓሜውም "እግዚአብሔር ያድናል" (ኢሱ 1፥1 እና ማብ ይመ) ማለት ነው። ይህም የማርያም ልጅ ወደፊት የሚያደርገውንና የወንጌልን የመጀመሪያ የተስፋ ቃል የሚገልጥ ነው። ኢየሱስ አዳኝ እንደ መሆኑ መጠን "ሕዝቡን ከኀጢ አታቸው ያድናቸዋል"። ኀጢአት ነፍስንና ሕይወትን የሚያጠፋ የሰው ልጅ ሁሉ ትልቅ ጠላት ነው። ወደ ኢየሱስ በንስሓ የሚመለሱ ሁሉ ስርየትን በሚያስገኘው በኢየሱስ ሞትና በሚቀድሰው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣ ከበደልና ከኀጢአት ባርነት ነጻ ይወጣሉ (ዮሐ 8፥31-36፤ ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 6፤ 8፥1-16 ይመ)።

**1፥23 ድንግል ... ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤** ማቴዎስና ሉቃስ ሁለቱም በመስማማት ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ መፀነሱንና (ቍ 18፤ ሉቃ 1፥34-35) ያለ ሥጋ አባት ድንግል ከሆነች እናት መወለዱን በማያሻማ ሁኔታ ጽፈዋል። ኢየሱስ ከድንግል መወለዱን የሚያበሥረውን አስተምህሮ ሊበራል የሥነ መለኮት ምሁራን ለዘመናት እንደ ተቃወሙት ነው። ይሁን እንጂ ነቢዩ ኢሳይያስ ስሙ፣ "አማኑኤል" የሚባል ልጅ ከድንግል እንደሚወለድ አስቀድሞ ትንቢት መናገሩ የማይካድ ነው፤ አማኑኤል የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ስያሜ ሲሆን፣ ትርጓሜው፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" (ኢሳ 7፥14) ማለት ነው። ይህ ትንቢት የተነገረው ክርስቶስ ከመወለዱ ከ700 ዓመት በፊት ነበር።

(1) በማቴ 1፥23 ላይ የተጠቀሰው "ድንግል" የሚለው ቃል በሰባ ሊቃናት ትርጕም በኢሳይያስ 7፥14 ላይ "ፓርቴኖስ" ለሚለው የግሪክ ቃል ትክክለኛ ትርጕም ነው። በኢሳይያስ መጽሐፍ በዕብራይስጡ ድንግል (አልማህ) የሚለው ቃል የተጠቀሰው ለጋብቻ የሚደረስበትን የድንግልና ዕድሜ የሚያመለክት ሲሆን፣ ቃሉ በሌላው የብሉይ ኪዳን ክፍል ይህንኑ ድንግልና ከማመልከት ውጭ በሌላ ፅንሰ ሐሳብ አልተጠቀሰም (ከዘፍ 24፥43፤ ከማሕ 1፥3 እና ከ6፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ኢሳይያስ በብሉይ ኪዳን፣ ማቴዎስና ሉቃስ ደግሞ በአዲስ ኪዳን ድንግልናን የገለጹት ከኢየሱስ እናት ከማርያም ጋር በማያያዝ ነው (ኢሳ 7፥14 እና ማብ ይመ)።

(2) ከድንግል የመወለድ ጉዳይ ከልክ በላይ ተጋንኖ ሊነገር አይችልም። ቤዛችን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ለኀጢአታችን ዋጋ ከፍሎ ድነትን ለማምጣት ብቁ ይሆን ዘንድ አንድ አካል ሆኖ ኀጢአት አልባ፣ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ መሆን ነበረበት (ዕብ 7፥25-26)። ከድንግል መወለድ የሚከተሉትን ሦስት መስፈርቶች ያሟላል፤ (ሀ) ኢየሱስ ሰው ሆኖ ለመወለድ ከሴት መወለድ ነበረበት፤ (ለ) ኀጢአት አልባ ሆኖ ለመወለድ በመንፈስ ቅዱስ መፀነስ ነበረበት (1፥20 ይመ፤ ከዕብ 4፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ሐ) መለኮት ሊሆን የሚችልበት ብቸኛ መንገድ እግዚአብሔር አብ አባቱ ከሆነ ብቻ ነበር። ከዚህ የተነሣ የተፀነሰውም ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን፣ ዲበ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ነበር፤ "ስለዚህ የሚወለደው ቅዱሱ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሉቃ 1፥35። እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ለእኛ የገለጠው ሁለት ባሕርያት ያሉትን አንድ መለኮታዊ አካል ይዞ ነው፤ እነርሱም መለኮታዊ ባሕርይና ኀጢአት አልባ የሆነ ሰብአዊ ባሕርይ ናቸው።

(3) ሰው ሆኖ በመኖሩና መከራን በመቀበሉ ኢየሱስ በድካማችን ይራራልናል (ዕብ 4፥15-16)። የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ እንደ መሆኑ መጠን፣ ከኀጢአት እስራትና ከሰይጣን ኀይል እኛን ለመታደግ ሥልጣን አለው (ሐሥ 26፥18፤ ቈላ 2፥15፤ ዕብ 2፥14፤ 7፥25)። ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው በመሆኑ፣ ለሰው ሁሉ ኀጢአት መሥዋዕት ሆኖ ለመቅረብና ወደ እግዚአብሔር ለሚመጡ ሁሉ ሊቀ ካህን ሆኖ ለመማለድ የሚያስችል ብቃት አለው (ዕብ 2፥9-18፤ 5፥1-9፤ 7፥24-28፤ 10፥4-12)።

**1፥25 እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤** "እስክትወልድ ድረስ" የሚለው ሐረግ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ ማርያምና ዮሴፍ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ መልኩ ያለውን ወግ ፈጽመው እንደ ነበር ያመለክታል። በተጨማሪም ኢየሱስ ወንድሞችና እኅቶች እንደ ነበሩት ተነግሯል (12፥46-47፤ ማር 3፥31-32፤ 6፥3፤ ሉቃ 8፥19-20)።

**2፥1 ጠቢባን፤** እነዚህ ሰዎች አሁን ኢራን ተብሎ ከሚጠራው አገር የመጡ ከተማረው የሃይማኖት ክፍል የተገኙ ሳይሆኑ አይቀሩም። የሥለጠኑበትም ሙያ የኮከብ ቈጠራ፣ ሕክምናና የተፈጥሮ ሳይንስ ነበር። እነዚህ ጠቢባን ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት የኢየሱስ ዕድሜ በ40 ቀንና (ከሉቃ 2፥22 ጋር ያነጻጽሩ) በሁለት ዓመት (ከቍ 16 ጋር ያነጻጽሩ) መካከል በነበረበት ጊዜ ነው። የዚህ ታሪክ ፋይዳ የሚከተለው ነው፤ (1) ኢየሱስ ከሰው ሁሉ የንጉሥነት ክብር ሊሰጠው ይገባል፤ (2) አሕዛብም ሆኑ አይሁድ በእግዚአብሔር የቤዛነት ዕቅድ ውስጥ ተካትተዋል (ከ8፥11፤ ከ28፥19፤ ከሮሜ 10፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

በምሥራቅ[a] ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት
መጥተናልና" ሲሉ ጠየቁ።
3ንጉሡ ሄሮድስ ይህን በሰማ ጊዜ ታወከ፤
እንዲሁም መላዪቱ ኢየሩሳሌም አብራ
ታወከች። 4እርሱም የካህናት አለቆችንና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን በሙሉ
ሰብስቦ ክርስቶስ[b] የት እንደሚወለድ
ጠየቃቸው። 5እነርሱም፣ "በይሁዳ ቤተ
ልሔም፤ ነቢዩ እንዲህ ብሎ ጽፎአልና
አሉ፤

6" 'በይሁዳ ምድር የምትገኚው አንቺ ቤተ
ልሔም፣
ከሊሎቹ የይሁዳ ገገሮች በምንም
አታንሽም፤
የሕዝቤ የእስራኤል ጠባቂ የሚሆን፣
ከአንቺ ይወጣልና።' "

7ከዚያም ሄሮድስ ጠቢባኑን በምስጢር
አስጠርቶ በማነጋገር ኮከቡ የታየበትን
ትክክለኛ ጊዜ ተረዳ። 8ጠቢባኑንም ወደ ቤተ
ልሔም ልኮ፣ "ሂዱና ሕፃኑን ፈልጉ፤ እኔም
ደግሞ ሄጄ እንድሰግድለት፣ እንዳገኛችሁት
ወደ እኔ ተመልሳችሁ የት እንዳለ ንገሩኝ"
አላቸው።
9ጠቢባኑ ንጉሡ ያለውን ከሰሙ በኋላ
ጕዞአቸውን ቀጠሉ። ይህም በምሥራቅ[c]
ያዩት ኮከብ እየመራቸው ሕፃኑ እስካለበት
ድረስ ወሰዳቸው። 10ኮከቡንም ሲያዩ
ከመጠን በላይ ተደሰቱ። 11ወደ ቤትም በገቡ
ጊዜ ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩ፤
ተንበርክከውም ሰገዱለት። ሣጥኖቻቸውን
ከፍተው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤም አቀረቡለት።
12እግዚአብሔርም ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ
በሕልም ባስጠነቀቃቸው መሠረት፣ መንገድ
አሳብረው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

## ወደ ግብፅ ሽሽት

13ጠቢባኑ ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ
ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣ "ተነሥ!
የምትመለስበትን ጊዜ እስክስታውቅህ ድረስ
ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ በመሸሽ
በዚያ ቈይ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው
ይሻልና" አለው።
14ስለዚህም ዮሴፍ ተነሣ፤ ሕፃኑንና
እናቱን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ሄደ፤
15በዚያም ሄሮድስ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ
ኖረ። በዚህም፣ "ልጄን ከግብፅ ምድር
ጠራሁት" በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ
እንደበት የተናገረው ቃል ተፈጸመ።
16ሄሮድስ ጠቢባኑ እንዳታለሉት በተረዳ
ጊዜ በጣም ተናደደ፤ ከጠቢባኑ በተነገረው
መሠረት ዕድሜያቸው ሁለት ዓመትና
ከዚያም በታች የሆኑትን የቤተ ልሔምንና
የአካባቢዋን መንደሮች ወንድ ልጆች ሁሉ
ልኮ አስገደለ። 17በዚህም በነቢዩ በኤርምያስ
እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤
18"የልቅሶና የታላቅ ዋይታ ድምጽ፣
በራማ ተሰማ፤
ራሔል ስለ ልጆቿ አለቀሰች፤
መጽናናትም አልቻለችም፤
ልጆቿ ሁሉ አልቀዋልና።"

## ከግብፅ ወደ ናዝሬት

19ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር
መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣
20"ተነሣ፤ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ
እስራኤል ምድር ተመለስ፤ ሕፃኑን
ለመግደል የሚሹት ሞተዋልና" አለው።

2፥5 ዮሐ7፥42
2፥6 2ሳሙ5፥2፤ ሚክ5፥2
2፥11 መዝ72፥10፤ ኢሳ60፥3
2፥12 ቍ13፥19፥22፤ ማቴ27፥19፤ ዕብ11፥7
2፥13 ቍ12፥19፥22፤ ማቴ27፥19፤ ሐሥ5፥19፤ ራእ12፥4
2፥15 ቍ17፥23፤ ዘፀ4፥22፥23፤ ሆሴ11፥1፤ ማቴ1፥22
2፥17 ቍ15፥23፤ ማቴ1፥22
2፥18 ዘፍ35፥19፤ ኤር31፥15
2፥19 ቍ12፥13፥22፤ ማቴ27፥19፤ ሐሥ5፥19
2፥20 ዘፀ4፥19

[a]2፥2 ወይም ኮከቡ ሲነሣ አይተን
[b]2፥4 ወይም መሲሕ
[c]2፥9 ወይም ሲነሣ አይተው

---

**2፥4 የካህናት አለቆችንና የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን፤** የካህናት አለቆች አምልኮን በተመለከተ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ሲሆኑ፤ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ደግሞ ከምርኮ ዘመን በኋላ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቅጅ የሚገለብጡ ነበሩ። የብሉይ ኪዳንን ሕግ እንዲያስተምሩና ተግባራዊነቱን እንዲያሳዩ የሥልጣኑ ሲሆኑ፤ "የኦሪት ሕግ ዐዋቂ" ተብለውም ይጠራሉ (ማቴ 22፥35)። የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና የካህናት አለቆች በአንድነት የአይሁድ ሸንጎ ወይም የአይሁድ ምክር ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት አባላት ናቸው። ይህ አካል በአይሁድ የሕዝብና የሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በሚሾሙ 70 ወይም 71 ወንዶች የተዋቀረ ሲሆን፣ በሮማውያን ገዦች የተወሰነ ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። **2፥13 ወደ ግብፅ በመሸሽ፤** ሄሮድስ ኢየሱስን ለመግደል ያደረገው ሙከራና እግዚአብሔር ልጁን ለመጠበቅ የተጠቀመበት መንገድ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራትና ለመጠበቅ ስለሚጠቀምበት ዘዴ አያሌ እውነቶችን ይገልጣል፤ (፩) እግዚአብሔር ዮሴፍንና ማርያምን እንዲሁም ልጃቸውን ያለ እነርሱ ትብብር አልጠበቃቸውም (ቍ13፥ 19-20፥22)። የእግዚአብሔርን ጥበቃ ለማግኘት የእግዚአብሔርን ምሪት ተቀብሎ መታዘዝ ያስፈልጋል፤ በዚህ ታሪክ ውስጥ የታየውም መታዘዝ ከአገር መሸሽ ነበር (ቍ 14)።

(2) እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ሲል ፈጽሞ ልናስተውላቸው የማንችል እጅግ ከባድ የሆኑ ፈተናዎች በሕይወታችን ላይ እንዲደርሱ ይፈቅዳል (በገጽ 744 ላይ፣ *"የጻድቃን መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። እንደ እውነቱ ከሆነ ክርስቶስ ሕይወትን የጀመረው በሌላ አገር ስደተኛና መጻተኛ በመሆን ነበር (ቍ 14-15)። ውሱን በሆነው እንደ እኛ መረዳት ከሆነ፣ እግዚአብሔር በፍጥነት ሄሮድስን በማስወገድ ወደ ግብፅ የተደረገውን ሽሽትና ከዚህ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መልኩ የደረሱትን መከራዎች ሁሉ ማስቀረቱ ቀላል በሆነ ነበር።

(3) አንድ የተወሰነ መከራ ካታለፈ በኋላ እንኳ ሌሎችን ችግሮች የመጋፈጥ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል (ቍ 19-23)። ጠላት ዲያብሎስ ለጌታ ታማኝ በሆኑት ላይ የሚሰነዝረውን ጥቃት ስለማያቆም፣ የእግዚአብሔር ጥበቃና እንክብካቤ ምንጊዜም ያስፈልጋል (ኤፌ 6፥10-18፤ 1ጴጥ 5፥8 ይመ፤ በገጽ 100 ላይ፣ *"መግቦተ እግዚአብሔር"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።
**2፥16 ወንድ ልጆች ሁሉ … አስገደለ፤** ቤተ ልሔምና አካባቢው ይህን ያህል ሰፊ አልነበረም፤ የነዋሪውም ብዛት ከአንድ ሺህ እስከ ሁለት ሺህ ባለው ቍጥር መካከል ቢሆን ነው፤ በዚህም መሠረት የተገደሉት ወንድ ሕጻናት ቍጥር በዘልማድ ተጋንኖ እንደሚነገረው ላይሆን ይችላል።

[21]ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን
በመያዝ ወደ እስራኤል ምድር ተመለሰ፤
[22]ነገር ግን አርኬላዎስ በአባቱ በሄሮድስ
ቦታ በይሁዳ መንግሥት በሰማ ጊዜ ወደዚያ
መሄድ ፈራ። ጌታ በሕልም ስላስጠነቀቀው፣
ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ፤ [23]ናዝሬት
ወደምትባል ከተማም ሄዶ መኖር ጀመረ።
በዚህም በነቢያት፣ "ናዝራዊ ይባላል"
ተብሎ የተነገረው ትንቢት ተፈጸመ።

## የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

*3፥1-12 ተጓ ምብ — ማር 1፥3-8፤ ሉቃ 3፥2-17*

**3** በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይ
ሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ።
[2]ስብከቱም፣ "መንግሥተ ሰማያት
ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" የሚል ነበር። [3]በነቢዩ
በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረለት
እርሱ ነው፤

"በምድረ በዳ፣
'የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤
ጎዳናውንም አስተካክሉ' እያለ
የሚጮህ ድምፅ።"
[4]የዮሐንስ ልብስ የግመል ጠጕር ሲሆን፣
ወገቡንም በጠፍር ይታጠቅ ነበር። ምግቡም
አንበጣና የበረሃ ማር ነበር። [5]ከኢየሩሳሌም፣
ከመላው ይሁዳና በዮርዳኖስ ዙሪያ ካለው
አገር ሁሉ ሰዎች ወደ ዮሐንስ ይጐርፉ፣
[6]ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ
ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር።
[7]ብዙ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደሚ
ያጠምቅበት ስፍራ ሲመጡ ባየ ጊዜ እንዲህ
አላቸው፤ "እናንተ የእፉኝት ልጆች! ለመሆኑ
ከሚመጣው ቍጣ እንድታመልጡ ማን
መከራችሁ [8]ለንስሓ የሚገባ ፍሬ አፍሩ፤

2፥22 ቍ 12:13:19፤ ማቴ 27፥19፤ ሉቃ 2፥39
2፥23 ቍ 15:17፤ ማቴ 1፥22፤ ማር 1፥9:24፤ 6፥1፤ ሉቃ 1፥26፤ 2፥39:51፤ 4፥16:23፤ ዮሐ 1፥45:46
3፥1 ቍ 13:14፤ ማቴ 9፥14፤ 11፥2-14፤ 14፥1-12፤ ሉቃ 1፥13:57-66፤ 3፥2-19፤ ሐሥ 19፥3:4
3፥2 ዳን 7፥14፤ ማቴ 4፥17፤ 6፥10፤ 7፥21፤ 25፥34፤ ሉቃ 11፥20፤ 17፥20:21፤ 19፥11፤ 21፥31፤ ዮሐ 3፥3:5፤

3፥2 ሐሥ 1፥3:6 3፥3 ኢሳ 40፥3፤ ሚል 3፥1፤ ሉቃ 1፥76፤ ዮሐ 1፥23 3፥4 ዘሌ 11፥22፤ 2ነገ 1፥8፤ ማቴ 3፥1 3፥6 ቍ 11፤ ማር 1፥4 3፥7 ማቴ 12፥34፤ 23፥33፤ ሮሜ 1፥18
3፥8 ሐሥ 26፥20

**2፥22 በሕልም ስላስጠነቀቀው፤** ከሁለቱ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያዎች (ቍ 12:22)፥ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን እንዴት እንደሚጠብቃቸው፣ የክፉዎችንም ዕቅድ እንዴት አድርጎ በዐዱር ማስቀረት እንደሚችልና ታማኞቹንም ሊጐዷቸው ከሚፈልጉ ሰዎች እጅም እንዴት እንደሚታደጋቸው እንማራለን።

**3፥2 ንስሓ ግቡ፤** ንስሓ የመግባት መሠረታዊ ትርጕም (በግሪክ "ሜታኖ") "መመለስ" ማለት ነው። ይኸውም ከክፉ መንገድ ዘወር ብሎ ወደ ክርስቶስ መመለስ ማለት ሲሆን፣ በክርስቶስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው (ዮሐ 14፥1:6፤ ሐሥ 8፥22፤ 26፥18፤ 1ጴጥ 2፥25)።

(1) ከኃጢአት ዘወር ማለትና ክርስቶስን በድነት ለመቀበል መወሰን፣ ክርስቶስን ከኃጢአት ቅጣት የሚታደግ አዳኝ አድርጎ መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ የሕይወት ጌታ አድርጎ መቀበልንም ያካትታል። ስለዚህ ንስሓ መግባት አንዱ ጌታ በሌላው ጌታ መለወጡን ያሳያል፥ ይኸውም ከሰይጣን ተገዥነት ተላቆ (ኤፌ 2፥2) ለክርስቶስና ለቃሉ (ሐሥ 26፥18) ተገዥ መሆን ማለት ነው።

(2) ንስሓ ኃጢአተኞች ወንጌልን ሲሰሙና ሲያምኑ በሚያገኛቸው ጸጋ የሚወስኑት ነጻ ውሳኔ ነው (ሐሥ 11፥21 ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፥ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) ንስሓ መግባትን በተመለከተ ክርስቶስ ከሚጠይቀው አንጻር አዳኝ አድርጎ ክርስቶስን በመቀበል "መታመን ብቻ" ለድነት ለማያበቃው እምነት በቂ አይደለም። ኃጢአትን እርግፍ አድርጎ ከመተው ውጭ ለድነት የሚያበቃውን እምነት መተርጐም ማለት የቤዛነትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጕም በአደገኛ ሁኔታ ማዛባት ነው። ንስሓ መግባትን የሚያካትት እምነት ምንጊዜም ለድነት ያበቃል (ከማር 1፥15፥ ከሉቃ 13፥3:5፤ ከሐሥ 2፥38፤ 3፥19፥ 11፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

(4) ንስሓ የብሉይ ኪዳን ነቢያት (ኤር 7፥3፤ ሕዝ 18፥30፥ ኢል 2፥12-14፤ ሚል 3፥7)፣ የመጥምቁ ዮሐንስ (ማቴ 3፥2)፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 4፥17፤ 18፥3፤ ሉቃ 5፥32) እና የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች (ሐሥ 2፥38፤ 8፥22፤ 11፥18፤ 2ጴጥ 3፥9) መሠረታዊ መልእክት ነው። የንስሓ ስብከት ከወንጌል መልእክት ጋር ምንጊዜም የተሳሰረ ነው (ሉቃ 24፥47)።

**3፥7 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን፤** በአይሁድ እምነት ውስጥ ሁለቱ ዐበይት የሃይማኖት ቡድኖች ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ።

(1) ፈሪሳውያን የሚባሉት የሃይማኖት ቡድኖች በአጠቃላይ እነርሱ ለብሉይ ኪዳን የሚሰጡትን የግል ትርጓሜ እንዳለ የሚቀበሉ ናቸው። እነዚህ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሕግ ቃል በቃል በመከተልና እነርሱ ለዚያ ሕግ በሚሰጡት ትርጓሜ በማመን ድነት እንደሚገኝ በአጽንዖት ይናገራሉ። የሚመጣው መሲሕ እስራኤልን በመታደግ አሕዛብን የሚገዛና ሕዝቦችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሕግ እንዲገዙ በኀይል የሚያስገድድ ምድራዊ ገዥ እንደሚሆን ያስቡ ነበር። ሃይማኖታቸው ውጫዊ ቅርጽ ያለው ከመሆን በቀር ልባዊ የሆነ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለበት ውስጣዊ ለውጥ አይታይበትም ነበር (23፥25)፥ ውስጣዊ ባዶነታቸውንም ለመረዳት አልፈለጉም። ብዙውን ጊዜ ሃይማኖት የልብና የመንፈስ ጕዳይ እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትእዛዞች እንደ ሕግ ለታይታ ያህል መጠበቅ ብቻ እንዳይደለ የሚያስተምረውን ኢየሱስንና መልእክቶቹንም ይቃወማሉ (ከ9፥14፥ ከ23፥2-4፥ ከሉቃ 18፥9-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ሰዱቃውያን በዚህ ዘመን የነበሩ ሊበራል የሥነ መለኮት ምሁራንና ዲበ ተፈጥሮአዊ የሆኑ ታምራትን የማይቀበሉ የሃይማኖት ቡድኖች ናቸው። የእግዚአብሔርን ሕግ አጥብቀው የሚከተሉ ይምሰሉ እንጂ፣ አብዛኛውን የሕጉን ትምህርት አይቀበሉም። የትንሣኤን፣ የመላእክትን፣ የታምራትን፣ የኢምንምግባራዊነትንና ስለሚመጣው ፍርድ የሚሰጠውን አስተምህሮ ይቃወማሉ። ሕይወታቸው ግብረገባዊ ልቅነትና ዓለማዊነት የሚታይበት ሕይወት ነው። ከዚህም በላይ የኢየሱስ ክርስቶስ አሳዳጆች ነበሩ (16፥1-4)።

**3፥8 ለንስሓ የሚገባ ፍሬ፤** እውነተኛ ንስሓ የጽድቅን ፍሬ ከማሳየት ጋር የተያያዘ ነው (ከ23፥23፤ ከሉቃ 3፥10-14፤ ከሐሥ 26፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። ለድነት የሚያበቃ እውነተኛ እምነትና መለወጥ ኃጢአትን በሚተዉና መንፈሳዊ ፍሬን በሚያፈሩ ሰዎች ሕይወት ይገለጣሉ (ዮሐ 15፥16 እና ማብ ይመ)። በክርስቶስ እናምናለን፣ የእግዚአብሔር ልጆች ነን እያሉ በሕይወታቸው መልካም ፍሬ የማይታይባቸው ሰዎች፥ ተቈርጠው ወደ እሳት እንደሚጣሉ ዛፎች ናቸው (ቍ 8-10:12)።

[9]'አብርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን
አታታልሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች
ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል
እላችኋለሁና። [10]እነሆ፤ ምሣር የዛፎችን
ሥር ሊቈርጥ ተዘጋጅቶአል፤ መልካም
ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ
እሳትም ይጣላል።
[11]"እኔ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤
ነገር ግን ጫማውን መሸከም የማይገባኝ፣
ከእኔ የሚበልጥ ኀያል ከእኔ በኋላ
ይመጣል። እርሱም በመንፈስ ቅዱስና
በእሳት ያጠምቃችኋል። [12]መንሹ በእጁ
ነው፤ ዐውድማውን ያጠራል፤ ስንዴውን
በጐተራ ይከታል፤ ገለባውን ግን በማይጠፋ
እሳት ያቃጥለዋል።"

### የኢየሱስ መጠመቅ

*3፥13-17 ተጓ ምብ — ማር1፥9-11፤ ሉቃ3፥21፡22፤ ዮሐ1፥31-34*

[13]በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ
ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ።
[14]ዮሐንስ ግን፣ "ይህማ አይሆንም፤ እኔ
ባንተ መጠመቅ ሲያስፈልገኝ እንዴት አንተ
ወደ እኔ ትመጣለህ?" ብሎ ተከላከለ።
[15]ኢየሱስም፣ "ግድ የለም ፍቀድልኝ፤
ይህንበማድረግጽድቅንሁሉመፈጸምይገባና
ልና" አለው፤ ዮሐንስም በነገሩ ተስማማ።
[16]ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው ወጣ፤
ወዲያውኑም ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር
መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ።
[17]እነሆ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ
ይህ ነው" የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።

### የኢየሱስ መፈተን

*4፥1-11 ተጓ ምብ — ማር 1፥12፡13፤ ሉቃስ 4፥1-13*

4 ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን
በዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ

3፥9 ሉቃ3፥8
3፥10 ማቴ7፥19፤ ሉቃ3፥9፤ 13፥6-9፤ ዮሐ15፥2፡6
3፥11 ቍ6፤ ኢሳ4፥4፤ ማር1፥4፡8፤ ሐሥ2፥3፡4
3፥12 ማቴ13፥30፤ 25፥41
3፥13 ማቴ3፥1፤ ማር1፥4
3፥16 ኢሳ11፥2፤ 42፥1፤ ሕዝ1፥1፤ ዮሐ1፥51፤ ሐሥ7፥56፤ 10፥11፤ ራእ4፥1፤ 19፥11
3፥17 ዘጸ4፥12፤ መዝ2፥7፤ ኢሳ42፥1፤ ማቴ12፥18፤ 17፥5፤ ማር1፥11፤ 9፥7፤ ሉቃ3፥22፤ 9፥35፤ ዮሐ12፥28፤ ሐሥ13፥33፤ ዕብ1፥1-5፤ 5፥5፤ 2ጴጥ1፥17፡18
4፥1 ዘፍ3፥1-7፤ ዕብ4፥15

**3፥11 በመንፈስ ቅዱስ ... ያጠምቃችኋል፤** የሚመጣው መሲሕ ዋና ሥራ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ማጥመቅ ማለትም ለክርስቶስ ለመኖርና ለመመስከር ታላቅ ኀይል የሚሆነውን ጥምቀት መስጠት እንደ ሆነ መጥምቁ ዮሐንስ ያስተምራል (ሉቃ 3፥16 ላይ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ የተሰጠውን ማብ ይመ)።

**3፥13 ኢየሱስ ... ለመጠመቅ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤ (1) "ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም" (ቍ 15 ይመ፤ ከዘሌ 16፥4፤ ከገላ 4፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ በጥምቀት አማካይነት በይፋ ራሱን ለእግዚአብሔርና ለመንግሥቱ በመቀደስ ለየ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔርን የጽድቅ መስፈርት አሟላ። (2) ኢየሱስ ንስሓ መግባት ባያስፈልገውም እንኳ፣ ራሱን ከኀጢአተኞች ጋር አንድ ለማድረግ ሲል ተጠመቀ (2ቆሮ 5፥21፤ 1ጴጥ 2፥24)። (3) እያንዳንዱን ሰው ለንስሓ ወደሚጠራው ወደ አዲሱ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ውስጥ ራሱን ለማስገባት ነው፤ የመጥምቁ ዮሐንስ መልእክት ለመሲሑ መምጣት መንገድ ጠራጊ እንደ ሆነ ልብ ይበሉ (ዮሐ 1፥23፡32-33)።

**3፥16 የእግዚአብሔር መንፈስ ... ሲወርድበት፤** ኢየሱስ ያደረገውን ማንኛውንም ነገር፤ ስብከቱን፣ የፈውስ አገልግሎቱን፣ የተቀበለውን መከራ፣ በኀጢአት ላይ የተቀዳጀውን ድል የፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነበር፤ ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ኀይል ውጪ ምንም ነገር ማድረግ ካልቻለ፣ እኛ የቱን ያህል የበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ያስፈልገን ይሆን? (ከሉቃ 4፥1፡14፡18፤ ከዮሐ 3፥34፤ ከሐሥ 1፥2፤ 10፥38 ጋር ያነጻጽሩ)። መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሱስ የመጣው የቤዛነት ሥራውን ለመፈጸም የሚያስችለውን ኀይል ለማስታጠቅ ነው (ሉቃ 3፥22 እና ማብ ይመ)። ኢየሱስ ራሱም በኋላ ተከታዮቹ የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ይኖራቸው ዘንድ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃቸዋል (ማቴ 3፥11 እና ማብ ይመ፤ ሐሥ 1፥5፡8፤ 2፥4)።

**3፥17 በዚህ ስፍራ የሥላሴ አንድነት በምሳሌ ቀርቦአል፤** የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት አስደናቂ በሆነ ሁኔታ የሥላሴ መገለጥ የታየበት ነው፤ (1) ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል መሆኑ ተገለጠ (ዮሐ 10፥10)፤ በዮርዳኖስም ተጠመቀ። (2) ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል የሆነው መንፈስ ቅዱስ (ሐሥ 5፥3-4) በኢየሱስ ላይ እንደ ርግብ ወረደ። (3) እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ደስ እንደ ተሰኘ ገለጠ። እንግዲህ ሦስት እኩል የሆኑ መለኮታውያን አካላት እንዳሉ እናስተውላለን፤ ይህን ሁኔት ከዚህ ውጭ በሌላ መንገድ ለመግለጽ መሞከር፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት አጠቃላይ ሐሳብ ጋር መቃረን ነው። ስለ ሥላሴ የሚሰጠው ትምህርት እነዚህ ሦስት መለኮታውያን አካላት በአንድ አምላክነት በአንድነት መኖራቸውን ያስተምራል (ማር 1፥11 እና ስለ ሥላሴ የተሰጠውን ማብ ይመ፤ ከማቴ 28፥19፤ ከዮሐ 15፥26፤ ከ1ቆሮ 12፥4-13፤ ከኤፌ 2፥18፤ ከ1ጴጥ 1፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥1-11 በእነዚህ ቍጥሮች ውስጥ የኢየሱስ መፈተን ተዘርዝሮ ተጽፎአል።** ሰይጣን ኢየሱስን የፈተነው ለእግዚአብሔር ፈቃድ በሚገባ ለመታዘዝ ከሚወስደው መንገድ አሳስቶ ለማስወጣት ነው። ኢየሱስ በእያንዳንዱ ፈተና ወቅት ለሰይጣን ምኞት ራሱን አሳልፎ ከመስጠት ይልቅ ለእግዚአብሔር ቃል ራሱን ማስገዛቱን ልብ ይበሉ (ቍ 4፡7፡10)። ክርስቶስ ከደረሰበት ፈተና ምን መማር እንችላለን?

(1) ሰይጣን ዋና ጠላታችን ነው። ክርስቲያን እንደ መሆናችን መጠን ከማይታዩ ነገር ግን እውነተኛ ከሆኑ የክፉ ኀይላት ጋር መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንዳለን መገንዘብ አለብን (ኤፌ 6፥12 እና ማብ ይመ)።

(2) ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ካልታገዘና በእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ካልተጠቀመ ኀጢአትንና ፈተናን ማሸነፍ አይችልም። የሚከተሉት ሐሳቦች ፈተናን ለማሸነፍ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት መጠቀም እንደሚቻል የሚረዱ ናቸው፤ (ሀ) ሰይጣን ለሚያቀርበው ለማንኛውም ዐይነት ጥያቄ በቃሉ አማካኝነት መቋቋም የሚያስችል ኀይል እንዳለ ማስተዋል (ዮሐ 15፥3፡7)፤ (ለ) በልብና በአእምሮ የእግዚአብሔርን ቃል በመያዝ በቃል ማጥናት (ያዕ 1፥21 እና ማብ ይመ)፤ (ሐ) በቃል የተጠኑትን ጥቅሶች ቀንና ማታ ማሰላሰል (ዘዳ 6፥6 እና ማብ፤ መዝ 1፥2 እና ማብ፤ 119፥47-48 እና ማብ ይመ)፤ (መ) ፈተና በኃጠመን ወቅት በቃል ያጠናውን ጥቅስ ለራሳችንና ለእግዚአብሔር

በዳ ወሰደው። 2አርባ ቀንና አርባ ሌሊት
ከጾመ በኋላ ተራበ። 3ፈታኙም ወደ ኢየሱስ
ቀርቦ፣ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ እነዚህን
ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ" አለው።
4ኢየሱስም፣ " 'ሰው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ
አይኖርም' ተብሎ ተጽፎአል" ሲል መለሰ
ለት።
5ቀጥሎም ዲያብሎስ ኢየሱስን ወደ
ቅድስት ከተማ በመውሰድ ከቤተ መቅደሱም
ፀናት ላይ አውጥቶ፣ 6"የእግዚአብሔር ልጅ
ከሆንህ ራስህን ወደ መሬት ወርውር፤
እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
" 'እግርህ በድንጋይ እንዳይሰናከል፣
በእጃቸው ያነሡህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል።' "
7ኢየሱስም፣ "እንደዚሁም በመጻሕፍት፣
'እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው'
ተብሎ ተጽፎአል" በማለት መለሰለት።
8እንደ ገናም ዲያብሎስ ኢየሱስን እጅግ
ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው፤ የዓለምንም
መንግሥታት ከነክብራቸው አሳየውና፤
9"ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥ
ሃለሁ" አለው።
10ኢየሱስም፣ "አንተ ሰይጣን ከፊቴ ራቅ!

4፥2 ዘፀ34፥28፤ 1ነገ19፥8
4፥3 ማቴ3፥17፤ 14፥33፤ 16፥16፤ 27፥54፤ ማር3፥11፤ ሉቃ1፥35፤ 22፥70፤ ዮሐ1፥34፡49፤ 5፥25፤ 11፥27፤ 20፥31፤ ሐሥ9፥20፤ ሮሜ1፥4፤ 1ተሰ3፥5፤ 1ዮሐ5፥10-13፡20፤ ራእ2፥18
4፥4 ዘዳ8፥3፤ ዮሐ4፥34

4፥5 ነህ11፥1፤ ዳን9፥24፤ ማቴ27፥53 4፥6 ቆላ3፥ መዝ91፥11፡12 4፥7 ዘዳ6፥16 4፥10 ዘዳ6፥13፤ 1ሳሙ21፥1፤ ኢዮ1፥6-9፤ ማቴ16፥23፤ ማር4፥15፤ ሉቃ10፥18፤ 13፥16፤ 22፥3፡31፤ ሮሜ16፥20፤ 2ቆሮ2፥11፤ 11፥14፤ 2ተሰ2፥9፤ ራእ12፥9

መናገር (ቆላ 4፡7፡10)፡ (ሠ) ለእግዚአብሔር ቃል እንድንታዘዝ የሚያነሣሣንን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መለየትና መታዘዝ (ሮሜ 8፥12-14፤ ገላ 5፥18)፡ (ረ) ከላይ የተጠቀሱትን ርምጃዎች ሁሉ በጸሎት በመደገፍ መፈጸም (ኤፌ 6፥18)።

ለሚያጋጥመን ፈተና እንዲረዱን በቃል የምናጠናቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው፤ ለአጠቃላይ ፈተና (ሮሜ 6 እና 8)፣ ተለይቶ ለታወቀ ነገር፥ ለምሳሌ ስለ ኢግብረገባዊነት (ሮሜ 13፥14)፣ ስለ ውሸት (ዮሐ 8፥44፤ ቈላ 3፥9)፥ ስለ ሐሜት (ያዕ 4፥11)፥ ወላጆችን ስላለመታዘዝ (ዕብ 13፥17)፣ ተስፋ ስለ መቍረጥ (ገላ 6፥9)፣ ስለ ወደ ፊት ሥጋት (2ጢሞ 1፥7)፣ ስለ ምንዝርና (ማቴ 5፥28፥ 2ጢሞ 2፥22)፣ ስለ ቂም በቀል (ማቴ 6፥15)፣ የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ስለ ማለት (ማቴ 4፥4)፣ ስለ ገንዘብ ችግር (ማቴ 6፥24-34፡ ፊል 4፥6)።

**4፥2 አርባ ቀንና ... ከጾመ በኋላ፤** አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ኢየሱስ ተራበ፡ ምግብ እንዲበላም በሰይጣን ተፈተነ። ክርስቶስ የሰው ልጅ ተወካይ እንደ መሆኑ መጠን፣ ፈተናን መጋፈጥ ነበረበት (ከዕብ 2፥17፤ ከ4፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ማንኛውም አማኝ ፈተና ሲደርስበት የሚጠቀምበትን መንገድ ከመከተል በቀር፣ ክርስቶስ ከደረሰበት ፈተና ለመሸሽ ምንም ዐይነት ዘዴ አልተጠቀመም (ዘፀ 34፥28 እና ማብ፡ 1ነገ 19፥8 እና ማብ፡ ማቴ 6፥16 እና ስለ ጾም የተሰጠውን ማብ ይመ)። በአርባ ቀኑ የጾም ጊዜ ኢየሱስ ከአባቱ የተሰጠውን ሥራ ይፈጽም ዘንድ፥ በጸሎትና የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል ራሱን ያዘጋጅ ነበር ማለት ተገቢ ነው።

**4፥6 እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤** ሰይጣን በእግዚአብሔር ቃል የተጠቀመው ክርስቶስን ለመፈተን ነበር። አንዳንድ ጊዜ ዓለማዊ ሰዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ፣ አማኞች ስሕተት ወይም ተገቢ እንዳልሆነ የሚያውቁትን እንዲያደርጉ በመገፋፋት ሊፈትኗቸው ይሞክራሉ። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ከዐውዱ ውጭ ከታዩ ወይም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ካሉ ከሌሎች ምንባቦች ጋር ካልተነጻጸሩ በቀር፣ በነቢአት የተሞላ ባሕርይን የሚደግፉ ሊመስሉ ይችላሉ (ለምሳሌ 1ቆሮ 6፥12 ይመ)። አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀት ማወቅ አለባቸው፤ የሰውን ኀጢአተኛ ባሕርይ ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሚያጣምሙ ሰዎች ትምህርትም መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል። ሐዋርያው ጴጥሮስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስለሚያጣምሙ ሰዎች ለራሳቸው መጥፊያ እንደሚያጣምሙ ተናግሮአል (2ጴጥ 3፥16)።

**4፥8 የዓለምንም መንግሥታት፤** ሉቃ 4፥5 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**4፥10 ሰይጣን፤** የስሙ ትርጕም በዕብራይስጥ "ከሳሽ" ወይም "ጠላት" ማለት ሲሆን፣ ፍጹምና መልካም ሆኖ የተፈጠረ ታላቅ መልአክ ነበር። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እንዲያገለግል ተሹሞ ነበር፥ ይሁን እንጂ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፣ በማመፅ የእግዚአብሔርና የሰው ልጆች ዋና ጠላት ሆነ (ሕዝ 28፥12-15)።

(1) ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ፤ ከወደቁ በኋላ ምናልባት አጋንንት ወይም ክፉ መናፍስት በመባል የሚታወቁትን አያሌ ታናናሽ መላእክትን ለራሱ ዓላማ አሰልፎአል (ቢገጽ 1499 ላይ፣ "በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ሰይጣንና እነዚህ ታናናሽ መላእክት ወደ ምድርና በዙሪያው ወዳለው ከባቢ አየር ተጣሉ፤ በዚሁ ክልል ብቻ በእግዚአብሔር ይሁንታዊ ፈቃድ ሥር እንዲሠሩም ተፈቀደላቸው።

(2) "እባቡ" በመባል የሚታወቀውም ሰይጣን ለሰው ልጅ ውድቀት ምክንያት ሆነ (ዘፍ 3፥1-6 ይመ፥ 1ዮሐ 5፥19 እና ማብ ይመ)።

(3) የሰይጣን መንግሥት (12፥26) በአየሩ መንግሥት (ኤፌ 2፥2)፣ በወደቁት መላእክት (25፥41፥ ራእ 12፥7)፥ ዳግም ልደት ባልተቀበለው የሰው ዘር (ቆላ 8-9፥ ዮሐ 12፥31፤ ኤፌ 2፥2) እና በዓለም ላይ (ሉቃ 4፥5-6፥ 2ቆሮ 4፥4፥ 1ዮሐ 5፥19 እና ማብ ይመ) ሥልጣን ያለው በከፍተኛ ደረጃ የተጠናከረ የክፋት ግዛት ነው። ሰይጣን በሁሉ ቦታ የሚገኝ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል ወይም ሁሉን ዐዋቂ አይደለም፥ ስለዚህ ብዙውን ተግባሩን ለአጋንንቱ ሰጥቶአል (8፥28፤ ራእ 16፥13-14 ይመ፤ ኢዮ 1፥12 እና ማብ ይመ)።

(4) ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የሰይጣንን ሥራ ለማፍረስ (1ዮሐ 3፥8)፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመመሥረትና በሰይጣን ከመገዛት ነጻ ሊያወጣን ነው (12፥28፥ ሉቃ 4፥18፥ 13፥16፥ ሐሥ 26፥18)። ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው በመጀመሪያ ሰይጣን እንዲሸነፍ አደረገ፡ ከዚያም እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ የወሰነውን የመጨረሻ ድል አረጋገጠ (ዕብ 2፥14)።

(5) በዘመኑ ፍጻሜ ላይ ሰይጣን በጥልቁ ውስጥ ሺህ ዓመት መታሰር ይኖርበታል (20፥1-3)። ሰይጣን ከተፈታ በኋላ የእግዚአብሔርን የክብር ሰፍራ ለመያዝ የመጨረሻ ሙከራ ያደርጋል፡ የዐመፁ ውጤትም የመጨረሻ ጊዜ ሽንፈቱንና በእሳት ባሕር ውስጥ መጣሉን ያስከትላል (ራእ 20፥7-10)።

(6) በአሁኑ ዘመን ሰይጣን እግዚአብሔርንና ሕዝቡን

‘ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም
ብቻ አምልክ’ ተብሎ ተጽፎአልና” አለው።
[11]ከዚያም ዲያብሎስ ትቶት ሄደ፤ መላ
እክትም መጥተው አገለገሉት።

## ኢየሱስ ስብከት መጀመሩ

[12]ኢየሱስ የዮሐንስን መታሰር በሰማ ጊዜ
ወደ ገሊላ ተመለሰ። [13]የናዝሬትንም ከተማ
ትቶ፣ በዛብሎንና በንፍታሌም አካባቢ
በባሕሩ አጠገብ በምትገኘው በቅፍርናሆም
ከተማ መኖር ጀመረ። [14]በዚህም በነቢዩ
ኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው ትንቢት
ተፈጸመ፤
[15]“የዛብሎን ምድር፣ የንፍታሌም ምድር፣
ከዮርዳኖስ ማዶ በባሕር መንገድ
አጠገብ፣
ያለው የአሕዛብ ገሊላ፤
[16]በጨለማ የሚኖር ሕዝብ፣
ታላቅ ብርሃን አየ፤
በሞት ጥላ ምድር ላለው፣
ብርሃን ወጣለት።”
[17]ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ፣ “ንስሓ
ግቡ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና”
እያለ መስበክ ጀመረ።

## የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መጠራት

*4፥18-22 ተጓ ምብ — ማር1፥16-20፤ ሉቃ5፥2-11፤ ዮሐ1፥35-42*

[18]ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠገብ
ሲያልፍ፣ ሁለት ወንድማማቾች ማለትም
ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንንና ወንድሙን
እንድርያስን አያቸው። ዓሣ አጥማጆች
ነበሩና መረባቸውን ወደ ባሕሩ ይጥሉ ነበር።
[19]ኢየሱስም፣ “ኑ፣ ተከተሉኝ፤ ሰዎችን አጥ
ማጆች አደርጋችኋለሁ” አላቸው። [20]ወዲ
ያው መረባቸውን ትተው ተከተሉት።
[21]አለፍ እንዳለም፣ ሌሎች ሁለት
ወንድማማቾች፣ የዘብዴዎስን ልጅ
ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን አየ።
ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ
ውስጥ መረባቸውን ያበጁ ነበር። ኢየሱስም
ጠራቸው፤ [22]ወዲያውኑ ጀልባቸውንም ሆነ
አባታቸውን ትተው ተከተሉት።

## የበሽተኞች መፈወስ

[23]ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው
እያስተማረ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት
የምሥራች ቃል እየሰበከ፣ በሕዝቡ መካከል
ማንኛውንም ደዌና ሕመም እየፈወሰ በመላው
ገሊላ ይዘዋወር ነበር። [24]ከዚህም የተነሣ
ዝናው በመላዋ ሶርያ ተሰማ፤ ሕዝቡም
በተለያዩ በሽታዎች የታመሙትን፣ በክፉ
ደዌ የሚሠቃዩትን፣ አጋንንት ያደሩባቸውን፣
የሚጥል በሽታ ያለ ባቸውን፣ ሽባዎችን ሁሉ ማቴ 8፥16-17
ወደ እርሱ አመጡ፤ ፈወሳቸውም። [25]ከዚህም
የተነሣ ከገሊላ፣ ከ ‘ዐሥሩ ከተሞች’፣
ከኢየሩሳሌም፣ ከይሁዳና ከዮርዳኖስ ማዶ
የመጡ ብዙ ሰዎች ተከተሉት።

## የተራራው ስብከት

*5፥3-12 ተጓ ምብ — ሉቃ 6፥20-23*

**5** ብዙ ሕዝብ እንደ ተሰበሰበ ባየ ጊዜ፣
ወደ ተራራ ወጣና ተቀመጠ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም ወደ እርሱ መጡ። [2]እንዲህም
እያለ ያስተምራቸው ጀመር፤
[3]“በመንፈስ ድኾች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤

4፥11 ማቴ26፥53፤ ሉቃ22፥43፤ ዕብ1፥14፤ ያዕ4፥7 4፥12 ማቴ14፥3፤ ማር1፥14 4፥13 ማር1፥21፤ 9፥33፤ ሉቃ4፥23፡31፤ ዮሐ2፥12፤ 4፥46፡47 4፥14 ማቴ1፥22 4፥16 ኢሳ9፥1፡2፤ ሉቃ2፥32፤ ዮሐ1፥4፡5፡9 4፥17 ማቴ3፥2 4፥18 ማቴ15፥29፤ 16፥17፡18፤ ማር7፥31፤ ዮሐ6፥1 4፥19 ቆላ20፡22፤ ማቴ8፥22፤ ማር10፥21፡28፡ 52፤ ሉቃ5፥28፤ ዮሐ1፥43፤ 21፥19፡22 4፥20 ቍ19 4፥21 ማቴ17፥1፤ 20፥20፤ 26፥37፤ ማር3፥17፤ 13፥3፤ ሉቃ8፥51፤ ዮሐ21፥2 4፥22 ቍ19 4፥23 ማቴ3፥2፤ 8፥16፤ 9፥35፤ 13፥54፤ 14፥14፤ 15፥30፤ ማር1፥14፡21፡39፤ 3፥10፤ ሉቃ4፥15፡44፤ 7፥22፤ ዮሐ6፥59፤ 18፥20፤ ሐሥ10፥38፤ 20፥25፤ 28፥23፡31 4፥24 ማቴ8፥6፡16፡28፤ 9፥2፡32፤ 12፥22፤ 15፥22፤ 17፥15፤ ማር1፥32፤ 2፥3፤ 5፥15፡16፡18፤ ሉቃ2፥2 4፥25 ማር3፥7፡8፤ ሉቃ6፥17 5፥3 ቍ10፥19፤ ማቴ25፥34

---

ይዋጋል (ኢዮ 1—2፤ ኤፌ 6፥11-18)፤ ሕዝቡን የሚዋጋውም ለክርስቶስ ታማኞች እንዳይሆኑ (2ቆሮ 11፥3)፣ ለአሁኑ ዘመን የዓለም ሥርዐት ኀጢአትና ባርነት ተገዢም (ከ2ቆሮ 11፥13፤ ከ1ጢሞ 5፥15፤ ከ1ዮሐ 5፥16 ጋር ያነጻጽሩ) ለማድረግ ነው። አማኞች ከሰይጣን ነጻ ለመውጣት ሳያቋርጡ መጸለይ አለባቸው (ማቴ 6፥13)፤ ሰቅዱንና ፈተናውን ከንቱ ለማድረግም ነቅተው መጠበቅ ይገባቸዋል (ኤፌ 6፥11)፤ በእምነት በመጽናትም (ኤፌ 6፥10-18፤ 1ጴጥ 5፥8-9) በመንፈሳዊ ጦርነት ሊቋቋሙት ያስፈልጋል።

**4፥19 ሰዎችን አጥማጆች፤** አንድ ሰው መጋቢ፣ ወንጌላዊ፣ ሚስዮናዊ፣ ጸሓፊ፣ አስተማሪ፣ ዲያቆን ወይም ተራ ምእመን ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ እርሱ ወይም እርሷ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ጥረት የማያደርጉ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ሥራ እየፈጸሙ አይደሉም (28፥19፤ ሉቃ 5፥10፤ ዮሐ 15፥16፤ ሐሥ 1፥8፤ 1ቆሮ 9፥19 ይመ)።

**4፥23 የእግዚአብሔርን መንግሥት ... እየፈወሰ፤** በወንጌሎች ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ከፈውስ፣ ታምራትን ከማድረግና አጋንንትን ከማስወጣት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው (4፥23-24፤ 9፥35፤ 10፥7-8፤ 12፥28፤ ሉቃ 9፥1-2 ይመ፤ ከሐሥ 8፥6-7፡12 ጋር ያነጻጽሩ)። የእግዚአብሔር መንግሥት ለሥጋም ሆነ ለነፍስ የሚሆኑትን በረከቶች ሁሉ አካትቶ ይዞአል (በገጽ 1433 ላይ፤ «መለኮታዊ ፈውስ» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5—7 የተራራው ስብከት፤** ከምዕራፍ 5—7 ያለው ክፍል በአብዛኛው የክርስቶስ የተራራ ስብከት በመባል ይታወቃል፤ ይኸውም ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን (ገላ 2፥20) እና በውስጣቸው በሚያድረው በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ (ከሮሜ 8፥2-14፤ ከገላ 5፥16-25 ጋር ያነጻጽሩ) የሚኖሩባቸውን የእግዚአብሔርን የጽድቅ መመሪያዎች የያዘ ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉ ሁሉ ክርስቶስ በስብከቱ ያስተማረው ጽድቅ ጥልቅ ረኀብና ጥማት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል (5፥6 እና ማብ ይመ)።

**5፥3 በመንፈስ ድኾች ... ብፁዓን ናቸው፤** «ብፁዓን» የሚለው ቃል ከክርስቶስና ከቃሉ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው አማኞች የሚኖራቸውን ደኅንነት የሚያመለክት ነው፤ እነርሱም ፍቅሩን፣ እንክብካቤውን፣ ድነቱንና የየዕለት ሀልዎቱን አካትቶ የያዘውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ይቀበላሉ (14፥19 እና ማብ፤ ሉቃ 24፥50 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔርን መንግሥት በረከቶች ለመቀበል ከፈለግን የተወሰኑ ግዴታዎች አሉ፤ ይኸውም በዓለም መንገዶችና እሴቶች መመራት ሳይሆን፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተገለጡት

መንግሥት ሰማይ የእነርሱ ናትና።
4 የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤
መጽናናትን ያገኛሉና።
5 የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤
ምድርን ይወርሳሉና።
6 ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን
ናቸው፤ ይጠግባሉና።
7 ምሕረት የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤
ምሕረትን ያገኛሉና።

5፥4 ኢሳ61፥2-3፤ ራእ7፥17
5፥5 መዝ37፥11፤ ሮሜ4፥13
5፥6 ኢሳ55፥1-2
5፥7 ያዕ2፥13
5፥8 መዝ17፥15፤ 24፥3-4፤ 42፥2፤ 73፥1፤ ዕብ12፥14፤ ራእ22፥4

8 ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤
እግዚአብሔርን ያዩታልና።
9 ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤
የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው
ይጠራሉና።
10 ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ ብፁዓን
ናቸው፤

5፥9 ዮሐ44፥45፤ ሮሜ8፥14፤ 14፥19፤ ያዕ3፥18
5፥10 ዮሐ3፥19፤ ማቴ25፥34፤ 1ጴጥ3፥14

የእግዚአብሔር መንገዶችና እሴቶች መመራት አለብን። ከእነዚህም ግዴታዎች የመጀመሪያው "በመንፈስ ድኾች" መሆን ነው። በመንፈሳዊ ረገድ በራሳችን ብቁ እንዳልሆንን መገንዘብ ይኖርብናል፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ እንችል ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት፣ ኀይልና የሚረዳ ጸጋ ያስፈልገናል።

**5፥4 የሚያዝኑ፤** "ማዘን" ማለት ለእግዚአብሔር የጽድቅ መለኪያና ለመንግሥቱ ኀይል (ቍ 6፤ 6፥33) የማንበቃ መሆናችንን በመረዳት ስለ ራሳችን ድካም በእጅጉ መጸጸትና መቈዘም ማለት ነው። ደግሞም ማዘን ሲባል እግዚአብሔር በሚያዝንባቸው ነገሮች አብሮ ማዘንን፥ እግዚአብሔር የሚሰማው ስሜት የእኛም ስሜት መሆኑን፣ ከኀጢአት የተነሣ በመንፈሳችን በእጅጉ መጐዳታችንን፣ በዓለም ላይ በሚከሠተው ኢሥነምግባራዊነትና ጭካኔ ልባችን መነካቱን ያካትታል (ሉቃ 19፥41 እና ማብ ይመ፤ ሐሥ 20፥19 ይመ፤ 2ጴጥ 2፥8 እና ማብ ይመ)። የሚያዝኑ ከአብ፣ "በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት" (ሮሜ 14፥17) በመቀበል ይጽናናሉ።

**5፥5 የዋሆች፤** "የዋሆች" የተባሉት በእግዚአብሔር ፊት ትሑትና ታዛዥ የሆኑት ናቸው። በእርሱ ይኖራሉ፤ መንገዳቸውንም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈው ይሰጣሉ። በግል ሕይወታቸው ከሚደርስባቸው ነገር ይልቅ ስለ እግዚአብሔር ሥራና ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ በእጅጉ ይጨነቃሉ (ከመዝ 37፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዕብሪተኞች ይልቅ ትሑታን በመጨረሻ ምድርን ይወርሳሉ።

**5፥6 ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ፤** ይህ ጥቅስ በተራራው ስብከት ውስጥ ከሚገኙት ጥቅሶች መካከል እጅግ አስፈላጊው ጥቅስ ነው፤ (1) እግዚአብሔርን ፈርቶ ለመኖር እጅግ መሠረታዊ የሆነው አስፈላጊ ጕዳይ ጽድቅን መራብና መጠማት ነው (ከ6፥33 ጋር ያነጻጽሩ)። እንዲህ ዐይነቱ መንፈሳዊ ረኃብ በሙሴ (ዘፀ 33፥18)፣ በመዝሙረኛው (መዝ 42፥2፡6 እና ማብ፤ 63፥1 እና ማብ ይመ) እና በሐዋርያው ጳውሎስ (ፊል 3፥10) ላይ ታይቶአል። የክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሁኔታ በኑሯቸው ሁሉ የሚወሰነው ለሚከተሉት ጕዳዮች ባላቸው ረኃብና ጥማት ነው፤ (ሀ) ለእግዚአብሔር ህልዎት (ዘዳ 4፥29)፣ (ለ) ለእግዚአብሔር ቃል (መዝ 119)፥ (ሐ) ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለማድረግ (ፊል 3፥8-10)፣ (መ) ለመንፈስ ቅዱስ ኅብረት (ዮሐ 7፥37-39፤ 2ቆሮ 13፥14)፥ (ሠ) ለጽድቅ (5፥6)፥ (ረ) ለእግዚአብሔር መንግሥት ኀይል (6፥33)፣ (ሰ) ለጌታ ዳግም ምጽአት (2ጢሞ 4፥8)።

(2) ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ጕዳይ ያለው ረኃብ ስለ ዓለም መጨነቅ፣ ለሀብት በመታለል (13፥22)፣ ሌሎች ነገሮችን በመመኘት (ማር 4፥19)፣ በሕይወት በሚታየው ብልጥግናና ደስታ (ሉቃ 8፥14) እና በክርስቶስ ጸንቶ ለመኖር ባለመቻል (ዮሐ 15፥4 እና ማብ ይመ) ይበላሻል። አማኞች ለእግዚአብሔርና ለጽድቁ ሊኖራቸው የሚገባ ረሐብ ሲበላሽ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይሞታሉ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ለሚያከናውነው የመውቀስ ሥራ ንቁ እንድንሆን ያስፈልጋል (ዮሐ 16፥8-13፤ ሮሜ 8፥5-16 ይመ)።

**5፥7 ምሕረት የሚያደርጉ፤** ምሕረት የሚያደርጉ ሁሉ በኀጢአት ወይም በሐዘን ውስጥ ያሉትን ለመርዳት በርኅራኄና በሐዘኔታ የተሞሉ ናቸው። ምሕረትን የሚያደርጉ እንዲህ ዐይነቱ ሥቃይ እንዲቃለል በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ጸጋና ርዳታ ሰዎችን በታማኝነት ያቀርባሉ (ከ18፥23-35፤ ከሉቃ 10፥30-37፤ ከዕብ 2፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። ለሌሎች ምሕረትን ብናደርግ፣ እኛም ምሕረት ይደረግልናል።

**5፥8 ልባቸው ንጹሕ የሆነ፤** "ልባቸው ንጹሕ የሆነ" በእግዚአብሔር ጸጋ ከኀጢአት ኀይል ነጻ የወጡ ሲሆኑ፣ አሁን ደግሞ ያለምንም ማታለል እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘትና ማክበር የሚፈልጉ፣ እርሱንም ለመምሰል የሚሹ ናቸው፤ (1) የእግዚአብሔር የልብ ዝንባሌ የእነርሱም እንዲሆን የሚሹ ናቸው፥ ይህም ዝንባሌ ጽድቅን መውደድና ኀጢአትን መጥላት ነው (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)። ልባቸው (ይህም አእምሮን፣ ፈቃድንና ስሜትን ያካትታል፤ በገጽ 932 ላይ፣ "ልብ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ከእግዚአብሔር ልብ ጋር የሚስማማ ነው (1ሳሙ 13፥14፤ ማቴ 22፥37፤ 1ጢሞ 1፥5)። (2) ልበ ንጹሓን ብቻ "እግዚአብሔርን ያዩታል"። እግዚአብሔርን ማየት ማለት ልጁ መሆንና አሁንም ሆነ በሚመጣው በእርሱ መንግሥት በህልዎቱ ውስጥ መኖር ማለት ነው (ዘፀ 33፥11፤ ራእ 21፥7፤ 22፥4)።

**5፥9 ሰላምን የሚያወርዱ፤** "ሰላምን የሚያወርዱ" ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ናቸው። በመስቀሉ አማካይነት ከእርሱ ጋር ታርቀው ሰላምን አግኝተዋል (ሮሜ 5፥1፤ ኤፌ 2፥14-16 ይመ፤ በገጽ 1150 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር ሰላም*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። አሁን በምስክርነታቸውና በሕይወታቸው ሌሎችን፣ ጠላቶቻቸውንም ጨምሮ ወደ እግዚአብሔር ሰላም ለማምጣት ጥረት ያደርጋሉ።

**5፥10 ስለ ጽድቅ ብለው የሚሰደዱ፤** ለጽድቅ ሲሉ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተስማምተው ለመኖር የሚሹ ሰዎች ሁሉ ስደት ዕጣ ፈንታቸው ነው፤ (1) የእግዚአብሔርን የእውነት፣ የፍትሕና የንጽሕና መስፈርት ጠብቀው የሚይዙ እንዲሁም ከኢሁኑ ክፉ ኅብረተ ሰብ ወይም የተለሳለሰ የኑሮ ዘይቤ ካላቸው አማኞች ጋር ተስማምተው የማይጓዙ (ራእ 2፥3፥1-4፥14-22 ይመ) ትችትና ተቃውሞ ያጋጥማቸዋል፤ ተቀባይነትንም ያጣሉ። ስደትና ተቃውሞ ከዓለም ዘንድ ይመጣሉ (10፥22፤ 24፥9፤ ዮሐ 15፥19)፤ አንዳንድ ጊዜም ከቤተ ክርስቲያን ይነሣል (ሐሥ 20፥28-31፤ 2ቆሮ 11፥3-15፤ 2ጢሞ 1፥15፤ 3፥8-14፤ 4፥16)። ክርስቲያኖች ይህን ሥቃይ ሲቀበሉ፣ ደስ ሊሰኙ ይገባል (ቍ 12)፤ ከባድ ሥቃይ ለሚደርስባቸው፣ እግዚአብሔር ከፍተኛውን በረከት ያፈስላቸዋልና (2ቆሮ 1፥5፤

መንግሥተ ሰማይ የእነርሱ ናትና።
11 "ሰዎች በእኔ ምክንያት ቢሰድቧችሁ፣
ቢያሳድዱችሁና ክፉውን ሁሉ በሐሰት ቢያ
ስወሩባችሁ፤ ብፁዓን ናችሁ። 12 በሰማይ
የምትቀበሉትዋጋታላቅስለሆነደስ ይበላችሁ፤
ሐሤት አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነ
በሩትን ነቢያት እንደዚሁ አሳደዋቸዋልና።

## ጨውና ብርሃን

13 "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው
የጨውነት ጣዕሙን ቢያጣ ጣዕሙን መልሶ
ሊያገኝ ይችላልን? ወደ ውጪ ተጥሎ በሰው
ከመረገጥ በቀር ጥቅም አይኖረውም።
14 "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤
በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትደበቅ
አትችልም፤ 15 ሰዎችም መብራት አብርተው
ከዕ ንቅብ ሥር አያስቀምጡትም፤ በቤት
ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ በመቅረዝ
ላይ ያስቀምጡታል እንጂ። 16 እንደዚሁም
ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው
በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ
ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ። ማቴ 6፥19-24

## የሕግ ፍጻሜ

17 "ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር
የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም
እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። 18 እውነት
እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ
ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ
አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ
እንኳ አትሻርም። 19 ስለዚህ ማንም ከእነዚህ

5፥11 ኢሳ51፥7፤ ዮሐ15፥21
5፥12 2ዜና36፥16፤ መዝ9፥2፤ ማቴ23፥31፡37፤ ሐሥ5፥41፤ 7፥52፤ 2ቆሮ6፥10፤ 12፥10፤ ቆላ1፥24፤ 1ተሰ2፥15፤ ዕብ11፥32-38፤ ያዕ1፥2፤ 1ጴጥ1፥6፤ 4፥13፡16
5፥13 ማር9፥50፤ ሉቃ14፥34፡35
5፥14 ዮሐ8፥12
5፥15 ማር4፥21፤ ሉቃ8፥16፤ 11፥33
5፥16 ማቴ9፥8፤ 1ቆሮ10፥31፤ ፊል1፥11፤
5፥16 ቲቶ2፥14 5፥17 ዮሐ10፥34፡35፤ ሮሜ3፥31
5፥18 መዝ119፥89፤ ኢሳ40፥8፤ 55፥11፤ ማቴ24፥35፤ ማር13፥31፤ ሉቃ16፥17፤ 21፥33 5፥19 ያዕ2፥10

2ጢሞ 2፥12፤ 1ጴጥ 1፥7፤ 4፥13)። (2) ክርስቲያኖች ከነፍረት፣ ከውርደት ወይም ከማጣት ለመሸሽ ሲሉ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳይፈጽሙ ከሚፈታተናቸው ሁሉ መጠበቅ አለባቸው (10፥33፤ ማር 8፥38፤ ሉቃ 9፥26፤ 2ጢሞ 2፥12)። የእግዚአብሔር መንግሥት መመሪያ ፈጽሞ አልተለወጠም፤ ይኸውም፣ "በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ" (2ጢሞ 3፥12) ይላልና። በጽድቅ ምክንያት ሥቃይን የሚቀበሉና የሚታገሡ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚወርሱ፣ ሰማያዊ ሽልማቶችንም እንደሚቀበሉ ቃል ተገብቶላቸዋል።

**5፥13 የምድር ጨው፤** ጨው ጣዕም ለመስጠትና ምግብን ከመበላሸት ለመጠበቅ እንደሚጠቅም ሁሉ፣ አማኞችና ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን የመፍራት ምሳሌ በመሆን በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ያለውን ግብረገባዊ ንቅዘትና ብልሽት መከላከል አለባቸው። (1) ቸልተኛ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈስ ቅዱስን ኀይል ያጠፋሉ፤ በዓለም ላይ ገንኖ የሚገኘውን በእግዚአብሔር የተጣለውን መንፈስ መቃወም ያቅታቸዋል (ራእ 3፥15-16 እና ማብ ይመ)። (2) ከዚህም የተነሣ "በሰዎች ይረገጣሉ"፤ ይኸውም ቸልተኛ በሆኑ ሰዎች ነው፤ እንዲሁም ከነቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔርን በማይፈራ ኅብረተ ሰብ መንገድና የኑሮ ዘይቤ ይጠፋሉ (ከዘዳ 28፥13፡43፡48፤ ከመሳ 2፥20-22 ጋር ያነጻጽሩ።)

**5፥17 ሕግንና ... ለመፈጸም፤** ክርስቶስ በተከታዮቹ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈጸም የሚያስችል አስፈላጊ ነገር እንዲከናወን ይሻል (ሮሜ 3፥31፤ 8፥4)። አማኞች ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚከተሉትን ያካትታል፦

(1) አማኝ ሊጠብቀው የሚገባው ሕግ የብሉይ ኪዳንን ሥነምግባራዊና ግብረገባዊ መመሪያዎች (7፥12፤ 22፥36-40፤ ሮሜ 3፥31፤ ገላ 5፥14 ይመ፤ በገጽ 144 ላይ፣ "የብሉይ ኪዳን ሕግ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) እንዲሁም የክርስቶስንና የሐዋርያትን ትምህርቶች (28፥20፤ 1ቆሮ 7፥19፤ 9፥21፤ ገላ 6፥2) የሚያካትት ነው። እነዚህ ሕጎች በሰዎች ሁሉ ዘንድ መኖር የሚገባውን የእግዚአብሔርን ባሕርይና ፈቃድ የሚገልጡ ሲሆኑ፣ ዛሬም ቢሆን አገባብነት አላቸው። የእስራኤልን ሕዝብ በተመለከተ በቀጥታ የተገለጡት የብሉይ ኪዳን ሕጎች ለምሳሌ መሥዋዕት ማቅረብን፣ ሥርዐትን፣ ማኅበራዊ ወይም ሕዝባዊ ሕጎችን በተመለከተ የተጠቀሱት ሕጎች ለዚህ ጊዜ ተገቢነት የላቸውም (ዕብ 10፥1-4 ለምሳሌ ዘሌ 1፥2-3፤ 24፥10)።

(2) አማኞች ሕግን ይቅርታንና ድነትን ማግኛ የሕግ ትእዛዛት ሥርዐት አድርገው መመልከት የለባቸውም (ገላ 2፥16፡19)። ከዚህ ይልቅ ሕጉ ከእግዚአብሔር ጋር የድነት ግንኙነት ባላቸውና በመታዘዝ በውስጣቸው የክርስቶስን ሕይወት በሚያንጸባርቁ ሰዎች ዘንድ ግብረገባዊ ሕግ ተደርጎ መታየት አለበት (ሮሜ 6፥15-22)።

(3) በክርስቶስ ማመን ሕግን ለመፈጸም መነሻ ርምጃ ነው። በክርስቶስ ስናምን እግዚአብሔር አባታችን ይሆናል (ከዮሐ 1፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ አማኞች በመሆናችን መታዘዛችን እውን የሚሆነው፣ ሉዓላዊ ሕግ ሰጪ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙነት አንጻር ብቻ ሳይሆን፣ ልጆች ከአባታቸው ጋር ካላቸው ግንኙነት አኳያም ጭምር ነው (ገላ 4፥6)።

(4) በክርስቶስ በማመን አማኞች በእግዚአብሔር ጸጋ (ሮሜ 5፥21) እና በውስጣቸው በሚያድረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት (ሮሜ 8፥13፤ ገላ 3፥5፡14) የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈጸም ውስጣዊ ግፊትና ኀይል ተሰጥቷቸዋል (ሮሜ 16፥25-26፤ ዕብ 10፥16)። ሕጉን እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በመኖር እንፈጽመዋለን (ሮሜ 8፥4-14)። መንፈስ ቅዱስ የሥጋን ክፉ ሥራ ለማጥፋትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ይረዳናል (ሮሜ 8፥13፤ ማቴ 7፥21 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ በውጫዊ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር መስማማት ከልባችንና ከመንፈሳችን ውስጣዊ ለውጥ ጋር አብሮ መሄን አለበት (ከቆሎ 21-28 ጋር ያነጻጽሩ)።

(5) ከኀጢአት ኀይል ነጻ በመውጣት፣ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ባሮች በመሆን (ሮሜ 6፥18-22)፤ አማኞች "በክርስቶስ ሕግ ሥር" (1ቆሮ 9፥21) ሆነው "የእምነት" መርሕን ይከተላሉ። ይህን በማድረግ "የክርስቶስን ሕግ" (ገላ 6፥2) እንፈጽማለን፤ ስለዚህም ለሕግ ግዴታዎች ታማኞች እንሆናለን (ሮሜ 7፥4 እና ማብ፤ 8፥4 እና ማብ፤ ገላ 3፥19 እና ማብ፤ 5፥16-25 ይመ)።

(6) የሰማይ አባቱን ፈቃድ ማድረግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚያስችል የማያቋርጥ ግዴታ መሆኑን ኢየሱስ በአጽንዖት አስተምሮአል (7፥21 እና ማብ ይመ)።

**5፥19 በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ፤** በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አማኞች ያላቸው ስፍራ የሚወሰነው፣ ለእግዚአብሔር ሕግ ባለን አመለካከት እንዲሁም በምናስተምረው ትምህርትና ይህንኑም በተግባር ላይ በምናውልበት ሁኔታ ነው። በዚህ ረገድ ያለን ታማኝነት

ትእዛዞች አነስተኛዪቱን እንኳን ቢተላለፍ፣
ሌሎችንም እንዲተላለፉ ቢያስተምር
በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤
ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈጸመ
ሌሎችም እንዲፈጽሙ የሚያስተምር
በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይባላል።
[20]ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ
መምህራን ጽድቅ ልቆ ካልተገኘ መንግሥተ
ሰማይ መግባት አትችሉም።

## ነፍስ መግደል አይገባም

*5፥25፡26 ተጓ ምብ — ሉቃ 12፥58፡59*

[21]"ለቀደሙት ሰዎች፣'አትግደል፤የገደለ
ይፈረድበታል' እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤
[22]እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ወንድሙን ያለ አግ
ባብ የሚቈጣ ይፈረድበታል፤ ማንም ወንድ
ሙን 'ጅል' የሚል በሸንጎ ፊት ይጠየቅበ
ታል፤ 'ደደብ' የሚለው ደግሞ የገሃነመ
እሳት ፍርድ ይጠብቀዋል።
[23]"ስለዚህ መባህን በመሠዊያው ላይ
ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ወንድምህ
የተ ቀየመብህ ነገር መኖሩ ትዝ ቢልህ፣
[24]መባ ህን በዚያው በመሠዊያው ፊት
ተወው፤ በመጀመሪያ ሂደህ ከወንድምህ
ጋር ተስማማ፤ ከዚያም ተመልሰህ መባህን
ለእግዚአብሔር አቅርብ።
[25]"የከሰሰህ ባላጋራህ እንዳያስፈርድብህ፣
ዳኛውም ለእሳሪ አሳልፎ እንዳይሰጥህ፣
በወህኒም እንዳትጣል፣ በመንገድ ላይ
ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ።
[26]እውነት እልሃለሁ፤ ካስፈረደብህ ግን
የመጨረሻዋን ሳንቲም[ሀ] እስክትከፍል ድረስ
ከዚያ አትወጣም።

## ማመንዘር አይገባም

[27]"'አታመንዝር' እንደ ተባለ
ሰምታችኋል። [28]እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን
በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ
ከእርሷ ጋር አመንዝሯል።[29]ቀኝ ዓይንህ
የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ
ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም
ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ
ይሻልሃል። [30]ቀኝ እጅህ የኀጢአት ሰበብ
ቢሆንብህ ቈርጠህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ
በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ
አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል።
[31]"'ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ የፍቺ
ወረቀት መስጠት አለበት' እንደተባለ
ሰምታችኋል። [32]እኔ ግን እላችኋለሁ፤
በሳዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፣
ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እንድታመነዝር
ያደርጋታል፤ በዚህ ሁኔታ የተፈታችውን
ሴት ያገባም እንዳመ ነዘረ ይቈጠራል።

## ስለ መሐላ

[33]"ለቀደሙት ሰዎች፣ 'በሐሰት

[ሀ]5፥26 ግሪኩ ኮድራንቲስ ይላል

5፥20 ኢሳ26፥2፡ ማቴ18፥3፡ ዮሐ3፥5
5፥21 ዘፀ20፥13፡ 21፥12፡ ዘዳ5፥17
5፥22 መክ7፥9፡ ማቴ18፥9፡ 26፥59፡ ማር9፥43፡48፡ ሉቃ16፥24፡ ዮሐ11፥47፡ ሐሥ5፥21፡27፡ 34፡41፡ 6፥12፡ 1ቆሮ13፥5
5፥27 ዘፀ20፥14፡ ዘዳ5፥18
5፥28 ምሳ6፥25፡ 2ጴጥ2፥14
5፥29 ቍ 30፡ ማቴ18፥6፡8፡9፡ ማር9፥42-47፡ ሉቃ17፥2፡ ሮሜ14፥21፡ 1ቆሮ8፥13፡ 2ቆሮ6፥3፡ 11፥29፡ ኤፌ4፥26፡ ያዕ1፥19፡20፡ 3፥6፡ 1ዮሐ3፥15
5፥30 ቍ 29
5፥31 ዘዳ24፥1-4
5፥32 ሉቃ16፥18
5፥33 ዘሌ19፥12፡ ዘኍ30፥2፡ ዘዳ23፥21፡ ማቴ23፥16-22

---

በእግዚአብሔር መንግሥት የሚኖረንን የክብር ደረጃ ይወስናል (በገጽ 1822 ላይ፣ *"በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**5፥20 ጽድቃችሁ ... ልቆ ካልተገኘ፤** የፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን ጽድቅ የታይታ ጽድቅ ብቻ ነበር:: ፈሪሳውያን ብዙ ሕጎችን አከበሩ፡ ይጸልዩ፣ ያመሰግኑ፣ ይጾሙ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል ያነቡ፡ ደግሞም ልዩ ልዩ የአምልኮ ስብሰባዎችን ያደርጉ ነበር:: ይሁን እንጂ መኖር የሚገባውን ትክክለኛ ውስጣዊ ሁኔታ በውጫዊ ድርጊቶች ተክተው ነበር:: እግዚአብሔር ከአማኙ የሚሻው ጽድቅ ግን ከዚህ የበለጠ መሆን እንዳለበት ጌታ ኢየሱስ አስተማረ:: ውጫዊ ድርጊቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ልብና መንፈስም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር በእምነትና በፍቅር ሊስማሙ ይገባል (ማር 7፥6 እና በሕግ አክራሪነት ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)::

**5፥22 የሚቈጣ ... ጅል ... ደደብ፤** ኢየሱስ በክፉዎችና ትክክለኛ ባልሆኑ ሰዎች ላይ ሊሰነዘር ስለሚገባው የጽድቅ ቍጣ መናገሩ ሳይሆን (ከዮሐ 2፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሰው ይጐዳ ዘንድ ስለሚያደርግ ቂም በቀል የተሞላበት ቍጣ ነው:: "ጅል" የሚለው ቃል ሌላውን ሰው የመናቅና የማዋረድ ቃል ሲሆን፣ ባዶ ቅል እንደ ማለት ነው:: ሰውን በመቈጣትና በማዋረድ፣ "እግዚአብሔርን የማይፈራ ደደብ" የሚል ራሱን፣ "ለገሃነመ እሳት ፍርድ" በመዳረግ የልቡን ሐሳብ ሊገልጥ ይችላል::

**5፥28 በምኞት ዓይን የተመለከተ፤** ክርስቶስ እዚህ ላይ የሚያወግዘው ድንገት ሰይጣን በሰው አእምሮ ውስጥ ሊያስቀምጥ የሚችለውን ወይም ድንገት የሚነሣሣውን ተገቢ ያልሆነ ምኞት አይደለም፤ ያወገዘው በራስ አነሳሽነት ወይም ፈቃድ የተነሣሣውን በጥል ሐሳብ ነው:: ኢጋጣሚ ከተገኘ ኢግብረገባዊ የሆነውን ምኞት ለመፈጸም የሚያነሣሣ ፍላጎት ነው:: ተገቢ ባልሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ደስታን ለማግኘት የሚፈታተንን የውስጥ መሻት ለመፈጸም አጥብቆ ማሰብና ይህን ስሜት በቈራጥነት አለመቃወም ኀጢአት ነው (በገጽ 1980 ላይ፣ *"ሩካቤ ሥጋ የሚገዛበት ሥነ ምግባር"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(1) ክርስቲያን በተለይም አሳፋሪ የሆኑ ኢሥነምግባራዊ ትዕይንቶችን ማለትም ወሲባዊ ግንኙነትን የሚያሳዩ ፊልሞችን ከማየት ወይም የወሲብ ፍላጎትን የሚያነሣሡ ጽሑፎችን ከማንበብ ራሱን ለመጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል (ከ1ቆሮ 6፥15፡18፡ ከገላ 5፥19፡21፡ ከኤፌ 5፥5፡ ከቈላ 3፥5፡ ከ2ጢሞ 2፥22፡ ከቲቶ 2፥12፡ ከዕብ 13፥4፡ ከያዕ 1፥14፡ ከ1ጴጥ 2፥11፡ ከ2ጴጥ 3፥3፡ ከ1ዮሐ 2፥16 ጋር ያነጻጽሩ)::

(2) የወሲባዊ ግንኙነትን ቅድስና በተመለከተ ሴትም ሆነች ወንድ ኀላፊነት አለባቸው:: ስለዚህም ክርስቲያን ሴት የወንዶችን ዓይን ወደ አካሏ በሚስብ ሁኔታ በመልበስ፣ ወንዶች ለዝሙት እንዲነሣሡና ለፈተና እንዲጋለጡ ከሚያደርግ ማንኛውም ድርጊት ራሷን መጠበቅ ይኖርባታል:: ወሲባዊ ስሜትን የሚያነሣሣ ተገቢ ያልሆነ አለባበስ ኀጢአት ነው (1ጢሞ 2፥9፡ 1ጴጥ 3፥2-3)::

**5፥29 ገሃነም፤** ማር 9፥43 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**5፥32 በሳዩ ላይ ስታመነዝር ካላገኛት በስተቀር፤** 19፥9 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

አትማል፤ በእግዚአብሔር ፊት የማልኸውንም
ጠብቅ' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 34እኔ ግን
ፈጽሞ አትማሉ እላችኋለሁ፤ በሰማይም
ቢሆን አትማሉ፤ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤
35በምድርም ቢሆን አትማሉ፤ የእግዚአብሔር
የእግሩ ማረፊያ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም
አትማሉ፤ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና
36በራሳችሁም ቢሆን አትማሉ፤ ከጠጕራችሁ
መካከል አንዲቷን እንኳ ነጭ ወይም ጥቍር
ማድረግ አትችሉምና። 37ስለዚህ ስትነጋገሩ
ቃላችሁ፣ 'አዎን' ከሆነ፣ 'አዎን'፤
አይደለም፣ ከሆነ 'አይደለም' ይሁን፤ ከዚህ
ውጭ የሆነ ሁሉ ከክፉው የሚመጣ ነውና።

## ስለ መበቀል

38"'ዓይን ስለ ዓይን፣ ጥርስ ስለ
ጥርስ' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 39እኔ
ግን እላችኋለሁ፤ 'ክፉ አድራጊውን ሰው
አትቃወሙት'፤ ነገር ግን ቀኝ ጕንጭህን
ለሚመታህ ሌላውን ጕንጭህን ደግሞ
አዙርለት። 40አንድ ሰው እጀ ጠባብህን
ሊወስድ ቢከስህ ካባህን ጨምረህ ስጠው።
41አንድ ሰው አንድ ኪሎ ሜትር ተኩል
የሚያህል ርቀት እንድትሄድ ቢያስገድድህ
ዕጥፉን መንገድ አብረኸው ሂድ።
42ለሚለምንህ ስጥ፤ ከአንተም ሊበደር
የሚሻውን ፊት አትንሣው።
43"'ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላትህን
ጥላ' እንደ ተባለ ሰምታችኋል። 44እኔ ግን
ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣† ለሚያሳድዷችሁም
ጸልዩ እላችኋለሁ። 45እንደዚህም
በማድረጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ
ልጆች ትሆናላችሁ፤ እርሱ ፀሓዩን
ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም
ለኀጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል።
46የሚወዷችሁን ብቻ የምትወዱ ከሆነ
ምን ዋጋ ታገኛላችሁ? ቀራጮችስ ይህንኑ

5፥34 ኢሳ66፥1፤ ማቴ23፥22፤ ያዕ5፥12
5፥35 መዝ48፥2
5፥37 ማቴ6፥13፤ 13፥19፡38፤ ዮሐ17፥15፤ ኤፌ6፥16፤ 2ተሰ3፥3፤ ያዕ5፥12፤ 1ዮሐ2፥13፡14፤ 3፥12፤ 5፥18፡19
5፥38 ዘፀ21፥24፤ ዘሌ24፥20፤ ዘዳ19፥21
5፥39 ሉቃ6፥29፤ ሮሜ12፥17፡19፤ 1ጴጥ3፥9
5፥42 ዘዳ15፥8፤ ሉቃ6፥30
5፥43 ዘሌ19፥18፤ ዘዳ23፥6፤ መዝ139፥21፡22፤ ማቴ19፥19፤ 22፥39፤ ማር12፥31፤ ሉቃ10፥27፤ ሮሜ13፥9፤ ገላ5፥14፤ ያዕ2፥8
5፥44 ሉቃ6፥27፡28፤ 23፥34፤ ዮሐ15፥20፤ ሐሥ7፥60፤ ሮሜ8፥35፤ 12፥14፤ 1ቆሮ4፥12፤ 1ጴጥ2፥23
5፥45 ቍ9፤ ኢዮ25፥3፤ ሉቃ6፥35፤ ሮሜ8፥14
5፥46 ሉቃ6፥32
5፥48 ዘሌ19፥2፤ 1ጴጥ1፥16
6፥1 ማቴ5፥16፤ 23፥5

ያደርጉ የለምን? 47ወንድሞቻችሁን ብቻ
እጅ የምትነሡ ከሆነ ከሌሎች በምን
ትሻላላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደ ርጉ
የለምን? 48ስለዚህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም
እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።"

## ስለ ምጽዋት አሰጣጥ

6 "ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም
ሥራችሁን በፊታቸው ከማድረግ
ተጠንቀቁ፤ እንዲህ ካደረጋችሁ ከሰማዩ
አባታ ችሁ ዋጋ አታገኙም።
2"በሰዎች ዘንድ ለመከበር ብለው
በየኵራናውና በየምኩራቡ ጥሩምባ
እንደሚያስነፉ ግብዞች፣ እናንተም ለድኾች
ምጽዋት በምትሰጡበት ጊዜ ይታይልኝ
ብላችሁ አታድርጉ፤ እውነት እላችኋለሁ
እንዲህ የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ
ተቀብለዋል። 3እናንተ ግን ለድኾች ስትሰጡ
ቀኝ እጃችሁ የሚያደርገውን ግራ እጃችሁ
አይወቅ፤ 4ምጽዋታችሁ በስውር ይሁን፤
በስውር የተደረገውን የሚያይ አባታችሁም
ዋጋችሁን ይከፍላችኋል።

## ስለ ጸሎት

*6፥9-13 ተጓ ምብ — ሉቃ 11፥2-4*

5"ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤
እነርሱ ለሰዎች ለመታየት ሲሉ በየምኩራቡና
በየመንገዱ ማእዘን ላይ ቆመው መጸለይ
ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ሙሉ
ዋጋ ቸውን ተቀብለዋል። 6አንተ ግን
ስትጸልይ ወደ ክፍልህ ግባ፤ በሩንም ዘግተህ
በስውር ወዳለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር

6፥4 ቍ6፥18፤ ቈላ3፥23፡24 6፥5 ማር11፥25፤ ሉቃ18፥10-14 6፥6 2ነገ4፥33

*†5፥44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ ይላሉ*

---

**5፥39 ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወሙት፤** ኢየሱስ ይህን የተናገረው ክፉ ሥራ በሚሠሩ ሰዎች ላይ የሚወሰደውን ተገቢ የአስተዳደር ርምጃ በመቃወም አይደለም (ከሮሜ 13፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህ ሐሳብ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች (ቍ 43-48) ጠላትን ስለመውደድ የተናገረ መሆኑን ያመለክታሉ (ቍ 44፤ ሉቃ 6፥27)። ክፉ ነገር ሲደርስብን በጥላቻ መንፈስ ምላሽ መስጠት የለብንም፤ ነገር ግን በክርስቶስና በመንግሥቱ ላይ የተመሠረቱ ፋይዳዎች እንዳሉን በሚያሳይ መንገድ ምላሽ መስጠት ይኖርብናል። ክፉ ነገር ላደረሱብን ሰዎች የምንሰጠው ምላሽ፣ እነርሱ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉት የሚያበቃቸው መሆን አለበት። ይህን መንፈሳዊ ልምምድ ከሚከተሉት ምሳሌዎች ጋር አነጻጽሩ፤ ዘፍ 13፥1-13ን ከዘፍ 14፥14 ጋር፤ ዘፍ 50፥19-21ን ከዘፍ 37፥18-28 ጋር፤ እንዲሁም 1ሳሙ 24 እና 26፤ ሉቃ 23፥34፤ ሐሥ 7፥60 ይመልከቱ።

**6፥1 ሰዎች እንዲያዩላችሁ፣ መልካም ሥራችሁን፤** በዚህ ስፍራ የተገለጸው መርሕ በጽድቅ ለመሥራት ካለን ተነሣሽነት ጋር የተያያዘ ነው፤ (1) አማኞች ማለት አገልጋዮችም ሆኑ ተራ ምእመናን መልካም ነገርን የሚያደርጉት ሌሎች እንዲያደንቋቸው ወይም ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ከሆነ፣ ዋጋቸውንና ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን ሽልማትና ዋጋ ያጣሉ። ይልቁንም ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ሽፋን ለራሳቸው ክብርን የሚሹ ግብዞች መሆናቸው ይጋለጣል።

(2) ጌታ ኢየሱስ መልካም ሥራን አስመልክቶ ስለሚከተሉት ሦስት አቅጣጫዎች ይገልጻል፤ እነርሱም መስጠት (ቍ 2-4)፣ ጸሎት (ቍ 5-8) እና ጾም (ቍ 16-18) ናቸው። ለታይታ ሲባል የሚደረገውን መልካም ሥራ ማውገዙ የዚህን ዘመን ክርስቲያናዊ ተግባር አጠያያቂ እንዲሆን ያደርገዋል፤ ይኸውም ታላቅ ለመሆን የማድረግ ፉክክርን፣ የራስን ስኬታማነት ማግነንን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መስሎ መታየትንና ተዝናንቶ መኖርን፣ በሁሉ ነገር ቀዳሚ ለመሆን መፈለግን ይጨምራል (1ቆሮ 3፥13-15፤ 4፥5 ይመ)።

**6፥6 በስውር ... ጸልይ፤** ማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ከአምላኩ ጋር ለብቻው የሚሆንበት ስፍራ ሊኖረው ይገባል። እንዲህ ዐይነቱ ስፍራ ከሌለ ስውር ጸሎት ሊረዝም ወይም በተከታታይነት ሊዘወትር አይችልም። ጌታ ኢየሱስ ስውር የጸሎት ስፍራዎች

የተደረገውን የሚያይ አባትህም ዋጋህን
ይከፍልሃል። 7ስትጸልዩ፣ ከንቱ ቃላት
በመደጋገም ጸሎታቸው የሚሰማላቸው
እንደሚመስላቸው አሕዛብ ነገራችሁን
አታስረዝሙ። 8እነርሱን አትምሰሏቸው፤
አባታችሁ ከመለመናችሁ በፊት ምን
እንደሚያስፈልጋችሁ ያውቃልና።
9"እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤
" 'በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤
ስምህ ይቀደስ፤
10መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣
እንዲሁ በምድር ትሁን።
11የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን።
12እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር
እንደምንል፣
በደላችንን ይቅር በለን።
13ወደ ፈተናም አታግባን
ከክፉው አድነን እንጂ፣
*መንግሥት፣ ኀይል፤ ክብርም፣*
*ለዘላለሙ ያንተ ነውና፤*
*አሜን።*[a]'

6፥7 1ነገ18፥26-29፤ መክ5፥2
6፥8 ቍ32
6፥9 ኤር3፥19፤ ሚል2፥10፤ 1ጴጥ1፥17
6፥10 ማቴ3፥2፤ 26፥39
6፥11 ምሳ30፥8
6፥12 ማቴ18፥21-35
6፥13 ማቴ5፥37፤ ያዕ1፥13

[a]6፥13 በግሪኩ ይህ የለም፤ ሆኖም በሌሎች የተንት ትርጕሞች ይገኛል

ነበሩት (14፥23፤ ማር 1፥35፤ ሉቃ 4፥42፤ 5፥16፤ 6፥12)። ስውር ጸሎት በተለይ በሚከተሉት ምክንያቶች እጅግ አስፈላጊ ነው፤ (1) በማለዳ የቀን ውሎአችንን ለእግዚአብሔር ለማስረከብ፤ (2) በምሽት ስለ ምሕረቱ ምስጋናችንን ለማቅረብ፣ (3) መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ በሚያነሣሣን ጊዜ ለመጸለይ። አባታችን በግልጽ ዋጋችንን ሊከፍለን የተስፋ ቃል ሰጥቶናል፤ ይኸውም ጸሎታችንን ሊመልስልን፣ ሀልዎቱን ሊያረጋግጥልንና ለዘላለም ሕይወትም እውነተኛ ክብርን ሊያጐናጽፈን ነው (6፥9 እና ስለ እግዚአብሔር አባትነት የተሰጠውን ማብ ይመ)።

**6፥9 እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤** በዚህ የጸሎት ዐይነተኛ ምሳሌ ክርስቶስ የክርስቲያን ጸሎት ምን ምን ማካተት እንዳለበት አመልክቶአል። ይህ የጸሎት ዐይነተኛ ምሳሌ ስድስት ልመናዎችን ይዞአል፤ ሦስቱ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ፈቃድ በተመለከተ የሚቀርቡ ሲሆኑ፣ የቀሩት ሦስቱ ደግሞ የግል ፍላጎታችንን በተመለከተ የሚቀርቡ ናቸው። የጸሎቱ ዐጭር መሆን ስለ ግል ጕዳዮችን ብቻ በዐጭሩ መጸለይ እንዳለብን የሚያሳይ አይደለም። ክርስቶስ ሌሊቱን ሙሉ የጸለየበት ጊዜ ነበርና (ሉቃ 6፥12)።

**6፥9 በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤** ጸሎት የሰማይ አባታችንን ማምለክን ይጨምራል፤ (1) እግዚአብሔር አባታችን በመሆኑ ይወደናል፤ ይንከባከበናል፤ እኛ ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረትና አንድነት በደስታ ይቀበላል። በክርስቶስ በኩል በማንኛውም ጊዜ እርሱን ለማምለክና ፍላጎታችንን ለእርሱ ለመግለጽ እንችላለን (ቍ 25-34)። (2) አባታችን እግዚአብሔር እንደ ምድራዊ አባት ልጆቹ ክፋት ሲሠሩ እያየ እንዲሁ የሚያልፍ ወይም ሳይገሥጽና ሳይቀጣ የሚተው አይደለም። እግዚአብሔር ኀጢአትን የሚቃወም የቅድስና አባት ነው። አባታችን ብለው የሚጠሩትን እንኳ ክፉ ሥራ ሲሠሩ አይታገሥም፤ ስሙ መቀደስ አለበትና። (3) የሰማይ አባት እንደ መሆኑ መጠን *መቀጣት ወይም መባረክ፤ መከልከል ወይም መስጠት፣ መፍረድ ወይም ምሕረትን ማድረግ ይችላል።* እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሰጠው ምላሽ የሚወሰነው በእርሱ ላይ ባላቸው እምነት ወይም ለእርሱ በሚያሳዩት መታዘዝ ነው።

**6፥9 ስምህ ይቀደስ፤** በምናደርገው ጸሎትና በምንኖረው ኑሮ ትልቁ ጕዳያችን የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ መሆን አለበት። እጅግ ከፍተኛና አስፈላጊ የሆነው ነገር እግዚአብሔር መቀደሱ፣ መከበሩና ከፍ ከፍ ማለቱ ነው (ከመዝ 34፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። በጸሎታችንና በዕለት ተዕለት ርምጃችን ለእግዚአብሔር፣ ለቤተ ክርስቲያኑ፤ ለወንጌሉና ለመንግሥቱ ክብር አጥብቀን ልናስብ ይገባል። በእግዚአብሔር ስምና ባሕርይ ላይ ነቀፌታን የሚያመጣ ነገርን መፈጸም፣ እግዚአብሔርን በግልጽ የሚያቃልል አስከፊ ኀጢአት ነው።

**6፥10 መንግሥትህ ትምጣ፤** ጸሎት አሁን በምድር ላይ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥትና ለወደፊት ይህ መንግሥት በመጨረሻ በሚደርስበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ማተኰር አለበት። (1) ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንዲሁም በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ላይ ስለሚመሠረተው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት መጸለይ አለብን (ራእ 21፥1 ይመ፤ ከ2ጴጥ 3፥10-12፤ ከራእ 20፥11፤ 22፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) አሁን የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ ሀልዎትና መገለጥ እውን እንዲሆን መጸለይ አለብን። ይህም የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ የእግዚአብሔርን ኀይል በሕዝቡ መካከል እንዲገለጥ ማድረግን፣ ድውያንን መፈወስን፤ የጠፉትን ማዳንን፣ የጽድቅን ሕይወት ማስፈንንና በሕዝቡ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲወርድ ማድረግን ያካትታል (በገጽ 1443 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር መንግሥት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥10 ፈቃድህ ... ትሁን፤** ፈቃድህ ትሁን ብሎ መጸለይ በዘላለም ዕቅዱ መሠረት የእግዚአብሔር ፈቃድና ዐላማ በእኛ ሕይወትና በቤተሰቦቻችን ሕይወት እንዲፈጸም በእውነት እንሻለን ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተገለጠው ቃሉ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስና በልባችን ውስጥ ምሪቱን በሚያሳየን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አስቀድመን ልናውቅ እንችላለን (ከሮሜ 8፥4-14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1075 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር ፈቃድ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸመው፣ "መንግሥቱና ጽድቁ" በመካከላችን ይገኙ ዘንድ በምንጸልይበት ጊዜ ነው (ቍ 33 ይመ፤ በገጽ 1443 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር መንግሥት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥11 የዕለት እንጀራችንን፤** ጸሎት እያንዳንዱ ግለሰብ በየዕለቱ የሚያስፈልገው እንዲሟላለት የሚያደርጉ ጥያቄዎችን የያዘ መሆን አለበት (ፊል 4፥19 ይመ፤ ሉቃ 11፥3 እና ማብ ይመ)።

**6፥12 የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ ... ይቅር በለን፤** ጸሎት ኀጢአትን መናዘዝና የበደሉንን ሰዎች ይቅር ለማለት ፈቃደኛ መሆንን የሚመለከት መሆን አለበት (ቍ14-15፤ ዕብ 9፥14፤ 1ዮሐ 1፥9)።

**6፥13 ከክፉው አድነን፤** አማኞች ሁሉ ለሰይጣን ጠላትነትና ለክፋት ዕቅድ ልዩ ዒላማ ናቸው። ስለዚህ ከእርሱ ኀይልና የተንኰል ሥራ እንድን ዘንድ መጸለይ የሚገባን መሆኑን ከቶ መርሳት የለብንም (ሉቃ 11፥26 እና ማብ፤ 18፥1 እና ማብ፤ 22፥31፤ ዮሐ 17፥15፤ 2ቆሮ 2፥11 ይመ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

14እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ
የሰ ማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር
ይላችኋል። 15ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት
ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም
ኀጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

### ስለ ጾም

16"ስትጾሙ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤
እነርሱ መጾማቸው እንዲታወቅላቸው ሆን
ብለው በፊታቸው ላይ የሐዘን ምልክት
ያሳያሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ እንዲህ
የሚያደርጉ ዋጋቸውን በሙሉ ተቀብለዋል።
17አንተ ግን በምትጾምበት ጊዜ ፊትህን
ታጠብ፤ ራስህንም ተቀባ፤ 18በዚህም መጾምህ
በስውር ያለው አባትህ ብቻ የሚያውቀው፣
ከሰዎች ግን የተሰወረ ይሆናል፤
በስውር የተደረገውን የሚያይ አባትህም
ዋጋ ህን ይከፍልሃል።

### ሰማያዊ ሀብት

*6፥22፡23 ተጓ ምብ — ሉቃ 11፥34-36*

19"ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣
ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በሚችልበት በዚህ
ምድር ላይ ለራሳችሁ ሀብት አታከማቹ።
20ነገር ግን ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣
ሌባም ቈፍሮ ሊሰርቀው በማይችልበት በዚያ
በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤ 21ሀብትህ
ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናልና።
22"ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤
ስለዚህ ዐይንህ ጤናማ ከሆነ መላው ሰውነትህ
በብርሃን የተሞላ ይሆናል። 23ዐይንህ ታማሚ
ከሆነ ግን መላው ሰውነትህ በጨለማ የተሞላ
ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ውስጥ ያለው
ብርሃን ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማው እንዴት
ድቅድቅ ይሆን?
24"አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል
አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን
ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን
ይን ቃል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ዮሐ 15፥18-20
ማገልገል አይቻልም።

### አለመጨነቅ

*6፥25-33 ተጓ ምብ — ሉቃ 12፥22-31*

25ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ

6፥14 ማቴ18፥21-35፤ ማር11፥25፡26፤ ኤፌ4፥32፤ ቆላ3፥13
6፥15 ማቴ18፥35
6፥16 ዘሌ16፥29፡31፤ 23፥27-32፤ ዘኍ29፥7፤ ኢሳ58፥5፤ ዘካ7፥5፤ 8፥19
6፥18 ቍ4፡6፤ ምሳ23፥4፤ ሉቃ12፥16-21፤ ዕብ13፥5፤ ያዕ5፥2፡3
6፥20 ማቴ19፥21፤ ሉቃ12፥33፤ 16፥9፤ 18፥22፤ 1ጢሞ6፥19
6፥21 ሉቃ12፥34
6፥24 ሉቃ16፥13
6፥25 ቍ27፡28፡31፡34፤ ሉቃ10፥41፤ 12፥11፡22

---

**6፥15 ይቅር የማትሉ ከሆነ፤** ጌታ ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ክርስቲያኖች የበደሏቸውን ሰዎች ይቅር ለማለት ዝግጁዎችና ፈቃደኞች መሆን እንዳለባቸው በአጽንዖት ተናግሯል። ንስሓ የሚገቡ በደለኞችን ይቅር የማይሉ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ይቅር አይላቸውም፤ ጸሎታቸውም ምንም ዐይነት ርዳታ አያመጣላቸውም። ይህ እግዚአብሔር ሰውን ይቅር የሚልበት መሠረታዊ መርሕ ነው (18፥35፤ ማር 11፥26፤ ሉቃ 11፥4)።

**6፥16 ስትጾሙ፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ጾም ለመንፈሳዊ ዐላማ ምግብ ላለመመገብ ራስን የመግዛትን ሥርዐት ያመለክታል። አብዛኛውን ጊዜ ከጸሎት ጋር የተያያዘ ቢሆንም እንኳ፣ በራሱ መንፈሳዊ ልምምድ እንደ ሆነ ሊቈጠር ይገባል። ይልቁንም ጾም፣ "ቃል አልባ ጸሎት" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

(1) በመጽሐፍ ቅዱስ ሦስት ዋና ዋና የጾም ዐይነቶች ተጠቅሰው ይገኛሉ፤ (ሀ) የተለመደው ጾም፤ ይህም ከውሃ በቀር ከደረቅ ወይም ከፈሳሽ ምግብ ሁሉ ራስን ማገድ ነው (4፥2 እና ማብ ይመ)። (ለ) ፍጹም ጾም፤ ይህ ደግሞ ከምግብና ከውሃ ራስን ማገድ ነው (አስ 4፥16፤ ሐሥ 9፥9)። እግዚአብሔር ካልረዳ በቀር እንዲህ ዐይነቱ ጾም አብዛኛውን ጊዜ ከሦስት ቀን በላይ አይቻልም፤ ሰውነታችን በውስጡ ያለውን ውሃ መጨረስ ይጀምራልና። ሙሴና ኤልያስ ለ40 ቀን ያህል ፍጹም ጾምን ጾመዋል፤ ይህም ሊሆን የቻለው በእግዚአብሔር መንፈስ ርዳታ ነበር (ዘፀ 34፥28፤ ዘዳ 9፥9፡18፤ 1ነገ 19፥8)። (ሐ) ከፊል ጾም፤ ይህ የተወሰኑ የምግብ ዐይነቶችን መተው እንጂ፣ ሙሉ በሙሉ ራስን ከምግብ ማገድ አይደለም (ዳን 10፥3)።

(2) ክርስቶስ ራሱ ጾሟል፤ የአንድ ክርስቲያን የሕይወት ልምምድ ክፍልና ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ክርስቲያን ራሱን የሚያዘጋጅበት ሥርዐት እንደ ሆነም ጌታ አስተምሯል (9፥15 እና ማብ ይመ)። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጾምን ትለማመድ ነበር (ሐሥ 13፥2-3፤ 14፥23፤ 27፥33)።

(3) ከጸሎት ጋር የሚደረግ ጾም የሚከተሉት አያሌ ዐላማዎች አሉት፦ (ሀ) እግዚአብሔርን ለማክበር (ቍ 16-18፤ ዘካ 7፥5፤ ሉቃ 2፥37፤ ሐሥ 13፥2)፤ (ለ) የበለጠ ጸጋ እንድናገኝና (1ጴጥ 5፥5) የእግዚአብሔርን ቅናብ ሀልዎት እንድንለማመድ (ኢሳ 57፥15፤ 58፥6-9) ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ለማዋረድ (ዕዝ 8፥21፤ መዝ 69፥10፤ ኢሳ 58፥3)፤ (ሐ) ስለ ግል ኀጢአትና ውድቀት በመጸጸት ለማልቀስ (1ሳሙ 7፥6፤ ነህ 9፥1-2)፤ (መ) ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሕዝብና ስለ ዓለም በደል ሁሉ በመጸጸት ለማልቀስ (1ሳሙ 7፥6፤ ነህ 9፥1-2)፤ (ሠ) ለአዲስ ሥራ ጸጋን ለመሻትና ለእግዚአብሔር መለየታችንን እንደ ገና ለማረጋገጥ (4፥2)፤ (ረ) ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እርሱን ለመፈለግና ተቃዋሚ መንፈሳዊ ኀይሎችን መታገል ይቻል ዘንድ በጸሎት ለመጽናት (መሳ 20፥26፤ ዕዝ 8፥21፡23፡31፤ ኤር 29፥12-14፤ ኢዩ 2፥12፤ ሉቃ 18፥3፤ ሐሥ 9፥10-19)፤ (ሰ) ንስሓ ለመግባትና እግዚአብሔር ሊያመጣ ያሰበውን ፍርድ እንዲያስቀር ለማድረግ (2ሳሙ 12፥16፡22፤ 1ነገ 21፥27-29፤ ኤር 18፥7-8፤ ኢዩ 2፥12-14፤ ዮና 3፥5፡10)፤ (ሸ) ሰዎችን ከክፉት እስራት ለማዳን (ኢሳ 58፥6፤ ማቴ 17፥14-21፤ ሉቃ 4፥18)፤ (ቀ) የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተመለከተ መገለጥንና ጥበብን ለማግኘት (ኢሳ 58፥5-6፡11፤ ዳን 9፥3፡21-22፤ ሐሥ 13፥2-3)፤ (በ) መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድና ክርስቶስ ለሕዝቡ ወደ ምድር ዳግም እንዲመጣ መንገድ ለመክፈት (9፥15 እና ማብ ይመ)።

**6፥24 ገንዘብን፤** (1) ገንዘብን ማምለክ ገንዘብን አምላክ አድርጎ መቀበር ማለት ነው፤ ይኸውም፣ (ሀ) መተማመኛችንንና እምነታችንን በእርሱ ላይ እናደርጋለን፤ (ለ) የሰላምና የጸጥታችን እንዲሁም የደስታችን ከፍተኛ ምንጭ እናደርገዋለን፤ (ሐ) የወደፊት ዋስተናችንን በማድረግ እንደገፍበታለን፤ (መ) ከእግዚአብሔር መንግሥትና ጽድቅ ይልቅ አብልጠን እንሻዋለን። (2) ሀብትን ማካበት አእምሮንና ሕይወትን ፈጥኖ ስለሚቈጣጠር የእግዚአብሔር ክብር ቅድሚያ እንዲሰጠው አያደርግም (በገጽ 1577 ላይ፣ "***ብልጽግናና ድህነት***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥25 አትጨነቁ፤** ኢየሱስ እንዲህ ሲል ለሥጋችን የሚያስፈልገንን ለማዘጋጀት መሥራት አያስፈልገንም

ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ
እንለብሳለን? በማለት አትጨነቁ። ሕይወት
ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን?
²⁶እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤
አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም
አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ
ይመግባቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ
አትበልጡምን?²⁷ለመሆኑ ከእናንተ መካከል
ተጨንቆ በዕድሜው ላይ አንዲት ሰዓት*
መጨመር የሚችል አለን?
²⁸"ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን
ትጨነቃላችሁ? እስቲ የሜዳ አበቦችን
ተመልከቱ፤ አይለፉም፤ ወይም
አይፈትሉም። ²⁹ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ያን
ያህል ክብር የነበረው ንጉሥ ሰሎሞን እንኳ
ከእነዚህ አበቦች እንደ አንዷ አልለበሰም።
³⁰እናንተ እምነት የጐደላችሁ እግዚአብሔር ዛሬ
ታይቶ በነጋታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን
የሜዳ ሣር ይህን ያህል ካለበሰ እናንተንማ
እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁ? ³¹ስለዚህ፣
'ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ
እንለብሳለን?' ብላችሁ አትጨነቁ፤
³²አሕዛብ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማግኘት
ይጨነቃሉና፤ የሰማዩ አባታችሁም እነዚህ
ሁሉ ለእናንተ እንደሚያስፈልጓችሁ
ያውቃል። ³³ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን
የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤
እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል። ³⁴ስለዚህ
ለነገ በማሰብ አትጨነቁ፤ የነገ ጭንቀት

6፥26 ኢዮ38፥41፤ መዝ104፥21፤ 136፥25፤ 145፥15፤ 147፥9፤ ማቴ10፥29-31
6፥27 መዝ39፥5
6፥29 1ነገ10፥4-7
6፥30 ማቴ8፥26፤ 14፥31፥16፥8፤ ሉቃ12፥28
6፥32 ቍ8
6፥33 መዝ37፥4፤ ማቴ3፥2፤ 19፥29
7፥1 ሉቃ6፥37፤ ሮሜ14፥4፥10፥13፤ 1ቆሮ4፥5፤ 5፥12፤ ያዕ4፥11፥12
7፥2 ሕዝ35፥11፤ ማር4፥24፤ ሉቃ6፥38፤ ሮሜ2፥1
7፥7 1ነገ3፥5፤ ማቴ18፥19፤ 21፥22፤ ዮሐ14፥13፥14፤ 15፥7፥16፤ 16፥23፥24፤ ያዕ1፥5-8፤ 4፥2፥3፤ 5፥16፤ 1ዮሐ3፥22፤ 5፥14፥15

ለነገ ይደር፤ እያንዳንዱ ዕለት የራሱ የሆነ
በቂ ችግር አለውና"።

## በሌሎች ላይ አለመፍረድ

*7፥3-5 ተጓ ምብ — ሉቃ 6፥41፥42*

7 "እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ
አትፍረዱ፤ ²በምትፈርዱበትም ዐይነት
ይፈረድባችኋል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈ
ሪያ ይሰፈርላችኋል።
³"በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ
ሳትመለከት፣ በወንድምህ ዐይን ያለውን
ጕድፍ ለምን ታያለህ? ⁴በዐይንህ ውስጥ
ግንድ እያለ ወንድምህን፣ 'ዐይንህ ውስጥ
ያለውን ጕድፍ ላውጣልህ' ማለት እንዴት
ትችላለህ? ⁵አንተ ግብዝ፤ አስቀድመህ
በዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ አውጣ፤
ከዚያም በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን
ጕድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።
⁶"በእግራቸው እንዳይረግጡት፣
ተመልሰውም ነክሰው እንዳይቦጫጭቁቻችሁ፣
የተቀደሰ ነገር ለውሾች አትስጡ፤
ዕንቍቻችሁን ም በእሪያ ፊት አትጣሉ።

## ለምኑ፤ ፈልጉ፤ አንኳኩ

*7፥7-11 ተጓ ምብ — ሉቃ 11፥9-13*

⁷"'ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ፣

*6፥27 ወይም በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ

ማለቱ አይደለም (ከ2ቆሮ 12፥14፡ ከ1ጢሞ 5፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። እርሱ የከለከለው ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር አባታዊ እንክብካቤና ፍቅር ላይ እምነት እንደ ጠፋ የሚያሳየውን ሥጋት ወይም ጭንቀት ነው (ሕዝ 34፥12፤ 1ጴጥ 5፥7 እንዲሁም የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**6፥30 ይህን ያህል ካለበሰ፤** እነዚህ ቃሎች ችግርና አለመተማመን ባለበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ለልጆቹ ሁሉ ያለውን የተስፋ ቃል የያዙ ናቸው። እግዚአብሔር ምግባችንን፣ ልብሳችንንና የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚሰጠን የተስፋ ቃል ገብቶልናል። መጨነቅ የለብንም፤ እግዚአብሔር ሕይወታችንን እንዲገዛ የምንፈልግ ከሆነ (ቍ 33)፣ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ አሳልፈው ለሰጡት ጠቅላላ ኀላፊነት እንደሚወስድ ርግጠኞች ልንሆን እንችላለን (ፊል 4፥6፤ 1ጴጥ 5፥7 ይመ፤ በገጽ 100 ላይ፣ *"መግቦተ እግዚአብሔር"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥33 የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤** ክርስቶስን የሚከተሉት ከሁሉም በላይ የእርሱን መንግሥትና ጽድቁን እንዲሹ ይነግሣሉ። "እሹ" የሚለው ግስ አንድን ነገር ለማግኘት ሲባል ሳያቋርጡ በሚፈለገው ነገር መመሰጥን ወይም የሚፈለገውን ለማግኘት ብርቱና ትጋት የሞላበት ጥረት ማድረግን ያመለክታል (ከ13፥45 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ መሻታችን በሁለት ዐላማ ላይ ማተኮር እንዳለበት አመልክቶአል፤ (1) "የእግዚአብሔር መንግሥት" ማለትም የእግዚአብሔር ሕግና ኀይል በሕይወታችንና በጉባኤያችን መካከል እንዲገለጥ ከልብ መሻት አለብን። የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ ታላቅ ኀይል መጥቶ ኀጢአተኞችን እንዲያድን፣ በአጋንንት አሰራት ያሉትን እንዲፈታ፣ ደዌያንን እንዲፈውስና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከፍ ከፍ እንዲያደርግ መጸለይ አለብን (በገጽ 1443 ላይ፥ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) "ጽድቁን" ማለትም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለክርስቶስ ሕጎች መታዘዝን፣ የክርስቶስን ጽድቅ መውረስን፥ ከዓለም ተለይቶ መኖርንና የክርስቶስን ፍቅር ለሁሉም ሰው ማሳየትን መሻት አለብን (ከፊል 2፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

**7፥1 አትፍረዱ፤** የራስን ስሕተት ችላ ብሎ ሌላውን ሰው የማውገዝ ልማድን ኢየሱስ ያወግዛል። አማኞች የሌሎች ክርስቲኖችን ባሕርይና እንቅስቃሴ ለመመርመር ሙከራ ከማድረጋቸው በፊት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የጽድቅ መለኪያዎች ማስገዛታቸውን ርግጠኞች መሆን አለባቸው (ቍ 3-5)። ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ መፍረድ ጥፋተኛ የሆነው ሰው ወደ እግዚአብሔርና ወደ መንገዶቹ ተመልሶ ያለማየት ፍላጎትን ያከትታል (ሉቃ 6፥36-37)።

(1) ክርስቶስ ሌሎች ላይ የሚታዩን ኀጢአት በተመለከተ ለይቶ ለማወቅ ጥረት የማድረግን ወይም ተገቢ ፍርድ የመስጠትን አስፈላጊነት አልተቃወመም። በሌላ ስፍራ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ሐሰተኛ አገልጋዮችን እንድንለይና (ቍ 15) የግለሰቦችንም ባሕርይ እንድንመዝን ታዘናል (ቍ 6 ይመ፤ ከዮሐ 7፥24፤ ከ1ቆሮ 5፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ፤ 1ዮሐ 4፥1 ይመ)።

(2) ይህ ጥቅስ የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ሲጣስ በቸልታ ማለፍን አያደፋፍርም (18፥15 እና ማብ ይመ)።

**7፥7-8 ለምኑ ... ፈልጉ ... አንኳኩ፤** ኢየሱስ በጽናት መጸለይን ያደፋፍራል። በቍ 8 ላይ የተጠቀሱት የግሪክ ግሶች ጊዜ የሚያመለክተው ቀጣይ ድርጊትን

ታገኛላችሁ፤ አንኳኩ፣ በሩም
ይከፈትላችኋል። 8የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤
የሚፈልግም ያገኛል፤ ለሚያንኳኳም በሩ
ይከፈትለታል።
9"ከእናንተ መካከል ልጁ ዳቦ ቢለምነው፣
ድንጋይ የሚሰጥ አባት አለ? 10ወይንም ዓሣ
ቢለምነው እባብ የሚሰጥ ይኖራልን? 11ታዲያ
እናንተ ክፉዎች ሳላችሁ ለልጆቻችሁ
መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፣
የሰማዩ አባታችሁማ ለሚለምኑት መልካም
ስጦታን እንዴት አብልጦ አይሰጣቸውም?
12ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን
ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም፣
ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና።

## ጠባቡና ሰፊው በር

13"በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት
የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤
ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ። 14ወደ ሕይወት የሚ
ያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ
ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

## ሐሰተኛ ነቢያት

15"በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች ሆነው
ሳሉ የበግ ለምድ ለብሰው መካከላችሁ
በመግባት ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት
ተጠንቀቁ። 16ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤
ከእሾህ ቍጥቋጦ ወይን፣ ከኵርንችትስ በለስ
ይለቀማልን? 17እንዲሁም ጥሩ ዛፍ ሁሉ
ጥሩ ፍሬ፣ መጥፎ ዛፍ ግን መጥፎ ፍሬ
ያፈራል። 18ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ፣ መጥፎም
ዛፍ ጥሩ ፍሬ ማፍራት አይችልም። 19ጥሩ
ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ
እሳትም ይጣላል። 20ስለዚህ በፍሬአቸው ማቴ
ታውቋቸዋላችሁ። 12፡33
21"በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ

7፡8 ምሳ8፡17፤ ኤር29፡12፡13
7፡11 ያዕ1፡17
7፡12 ሉቃ6፡31፤ ሮሜ13፡8-10፤ ገላ5፡14
7፡13 ሉቃ13፡24፤ ዮሐ10፡7፡9
7፡15 ኤር23፡16፤ ሕዝ22፡27፤ ማቴ24፡24፤ ሉቃ6፡26፤ ሐሥ20፡29፤ 2ጴጥ2፡1፤ 1ዮሐ4፡1፤ ራእ16፡13
7፡16 ማቴ12፡33፤ ሉቃ6፡44፤ ያዕ3፡12
7፡18 ሉቃ6፡43
7፡19 ማቴ3፡10
7፡21 ሆሴ8፡2፤ ማቴ3፡2፤ 12፡50፤ 25፡11፤
7፡21 ዮሐ13፡13፤ ሮሜ2፡13፤ 1ቆሮ12፡3፤ ያዕ1፡22፤ 1ዮሐ3፡18

ነው። ይህም ልመናችንን፣ ፍላጎታችንንና ማንኳኳታችንን ሳናቋርጥ መቀጠል አለብን ማለት ነው። ልመና የአንድን ነገር አስፈላጊነት መገንዘብንና እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማ ማመንን ያካትታል። ፍለጋ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ከመታዘዝ ጋር ከልብ የሆነን ልመና ያሳያል። ማንኳኳት እግዚአብሔር ፈጥኖ ባይመልስም እንኳ፣ ሳያቋርጡ ወደ እርሱ መቅረብን ይጨምራል። ክርስቶስ የሚለምኑ ሁሉ የጠየቁትን እንደሚያገኙ በማረጋገጥ የተናገረው፣ ልመናቸው በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ከሆነ ነው፡- (1) አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመፈለግ (6፡33 እና ማብ)፤ (2) የእግዚአብሔርን አባታዊ ቸርነትና ፍቅር በማወቅ (6፡8፤ 7፡11፤ ዮሐ 15፡16፤ 16፡23፡26 ... ፤ ቈላ 1፡9-12)፤ (3) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመጸለይ (ማር 11፡24፤ ዮሐ 21፡22፤ 1ዮሐ 5፡14)፤ (4) ከክርስቶስ ጋር ያለውን ኅብረት በመጠበቅ (ዮሐ 15፡7) እና (5) ክርስቶስን በመታዘዝ (በገጽ 528 ላይ፣ ***"መልስ የሚያስገኝ ጸሎት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**7፡11 አባታችሁማ ... መልካም ስጦታን ... አይሰጣቸውም?** በሰማይ ያለው አባት ልጆቹን ተስፋ እንደማያስቈርጥ ክርስቶስ ቃል ገብቶአል። ደግ የተባለ ምድራዊ አባት ልጆቹን ከሚወደው በላይ እግዚአብሔር ይወደናል፤ መልካም የሆነውንም ሊሰጠን ቃል በመግባት የሚያስፈልገንን ሁሉ እንድንጠይቀው ይፈልጋል። ለችግሮቻችን መፍትሔዎችንና በየዕለቱ የሚያስፈልገንን እንጀራ ሊሰጠን ይሻል። ከሁሉም በላይ መንፈስ ቅዱስን አጽናኛቸውና ረዳታቸው እንዲሆን ለልጆቹ ይሰጣል (ሉቃ 11፡13፤ ዮሐ 14፡16-18)።

**7፡14 በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው፤** ወደ ሕይወት በሚመራው መንገድ ብዙኃኑ እርሱን እንደሚከተሉት እናምን ዘንድ ክርስቶስ አላስተማረም። (1) በሌላም በኩል ጥቂቶች ራሳቸውን ክደው ኢየሱስን በመከተል፤ ከልብ ትእዛዛቱን ለማክበር በመጣር፣ በትጋት መንግሥቱንና ጽድቁን በመሻት፣ እንዲሁም እስከ መጨረሻው በእውነተኛ እምነት፥ ንጽሕናና ፍቅር በመጽናት ልባዊ በሆነ ንስሓ በጠባቧ በር ይገባሉ።

(2) ኢየሱስ በተራራ ስብከቱ ውስጥ በመንግሥቱ እውን ከሆነው ደቀ መዝሙርነት ጋር የተያያዙትን ታላላቅ በረከቶች በዝርዝር ጠቅሶአል (5፡3-12)፤ ነገር ግን ደቀ መዛሙርቱ ክስደት እንደማያመልጡ በአጽንዖት ተናግሮአል (5፡10-12)። ከዚህም በላይ አንዳንድ ወንጌላውያን "ድነትን ማግኘት" በዓለም ከሚገኙ ቀላል ነገሮች አንዱ ነው ብለው ከሚያስተምሩት በተቃራኒ፣ ጌታን መከተል በጽድቅ መኖርን፣ ስደትን መቀበልን፣ ጠላትን መውደድንና ራስን መካድን እንደሚጠይቅ ጌታ ኢየሱስ አስተምሮአል።

**7፡15 ከሚያሸምቁ ሐሰተኛ ነቢያት ተጠንቀቁ፤** በገጽ 1519 ላይ፣ ***"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**7፡16 ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤** ከውጭ ሲታዩ ጻድቃን፥ ነገር ግን "በውስጣቸው ነጣቂ ተኵላዎች" (ቍ 15) የሆኑ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ በፍሬያቸው ሊታወቁ ይችላሉ። የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ፍሬ በተከታዮቻቸው ሕይወት ቀጥሎ በተጠቀሱት አስቸጋሪ ባሕርያት ይገለጣል (1ዮሐ 4፡5-6)፤ (1) ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ለሰዎች ታማኝነታቸውን የሚገልጹና በአንደበታቸው ብቻ ክርስቲያን መሆናቸውን የሚናገሩ ናቸው (ቍ 21)። በፈጣሪ ፈንታ ፍጡርን የሚያመልኩ ናቸው (ከሮሜ 1፡25 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ከእግዚአብሔር ክብርና ሞገስ ይልቅ ለግል ፍላጎታቸው እጅግ ይጨነቃሉ። አስተምህሮአቸውም እግዚአብሔርን ማእከል ያደረገ ሳይሆን፣ የራሳቸውን ፍላጎት ያማከለ ነው (ቍ 21-23፤ 2ጢሞ 4፡3 እና ማብ ይመ)።

(3) ትምህርታቸው የእግዚአብሔርን ቃል ቢቃረንም እንኳ (ቍ 24-27፤ 1ዮሐ 4፡6)፣ የሰዎችን ትምህርትና ወግ ይቀበላሉ።

(4) በእግዚአብሔር ቃል ምክር እምነታቸውን ከመመሥረት ይልቅ፥ የእውነት የመጨረሻ ማረጋገጫቸው በማድረግ ሃይማኖታዊ ልምምዶችንና ዲበ ተፈጥሮአዊ ክሥተቶችን ይሻሉ፤ (ቍ 22-23) በእነርሱም ይረካሉ።

(5) ትክክለኛውን አስተምህሮ አይቀበሉም፥ ነገር ግን ጽድቅ የሌለበትን "በሰፊው በር" እንዲገቡ የሚያሳስበውን ትምህርት የሚሰጧቸውን አስተማሪዎች ይሻሉ (ቍ13-14፡23፤ 2ጢሞ 4፡3 እና ማብ ይመ)።

**7፡21 ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም፤** የሰማይ

ሳይፈጽም 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤' የሚለኝ
ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም።
[22]በዚያ ቀን ብዙዎች፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ
ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን?
በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ
ብዙ ታምራት አላደረግንምን?' ይሉኛል።
[23]በዚያ ጊዜ፣ 'ከቶ አላወቅኋችሁም፤
ማት 19፥16-26 እናንት ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ' ብዬ በግልጽ
እነግራቸዋለሁ።

7፥22 ማቴ10፥15፤ ሉቃ10፥20፤ ሐሥ19፥13፤ 1ቆሮ13፥1-3
7፥23 መዝ6፥8፤ ማቴ25፥12፡41፤ ሉቃ13፥25-27
7፥24 ቍ 21፤ ያዕ1፥22-25

## ብልኅና ሞኝ ቤት ሠሪ

*7፥24-27 ተጓ ምብ — ሉቃ 6፥47-49*

[24]"እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ
በተግባር የሚያውለው፣ ቤቱን በዐለት ላይ
የሠራን ብልኅ ሰው ይመስላል። [25]ዶፍ
ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤
ያንን ቤት መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ
ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። [26]ይህን ቃሌን
ሰምቶ በተግባር የማያውለው ግን ቤቱን
በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል።
[27]ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም

---

አባቱን ፈቃድ መፈጸም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚያስችል መሆኑን ኢየሱስ በአጽንዖት አስተምሯል (ከቍ 22-27፤ ከ19፥16-26፤ ከ25፥31-46 ጋር ያነጻጽሩ)። እንደዚህ ስለ ተባለ ግን በራሳችን ጥረት ወይም ሥራ ብቻ ድነትን እናገኛለን ወይም እንቀበላለን ማለት አይደለም። ይህም ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ እውነት ነው፦ (1) የእግዚአብሔር ምሕረት ወደ እኛ የሚመጣው በክርስቶስ የመሥዋዕትነት ሞትና ጸጋ የተፈጸመውን ስናምንና ንስሓ ስንገባ ነው (26፥28 እና ማብ፤ ሉቃ 15፥11-32፤ 18፥9-14 ይመ)።

(2) ክርስቶስ የሚፈልግብን ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ ጉዳይ በርግጥ ለድነት አስፈላጊ የሆነ የማያቋርጥ ሂደት ነው፤ ይሁን እንጂ ይህ መታዘዝ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ካለው ድነት የሚያበቃ ጸጋ መሆኑንም ክርስቶስ ዐውጆአል። ስለዚህ ይህ መታዘዝ ይበዛልን ዘንድ በጽኑ እምነትና በፍጹም ትጋት ሳናቋርጥ መጸለይ ይገባናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጸለየውንና (6፥9-13) አማኞች ለኀጢአት በመሞት ራሳቸውን ሕያው መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንደሚገባቸው የተሰጡትን አያሌ ምክሮች ልብ ይበሉ (ከሮሜ 6፥1-23፤ 8፥1-17፤ 12፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 5፥6 ይመ፤ እንዲሁም ጽድቅን ስለ መራብና ስለ መጠማት የቀረበውን ማብራሪያ ይመ፤ በገጽ 1075 ላይ፥ *«የእግዚአብሔር ፈቃድ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በዚህ በጎ ስጦታ አማካይነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግና የጽድቅን ሕይወት ለመኖር እንችላለን፤ ይህ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ በክርስቶስ በኩል ባለማቋረጥ የተሰጠን ኀይልና መንፈሳዊ ሕይወት ነው (ኤፌ 2፥5)። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፥ «በእምነት፥ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም ... የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን» (ኤፌ 2፥8-10)።

(4) እግዚአብሔር ከእኛ የሚሻውን መታዘዝ እንፈጽም ዘንድ የሚያስችለንን ዐቅም ሁልጊዜ ይሰጠናል። ይህም በእግዚአብሔር የቤዛነት ሥራ ውስጥ የተካተተ ነው። «እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና» (ፊል 2፥13 እና ማብ ይመ)። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የሰውን ኀላፊነት ወይም ድርጊት ድርሻ አልባ አያደርገንም። እግዚአብሔር ለሰጠን የመታዘዝ ጸጋ እምነታዊ ምላሽ መስጠት አለብን (ኤፌ 4፥22-32፤ ይሁ 1፥20-21፡24፤ ፊል 2፥12 እና ማብ ይመ)፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቃወም፣ በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ላለመሻት (ዕብ 7፥25 እና ማብ)፣ መጸለይን ላለመፈለግ እንዲሁም የመታዘዝን ሕይወት ላለመቀበል የግል ፈቃድ አለንና (5፥6 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ *«እምነትና ጸጋ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**7፥22 ብዙዎች፣ ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ ... ይሉኛል፤** «ብዙዎች» በስሙ በቤተ ክርስቲያን እንደሚያገለግሉና አገልጋዮቹም እንደ ሆኑ የሚያምኑ፣ ነገር ግን በርግጥ እርሱ ከቶ እንደማያውቃቸው ኢየሱስ በአጽንዖት ተናገረ (ቍ 23)። ከመጨረሻው ዘመን አታላይነት ለማምለጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም ደቀ መዛሙርት ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለተገለጠው እውነትና ጽድቅ (ራእ 22፥19 እና ማብ ይመ) ራሳቸውን መስጠት አለባቸው እንጂ፣ «የአገልግሎት ስኬታማነትን» ከክርስቶስ ጋር ላላቸው ግንኙነት መሠረታዊ ነገር አድርገው ሊቈጥሩት አይገባም።

**7፥23 ከቶ አላወቅኋችሁም፤** ራሳቸው በክርስቶስ በኩል ለድነት የሚያበቃ እውነተኛ እምነት ሳይኖራቸው፣ ሰባኪዎች በክርስቶስ ስም ወንጌል ሊሰብኩ፣ አጋንንት ሊያስወጡና ታምራትን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይህ የክርስቶስ ቃል ያለምንም ጥርጥር በግልጽ ያመለክታል። (1) በኃለ ስሜት የሚቀርብ የወንጌል ስብከት፣ አስመሳይ የጽድቅ ፍላጎት፣ ታምራትን ማድረግ በዚህ ዘመን በሰይጣን ግፊትና ኀይል እንደሚከናወን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምራሉ። ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲህ በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል፥ «ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል። እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም፣» (2ቆሮ 11፥14-15 ይመ፤ ከማቴ 24፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። ሐዋርያው ጳውሎስ አስመሳይ የሆነ ቅባት፣ «የሰይጣን ሥራ» ሊሆን እንደሚችል በግልጽ ተናግሯል (2ተሰ 2፥9-10፤ ራእ 13፥3፡12 ይመ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ *«የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በቅንነት ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ ለሚሰጡት ድነትን ወይም ፈውስን ለማምጣት በሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የሚሠራውን የሰይጣንን አሠራር ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ይሽረዋል (ፊል 1፥15-18 ይመ)። ወንጌል ሰባኪዎች ምንጊዜም ጻድቃን ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው (1ጢሞ 3፥1-7 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ክፉ ወይም ኢግብረ ገባዊ የሆነ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰብክበት ጊዜ፥ ራሳቸውን ለክርስቶስ በመስጠት ቃሉን በሚቀበሉ ሰዎች ልብ ውስጥ እግዚአብሔር ሊሠራ ይችላል። እግዚአብሔር ጻድቅ ላልሆነ የወንጌል ሰባኪ ድጋፍ አይሰጥም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትንና ይህንኑ እውነት ያንን በእምነት የሚቀበሉትን ሰዎች ግን ይደግፋል።

ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ ቤቱም ወደቀ፤
አወዳደቁም የከፋ ነበር።"
[28]ኢየሱስ ማስተማሩን በፈጸመ ጊዜ፣
ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ። [29]ምክንያቱም
እንደ አይሁድ ሃይማኖት መምህራኖቻቸው
ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን አስተምሮአቸው
ስለ ነበር ነው።

### የለምጻሙ መንጻት

*8፥2-4 ተጓ ምብ — ማር 1፥40-44፤ ሉቃ 5፥12-14*

**8** ከተራራው በወረደ ጊዜም ብዙ ሕዝብ
ተከተለው። [2]እነሆ፤ አንድ ለምጻም*
ሰው ወደ ኢየሱስ ቀረበና ከፊቱ ተንበርክኮ
እየሰገደለት፣ "ጌታ ሆይ፤ ብትፈቅድስ
ልታነጻኝ ትችላለህ" አለው።
[3]ኢየሱስም እጁን ዘርግቶ ዳሰሰውና፣
"ፈቃዴ ነው፤ ንጻ!" አለው። ሰውየውም
ወዲያውኑ ከለምጹ ነጻ። [4]ከዚያም ኢየሱስ፣
"መፈወስ ህን ለማንም አታውራ፤ ነገር
ግን ሂደህ ራስህን ለካህን አሳይ፤ ሙሴ
ያዘዘውንም መባ አቅርብ፤ ይህም ምስክር
ይሆንላቸዋል" አለው።

### የመቶ አለቃው እምነት

*8፥5-13 ተጓ ምብ — ሉቃ 7፥1-10*

[5]ኢየሱስ ቅፍርናሆም እንደ ደረሰ አንድ
የመቶ አለቃ ቀርቦ፣ እንዲህ ሲል ለመነው፤
[6]"ጌታ ሆይ፤ አገልጋዩ ሽባ ሆኖ እጅግ
በመሠቃየት ከቤት ተኝቶአል" አለው።
[7]ኢየሱስም፣ "እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ"
አለው።
[8]የመቶ አለቃው ግን መልሶ እንዲህ አለ፤
"ጌታ ሆይ፤ ወደ ቤቴ እንድትገባ የሚገባኝ
አይደለሁም፤ ነገር ግን ከዚሁ ሆነህ አንዲት
ቃል ብቻ ተናገር፤ አገልጋዩም ይፈወሳል፤
[9]እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች፣ ለእኔም
የሚታዘዙ የበታቾች አሉኝ፤ ከእነርሱ
አንዱን፣ 'ሂድ!' ስለው ይሄዳል፤ ሌላውን፣
'ና!' ስለው ይመጣል፤ አገልጋዬንም፣ 'ይህን
አድርግ' ስለው ያደርጋል።"
[10]ኢየሱስም በመልሱ ተደንቆ ይከተሉት
ለነበሩት እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፣ ከእስራኤል መካከል እንኳ
እንዲህ ያለ እምነት ያለው አንድ ሰው
አላገኘሁም፤ [11]እላችኋለሁ፣ ብዙዎች
ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፤
በመንግሥተ ሰማይ ማእድ ዙሪያ

7፥28 ማቴ11፥1፤ 13፥53፡54፤ 19፥1፤ 22፥33፤ 26፥1፤ ማር1፥22፤ 6፥2፤ 11፥18፤ ሉቃ4፥32፤ ዮሐ7፥46
8፥2 ዘሌ13፥45፤ ማቴ9፥18፤ 10፥8፤ 11፥5፤ 15፥25፤ 18፥26፤ 20፥20፤ 26፥6፤ ሉቃ5፥12፤ 17፥12
8፥4 ዘሌ14፥2-32፤ ማቴ9፥30፤ 12፥16፤ ማር5፥43፤ 7፥36፤ 8፥30፤ ሉቃ4፥41፤ 17፥14
8፥6 ማቴ4፥24
8፥8 መዝ107፥20
8፥10 ማቴ15፥28
8፥11 መዝ107፥3፤ ኢሳ49፥12፤ 59፥19፤ ሚል1፥11፤ ሉቃ13፥29
8፥12 ማቴ13፥38፡42፡50፤ 22፥13፤ 24፥51፤ 25፥30፤ ሉቃ13፥28
8፥13 ማቴ9፥22
8፥16 ማቴ4፥23፡24
8፥17 ኢሳ53፥4፤ ማቴ1፥22
8፥18 ማር4፥35
8፥20 ዳን7፥13፤ ማቴ12፥8፡32፡40፤ 16፥13፡27፡28፤ 17፥9፤ 19፥28፤ ማር2፥10፤ 8፥31
8፥22 ማቴ4፥19

ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ
ጋር ይቀመጣሉ፤ [12]መንግሥተ ሰማይ
ተዘጋጅቶላቸው የነበሩት ግን ወደ ውጭ
ወደ ጨለማው ይጣላሉ። በዚያም ልቅሶና
ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።"
[13]ኢየሱስም መቶ አለቃውን፣ "ሂድ እንደ
እምነትህ ይሁንልህ" አለው። አገልጋዩም
በዚያች ቅጽበት ተፈወሰ።

### ኢየሱስ ብዙዎችን መፈወሱ

*8፥14-16 ተጓ ምብ — ማር 1፥29-34፤ ሉቃ 4፥38-41*

[14]ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ቤት ገራ ሲል
የጴጥሮስ ሀማት በትኩሳት ታማ ተኝታ
አገኛት። [15]እጇን ዳሰሳት፤ ትኩሳቱም ለቀ
ቃት፤ ተነሥታም አገለገለችው።
[16]በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ
ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም
መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም
ሁሉ ፈወሰ። [17]በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ
ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤

"እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤
ሕመማችንንም ተሸከመ።" ማቴ 10፥1

### የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን ውሳኔ ይጠይቃል

*8፥19-22 ተጓ ምብ — ሉቃ 9፥57-60*

[18]ኢየሱስ ብዙ ሰዎች በዙሪያው
ተሰብስበው ባየ ጊዜ ወደ ባሕሩ ማዶ
እንዲሻገሩ አዘዛቸው። [19]በዚህ ጊዜ አንድ
የአይሁድ ሃይማኖት መምህር ወደ እርሱ
ቀርቦ፣ "መምህር ሆይ፤ ወደምትሄድበት
ሁሉ እከተልሃለሁ" አለው።
[20]ኢየሱስም፣ "ቀበሮዎች ጕድጓድ፣
የሰማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ
ግን ራሱን የሚያስጠጋበት ቦታ የለውም"
ሲል መለሰለት።
[21]ደቀ መዝሙር የሆነ አንድ ሌላ ሰው
ደግሞ፣ "ጌታ ሆይ፤ መጀመሪያ ሂጄ አባቴን
እንድቀብር ፍቀድልኝ" አለው።
[22]ኢየሱስ ግን፣ "ሙታን ሙታናቸውን
ይቅበሩ፤ አንተ ተከተለኝ" አለው።

*8፥2 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል

**8፥10 እንዲህ ያለ እምነት፤** የመቶ አለቃው እምነት ኢየሱስ በአይሁድ ዘንድ ካገኘው ማንኛውም ነገር የበለጠ ሆኖ ተገኘ፤ ይኸውም በክርስቶስ ካለው ታላቅ እምነት ጋር ስለ ሌላ ሰው በፍቅር ማሰቡን የሚያካትት ስለ ሆነ ነው። ይህ ታሪክ ከማያምኑት አይሁድ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር ክርስቶስ ካስተማረው ትምህርት ጋር አንድ ላይ ሆኖ (ቍ 11-12)፣ የሰዎችን ቁል በማክበራችን ወይም በእግዚአብሔር መንግሥት ኀይል ባለማመናችን፣ እግዚአብሔር ከሚሠራው ሥራ ልንወጣ እንደምንችል ያስጠነቅቀናል።

**8፥16-17 በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ፤** በገጽ 1433 ላይ፣ *"መለኮታዊ ፈውስ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**8፥22 ሙታን ሙታናቸውን ይቅበሩ፤** የዚህ አባባል ትርጕም፣ "በመንፈሳዊ ነገር ሙታን የሆኑ በአካል ሙታን የሆኑትን ይቅበሩ" ማለት ነው። በቍ 21 ላይ የተጠቀሰው ደቀ መዝሙር ሽማግሌ የሆነው አባቱ እስኪሞት ድረስ አብሮት ለመቈየት የፈለገ ይመስላል።

## ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አደረገ

*8፥23-27 ተጓ ምብ — ማር 4፥36-41፤*
*ሉቃ 8፥22-25*
*8፥23-27 ማመ — ማቴ 14፥22-23*

[23]ከዚያም ኢየሱስ ወደ ጀልባ ገባ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተከትለውት ገብተው ሄዱ። [24]ድንገት ኀይለኛ ማዕበል በባሕሩ ላይ ተነሥቶ ጀልባዪቱን እስኪሸፍን ድረስ አወካቸው፤ በዚህ ጊዜ ግን ኢየሱስ ተኝቶ ነበር። [25]ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው ቀሰቀሱትና፣ "ጌታ ሆይ! ጠፋን፤ አድነን" አሉት።

[26]ኢየሱስም፣ "እናንተ እምነት የጐደላችሁ፤ ለምን ይህን ያህል ፈራችሁ?" አላቸው፤ ከዚያም ተነሥቶ ነፋሱንና ማዕበሉን ገሠጸ፤ ወዲያውም ጸጥታ ሰፈነ።

[27]ሰዎቹም፣ "ነፋስና ባሕር እንኳ የሚታዘዙለት፣ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው?" እያሉ ተደነቁ።

## ክርኩሳን መናፍስት ስለ ተፈወሱ ሁለት ሰዎች

*8፥28-34 ተጓ ምብ — ማር 5፥1-17፤*
*ሉቃ 8፥26-27*

[28]ባሕሩን ተሻግሮ ጌርጌሴኖን[a] ወደሚባል አገር እንደ ደረሰ፣ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከሚኖሩበት የመቃብር ቦታ ወጥተው ተገናኙት። በዚያ መንገድ ሰው ማለፍ እስከማይችል ድረስ እጅግ አደገኞች ነበሩ። [29]እነርሱም "የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፤ ከእኛ ምን ጉዳይ አለህ? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን መጣህን?" እያሉ ጮኹ።

[30]ከእነርሱ ትንሽ ራቅ ብሎ፣ የብዙ ዐሣማ መንጋ ተሰማርቶ ነበር። [31]አጋንንቱም ኢየሱስን፣ "የምታስወጣን ከሆነ ዐሣማዎቹ መንጋ ውስጥ እንድንገባ ፍቀድልን" ብለው ለመኑት። [32]ኢየሱስም፣ 'ሂዱ!' አላቸው። አጋንንቱም ከሰዎቹ ወጥተው ዐሣማዎቹ ውስጥ ገቡ፤ ዐሣማዎቹም በሙሉ ከነበሩበት አፋፍ እየተጣደፉ ባሕሩ ውስጥ በመግባት ውሃው ውስጥ ሰጥመው ሞቱ። [33]የዐሣማ ምቹ ጠባቂዎችም ሸሽተው ወደ ከተማ በመሄድ፣ የሆነውን ሁሉና በአጋንንት ተይዘው በነበሩት ሰዎች ላይ የተደረገውን ነገር
ማቴ 17፥14-18 አወሩ። [34]እነሆም፤ መላው የከተማ ነዋሪ ኢየሱስን ለመገናኘት ወጣ፤ ባዩትም ጊዜ አገራቸውን ለቅቆ እንዲሄድ ለመኑት።

8፥26 መዝ65፥7፤ 89፥9፤ 107፥29፤ ማቴ6፥30
8፥28 ማቴ4፥24
8፥29 መሳ11፥12፤ 2ሳሙ16፥10፤ 1ነገ17፥18፤ ማር1፥24፤ ሉቃ4፥34፤ ዮሐ2፥4፤ 2ጴጥ2፥4
8፥34 ሉቃ5፥8፤ ሐሥ16፥39
9፥1 ማቴ4፥13
9፥2 ቆ 22፤ ማቴ4፥24፤ ዮሐ16፥33፤ ሉቃ7፥48
9፥3 ማቴ26፥65፤ ዮሐ10፥33
9፥4 መዝ94፥11፤ ማቴ12፥25፤ ሉቃ6፥8፤ 9፥47፤ 11፥17፤ ዮሐ2፥25
9፥6 ማቴ8፥20
9፥8 ማቴ5፥16፤ 15፥31፤ ሉቃ7፥16፤ 13፥13፤ 17፥15፤ 23፥47፤ ዮሐ15፥8፤ ሐሥ4፥21፤ 11፥18፤ 21፥20
9፥9 ማቴ4፥19
9፥11 ማቴ11፥19፤ ሉቃ5፥30፤ 15፥2፤ 19፥7፤ ገላ2፥15
9፥13 ሆሴ6፥6፤ ሚክ6፥6-8፤ ማቴ12፥7፤ ሉቃ19፥10፤ 1ጢሞ1፥15

## የሽባው ሰው መፈወስ

*9፥2-8 ተጓ ምብ — ማር 2፥3-12፤*
*ሉቃ 5፥18-26*

**9** ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ባሕሩን በጀልባ ተሻግሮ ወደ ራሱ ከተማ መጣ። [2]በዚያም ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በቃሬዛ ተሸክመው ወደ እርሱ አመጡ። ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን፣ "አይዞህ አንተ ልጅ፤ ኀጢአትህ ተሰርዮልሃል" አለው።

[3]በዚህን ጊዜ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን፣ "ይህማ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው" በማለት በልባቸው አጕረመረሙ።

[4]ኢየሱስ ሐሳባቸውን ተረድቶ እንዲህ አለ፤ "ክፉ ነገር በልባችሁ ለምን ታስባላችሁ? [5]ለመሆኑ፣ 'ኀጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል' ከማለትና 'ተነሥተህ ሂድ' ከማለት የቱ ይቀላል? [6]ነገር ግን የሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን የማስተስረይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ነው' ብሎ፣ ሽባውን፣ 'ተነሣ! ቃሬዛህን ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ' አለው።" [7]ሽባውም ተነሥቶ ወደ ቤቱ ሄደ። [8]ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ በመደነቅ፣ በፍርሃት ተሞልተው፣ እንደዚህ ያለ ሥልጣን ለሰው የሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

## የማቴዎስ መጠራት

*9፥9-13 ተጓ ምብ — ማር 2፥14-17፤*
*ሉቃ 5፥27-32*

[9]ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው በቀረጥ ማስከፈያ ኬላ ተቀምጦ አየ፤ "ተከተለኝ" አለው፤ እርሱም ተነሥቶ ተከተለው።

[10]ኢየሱስ በማቴዎስ ቤት በማእድ ላይ ሳለ፣ ብዙ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች መጥተው ከእርሱና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ሊበሉ ተቀመጡ። [11]ፈሪሳውያንም ይህን ባዩ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣ "መምህራችሁ ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢአተኞች ጋር እንዴት አብሮ ይበላል?" ብለው ጠየ ቋቸው።

[12]ኢየሱስም የተናገሩትን በመስማቱ እንዲህ አላቸው፤ "ሐኪም የሚያስፈልገው ለሕመምተኞች እንጂ ለጤነኞች አይደለም፤ [13]ሂዳችሁ፣ 'ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ' የሚለውን ቃል ትርጕም አጥኑ፤ ኀጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አል መጣሁምና።"

[a] 8፥28 አንዳንድ ቅጆች ጌራሴኖን ይላሉ

**8፥28 አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች፤** 17፥17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
**9፥11 ከኀጢአተኞች ጋር … አብሮ ይበላል?** ከቍ 11-13 ባለው ክፍል ከማያምኑ ሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በተመለከተ ኢየሱስ መመሪያዎችን ሰጥቶናል፤ ግንኙነታችን ለደስታ ወይም ለቅርብ ወዳጅነት ሳይሆን፣ ለእነርሱ መልካሙን ነገር ለማድረግና የድነትን መንገድ ለማሳየት ነው (ቈ 12፤ መዝ 1፥1)። በምንም ዐይነት መንገድ አማኝ የማያምን ሰውን ለእሾኽንት ወይም ለጋብቻ ማሰብ የለበትም (1ቆሮ 7፥39 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

# መለኮታዊ ፈውስ

*ማቴ 8፥16-17 "በዚያ ምሽት በአጋንንት የተያዙ ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ፤ እርሱም መናፍስትን በቃሉ አስወጣ፤ በሽተኞችንም ሁሉ ፈወሰ። በዚህም ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ፤ 'እርሱ ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ'።"*

---

**እግዚአብሔር በቤዛነት ያደረገው ቸርታ፤** (1) የሕመምና የበሽታ ችግር ኀጢአትና ሞት ከሚያስከትሉት ችግር ጋር የተሳሰረ ነው፤ ይህ የሰው ልጅ ውድቀት ውጤት ነው። የሕክምና ሳይንስ ዕውቀት የሕመምና የበሽታ መነሻ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ችግር እንደ ሆነ ቢያስተምርም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የችግሩ መንሥኤ መንፈሳዊ እንደ ሆነ ይናገራል፤ (ሀ) ኀጢአት፦ በመንፈሳዊና በአካላዊ ተፈጥሯችን ላይ ጕዳት አድርሶአል (ለምሳሌ ዮሐ 5፥5፡14)፤ (ለ) ሰይጣን፦ (ለምሳሌ ሐሥ 10፥38 ይመ፤ ከማር 9፥17፡20፡25፤ ከሉቃ 13፥11፤ ከሐሥ 19፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) የውድቀት ውጤቶች ሰፊ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር የቤዛነት መግቦት እጅግ ሰፊ ነው። ለኀጢአት፣ እግዚአብሔር ይቅርታን ሰጥቶአል፤ ለሞት፣ የዘላለምንና የትንሣኤን ሕይወት ሰጥቶአል፤ ለሕመም፣ ፈውስን ሰጥቶአል (ከመዝ 103፥1-5፤ ከሉቃ 4፥18፤ ከ5፥17-26፤ ከያዕ 5፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የአገልግሎቱ ሦስትዮሽ ዘርፍ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር፣ ንስሓንና (ኀጢአትን በተመለከተ) የእግዚአብሔርን መንግሥት በረከቶች (ሕይወትን በተመለከተ) መስበክ፣ እንዲሁም በሕዝቡ ላይ ያለውን ማንኛውንም ዐይነት ሕመም፣ በሽታና ድካም ሁሉ መፈወስ ነበር (ማቴ 4፥23-24)።

**የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚመለከት መገለጥ፤** በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ፈውስን በተመለከተ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ በአራት መንገድ ተጠቅሶአል፤ (1) እግዚአብሔር ራሱ ያወጀው ዐዋጅ፤ በዘፀአት 15፥26 ላይሕዝቡ ኪዳኑንና ትእዛዛቱን በመጠበቅ በታማኝነት የሚጸኑ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ጤንነትንና ፈውስን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸዋል (ዘፀ 15፥26 እና ማብ ይመ)። ዐዋጁ የሚከተሉት ሁለት ባሕርያት አሉት፤ እነርሱም፦ (ሀ) "በግብፃውያን ላይ ያመጣሁባቸውን ማንኛውንም ዐይነት በሽታ (ፍርድ በማድረግ) በእናንተ ላይ አላመጣም" እና (ለ) "ፈዋሻችሁ (ቤዛ) እኔ እግዚአብሔር ነኝና" የሚሉት ናቸው። የእርሱን ፊት አጥብቀው በፈለጉና ለቃሉ በታዘዙ ቍጥር እግዚአብሔር ለብሉይ ኪዳን ሕዝቡ ሐኪምና ፈዋሽ መሆኑን ሳያቋርጥ ቀጠለ።

(2) የኢየሱስ አገልግሎት፤ ጌታችን ኢየሱስ ሥግው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ መጠን ትክክለኛውን የእግዚአብሔርን አካልና ባሕርይ ይወክላል (ዕብ 1፥3 ይመ፤ ከቈላ 1፥15፤ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። በምድራዊ አገልግሎቱ (ማቴ 4፥23-24፤ 8፥14-16፤ 9፥35፤ 15፥28፤ ማር 1፥32-34፡40-41፤ ሉቃ 4፥40፤ ሐሥ 10፥38) ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በግብር ገለጸ (ዮሐ 6፥38፤ 14፥10)፤ ይህንም ያደረገው የታመሙትንና በሰይጣን እየተጨቈኑ ያሉትን ሁሉ መፈወስ በእግዚአብሔር ልብ፣ ባሕርይና ዐላማ ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ ነው።

(3) የክርስቶስ ኀጢአትን የማስተስረይ መግቦት (ኢሳ 53፥4-5፤ ማቴ 8፥16-17፤ 1ጴጥ 2፥24) የኢየሱስ ክርስቶስ የማስተስረያ ሞት ሙሉውን ማለትም መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ የሆነውን ሰው ለመቤዠት ፍጹምና ብቁ ነው። ኀጢአትና ሕመም ጣምራ ጠላቶች በመሆን እኛን ለማጥፋት በሰይጣን ቢቃጡብንም፣ የኀጢአት ይቅርታና ፈውስ ደግሞ ጣምራ በረከቶች በመሆን ሊቤዡንና ሙሉ ሊያደርጉን በእግዚአብሔር ታቅደውልናል (ከመዝ 103፥3፤ ከያዕ 5፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ)። አማኝ የአካል ፈውስን ጨምሮ በክርስቶስ የስርየት ሞት የተገኘውን ሙሉ በረከት ለመውረስ በትሕትናና በእምነት ጕዞውን መቀጠል አለበት።

(4) እየተከናወነ ያለው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማወጅ ውስጥ ሕሙማንን መፈወስን የአገልግሎታቸው አካል አድርገው እንዲፈጽሙት ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ሾማቸው (ሉቃ 9፥1-2፡6)። በኋላም ሰባውን ደቀ መዛሙርት ይህንኑ ተመሳሳይ ተልእኮ እንዲፈጽሙ አዘዛቸው (ሉቃ 10፥1፡8-9፡19)። ከበዓለ ኀምሳ ቀን በኋላ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስን የፈውስ አገልግሎት ወንጌልን የመስበክ አንድ ክፍል አድርጋ የማከናወንን ተግባር ቀጠለችበት (ሐሥ 3፥1-10፤ 4፥30፤ 5፥16፤ 8፥7፤ 9፥34፤ 14፥8-10፤

19፥11-12 ይመ፡ ከማር 16፥18፤ ከ1ቆሮ 12፥9፡28፡30፡ ከያዕ 5፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ)። አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር የፈውስ ኀይል፥ እምነትም በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚተላለፋባቸው ሦስት መንገዶች ጠቅሶአል፡ (ሀ) እጅ በመጫን (ማር 16፥15-18፤ ሐሥ 9፥17)፤ (ለ) የታወቀ ኀጢአትን በመናዘዝ፣ ቀጥሎም በእምነት ጸልዮ በሽተኞችን በዘይት በመቀባት (ያዕ 5፥14-16) እና (ሐ) ለቤተ ክርስቲያን በተሰጡ የፈውስ ስጦታዎች (1ቆሮ 12፥9)። የእምነት ጸሎትን ሊጸልዩ የሚገባቸው ሽማግሌዎች መሆናቸውን ልብ ይበሉ።

***የፈውስ ዕንቅፋቶች፤*** አንዳንድ ጊዜ መለኮታዊ ፈውስን እንዳንቀበል የሚያደርጉ የሚከተሉት ዕንቅፋቶች አሉ፥ (1) ለንስሐ ያልበቃ ኀጢአት (ያዕ 5፥16)፣ (2) የአጋንንት ባርነት ወይም እስራት (ሉቃ 13፥11-13)፣ (3) ፍርሀት ወይም ብርቱ ጭንቀት (ምሳ 3፥5-8፤ ፊል 4፥6-7)፣ (4) የአሁኑን እምነት የሚያዳክሙ የቀደመው ጊዜ ተስፋ አስቈራጭ ክሥተቶች (ማር 5፥26፤ ዮሐ 5፥5-7)፣ (5) ሰዎች (ማር 10፥48)፣ (6) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ትምህርት (ማር 3፥1-5፤ 7፥13)፣ (7) ሽማግሌዎች የእምነት ጸሎት መጸለይ አለመቻላቸው (ማር 11፥22-24፤ ያዕ 5፥14-16)፥ (8) እግዚአብሔር እንዲፈጸም የሚፈልገውን የታምራትና የፈውስ ስጦታ ቤተ ክርስቲያን ለመሻት ወይም ለማግኘት አለመቻሏ (ሐሥ 4፥29-30፤ 6፥8፤ 8፥5-6፤ 1ቆሮ 12፥9-10፡29-31፤ ዕብ 2፥4)። (9) አለማመን (ማር 6፥3-6፤ 9፥19፡23-24) እና (10) ራስን ብቻ የመውደድ ባሕርይ (1ቆሮ 11፥29-30)። በሌላ በኩል ግን በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ለሚከሠት ጽኑ አካላዊ ሕመም ግልጽ የሆነ ምክንያት ማግኘት አይቻልም (ለምሳሌ ገላ 4፥13፤ 1ጢሞ 5፥23፤ 2ጢሞ 4፥20)። በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ቅዱሳን በሕመም ላይ እንዳሉ ወደ መንግሥቱ የሚወስድበት ጊዜ አለ (ከ2 ነገ 13፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

***መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች፤*** እግዚአብሔር በአካላችን ላይ ከተከሠተው ሕመም የተነሣ ፈውስን ይሰጠን ዘንድ ስንጸልይ ማድረግ የሚገባን ምንድ ነው? (1) ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ትክክለኛው ግንኙነት እንዳለን ርግጠኞች መሆን (ማቴ 6፥33፤ 1ቆሮ 11፥27-30፤ ያዕ 5፥16፤ ዮሐ 15፥7 እና ማብ ይመ)።

(2) የኢየሱስ ህልዎት በሕይወታችን ውስጥ እንዲገኝ መሻት፥ በልባችን ውስጥ ሊኖረን የሚገባንን እምነት የሚሰጠን እርሱ ነውና (ሮሜ 12፥3፤ 1ቆሮ 12፥9፤ ፊል 2፥13፤ ማቴ 17፥20 እና በእውነተኛ እምነት ላይ የተጻፈውን ማብ ይመ)።

(3) ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ቃል ምሉእ ማድረግ (ዮሐ 15፥7፤ ሮሜ 10፥17)።

(4) ፈውስን ባናገኝም እንኳ፣ በእርሱ ጸንተን መኖር (ዮሐ 15፥1-7)፤ ሕይወታችንን በመመርመር እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲሠራ የሚያደርገውን ለሙሉ መጠበቅ።

(5) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ዘይት ቀብተው እንዲጸልዩልን እንዲሁም ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችን እንዲማልዱልን ጥሪ ማቅረብ (ያዕ 5፥14-16)።

(6) የተከበረ የፈውስ አገልግሎትን የሚሰጥ ሰው ባለበት ጉባኤ ውስጥ መሳተፍ (ከሐሥ 5፥15-16፤ ከ8፥5-7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(7) ታምራትን መጠባበቅ፣ ይህም በክርስቶስ ኀይል መታመን ነው (ማቴ 7፥8፤ 19፥26)።

(8) በዕለቱ ፈውስ ቢመጣ ደስ መሰኘት፤ በዚያው ሰዓት ባይመጣም ደስ መሰኘት (ፊል 4፥4፡11-13)።

(9) እግዚአብሔር ጸሎትን ሳይመልስ የሚዘገየው እነዚያን የጸሎት ጥያቄዎችን ስላልተቀበለ እንዳልሆነ መገንዘብ፤ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ታላቅ ዐላማ ይኖረዋል፤ ፈውሱ ሲፈጸም የእርሱን ታላቅ ክብር የሚያሳይ ይሆናል (ከዮሐ 9፥3፤ 11፥4፡14-15፡45፤ ከ2ቆሮ 12፥7-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ለእኛም ሁሉ ለበጎ ይደረግልናል (ሮሜ 8፥28)።

(10) ራሳችንን ለእርሱ ሙሉ በሙሉ አሳልፈን የሰጠን ክርስቲያኖች ከሆንን፣ እግዚአብሔር እንደማይተወንና እንደማይረሳን መረዳት፥ እርሱ እጅግ በጣም ይወደናል፤ በእጆቹ መዳፍ ላይም ቀርጾናል (ኢሳ 49፥15-16)።

***ማስታወሻ፤*** መጽሐፍ ቅዱስ ሕክምናን በተገቢው ሁኔታ መከታተል ይደግፋል (ማቴ 9፥12፤ ሉቃ 10፥34፤ ቈላ 4፥14)።

### የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያልጾሙበት ምክንያት

*፡14-17 ተጓ ምብ — ማር 2፥18-22፤ ሉቃ 5፥33-39*

[14]የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ "እኛና ፈሪሳውያን
ስን ጾም፣ ያንተ ደቀ መዛሙርት ግን ለምን
አይጾሙም?" ብለው ጠየቁት።
[15]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሙሽራው
አብሮአቸው እያለ ሚዜዎቹ እንዴት ሊያዝኑ
ይችላሉ? ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት
ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ።
[16]"በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ዕራፊ
የሚጥፍ ሰው የለም፤ ይህ ከሆነ አዲሱ ዕራፊ
ካረጀው ልብስ ላይ ተቦጭቆ ቀዳዳውን
የባሰ ያሰፋዋል። [17]በአሮጌ አቍማዳ አዲስ
የወይን ጠጅ ማንም አይጨምርም፤ ይህ
ከሆነ አቍማዳው ይፈነዳል፤ የወይን
ጠጁም ይፈስሳል፤ አቍማዳውም ከጥቅም
ውጭ ይሆ ናል። ነገር ግን አዲስ የወይን
ጠጅ በአዲስ አቍማዳ ይጨመራል፤ በዚህ
ሁኔታ የወይን ጠጁና አቍማዳው በደህና
ተጠብቀው ይቈ ያሉ።"

9፥14 ማቴ3፥11፤ 11፥18፡19፤ ሉቃ18፥12
9፥15 ዮሐ3፥29፤ ሐሥ13፥2፡3፤ 14፥23
9፥18 ማቴ8፥2፤ ማር5፥23
9፥20 ማቴ14፥36፤ ማር3፥10፤ 6፥56፤ ሉቃ6፥19
9፥22 ቊ2፡29፤ ማቴ8፥13፤ 15፥28፤ ማር10፥52፤ ሉቃ7፥50፤ 17፥19፤ 18፥42፤ ዮሐ16፥33
9፥23 2ዜና35፥25፤ ኤር9፥17፡18

### ከሞት የተነሣችው ልጅና ከደም መፍሰስ የተፈወሰችው ሴት

*9፥18-26 ተጓ ምብ — ማር 5፥22-43፤ ሉቃ 8፥41-56*

[18]ኢየሱስ ሰዎቹን በማናገር ላይ ሳለ፣
አንድ ሹም ከፊቱ ተደፍቶ፣ "ልጄ ልትሞት
ተቃርባለች፤ በሕይወት እንድትኖር መጥ
ተህ እጅህን ጫንባት" አለው። [19]ኢየሱ ስም
ተነሥቶ አብሮት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ተከተሉት።
[20]ከዚያም ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ
ደም እየፈሰሳት ትሠቃይ የነበረች አንዲት
ሴት ከኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ነካች።
[21]እርሷም በልቧ፣ "የልብሱን ጫፍ እንኳ
ብነካ እፈወሳለሁ" የሚል እምነት ነበራት።
[22]ኢየሱስም ወደ ኋላ ዞወር ብሎ ሴቲቱን
አያትና፣ "አይዞሽ፤ ልጄ ሆይ፤ እምነትሽ
አድኖሻል" አላት። ሴቲቱም ወዲያውኑ
ተፈወሰች።
[23]ኢየሱስ ወደ ምኵራብ አለቃው ቤት

---

**9፥15 በዚያን ጊዜ ይጾማሉ፤** እርሱ ከሄደ በኋላ አማኞች መጾም እንዳለባቸው ኢየሱስ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው። አሁን ያለንበት ዘመን ማለትም ከዐረገበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ምጽአቱ ድረስ ያለው ጊዜ "ሙሽራው" በአካል የሌለበት ዘመን ነው። ቤተ ክርስቲያን የሙሽራውን ዳግም ምጽአት ትጠባበቃለች (25፥6፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ በተጠቀሰው ዘመን የሚጾመው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፤ (1) አማኝ የጌታን ዳግም ምጽአት መጠባበቁን የሚያሳይ ምልክት በመሆኑ፤ (2) ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ራስን የማዘጋጃ መንገድ በመሆኑ፤ (3) ክርስቶስ በምድር ስለሌለ የሐዘን መግለጫ በመሆኑ፤ (4) ስለ ኀጢአትና ስለ ዓለም ብክለት የሐዘን መግለጫ ምልክት በመሆኑ (6፥16 እና ማብ ይመ)።

**9፥17 በአሮጌ አቍማዳ አዲስ የወይን ጠጅ፤** ይህ ጥቅስ በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃርያን በተለያየ መንገድ ተተርጕሞአል። ሁለቱ አመለካከቶች የሚከተሉት ናቸው፤ (1) "አዲሱ የወይን ጠጅ" ከትኩስ የወይን ፍሬ የተጨመቀ ጭማቂ ነበር። እየፈላ ሲሄድ ማስቀመጫው አዲስ አቍማዳ ከሆነ ይለጠጣል እንጂ አይፈነዳም፤ አሮጌ አቍማዳ ከሆነ ግን ይፈነዳል። "አዲስ የወይን ጠጅ" አሮጌው የአይሁድ እምነት ሊይዘው የማይችለውንና ለውጥ የሚያመጣውን ወንጌልን ይወክላል። ይህ አመለካከት አጠያያቂ ነው፤ ይሁን እንጂ የወይን ጠጅን አፈላል ሂደት የሚያውቁ፣ አዲስና ጠንካራ የሆኑ አቍማዳዎች ቢታሸጉም እንኳ፤ ኀይለኛ ከሆነው የመፍላት እንቅስቃሴ የተነሣ ይፈነዳሉ በማለት ይናገራሉ (ኢዮ 32፥19)።

(2) ሁለተኛው ትርጓሜ አዲሱን የወይን ጠጅና አዲሱን አቍማዳ በደኅና ጠብቆ የመያዝን አስፈላጊነት በአጽንዖት እንደሚገልጽ ከመቍጠር አንጻር ይህን ምሳሌ ይመለከተዋል፤ (ሀ) "አዲሱ የወይን ጠጅ" ትኩስ ያልፈላ የወይን ፍሬ ጭማቂ ሲሆን፣ አዳኝ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን የመጀመሪያ መልእክትና በጴንጠቈስጤ ዕለት በኀይል የወረደውን መንፈስ ቅዱስን የሚወክል ነው። የኢየሱስ ዋነኛ ትኩረት መሠረታዊው ወንጌልና የመንፈስ ቅዱስ የመቤዠት ኀይል ከለውጥ ሁሉ፣ ከብክለትና ከጕድለት እንዲጠበቁ ማመልከት ነው። እንግዲህ ይህ ትርጓሜ በኢየሱስ ክርስቶስ ዋነኛ ትኩረት ይደገፋል፤ ይኸውም ወንጌል (አዲሱ የወይን ጠጅ) በፈሪሳውያን ትምህርትና (እርሾ) በአይሁድ እምነት መለወጥ እንደሌለበት ያመለክታል (የሚፈላ እርሾ ለውጥን የሚያመጣ ኀይል ነው፤ ከ16፥6፡12፤ ከዘፀ 12፥19፤ ከ1ቆሮ 5፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(ለ) በጥንት ዘመን የወይን ፍሬን ጭማቂ ባፋጭነት ለተወሰነ ጊዜ በደኅና ጠብቆ ለማቈየት ሰዎች ጭማቂውን በማጥለል ወይም በማፍላት በዕቃ አድርገው በቀዝቃዛ ስፍራ ያስቀምጡት ነበር (በገጽ 1547 ላይ፣ *"የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1"*) እና በገጽ 1603 ላይ፣ *"የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2"*) በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)። አዲስ አቍማዳዎች ያስፈልጋሉ፤ ምክንያቱም እንደ እርሾ ካለ ከሚፈላ ነገር ሁሉ ነጻ ስለሚሆኑ ነው። በአሮጌ አቍማዳ ውስጥ አዲስ የወይን ጠጅ ቢቀመጥ፣ ካለበት እርሾ የተነሣ በቀላሉ መፍላት ይጀምራል። የመፍላቱ ኀይል ውጤት ደግሞ አዲሱን የወይን ጠጅና አቍማዳዎቹን ማጣት ያስከትላል። በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ኮሉሜላ የተባለው ታላቁ ሮማዊ የእርሻ ሊቅ "ምንጊዜም ጣፋጭ የሆነውን" አዲስ የወይን ጠጅ በደኅና ሁኔታ ጠብቆ ለማቈየት በአዲስና በታሸገ ዕቃ ማስቀመጥ አስፈላጊ እንደ ሆነ ጽፎአል (ኮሉሜላ፤ ኦን አግሪካልቸር 12. 29)።

**9፥17 አዲስ የወይን ጠጅ ... በደኅና ተጠብቀው ይቈያሉ፤** ክርስቶስ በዚህ ስፍራ በአጽንዖት የተናገረው ለረዥም ጊዜ በተቻለ መጠን አዲስ የወይን ጠጅን በደኅና ጠብቆ ስለ ማቈየት ነው (ያለፈውን ማብ ይመ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የወይን ጠጅ ጣፋጭነቱን እንደ ጠበቀም ሆኖ ሳይፈላ ማቈየትን በተመለከተ የተዘረዘሩትን የተለያዩ ዘዴዎች በገጽ 1547 ላይ፣ *"የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1"*) እና በገጽ 1603 ላይ፣ *"የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2"*) በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመልከቱ።

እንደ ደረሰ የሐዘን እምቢልተኞችንና
የሚንጫጩትን ሕዝብ አይቶ፣ 24"ዞር
በሉ፤ ልጅቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም"
አላቸው፤ እነርሱ ግን ሣቁበት። 25ሕዝቡም
ከወጣ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ እጇን ያዘ፤
ልጅቱም ተነሥታ ቆመች። 26ወሬውም
በአካባቢው ሁሉ ተሰራጨ።

### የዐይነ ስውሮቹና የድዳው መፈወስ

27ኢየሱስም ከዚያ እንደ ሄደ ሁለት
ዐይነ ስውሮች፣ "የዳዊት ልጅ ሆይ፤ ማረን"
በማለት እየጮኹ ተከተሉት።
28ዐይነ ስውሮቹም ኢየሱስ ወደ
ገባበት ቤት ተከትለው ገቡ፤ ኢየሱስም፣
"ዐይናችሁን ላበራላችሁ እንደምችል
ታምናላችሁ?" ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ "አዎን፣ ጌታ ሆይ፤" ብለው
መለሱለት።
29ከዚያም ኢየሱስ ዐይናቸውን
ዳሰሰ፣ "እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ"
አላቸው። 30ዐይናቸውም በራ፤ ኢየሱስም፤
"ይህን ማንም እንዳያውቅ" ብሎ በጥብቅ
ማቴ 17፥20 አስጠነቀቃቸው። 31እነርሱ ግን ወጥተው
በአካባቢው ሁሉ ስለ ኢየሱስ አወሩ።
32ከዚያም ሲወጡ፣ በጋኔን የተያዘ ድዳ
ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 33ጋኔኑ ከወጣለት
በኋላ ድዳው መናገር ጀመረ፤ ሕዝ ቡም
ተደንቀው፣ "እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል
ምድር ታይቶ አያውቅም" አሉ።
34ፈሪሳውያን ግን፣ "አጋንንትን
የሚያወጣው፣ በአጋንንት አለቃ ነው" አሉ።

### ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው

35ኢየሱስ በምኵራቦቻቸው እያስተማረ፣
የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥራች እየሰበከ
እንዲሁም ደዌንና ሕመምን ሁሉ እየፈወሰ
በከተሞቹና በመንደሮቹ ዞረ። 36ሕዝቡም
እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና
ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ጊዜ አዘነላቸው።

9፥24 መዝ76፥5፤ ዳን12፥2፤ ዮሐ11፥11-14፤ ሐሥ7፥60፤ 13፥36፤ 20፥10፤ 1ቆሮ11፥30፤ 15፥6፡18፡20፤ 1ተሰ4፥13-16
9፥25 ሉቃ7፥14
9፥26 ቍ31፤ ማቴ4፥24፤ 14፥1፤ ማር1፥28፡45፤ ሉቃ4፥14፡37፤ 5፥15፤ 7፥17
9፥27 ማቴ1፥1፤ 12፥23፤ 15፥22፤ 20፥30፡31፤ 21፥9፡15፤ 22፥42፤ ማር10፥47
9፥28 ሐሥ14፥9
9፥29 ቍ22
9፥30 ማቴ8፥4
9፥31 ቍ26፤ ማር7፥36
9፥32 ማቴ4፥24፤ 12፥22-24
9፥33 ማር2፥12
9፥34 ማቴ12፥24
9፥35 ማቴ4፥23
9፥36 ዘኍ27፥17፤ 1ነገ22፥17፤ ሕዝ34፥5፡6፤ ዘካ10፥2፤ ማቴ14፥14፤ 15፥32፤ ማር8፥2
9፥37 ሉቃ10፥2፤ ዮሐ4፥35
10፥1 ማቴ4፥23፤ ማር3፥13-15፤ 6፥7፤ ሉቃ4፥36፤ 9፥1
10፥4 ማቴ26፥14-16፡25፡47፤ 27፥3፤ ማር14፥10፤ ዮሐ6፥71፤ 12፥4፤ 13፥2፡26፡27፤ ሐሥ1፥16
10፥5 1ነገ16፥24፤

37ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤
"መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን
ጥቂቶች ናቸው፤ 38ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ
መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።"

### የዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መላክ

*10፥2-4 ተጓ ምብ — ማር3፥16-19፤ ሉቃ 6፥14-16፤ የሐሥ1፥13*
*10፥9-15 ተጓ ምብ — ማር 6፥8-11፤ ሉቃ 9፥3-5፤ 10፥4-12*
*10፥19-22 ተጓ ምብ — ማር 13፥11-13፤ ሉቃ 21፥12-17*
*10፥26-33 ተጓ ምብ — ሉቃ 12፥2-9*
*10፥34፡35 ተጓ ምብ — ሉቃ 12፥51-53*

10 ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ
መዛሙርት ወደ እርሱ ጠርቶ ርኵሳን
መናፍስትን እንዲያወጡ፣ ደዌንና ሕማምን
ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው።
2የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም
የሚከተለው ነው፦ መጀመሪያ ጴጥሮስ
የተባለው ስምዖንና ወንድሙ እንድርያስ፣
የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብና ወንድሙ
ዮሐንስ፣ 3ፊልጶስና በርቶሎሜዎስ፣ ቶማስና
ቀረጥ ሰብሳቢው ማቴዎስ፣ የእልፍዮስ ልጅ
ያዕቆብና ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ፤
4ቀነናዊው* ስምዖንና በኋላ ኢየሱስን አሳልፎ
የሰጠው አስቆሮቱ ይሁዳ።
5እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን ኢየሱስ እንዲህ
ከሚል ትእዛዝ ጋር ላካቸው፤ "ወደ አሕዛብ
አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ
አትግቡ። 6ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደ
ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ። 7ሂዳችሁም፣

10፥5 2ነገ17፥24፤ ሉቃ9፥52፤ 10፥33፤ 17፥16፤ ዮሐ4፥4-26፡39፡40፤ 8፥48፤ ሐሥ8፥5፡25
10፥6 ኤር50፥6፤ ማቴ15፥24 10፥7 ማቴ3፥2

*10፥4 ቀነናዊ የሚለው ቃል አራማይክ ሲሆን፣ ቀነናውያን የተባሉት በዚያን ጊዜ የሮምን መንግሥት የሚቃወሙ የፖለቲካ ቡድን አባላት ነበሩ

9፥37 **መከሩ ብዙ ነው፤** ኢየሱስ አማኞች የጠፉትን ሁልጊዜ ማሰብ እንዳለባቸው አስጠነቀቀ፤ ምክንያቱም የጠፉት ሙድና ዘላለማዊ ነፍስ ያላቸው በመሆኑ፣ የዘላለምን ሕይወት በመንግሥተ ሰማይ ወይም በገሃነም ማሳለፍ ይችላሉ፤ ወንጌል ከተሰበከ ግን ከጠፉት አብዛኞዎቹ ድነው ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ (10፥28 እና ማብ ይመ)።

9፥38 **የመከሩ ጌታ ... እንዲልክ ለምኑት፤** ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ መርሖች የሚገልጽ ነው። ምንም ነገር ከማድረጉ በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለጸሎት ይጠራል። እግዚአብሔር ይህንን ሥራ የሚፈጽመው ሕዝቡ ከጸለየ በኋላ ብቻ ነው። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር ሥራውን በሕዝቡ ጸሎት ወስኖአል ማለት ነው። ከ9፥35—10፥1፡8 ባለው ዐውድ መሠረት ኢየሱስ በመንግሥቱ ሥራ ሠራተኞች እንዲሆኑለት የሚፈልጋቸው ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፤ (1) የመንግሥቱን ወንጌል የሚያስተምሩና የሚሰብኩ (9፥35)፣ (2) ሕሙማን የሚፈውሱ (9፥35፤ 10፥1፡8) እና (3) ርኩሳን መናፍስትን የሚያስወጡ (10፥1፡8)።

10፥1 **ርኩሳን መናፍስትን እንዲያወጡ ... ሥልጣን ሰጣቸው፤** ኢየሱስ ተከታዮቹ ርኩሳን መናፍስትን በማውጣትና ሕሙማንን በመፈወስ በክፉ ኀይላት ላይ ጦርነትን እንዲያውጁ ይፈልጋል። በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የሚሰነዘረው ይህ ብርቱ ክንድ በምድር ላይ ላለው የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጥ ቀዳሚ ክሥተት እንደ ሆነ ይታመናል (በገጽ 1443 ላይ፡ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

10፥7 **መንግሥተ ሰማያት ...** ስበኩ፤ ይህ ሐሳብ ያለበት ዐውድ (ቍ 1፡8) የእግዚአብሔርን መንግሥት መስበክ በነቢአት፣ በበሽታና በሰይጣን ኀይላት ላይ የእግዚአብሔርን ኀይል መግለጥን የሚጨምር መሆኑን ያመለክታል (በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የክርስቶስ ዐላማ መንግሥተ ሰማያትና ኀይሉ እንዲቀርቡና ድነትን፣ ጸጋንና ፈውስን ለእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲያመጡ ነው። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል መንግሥተ ሰማያት ካልተገለጠ፣ ሕዝቡ ከዓለም መንፈስና እግዚአብሔርን ከማያስደስተው ነገር ሁሉ ዘወር አይልም፤ "ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን

'መንግሥት ሰማያት ቀርባለች' ብላችሁ
ስበኩ። 8በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን
አስነሡ፤ ለምጻሞችን[a] አንጹ፤ አጋንንትን
አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትንም በነጻ
ስጡ። 9በመቀነታችሁ ወርቅም ሆነ ብር
ወይም መዳብ አትያዙ። 10ለመንገዳችሁም
ከረጢት፣ ትርፍ እጀ ጠባብ ወይም ጫማ
ወይም በትር አትያዙ፤ ለሠራተኛ የዕለት
ጕርሱ ይገባዋልና።
11"ወደ አንድ ከተማ ወይም መንደር
ስትገቡ ሊቀበላችሁ ፈቃደኛ የሆነ ሰው
ፈልጋችሁ በቤቱ ዕረፉ፤ እስክትወጡም
ድረስ በዚያው ቈዩ። 12ወደ ማንኛውም ሰው
ቤት ስትገቡ ሰላምታ አቅርቡ። 13ቤቱም
የሚገባው ሆኖ ከተገኘ፣ ሰላማችሁ ይደር
ሰው፤ የማይገባው ከሆነ ግን ሰላማችሁ
ወደ እናንተ ይመለስላችሁ። 14ማንም ሰው
ሊያስተናግዳችሁ ወይም የምትናገሩትን
ሊሰማ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ከቤቱ ወይም
ከከተማው ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ
አራግፉችሁ ውጡ። 15እውነት እላችኋለሁ፤
በፍርድ ቀን በዚያች ከተማ ከሚደርሰው
ቅጣት ይልቅ በሰዶምና በገሞራ
የሚደርሰው ይቀላል።
16"እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል
እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ብልጦች
እንደ ርግብ የዋሃን ሁኑ። 17"ሰዎች ይዘው
ለፍርድ ወደ ሸንጎ ያቀርቧችኋል፤ በምኵራ
ቦቻቸውም ይገርፏችኋል፤ ስለዚህ ከእነርሱ
ተጠንቀቁ። 18በእኔ ምክንያት ወደ ገዦችና
ወደ ነገሥታት ትወሰዳላችሁ፤ በእነርሱና

10፥9 ሉቃ22፥35
10፥10
1ጢሞ5፥18
10፥12
1ሳሙ25፥6
10፥14 ነህ5፥13፤
ማር6፥11፤
ሉቃ9፥5፤ 10፥11፤
ሐዋ13፥51፤
18፥6
10፥15
ዘፍ18፥20፤
19፥24፤
ማቴ11፥22፡24፤
12፥36፤
ሐዋ17፥31፤
2ጴጥ2፥6፡9፤
3፥7፤ 1ዮሐ4፥17፤
ይሁ6፡7
10፥16
ሉቃ10፥3፤
ሐዋ20፥29፤
1ቆሮ14፥20
10፥17
ማቴ5፥22፤
23፥34፤
ማር13፥9፤
ሐዋ5፥40፤
22፥19፤ 26፥11
10፥18
ሐዋ25፥24-26
10፥19 ዘፀ4፥12
10፥20
ሉቃ12፥11፡12፤
ሐዋ4፥8
10፥21 ቍ35፡36፤
ሚክ7፥6፤
ማር13፥12

በአሕዛብም ፊት ምስክር ትሆናላችሁ።
19በምትያዙበትም ጊዜ ምን እንናገራለን፣
ምንስ እንመልሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤
በዚያን ጊዜ የምትናገሩት ይሰጣችኋል፤
20በእናንተ የሚናገረው የሰማዩ አባታችሁ ማቴ
መንፈስ እንጂ እናንተ አይደላችሁምና። 24፥14
21"ወንድም ወንድሙን ለሞት
አሳልፎ ይሰጣል፤ አባትም ልጁን፤
ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ያምፃሉ፤
ያስገድሏቸዋልም። 22ስለ ስሜ ሰዎች ሁሉ
ይጠሏችኋል፤ ነገር ግን እስከ መጨረሻ
የሚጸና እርሱ ይድናል። 23በአንድ ስፍራ
ሲያሳድዱችሁ ወደ ሌላ ሽሹ፤ እውነት
እላችኋለሁ፣ የእስራኤልን ከተሞች
ሳታዳርሱ የሰው ልጅ ይመጣል።
24"ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፣ ሎሌም
ከጌታው አይበልጥም፤ 25ደቀ መዝሙር
መምህሩን፣ ሎሌም ጌታውን ከመሰለ
ይበቃዋል። ባለቤቱን 'ብዔልዜቡል'
ካሉት ቤተ ሰዎቹንማ እንዴት አብልጠው
አይሏቸውም!
26"ስለዚህ አትፍሯቸው፤ የተሸፈነ
መገለጡ፣ የተደበቀ መታወቁ አይቀርምና።
27በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን
አውሩት፤ በጆ ሮአችሁ የሰማችሁትን
በአደባባይ አውጁት፤ 28ሥጋን መግደል

10፥22 ማቴ24፥13፤ ማር13፥13፤ ሉቃ21፥19፤
ዮሐ15፥21፤ ራእ2፥10 10፥23 ሉቃ17፥30
10፥24 ዮሐ13፥16 10፥25 ማር3፥22 10፥26 ማር4፥22፤
ሉቃ8፥17 10፥28 ኢሳ8፥12፡13፤ ዕብ10፥31

[a]10፥8 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የቆዳ በሽታዎችን ያመለክታል

---

መንግሥትና ጽድቁን እሹ" (6፥33) እንዲሁም "መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች፣ እንዲሁም በምድር ትሁን" (6፥10 ይመ፤ ከማር 9፥29 ጋር ያነጻጽሩ) ብላችሁ ጸልዩ ተብሎአልና።

**10፥19 የምትናገሩት ይሰጣችኋል፤** ክርስቶስ የገባው የተስፋ ቃል በሐዋ 4፥8-12፡19-20፤ 21፥39—22፥21፤ 23፥1፡6፤ 24፥10-21፤ 26፥1-29 በሥራ ላይ እውን ሆኖ ታይቶአል። ከጰንጠቈስጤ ቀን በኋላም መንፈስ ቅዱስ ደቀ መዛሙርት ሲመሰክሩ ኀይልን ለመስጠት በሙላት ወርዶአል (ሐዋ 1፥8)።

**10፥23 የእስራኤልን ከተሞች፤** ክርስቶስ እርሱ እስኪመለስ ድረስ ወንጌል ለአይሁድ እንደሚሰበክ ለደቀ መዛሙርቱ እየነገራቸው ሳይሆን አይቀርም።

**10፥26፤ አትፍሯቸው፤** ደቀ መዛሙርት ለክርስቶስ የሚሠሩት ሥራና ከሰይጣን ጋር የሚያደርጉት ውጊያ ለሰይጣን አጸፋዊ ጥቃት ያጋልጣቸዋል (ቍ 16-25)፤ ሆኖም መፍራት አይገባቸውም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስና እግዚአብሔር አብ ይደግፏቸዋል (ቍ 20፡29-31)። በግሐድ፣ በግልጽና በድፍረት የክርስቶስን ቃል በመስበክ ታማኝነታቸውን በጽናት መግለጥ ይገባቸዋል።

**10፥28 በገሃነም፤** በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ቃል (በግሪክ ቋንቋ "ገና" ኤር 7፥31 እና ማብ ይመ) እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች የዘላለም ቅጣት የሚቀበሉበትን ስፍራ የሚያመለክት ነው (ከማር 9፥34፡48 ጋር ያነጻጽሩ)። የአንድ ሰው ህልውና በሞት እንደማያበቃ ነገር ግን በእግዚአብሔር ህልዎት ፊት ወይም በቅጣት ስፍራ ለዘላለም እንደሚቀጥል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። የጠፉት ስለሚያጋጥማቸው ሁኔታ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ልብ ይበሉ፡-

(1) በእግዚአብሔር ፊት ለተፈረደባቸው የዘላለም ቅጣት እንዳለ ኢየሱስ አስተምሮአል (5፥22፡29-30፤ 18፥9፤ 23፥15፡33፤ ማር 9፥43፡45፡47፤ ሉቃ 10፥15፤ 12፥5)። ይህም የማያቋርጥ ቅጣት የሚፈጸምበት አስደንጋጭ እውነታ ሲሆን፣ ቦታው፣ እሳቱ የማይጠፋበት (ማር 9፥43)፣ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ የተዘጋጀ የዘላለም እሳት (25፥41)፣ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ያለበት (13፥42፡50)፣ እስራትና ጨለማ ያለበት (22፥13) እንዲሁም ከመንግሥተ ሰማይ ተለይቶ በጭንቀትና በሥቃይ የሚኖርበት ነው (ሉቃ 16፥23)።

(2) የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ትምህርትም ይህንኑ የዘላለም ቅጣት የሚደግፍ ነው። ሐዋርያት ወንጌልን በማይታዘዙት ላይ (2ተሰ 1፥5-9) እግዚአብሔር በበቀል ስለሚያመጣባቸው ፍርድ፣ የጠፉት ከእግዚአብሔር ህልዎትና ክብር ስለ መለየታቸው (2ተሰ 1፥9) እንዲሁም በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ስለሚደርሰው መፈራረስ ተናግረዋል (ፊል 3፥18-19 ደግሞም ሮሜ 9፥22፤ 1ቆሮ 12፥22፤ ገላ 1፥9፤ 2ጢሞ 2፥12፤ ዕብ 10፥27፤ 2ጴጥ 2፥4፤ ይሁ 1፥7፤ ራእ 14፥10፤ 19፥20፤ 20፥10፡14 ይመ)።

(3) ክፉ አድራጊዎች መቀጣታቸው እንደማይቀር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። በዚህ ላይ የትምህርቱ ዋና ሐሳብ ውግዘት፣ ሥቃይና ለዘላለም ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ክርስቲያኖች በዚህ አስተምህሮ ደስ ላይሰኙ ወይም ላይረዱት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን መገዛት እንዲሁም የእግዚአብሔርን

እንጂ ነፍስን መግደል የማይችሉትን
አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንና ሥጋን በገሃነም
ማጥፋት የሚቻለውን ፍሩ። 29በእንድ
ሳንቲም^a ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች
እንዷቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር
ላይ አትወድቅም። 30የራስ ጠጉራችሁ እንኳ
አንድ ሳይቀር የተቈጠረ ነው። 31ስለዚህ
አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች ይልቅ ዋጋችሁ
የከበረ ነው።

32"በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣ እኔም
በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤
33ነገር ግን በሰው ፊት የሚክደኝን፣ እኔም
በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ።

34"እኔ የመጣሁት ሰላምን በምድር
ለማስፈን አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ
ሰላምን ለማውረድ አልመጣሁም። 35እኔ
የመጣሁት
" 'ልጅን ከአባት፣
ሴት ልጅን ከእናቷ
ምራትንም ከሀማቷ ለመለያየት ነው፤
36የሰው ጠላቶቹ፣
የገዛ ቤተ ሰዎቹ ይሆናሉ።'

37"ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን
የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ
ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ
ለእኔ ሊሆን አይገባም። 38መስቀሉን ተሸክሞ
የማይከተለኝ የእኔ ሊሆን አይገባውም።
39ሕይወቱን ሊያድን የሚፈልግ ያጠፋታል፤
ሕይወቱን ስለ እኔ አሳልፎ የሚሰጥ ግን
ያገኛታል።

40"እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤
እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።
41ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ

10፥30 1ሳሙ 14፥45፤ 2ሳሙ 14፥11፤ 1ነገ1፥52፤ ሉቃ21፥18፤ ሐሥ27፥34
10፥31 ማቴ6፥26፤ 12፥12
10፥32 ሮሜ10፥9
10፥33 ማር8፥38፤ 2ጢሞ2፥12
10፥35 ቍ 21
10፥36 ሚክ7፥6
10፥37 ሉቃ፥14፥26
10፥38 ማቴ16፥24፤ ሉቃ14፥27
10፥39 ዮሐ12፥25
10፥40 ዘዐ16፥8፤ ማቴ18፥5፤ ሉቃ9፥48፤ ሉቃ10፥16፤ ዮሐ12፥44፤ 13፥20፤ ገላ4፥14

^a10፥29 ግሪኩ አንድ አሳሪዮን ይላል

ውሳኔና ፍትሕ አምነን ልንቀበል ይገባል።

(4) ማንም ሰው እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ልጁን ይሞት ዘንድ እንደላከው ምንጊዜም ልብ ልንል ይገባል (ዮሐ 3፥16)። እግዚአብሔር ማንም ሰው ወደ ገሃነም እንዲገባ አይፈልግም ወይም አይሻም (2ጴጥ 3፥9)። ወደ ገሃነም የሚገቡት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ድነት የሚቃወሙ ናቸው (ሮሜ 1፥16—2፥10)። የገሃነም እውንነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁሉ ኃጢአትን አጥብቆ እንዲጠላ ያደርገዋል፤ የጠፉት ድነት እንዲያገኙ ባለማቋረጥ መሻትና ወደፊት ስለሚመጣው የጽድቅ ፍርድ ሰውን ሁሉ እንዲያስጠነቅቅም ይገፋፋዋል (ራእ 20፥14 እና ማብ ይመ)።

**10፥31 ዋጋችሁ የከበረ ነው፤** ታማኝ የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች በሰማያዊ አባታቸው ዘንድ ታላቅ ዋጋ እንዳላቸው ኢየሱስ አስተምሮአል። (1) እግዚአብሔር ለእናንተና ለግል ፍላጎታችሁ ዋጋ ይሰጣል፤ የእናንተን ፍቅርና ከእናንተ ጋር ኅብረት ለማድረግ ይሻል፡ ስለዚህ ስለ እናንተ በመስቀል ይሞት ዘንድ ኢየሱስን ላከው (ዮሐ 3፥16 እና ማብ ይመ)። ከእግዚአብሔር ሀልዎት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ፍጹም የራቃችሁ አይደላችሁም። እግዚአብሔር ፍላጎታችሁን፣ መከራችሁንና ሐዘናችሁን ሁሉ ያውቃል (6፥8)። (2) እናንተ ለእግዚአብሔር እጅግ ውድ ሰዎች ናችሁ፡ ስለዚህ እርሱ ከምድራዊ ነገሮች ሁሉ በላይ ለእናንተ ታማኝነት፣ ፍቅርና ታዛዥነት ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣል። በክርስቶስ ያላችሁ የማይናወጥ እምነት፣ በመከራና በችግር መካከል ጸንታችሁ መቆም መቻላችሁም የእግዚአብሔር ክብርና ግርማ ማረጋገጫ ነው። በመዝ 91፥14-16፤ 116፥15፤ በኢሳ 49፥19፤ በማቴ 11፥28-29፤ በሉቃ 12፥32፤ በዮሐ 13፥1፤ 14፥3፤ 17፥24፤ በሮሜ 8፥28፤ በ1ዮሐ 4፥19 ላይ የሚገኙትን የዋስትና ማረጋገጫ ሐሳቦች ያንብቡ።

**10፥32 በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፣** "መመስከር" (በግሪክ ቋንቋ "ሆሞሎጊኦ") ማለት ክርስቶስን የግል የሕይወት ጌታ አድርጎ ማወጅና በሌሎች ፊት ማለትም እርሱን፣ መንገዶቹንና የሕይወት መስፈርቶቹን በሚቃወሙት ሰዎች ፊት እንኳን ሳይቀር በግልጽ መናገር ማለት ነው።

**10፥34 ሰላምን ለማውረድ አልመጣሁም፤** ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "የሰላም ልዑል" ተብሎ ቢጠራም (ኢሳ 9፥6 ይመ፤ ከማቴ 5፥9፤ ከሮሜ 5፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እውነትም ሁልጊዜ በፍቅር መታወጅ ቢኖርበትም (ኤፌ 4፥15) የእርሱ መምጣትና የወንጌል መታወጅ መከፋፈልን የማምጣት አዝማሚያ አላቸው፡ ይህም ሆን ተብሎ የሚደረግበት ሁኔታ አለ (1) በክርስቶስ ማመን አማኝን ከኃጢአተኛና ከዓለም ይለያል (ቍ 32-37፤ ሉቃ 12፥51-53 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (2) የእግዚአብሔር ቃልና የቃሉ እውነት መታወጅ ተቃውሞን፣ መከፋፈልንና ስደትን ያመጣል (12፥24፤ 14፥4-12፤ 27፥13 ሐሥ 5፥17፤ 7፥54-60፤ 14፥22)፤ (3) በክርስቶስ ጻድቅ መስፈርት የሚመራ ሕይወት መሰደብንና ማላገጫ መሆንን ያስከትላል (5፥10-11)፤ (4) የአዲስ ኪዳንን ሐዋርያዊ እምነት ከኑፋቄ ትምህርት መከላከል መከፋፈልን ያመጣል (2ቆሮ 11፥12-15፤ ገላ 1፥9፤ ፊል 1፥15-17 ይመ፤ 2ጢሞ 1፥15 እና ማብ ይመ)፤ (5) ክርስቶስ ስለ ሰላምና ስለ አንድነት ያስተማረው ትምህርት፣ "ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማውረድ አልመጣሁም" ከሚለው ሐቅ ጋር በተለይ ውጥረት በበዛበት ወቅት በታማኝነት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል (ዮሐ 17፥21 እና ማብ ይመ)።

**10፥38 መስቀሉን ተሸክሞ፤** ማር 8፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**10፥41 ነቢይ ... ጻድቅ፤** ኢየሱስ በዚህ ስፍራ እውነትን የሚያውጁትንና ለፈሪሀ እግዚአብሔር ጽኑ አቋም ያላቸውን፣ አብዛኛውን ጊዜ ተቃውሞና ስደት የሚደርስባቸውን ነቢያትንና ጻድቃንን ስለ መቀበል ተናግሮአል (5፥10 ይመ)። ከዚህ የተነሣም ነቢያትን ወይም ጻድቃንን እንዲሁም መልእክቶቻቸውን የሚቀበሉ ከእግዚአብሔር ልዩ ሽልማትን ያገኛሉ። (1) ለእውነትና ለጽድቅ ያላችሁ መሰጠት ፍጹም ጽኑ ከሆነ፣ ጻድቃን ለሆኑ ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ሕይወታችሁን በመስጠት ያላችሁን ታካፍላላችሁ፤ በአገልግሎታቸው ትተባበሯቸዋላችሁ፤ ታጽናኗቸዋላችሁም፤ ስለዚህ ዋጋችሁ ያገለገላችኋቸውን ነቢያት ወይም ጻድቃን ዋጋ ያህል ይሆናል።

(2) በአንጻሩ አንድ ክርስቲያን በአዲስ ኪዳን በተገለጠው መሠረት የእግዚአብሔርን እውነት የማይሰብኩ ወይም እግዚአብሔር ባዘዘው የጽድቅ ሕይወት መስፈርት መሠረት የማይኖሩ አገልጋዮችንና ሰባኪዎችን መርዳት፣ መደገፍ ወይም ከእነርሱ ጋር መተባበር አይገባውም። እንደነዚህ ዐይነት ሰዎችን መርዳት እነርሱ ወደ ተወገዙበት ሁኔታ ውስጥ ያስገባል (2ዮሐ ይመ)።

ያገኛል፤ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚ ቀበል
የጻድቅን ዋጋ ያገኛል። 42ስለዚህ እውነት
እላችኋለሁ፣ ማንም ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች
ለአንዱ ደቀ መዝሙሬ በመሆኑ አንድ ጽዋ
ቀዝቃዛ ውሃ ቢሰጠው ዋጋ ውን አያጣም።"

## መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ የላከው ጥያቄ

*11፥2-19 ተጓ ምብ — ሉቃ 7፥18-35*

11 ኢየሱስ ለዐሥራ ሁለቱ ደቀ
መዛሙርቱ ትእዛዙን ሰጥቶ ከጨረሰ
በኋላ ለማስተማርና ለመስበክ ወደ ገሊላ
ከተሞች[a] ሄደ።
2ዮሐንስ በእስር ቤት ሆኖ ክርስቶስ
በማድረግ ላይ ያለውን ነገር በሰማ ጊዜ፣ ደቀ
መዛሙርቱን ወደ እርሱ ልኮ፣ 3"ይመጣል
ተብሎ የሚጠበቀው አንተ ነህ? ወይስ ሌላ
እንጠብቅ?" ሲል ጠየቀ።
4ኢየሱስም፣ እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
"ሄዳችሁ የምትሰሙትንና የምታዩትን
ለዮሐንስ ንገሩት፤ 5ዕውሮች ያያሉ፤
አንካሶች ይራመዳሉ፤ ለምጻሞች[b] ይነጻሉ፤
ደንቆሮዎች ይሰማሉ፤ ሙታን ይነሣሉ፤
ለድኾችም የምሥራች እየተሰበከ ነው፤
6በእኔ የማይሰናከልም ብፁዕ ነው።"
7የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከሄዱ በኋላ፣
ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤ "ወደ ምድረ በዳ ምን ልታዩ ወጣ
ችሁ? ሸምበቆ በነፋስ ሲወዛወዝ? 8ወይስ
ምን ልታዩ ወጣችሁ? ባማረ ልብስ ያጌጠ
ሰው? ባማረ ልብስ ያጌጡ በነገሥታት ቤት
አሉላችሁ። 9ታዲያ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይ
ልታዩ? አዎን፤ ከነቢይም የሚበልጥ ነው።
10እንዲህ ተብሎ የተጻፈለት እርሱ ነው፤

" 'በፊትህ መንገድህን ያዘጋጅልህ
ዘንድ፣
ከአንተ አስቀድሜ መልእክተኛዬን
እልካለሁ።'
11እውነት እላችኋለሁ፤ ከሴት ከተወለዱት
መካከል እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ያለ
አልተነሣም፤ ሆኖም በመንግሥተ
ሰማያት ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።
12ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ
አሁን ድረስ መንግሥተ ሰማይ በብዙ
ትገፋለች፤ የሚያገኟትም ብርቱዎች
ናቸው፤ 13ነቢያትም፣ የሙሴ ሕግም ሁሉ
እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናግረዋልና።
14እንግዲህ ልትቀበሉት ከፈቀዳችሁ
ይመጣል የተባለው ኤልያስ እርሱ ነው።
15ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።
16"ይህን ትውልድ በምን ልመስለው?
በገበያ ተቀምጠው ጓደኞቻቸውን እንዲህ
እያሉ የሚጣሩ ልጆችን ይመስላሉ፤
17" 'ዋሽንት ነፋንላችሁ፤
አልጨፈራችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤
አላለቀሳችሁም'
18ዮሐንስ ከመብልና ከመጠጥ ተቈጥቦ
በመምጣቱ፣ 'ጋኔን አለበት' ይሉታልና።
19የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፤
እነ ርሱም፣ 'በልቶ የማይጠግብ፣
ጠጪ እንዲሁም የቀረጥ ሰብሳቢዎችና
የኀጢአተኞች ወዳጅ' አሉት። ጥበብ ግን
በሥራዋ ጸደ ቀች።"

## ንስሓ ስላልገቡ ከተሞች የተነገረ ወዮታ

*11፥21-23 ተጓ ምብ — ሉቃ 10፥13-15*

20ከዚያም ኢየሱስ ብዙውን
ታምራት ያደረገባቸው ከተሞች ንስሓ
ባለመግባታቸው እንዲህ ሲል ወቀሳቸው፤
21"ወዮልሽ ኮራ ዚን፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤
በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና
በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ
ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሓ በገቡ
ነበር። 22ስለዚህ እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን

10፥42 ምሳ14፥31፤ 19፥17፤ ማቴ25፥40፤ ማር9፥41፤ ሐሥ10፥4፤ ዕብ6፥10
11፥1 ማቴ7፥28
11፥2 ማቴ3፥1፤ 14፥3
11፥3 መዝ118፥26፤ ዮሐ11፥27፤ ዕብ10፥37
11፥5 ኢሳ35፥4-6፤ 61፥1፤ ማቴ15፥31፤ ሉቃ4፥18፡19
11፥6 ማቴ13፥21፤ 26፥31
11፥7 ማቴ3፥1
11፥9 ማቴ14፥5፤ 21፥26፤ ሉቃ1፥76፤ 7፥26
11፥10 ሚል3፥1፤ ማር1፥2፤ ዮሐ3፥28፤ ሉቃ7፥27
11፥13 ሉቃ16፥16
11፥14 ሚል4፥5፤ ማቴ17፥10-13፤ ማር9፥11-13፤ ሉቃ1፥17፤ ዮሐ1፥21
11፥15 ማቴ13፥9፡43፤ ማር4፥23፤ ሉቃ14፥35፤ ራእ2፥7
11፥18 ማቴ3፥4፤ ሉቃ1፥15
11፥19 ማቴ9፥11
11፥21 ኢዩ3፥4፤ አሞ1፥9፤ ዮና3፥5-9፤ ማቴ15፥21፤ ማር3፥8፤ 6፥45፤ 8፥22፤ ሉቃ6፥17፤ 9፥10፤ ዮሐ1፥44፤ 12፥21፤ ሐሥ12፥20
11፥22 ቍ24፤ ማቴ10፥15

*[a] 11፥1 ግሪኩ ወደ ከተሞቻቸው ይላል*
*[b] 11፥5 የግሪኩ ቃል የግድ ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የተለያዩ የቆዳ በሽታዎችንም ያመለክታል*

11፥7 **ዮሐንስ፤** ክርስቶስ መጥምቁ ዮሐንስን 'በነፋስ የሚወዘወዝ ሸምበቆ አይደለም' በማለት የገለጸው፣ ዮሐንስ ጻድቅ ባሕርይ የነበረው፣ በጽኑ እምነቱም እውነትን በመስበክ ዝነኛ መሆኑን ለማመልከት ነበር። ዮሐንስ ለዘመን አመጣሽ አመለካከት ሳይንበረከክ፣ ሌሎችንም ሳይፈራ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰበከ። የሄሮድስን ግልጽ ኀጢአት የአይሁድ ባለሥልጣኖች ሁሉ በዝምታ አልፈውት ነበር፤ ዮሐንስ ግን ሳንዳፍታ እንኳ በዝምታ አላለፈውም። ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ፍጹም ታማኝ መሆኑን በመግለጥ ሄሮድስ የሠራውን ኀጢአት በጽናት ተቃወመ። ለሞት የሚዳርገው ቢሆንም እንኳ ኀጢአትን በመቃወም ከእግዚአብሔር ጋር ቆመ (14፥3-12)። ክርስቶስ የእያንዳንዱን አገልጋይ አገልግሎት፣ ባሕርይና በኀጢአት ላይ የሚወስደውን የተቃውሞ ርምጃ ስለሚመዝነው፣ የእግዚአብሔር ቃል ሰባኪ የሆነ ሁሉ ይህን ልብ ሊል ይገባል (ሉቃ 1፥17 እና ማብ ይመ)።

11፥11 **ይበልጠዋል፤** ይህ ዐረፍተ ነገር በአዲስ ኪዳን ዘመን ያሉ ታናናሾች ያላቸው መብት መጥምቁ ዮሐንስ ከነበረው መብት ይበልጣል ማለት ሊሆን ይችላል (በገጽ 1970 ላይ፣ *"የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። እነዚህ ታናናሾች ከእግዚአብሔር የተሰጠ የበለጠ የመገለጥ ሀብት ይኖራቸዋል (ከ13፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ታላላቅ ታምራትን ያለማመዳሉ (11፥5)፤ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ያያሉ፤ በጰንጠቈስጤ ዕለትም የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ይቀበላሉ (ሐሥ 2፥4)።

11፥12 **የሚያገኟትም ብርቱዎች ናቸው፤** በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

11፥19 **በልቶ የማይጠግብ፣ ጠጪ፤** ሉቃ 7፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ
ይቀልላቸዋል። 23አንቺም ቅፍርናሆም ወደ
ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት ፈለግሽ? ነገር ግን
ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው
ታምራት በሰ ዶም ቢደረግ ኖሮ፣ እስከ
ዛሬ በቆየች ነበር። 24ስለዚህ እልሻለሁ፤
በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ቅጣቱ ለሰዶም
ይቀልላታል።"

## ክርስቶስ የሚሰጠው ዕረፍት

*11፡25-27 ተጓ ምብ — ሉቃ 10፡21-22*

25በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤
"የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፤ ይህን
ከጥበበኞችና ከዐዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት
ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ 26አዎን
አባት ሆይ፤ ይህ በፊትህ በጎ ፈቃድህ ሆኖ
ተገኝቶአልና።
27"ሁሉ ነገር ከአባቴ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ
ሌላ ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድና
ወልድ ራሱ ፈቅዶ ከሚገልጥላቸው ሌላ
አብን የሚያውቅ የለም።
28"እናንት ሸክም የከበዳችሁና የደከማ
ችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት
እሰጣችኋለሁ። 29ቀንበሬን ተሸከሙ፤
ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት
ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤
30ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና።

## ሰንበትን ስለ ማክበር

*12፡1-8 ተጓ ምብ — ማር 2፡23-28፤ ሉቃ 6፡1-5*
*12፡9-14 ተጓ ምብ — ማር 3፡1-6፤ ሉቃ 6፡6-11*

12 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሰንበት ቀን
በእህል ዕርሻ ውስጥ አለፈ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ስለራባቸው እሸት ቀጥፈው
ይበሉ ጀመር። 2ፈሪሳውያንም ይህን

11፡23 ኢሳ14፡13-15፤ ማቴ4፡13
11፡24 ማቴ10፡15
11፡25 ማቴ13፡11፤ 16፡17፤ ሉቃ22፡42፤ 23፡34፤ ዮሐ11፡41፤ 12፡27፡28፤ 1ቆሮ1፡26-29
11፡27 ማቴ28፡18፤ ዮሐ3፡35፤ 10፡15፤ 17፡25፡26
11፡28 ዘፀ33፡14፤ ዮሐ7፡37
11፡29 መዝ116፡7፤ ኤር6፡16፤ ዮሐ13፡15፤ ፊል2፡5፤ 1ጴጥ2፡21፤ 1ዮሐ2፡6
11፡30 1ዮሐ5፡3 12፡1 ዘዳ23፡25 12፡2 ቍ10፤ ዘፀ20፡10፤ 23፡12፤ ዘዳ5፡14፤ ሉቃ13፡14፤ 14፡3፤ ዮሐ5፡10፤ 7፡23፤ 9፡16

---

**11፡28 ወደ እኔ ኑ፤** የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቸርነት ግብዣ፣ በዚህ ዓለም የኑሮ ችግርና ከራሳቸው ተፈጥሮ በሚመነጨ በደሎች አማካይነት፣ ሸክም ለከበዳቸውና ለደከሙ ሁሉ የቀረበ ነው። ወደ ኢየሱስ በመምጣት፣ የእርሱ አገልጋይ በመሆንና የእርሱን ትእዛዝ በመፈጸም፣ እጅግ ከባድ ከሆነው ሸክም ነጻ ትሆናላችሁ፤ እርሱም ዕረፍት፣ ሰላም እንዲሁም በሕይወት ጉዞ ይመራችሁ ዘንድ መንፈሱን ይሰጣችኋል። የምትሸከሙትን ማንኛውንም ችግርና ውጣ ውረድ ሁሉ መሸከም የምትችሉት በእርሱ ርዳታና ጸጋ ነው (ዕብ 4፡16 ይመ)።

**12፡1 በሰንበት፤** ሳምንታዊው ሰንበት (በግሪክ ቋንቋ ሳባቶን – ትርጒሙም ዕረፍት፣ ሥራን መተው ማለት ነው) የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ሲሆን፣ በሙሴ ሕግ መሠረት አንድ ሰው የተለመደ ሥራውን ትቶ ለዕረፍትና እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚጠቀምበት ቀን ነው (ዘፀ 20፡10፤ ዘዳ 5፡14፤ ዘፀ 20፡8 እና ማብ ይመ)። የሰንበት መርሕ በክርስቲያኖች ዘንድ በቋሚነት እንዲጠበቅ የሚያደርጉ በቂ ምክንያቶች አሉ፤ ቀጥሎ ያሉትም ከሳምንቱ ቀናት አንዱን ቀን የዕረፍትና የአምልኮ ቀን ማድረግ ተገቢ መሆኑን ያሳያሉ፦

(1) "እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከው" (ዘፍ 2፡3 እና ማብ ይመ፤ ከዘፀ 20፡11 ጋር ያነጻጽሩ) የሚለው ሐረግ፤ ከአይሁድ ሕግ በፊት የተቀደሰ የዕረፍት ቀን ተደንግጎ እንደ ነበር ያሳያል። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ከፍጥረት ጊዜ ጀምሮ ለአይሁድ ዘር ብቻ ሳይሆን ለሰው ሁሉ ከሰባቱ ቀን አንዱ የበረከት ምንጭ እንዲሆን መፈለጉን ነው።

(2) ኢየሱስ የዕረፍትን ቀን መርሕ ፈጽሞ አልሻረም፤ የሻረው ግን የአይሁድ መሪዎች ስለ ሰንበት የነበራቸውን የተዛባ አመለካከት ነው (ቍ 1-8፤ ሉቃ 13፡10-17፤ 14፡1-6)። የዕረፍት ቀን የተሰጠን ለመንፈሳዊና ለአካላዊ ደኅንነታችን መሆኑንም አስተምሮአል (ማር 2፡27)። ይህ መርሕ የተሻረ መሆኑን የሚያመለክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ክፍል አይገኝም።

(3) የሰባተኛው የዕረፍት ቀን መንፈሳዊ ዐላማ ክርስቲያኖችን የሚጠቅም ነው። በብሉይ ኪዳን ይህ ቀን ይጠቅም የነበረው ከሥራ ለማረፍና ራስን ለእግዚአብሔር ለማስረከብ ነው፤ ይህ ዕለት እግዚአብሔርን ለማወቅ ፊቱ የሚፈለግበትና የሚመለክበት ልዩ ቀን ሲሆን፣ በግልም ሆነ በጋራ በእግዚአብሔር ነገር ላይ ልዩ ትኩረት የሚሰጥበትም ነው (ዘሌ 24፡8፤ ዘኍ 28፡9)። ዛሬም ይህ ቀን እምነታችንንና ደስታችንን በዓለም፣ በራሳችን የግል መንገድ፣ ባለን ቁሳዊ ንብረት ወይም በግል ርካታችን ላይ እንድንጥል ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ መጣል ያለብን መሆኑን እንደገና እንድናረጋግጥ ዕድል ይሰጠናል (ከዘፀ 20፡10፤ 34፡21፤ ከኢሳ 38፡13 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ቀን ለክርስቶስ ያለንን የመጀመሪያውን መሰጠት የምናድስበት፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ያለንን አንድነት የምንገልጥበት፣ ከሰባቱ እጅ አንዱን ብቻ ሳይሆን ሁለንተናችን የእግዚአብሔር መሆኑን የምናስተውልበት ነው (ዕብ 4፡9-10)።

(4) ሰንበት እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸውን የሚገልጡበት የኪዳን ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ (ዘፀ 31፡16-17)፣ የክርስቲያን የአምልኮ ቀን እሑድም እኛ የክርስቶስ እንደ ሆንንና እርሱም ጌታችን እንደ ሆነ ለዓለም ምልክት ሆኖ ሊታይ ይችላል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች የሳምንቱን የመጀመሪያ ቀን እግዚአብሔርን የማምለኪያና የክርስቶስን ትንሣኤ የማክበሪያ ቀን በማድረግ ለይተውታል (ሐሥ 20፡7፤ 1ቆሮ 16፡2)።

(5) ሰንበት ቅዱስ ቀን እንዲሆን በእግዚአብሔር ተለይቶአል (ዘፍ 2፡3፤ ዘፀ 16፡23፤ 20፡11፤ 31፡14፤ ኢሳ 58፡13)። ስለዚህ ከሰባቱ ቀኖች አንደኛውን የሚቀድሱ አማኞች፤ እነርሱ ራሳቸው በጠማማ ትውልድ መካከል ተለይተው የቅድስና ሕይወት መኖር እንደሚገባቸው ማሰብ አለባቸው (ከዘፀ 31፡13፤ ከ1ጴጥ 2፡9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(6) በመጨረሻም ሰንበት እግዚአብሔር ለአማኞች ያለውን ፈቃድ እንደሚፈጽምና ፍላጎታቸውንም ለማሟላት ባለማቋረጥ በአጠገባቸው እንደሚገኝ የገባው ቃል ሆኖ ሊታይ ይችላል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ ጸሎታቸውን ለመስማት ፈቃደኛ ነው፤ ፍላጎታቸውንም ለመፈጸም ታማኝ ነው (ከዘፀ 31፡13፤ ከሕዝ 20፡12 ጋር ያነጻጽሩ)።

አይተው፣ "እነሆ፣ ደቀ መዛሙርትህ
በሰንበት ቀን መደረግ የሌለበትን እያደረጉ
ነው" አሉት።
[3]እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ዳዊትና
አብረውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ
እርሱ ምን እንዳደረገ አላነበባችሁምን? [4]ወደ
እግዚአብሔር ቤት ገባ፤ ለካህናት እንጂ ለእርሱም
ሆነ አብረውት ለነበሩት ያልተፈቀደውን
የተቀደሰ ኅብስት በላ። [5]ወይስ ካህናት
ሰንበትን ሽረው በቤተ መቅደስ ውስጥ ሥራ
ቢሠሩ በደል እንደማይሆንባቸው ከኦሪት
ሕግ አላነበባችሁም? [6]ነገር ግን እላችኋለሁ፤
ከቤተ መቅደስ የሚበልጥ[a] በዚህ አለ።
[7]'ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን እወዳለሁ'
የሚለው ቃል ምን ማለት እንደ ሆነ ብታውቁ
ኖሮ፣ በንጹሐን ላይ ባልፈረዳችሁ ነበር።
[8]የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።"
[9]ከዚያ ስፍራ ዕልፍ ብሎ በመሄድ ወደ
ምኵራባቸው ገባ፤ [10]በዚያም አንድ እጁ
ሽባ የሆነ ሰው ነበር፤ ኢየሱስን ሊከሱት
ምክንያት ፈልገው፣ "በሰንበት ቀን መፈወስ
ተፈቅዶአል?" ብለው ጠየቁት።
[11]እርሱም፣ "ከእናንተ መካከል የአንዱ
ሰው በግ በሰንበት ቀን ጕድጓድ ቢገባበት
ፀጕን ከገባበት ጕድጓድ ጎትቶ አያወጣው
ምን? [12]ታዲያ ሰው ከበግ እጅግ አይበል
ጥምን? ስለዚህ በሰንበት ቀን በጎ ማድረግ
ተፈቅዶአል" አላቸው።
[13]ከዚያም ሰውየውን፣ "እጅህን ዘርጋ"
አለው፤ ሰውየውም እጁን ዘረጋ፤ እንደ
ሌላኛውም እጁ ደህና ሆነለት። [14]ፈሪሳውያን
ግን ከዚያ ወጣ ብለው ኢየሱስን እንዴት
እንደሚገድሉት ተማከሩ።

## እግዚአብሔር የመረጠው አገልጋይ

[15]ኢየሱስ ሐሳባቸውን አውቆ ከዚያ
ዘወር አለ። ብዙ ሕዝብም ተከተሉት፤
ሕመምተኞችን ሁሉ ፈወሰ፤ [16]ማንነቱን
ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። [17]ይህም
የሆነው በነቢዩ በኢሳይያስ እንዲህ ተብሎ
የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው፤
[18]"እነሆ የመረጥሁት፣
የምወድደውና በእርሱ ደስ የሚለኝ
አገልጋዬ፣
መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤
እርሱም ለአሕዛብ ፍትሕን
ያውጃል።

12፥3 1ሳሙ21፥6
12፥4 ዘሌ24፥5:9
12፥5 ዘኍ28፥9:10፤ ዮሐ7፥22:23
12፥6 ቍ41:42
12፥7 ሆሴ6፥6፤ ሚክ6፥6-8፤ ማቴ9፥13
12፥8 ማቴ8፥20
12፥10 ቍ2፤ ማር3፥2፤ 12፥13፤ ሉቃ11፥54፤ 14፥1፤ 20፥20
12፥11 ሉቃ14፥5
12፥12 ማቴ6፥26፤ 10፥31
12፥14 ዘፍ37፥18፤ መዝ71፥10፤ ማቴ26፥4፤ 27፥1፤ ማር3፥6፤ ሉቃ6፥11፤ ዮሐ5፥18፤ 7፥1:19፤ 11፥53
12፥15 ማቴ4፥23
12፥16 ማቴ8፥4
12፥17 ማቴ1፥22
12፥18 ማቴ3፥17፤ ዮሐ3፥34
12፥21 ኢሳ42፥1-4
12፥22 ማቴ4፥24
12፥23 ማቴ9፥27
12፥24 ማቴ9፥34፤ ማር3፥22
12፥25 ማቴ9፥4
12፥26 ማቴ4፥10
12፥27 ቍ24፤ ሐሥ19፥13
12፥28 ማቴ3፥2
12፥30 ማር9፥40፤ ሉቃ11፥23
12፥31 ማር3፥28:29፤ ሉቃ12፥10

[19]አይጨቃጨቅም ወይም አይጮኽም፤
ድምፁም በአደባባይ አይሰማም።
[20]ፍትሕን ለድል እስኪያበቃ ድረስ፣
የተቀጠቀጠውን ሸምበቆ
አይሰብርም፤
የሚጤሰውንም የጧፍ ክር
አያጠፋም።
[21]አሕዛብ በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።"

## ኢየሱስ በአጋንንት ሥልጣን አጋንንትን ያወጣል መባሉ

*12፥25-29 ተጓ ምብ — ማር 3፥23-27፤ ሉቃ 11፥17-22*

[22]ከዚህ በኋላ በጋኔን ተይዞ ማየትና
መናገር የማይችል ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤
ኢየሱስም ፈወሰው፤ ሰውየውም ማየትና
መናገር ቻለ። [23]ሕዝቡም ሁሉ ተደንቀው ማቴ 15፥22-31
"ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?" አሉ።
[24]ነገር ግን ፈሪሳውያን ይህን በሰሙ
ጊዜ፣ "ይህ ሰው አጋንንትን የሚያወጣው
በአጋንንት አለቃ በብዔልዜቡል ብቻ መሆን
አለበት" አሉ።
[25]ኢየሱስም ሐሳባቸውን በውቀ እንዲህ
አላቸው፤ "እርስ በእርሱ የተከፋፈለ
መንግሥት ሁሉ ይወድቃል፤ እርስ በእርሱም
የተከፋፈለ ከተማ ወይም ቤት አይጸናም።
[26]ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያስወጣ ከሆነ፣
እርስ በእርሱ ተለያይቷል ማለት ነው፤
እንዲህ ከሆነ ደግሞ መንግሥቱ እንዴት
ጸንቶ ሊቆም ይችላል? [27]እኔ አጋንንትን
የማስወጣው በብዔልዜቡል ከሆነ፣
ልጆቻችሁ በምን ሊያ ስወጧቸው ነው?
ስለዚህ ልጆቻችሁ ይፈርዱባችኋል። [28]ነገር
ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር
መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ
እናንተ መጥታ ለች።
[29]"ወይስ አንድ ሰው ወደ ኀይለኛ ሰው
ቤት ገብቶ ንብረቱን ለመዝረፍ ቢፈልግ፣
አስቀድሞ ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር
እንዴት አድርጎ ይሳካለታል?
[30]"ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤
ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ሁሉ ይበትናል።
[31]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ኀጢአት መሥራትና
የስድብ ቃል ሁሉ መናገር ለሰዎች ይቅር
ይባልላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ

[a] 12፥6 ወይም አንድ ነገር፤ ቍ 41 እና 42 ይመ

12፥28 **የእግዚአብሔር *መንግሥት*፤** በገጽ 1443 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር መንግሥት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
12፥29 ***ያንን ኀይለኛ ሰው ሳያስር*፤** በገጽ 1499 ላይ፣ «*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
12፥31 **በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል፤** በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሆን ብሎ የሚነገር የስድብ ቃል ስለ ክርስቶስን ቃሉ ኀጢአትን በማውገዝ የሚያከናውነውን የመለወጥ ሥራ ባለማቋረጥ የሚደረግ ተቃውሞ ነው (ከዮሐ 16፥7-11 ጋር ያነጻጽሩ)። የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ የሚጋፉና የሚቃወሙ ወደ ይቅርታ ሊመራቸው ከሚችል ብቸኛ ኀይል ራሳቸውን ያርቃሉ። የሚከተሉት ሂደቶች በመንፈስ ቅዱስ ላይ ወደሚነገር የስድብ ቃል የሚመሩ ናቸው፦ (1) መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን (ኤፌ 4፥30)፤ ይህ በተከታታይ የሚደረግ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስን ወደ መቃወም ይመራል (ሐሥ 7፥51)፤ (2) መንፈስ ቅዱስን መቃወም የመንፈስ ቅዱስን እሳት ወደማጥፋት ይመራል (1ተሰ 5፥19)፤ (3) የመንፈስ ቅዱስን እሳት ማጥፋት ልብን ወደ ማደንደን ይመራል (ዕብ 3፥8-13)፤ (4) ልብን ማደንደን ለማይረባ አእምሮ ዐልፎ ወደ መሰጠትና ክፉውን መልካም፤ መልካሙን ደግሞ ክፉ ወደ ማለት ይመራል (ኢሳ 5፥20፤ ሮሜ 1፥28)። በእግዚአብሔር

ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ይቅር አይባልም።
32ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚናገረው
ክፉ ቃል ይቅር ይባላል፤ በመንፈስ ቅዱስ
ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን በዚህም ሆነ
በወዲያኛው ዓለም ይቅር አይባልም።
33"ዛፍ ሁሉ በፍሬው ስለሚታወቅ፣
መልካም ፍሬ እንድታገኙ መልካም ዛፍ
ሉቃ 6፡43-44 ይኑራችሁ፤ መጥፎ ዛፍ ቢኖራችሁ ግን
መጥፎ ፍሬ ታገኛላችሁ። 34እናንት የእፉኝት
ልጆች፤ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም
ነገር መናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ
ውስጥ የሞላውን አንደበት ይናገረዋልና።
35መልካም ሰው በልቡ ካከማቸው መልካም
ነገር በጎ ነገር ያወጣል፤ ክፉ ሰውም በልቡ
ካከማቸው ክፉ ነገር መጥፎ ነገር ያወጣል።
36ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለ ተናገሩት
ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል።
37ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤
ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃልና።"

## ማረጋገጫ ምልክት ስለ መሻት

*12፥39-42 ተጓ ምብ — ሉቃ 11፥29-32*
*12፥43-45 ተጓ ምብ — ሉቃ 11፥24-26*

38ከዚያም አንዳንድ የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራንና ፈሪሳውያን፣ "መምህር
ሆይ፤ ከአንተ ታምራዊ ምልክት ማየት
እንፈልጋለን" አሉት።
39እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን
ይጠይቃል፤ ነገር ግን ከነቢዩ ዮናስ ምልክት
በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም። 40ዮናስ
በዓሣ ዐንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት
ሌሊት እንደ ቈየ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ
ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ሆድ
ውስጥ ይቈያል። 41የነነዌ ሰዎች በፍርድ
ዕለት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው
ይፈርዱበታል፤ እነርሱ በዮናስ ስብከት
ንስሓ ገብተዋልና። እነሆ፤ ከዮናስ የሚ
በልጥ እዚህ አለ። 42በፍርድ ዕለት የደቡብ
ንግሥት ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ
ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ
ለመስማት ከምድር ዳርቻ መጥታለችና።
እነሆ፤ ከሰሎሞን የሚበልጥ እዚህ አለ።
43"ርኩስ መንፈስ ከሰው ከወጣ በኋላ
ዕረፍት ለማግኘት ውሃ በሌለበት ደረቅ ቦታ
ይንከራተታል፤ የሚሻውን ዕረፍት ግን አያ
ገኝም። 44ከዚያም፣ 'ወደ ነበርሁበት ቤት
ተመልሼ ልሂድ' ይላል፤ ሲመለስም ቤቱ
ባዶ ሆኖ፣ ጸድቶና ተዘጋጅቶ ያገኘዋል።
45ከዚያም ይሄድና ከራሱ የባሱ ሌሎች
ሰባት ክፉ መናፍስት ይዞ ይመጣል፤ እነር
ሱም ሰውየው ውስጥ ገብተው ይኖራሉ።
የዚያም ሰው የኋለኛው ሁኔታ ከፊተኛው
የከፋ ይሆናል። በዚህ ክፉ ትውልድም ላይ
እንዲሁ ይሆንበታል።"

## የኢየሱስ እናትና ወንድሞች

*12፥46-50 ተጓ ምብ — ማር 3፥31-35፤*
*ሉቃ 8፥19-21*

46ኢየሱስ ለሕዝቡ ሲናገር ሳለ፣ እናቱና
ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ
ቆመው ነበር። 47አንድ ሰውም፣ "እነሆ፣
እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው
በውጭ ቆመዋል" አለው።[a]
48ኢየሱስም፣ "እናቴ ማን ናት? ወንድ
ሞቼስ እነማን ናቸው?" ሲል መለሰለት።
49በእጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ
እንዲህ አለ፤ "እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ
ናቸው፤ 50በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ
የሚያደርግ ሁሉ፣ ወንድሜ፣ እኅቴና
እናቴም ነው።"

## የዘሪው ምሳሌ

*13፥1-15 ተጓ ምብ — ማር 4፥1-12፤*
*ሉቃ 8፥4-10*
*13፥16፡17 ተጓ ምብ — ሉቃ 10፥23፡24*
*13፥18-23 ተጓ ምብ — ማር 4፥13-20፤*
*ሉቃ 8፥11-15*

13 በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ
በባሕሩ ዳር አጠገብ ተቀመጠ። 2ብዙ
ሕዝብም ስለ ከበበው በባሕሩ ዳር ትቶአቸው

12፥32 ማር10፥30፤ ሉቃ20፥34፡35፤ ኤፌ1፥21፤ ቲቶ2፥12፤ ዕብ6፥5
12፥33 ማቴ7፥16፡17፤ ሉቃ6፥43፡44
12፥34 ማቴ3፥7፤ 15፥18፤ 23፥33፤ ሉቃ6፥45
12፥37 ኢዮ15፥6፤ ምሳ10፥14፤ 18፥21፤ ያዕ3፥2
12፥38 ማቴ16፥1፤ ማር8፥11፡12፤ ሉቃ11፥16፤ ዮሐ2፥11፡18፤ 4፥48፤ 6፥30፤ 1ቆሮ1፥22
12፥39 ማቴ16፥4፤ ሉቃ11፥29
12፥40 ማቴ8፥20፤ 16፥21
12፥41 ዮና1፥2፤ 3፥5
12፥42 1ነገ10፥1፤ 2ዜና9፥1
12፥45 2ጴጥ2፥20
12፥46 ማቴ1፥18፤ 2፥11፡13፡14፡20፤ 13፥55፤ ሉቃ1፥43፤ 2፥33፡34፡48፡51፤ ዮሐ2፥1፡5፡12፤ 7፥3፡5፤ 19፥25፡26፤ ሐሥ1፥14፤ 1ቆሮ9፥5፤ ገላ1፥19
12፥50 ማቴ6፥10፤ ዮሐ15፥14
13፥1 ቍ36፤ ማቴ9፥28
13፥2 ሉቃ5፥3

[a]12፥47 አንዳንድ ትርጒሞች ይህን ጥቅስ ይዘላሉ

ብቻ የሚወሰነው ይህ የልብ ድንዳኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፡ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው ወደ ንስሓ መምራቱን ያቆማል (ከዘፍ 6፥3 ጋር ያነጻጽሩ፡ ዘዳ 29፥18-21 እና ማብ፤ 1ሳሙ 2፥25 እና ማብ፤ ምሳ 29፥1 እና ማብ ይመ)። ይቅር የማይባል ኀጢአት ሠርተናል በማለት የሚጨነቁ፣ ምሕረትን ለመቀበል መፈለጋቸውና ኀጢአታቸውን ለመናዘዝ ፈቃደኛ መሆናቸው ይቅር የማይባል ኀጢአት ላለመሥራታቸው ማስረጃ ይሆናቸዋል (በገጽ 1962 ላይ፣ *"ክሕደት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**12፥36 በፍርድ ቀን፤** በገጽ 1822 ላይ፣ *"በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**12፥37 ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃልና፤** ሉቃ 13፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**12፥40 ዮናስ፤** ታሪካዊ እውነት እንደመሆኑ መጠን ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን የዮናስን ታሪክ መቀበሉ ግልጽ ነው (ዮና 1፥17 እና ማብ ይመ)። በብሉይ ኪዳን የተፈጸሙትን ታምራት የሚክዱ የዘመኑ ተጠራጣሪዎች ችላ ሊባሉ አይገባም፤ በኢየሱስ ቃል መሠረትም ሊፈረድባቸው ይገባል።

**12፥43 ርኩስ መንፈስ፤** በአጋንንት መያዝን በተመለከተ ከቍ 43-45 ያለው ክፍል ሦስት አስፈላጊ እውነቶችን ያስተምራል፤ (1) ርኩሳን መናፍስት ቀደም ብለው ይዘውት ወደ ነበረ ሰው መመለስን ይሻሉ (ቍ 44)፤ (2) በዚያ ሰው ልብ ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረ ከሆነ፣ ርኩሳን መናፍስት ተመልሰው ሊይዙት አይችሉም (ቍ 44 ይመ፤ ከ1ቆሮ 6፥19፤ ከ2ቆሮ 6፥15-16 ማብ ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) አንድ አገር ወይም ኅብረተ ሰብ በክፉ ነገር ደስ መሰኘትን የሚሻው፣ ያ ኅብረተ ሰብ ራሱ በአጋንንት የተያዘ ከሆነ ነው (ቍ 45 ይመ፤ ከራእ 16፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

# የእግዚአብሔር መንግሥት

*ማቴ 12፥28 "ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ መጥታለች።"*

**የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይ፤** የእግዚአብሔር መንግሥት (መንግሥተ ሰማይ) እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም መጥቶ በሰይጣን ግዛትና በዚህ ዓለም የአሁኑ አሠራር ላይ ኀይሉን፣ ክብሩንና ሥልጣኑን የሚያረጋግጥበትን ሁኔታ የሚገልጽ ሐሳብ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ከድንት ወይም ከቤተ ክርስቲያን ይበልጣል፤ እግዚአብሔር በሠራው ሥራ ሁሉ ላይ ራሱን በኀይል የሚገልጥበት ነውና።

(1) የእግዚአብሔር መንግሥት በመሠረቱ መለኮታዊ ኀይል በተግባር የሚረጋገጥበት ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ መንፈሳዊ አገዛዙን የሚጀምረው በሕዝቡ ልብና በሕዝቡ መካከል ነው (ዮሐ 14፥23፤ 20፥22)። እርሱ ወደ ዓለም በኀይል ይመጣል (ኢሳ 64፥1፤ ማር 9፥1፤ 1ቆሮ 4፥20)። ይህን ኀይል ቊሳዊ ወይም ፖለቲካዊ ኀይል አድርገን ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ኀይል አድርገን ማየት አለብን። የእግዚአብሔር መንግሥት የሃይማኖትና የፖለቲካ መለኮታዊ አገዛዝ አይደለም፤ በዚህ ዓለም ባሉት መንግሥታት ላይ ያለ የማኅበራዊና የፖለቲካዊ አገዛዝ ጒዳይም አይደለም (ዮሐ 18፥36)። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ዓለምን ለመቤዠትና ለማደስ ማኅበራዊ ወይም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አያደርግም፤ የኀይል እንቅስቃሴንም አይጠቀምም (ማቴ 26፥52፤ ዮሐ 18፥36 እና ማብ ይመ)። ዓለም በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላት ሆና ትቈያለች (ዮሐ 15፥19፤ ሮሜ 12፥1-2፤ ያዕ 4፥4፤ 1ዮሐ 2፥15-17፤ 4፥4)። እግዚአብሔር በግልጽ ፍርድና ኀይል የሚገዛበት ዘመን የሚመጣው በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ ብቻ ነው (ራእ 19፥11-12)።

(2) እግዚአብሔር ራሱን በኀይል ስለሚገልጽ፣ ዓለም በቀውስ ውስጥ ትገባለች። የእግዚአብሔር ኀይል መገለጥ፣ የዲያብሎስን ግዛት በሥጋት እንዲሞላ ያደርገዋል (ማቴ 4፥3 ...፤ 12፥29፤ ማር 1፥24)፤ ስለዚህ ማንኛውም ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት ከመገዛት ወይም ካለመገዛት ውሳኔ ጋር ይጋፈጣል (ማቴ 3፥1-2፤ 4፥17፤ ማር 1፥14-15)። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት አስፈላጊውና መሠረታዊው ሁኔታ፣ "ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ" (ማር 1፥15) የሚለውን ቃል መቀበል ነው።

(3) በመለኮታዊ ኀይል ወደ ዓለም ዘልቆ መግባት የሚከተሉትን ያካትታል፤ (ሀ) በሰይጣን አገዛዝና ግዛት ላይ የመንፈሳዊ ኀይልን የበላይነት ማስፈንን (ማቴ 12፥28፤ ዮሐ 18፥36)፤ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት የሰይጣንን አገዛዝ የሚፈራርስና (ዮሐ 12፥31፤ 16፥11) የሰውን ዘር ከአጋንንት (ማር 1፥34፡39፤ 3፥14-15፤ ሐሥ 26፥18) እና ከኀጢአት (ሮሜ 6) ኀይል ነጻ የማውጣት ጅማሬ ነው። (ለ) ታምራትን ለማድረግና ድዉያንን ለመፈወስ የማያስችል ኀይል መለቀቅን (ማቴ 4፥23፤ 9፥35፤ ሐሥ 4፥30፤ 8፥7 ይመ፤ በገጽ 1433 ላይ፣ "መለኮታዊ ፈውስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኲረት ጽሑፍ ይመ)። (ሐ) ኀጢአትን፣ ጽድቅንና ፍርድን በተመለከተ ወቀሣን የሚያስከትል የወንጌል ስብከትን (ማቴ 11፥5፤ ዮሐ 16፥8-11፤ ሐሥ 4፥33)። (መ) ንስሓ በመግባት በወንጌል የሚያምኑ ሰዎች ድነትን ማግኘትንና መቀደስን (ዮሐ 3፥3፤ 17፥17፤ ሐሥ 2፥38-40፤ 2ቆሮ 6፥14-18 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፤ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኲረት ጽሑፍ ይመ)። (ሠ) ስለ ክርስቶስ ለመመስከር የሚያስችል ኀይልን ለመቀበል በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን (ሐሥ 1፥8 እና ማብ፤ 2፥4 እና ማብ ይመ)።

(4) አንድ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት በሕይወቱ መለማመዱን የሚያረጋግጥበት አስፈላጊ ማስረጃ፣ "በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት ነው" (ሮሜ 14፥17)።

(5) ይህኛው የእግዚአብሔር መንግሥት የአሁንም ሆነ የወደፊት እውነታ ነው። በዛሬው ዓለም የሚፈጸም የአሁኑ ዘመን እውነታ ነው (ማር 1፥15፤ ሉቃ 18፥16-17፤ ቈላ 1፥13፤ ዕብ 12፥28)፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር አገዛዝና ኀይል ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ አልሆኑም። የሰይጣንና የክፉ ሰዎች ሥራና ተጽዕኖ እስከዚህ ዘመን ፍጻሜ ድረስ ይቀጥላል (1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 3፥1-5፤ ራእ 19፥19-20፥10)። የወደፊቱ የእግዚአብሔር ክብር፣ ኀይልና መንግሥት የሚገለጠው ኢየሱስ በዓለም ላይ ሊፈርድ ተመልሶ ሲመጣ ነው (ማቴ 24፥30፤ ሉቃ 21፥27፤ ራእ 19፥11-20፤ 20፥1-6)። የእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛ የፍጻሜ ደረጃ ላይ የሚደርሰው፣ ክርስቶስ በመጨረሻ በክፉ ሁሉ ላይና በተቃዋሚ ኀይል ላይ ድል በሚያገኝበትና መንግሥቱን

ለእግዚአብሔር አብ በሚያስረክብበት ጊዜ ነው (1ቆሮ 15፥24-28፤ ራእ 20፥7-21፥8 እና ማር 1፥15 እንዲሁም በቤዛነት ታሪክ ውስጥ ስለ *መንግሥቱ* መገለጥ የተጠቀሱትን *አያሌ ማብራሪያዎች ይመ*)።

**በመንግሥቱ ውስጥ የአማኞች ድርሻ፤** አዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር *መንግሥት* ውስጥ ስላለው የአማኞች ድርሻ የሚናገራቸው አያሌ ነገሮች አሉት።

(1) የእግዚአብሔር *መንግሥት*፣ በሚገለጥበት በማንኛውም ነገር ሁሉ ላይ ማለትም የእግዚአብሔር ሀልዎትና ኀይል በግል ሕይወታቸውና በክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ሕይወት ይገለጥ ዘንድ አማኞች ያለማቋረጥ የመፈለግ፣ የመራብና የመጠማት ኀላፊነት አለባቸው (ማቴ 5፥10 እና ማብ፤ 6፥33 እና ማብ ይመ)።

(2) በማቴ 11፥12 ላይ ኢየሱስ በእግዚአብሔር *መንግሥት* ውስጥ ስለሚኖሩ ሰዎች ባሕርይ ተጨማሪ መረጃ ሰጥቶአል። በዚያም የእግዚአብሔር *መንግሥት* ኀይልን በተሞሉ ሰዎች እንደምትያዝ አመልክቶአል፤ እነዚህም ሰዎች በኀጢአት ከተሞላ ከሰው ዘር ድርጊቶች በመለየት ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው ወደ ክርስቶስ፣ ወደ ቃሉና ወደ ጻድቅ መንገዱ የተመለሱ ናቸው። የቱንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍልም እንደነዚህ ያሉት ሰዎች የእግዚአብሔርን *መንግሥት* ከሙሉ ኀይሉ ጋር በብርታት ይፈልጋሉ። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔርን *መንግሥት*ና በረከቶቹን ሁሉ መለማመድ፣ ብርቱ ጥረትንና የማያቋርጥ ልፋትን ይጠይቃል፤ ይህም ሰይጣንን፣ ኀጢአትንና ዘወትር ብልሹ ሆኖ የሚገኘን ኅብረተ ሰብ ለመቃወም ከሚያስችል ብርቱ ፈቃደኝነት ጋር የእምነት ተጋድሎን ማሳየት ነው።

(3) የእግዚአብሔር *መንግሥት* ዐልፎ ዐልፎ ለሚጸልዩ ወይም ከዓለም ጋር ተመሳስለው ለሚኖሩ፣ ቃሉን ችላ ለሚሉና አነስተኛ ጥማት ላላቸው ሰዎች የሚሆን አይደለም። እንደ ዮሴፍ (ዘፍ 39፥9)፣ እንደ ናታን (2ሳሙ 12፥7)፣ እንደ ኤልያስ (1ነገ 18፥21)፣ እንደ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ (ዳን 1፥8፤ 3፥16-18)፣ እንደ መርዶክዮስ (አስ 3፥4-5)፤ እንደ ጴጥሮስና ዮሐንስ (ሐሥ 4፥19-20)፣ እንደ እስጢፋኖስ (ሐሥ 6፥8፤ 7፥51) እና እንደ ጳውሎስ (ፊል 3፥13-14) ላሉ ሰዎች ሲሆን፣ እንደ ዲቦራ (መሳ 4፥9)፣ እንደ ሩት (ሩት 1፥16-18)፤ እንደ አስቴር (አስ 4፥16)፤ እንደ ማርያም (ሉቃ 1፥26-35)፣ እንደ ሐና (ሉቃ 2፥36-38) እና እንደ ልድያ (ሐሥ 16፥14-15፡40) ላሉ ሴቶችም ጭምር ነው።

## የአይሁድ ወገኖች

### ፈሪሳውያን

ሥረ መሠረታቸው እስከ ሁለተኛው ምእተ ዓመት ዓ.ቅ.ክ. ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን፣ ይህም እስከ ሐሲዲም ዘመን ድረስ ነው።
1. ከቶራህ ጋር -የሙሴ መጻሕፍት? ትውፊቶችን ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት በመቁጠር ተቀብለዋል።
2. ነጻ ፈቃድንና ውሳኔን በተመለከተ የማቻቻል አቋም አላቸው፤ ይህም ከነጻ ፈቃድና ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ከሁለቱ አንዱን ለመምረጥ የማያስችል ሁኔታ ነው።
3. መላእክትና አጋንንት ጉልሕ የሆነ የሥልጣን ተዋረድ እንዳላቸው አምነዋል።
4. ሙታን የወደፊት ትንሣኤ እንዳላቸው አስተምረዋል።
5. በነፍስ ዘላለማዊነት፣ ከሞት በኋላም ሽልማት ወይም ቅጣት እንዳለ አምነዋል።
6. ለሰው ልጅ እኩልነት ጥብቅና የሚቆሙ ነበሩ።
7. የትምህርታቸው ይዘት ከትምህርተ መለኮት ይልቅ ሥነ ምግባር ላይ የሚያተኩር ነበር።

### ሰዱቃውያን

ምሥረታቸው በሀስሞንያን ዘመን እንደ ሆነ ይገመታል (ዓ.ቅ.ክ. 166—63) በ 70 ዓ.ም ከኢየሩሳሌም ከተማ መፍረስ ጋር የእነርሱም እንቅስቃሴ አከተመ
1. በትውፊት ውስጥ ያሉ ሕግጋት አይደሉም ባጥች ናቸው።
2. ከፈሪሳውያን ይልቅ የሙሴን ሕግ ቃል በቃል ይተረጉማሉ።
3. በሌዋውያን የመንጻት ሥርዓት ላይ ያተኩራሉ።
4. ሁሉ ነገር በነጻ ፈቃድ እንደሚከናወን ያምናሉ።
5. የሙታን ትንሣኤም ሆነ የዘላለም ሕይወት እንዳለ አያምኑም።
6. መላእክትና አጋንንት እንዳሉ አያምኑም።
7. መንፈሳዊ ዓለም አለ የሚለውን ሐሳብ አይቀበሉም።

© 2000 The Zondervan Corporation

ጀልባ ላይ ወጥቶ ተቀመጠ። 3ብዙ ነገሮችን
በምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ "አንድ
ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ። 4ሲዘራም ሳለ፣
አንዳንዱ ዘር መንገድ ዳር ወደቀ፤ ወፎችም
መጥተው ለቀሙት በሉት። 5አንዳንዱ ዘር
ዐፈሩ ስስ በሆነ፣ ድንጋያማ መሬት ላይ
ወደቀ፤ ዐፈሩ ስስ ስለ ሆነም ፈጥኖ በቀለ።
6ነገር ግን ፀሓይ ሲመታው ጠወለገ፤ ሥር ባለ
መስደዱም ደረቀ። 7አንዳንዱም ዘር በእሾኽ
መካከል ወደቀ፤ እሾኹም አደገና ቡቃያውን
አንቆ አስቀረው፤ 8ሌላው ዘር ደግሞ በጥሩ
መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ
መቶ፣ አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ
ፍሬ ሰጠ። 9የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!"።
10ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው፣ "ለምን ለሕዝቡ በምሳሌ
ትናገራለህ?" አሉት።
11እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ለእናንተ
የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ
ተሰጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸ
ውም። 12ላለው ይጨመርለታል፤
ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያ ያለው እንኳ
ይወሰድበታል። 13ስለዚህ እንዲህ በማለት
በምሳሌ የምናገራቸው ለዚህ ነው፤
"እያዩ ስለማያዩ፣
እየሰሙ ስለማይሰሙ ወይም
ስለማያስተውሉ ነው።
14እንዲህ ተብሎ የተነገረው የኢሳይያስ
ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል፤
" 'መስማትንስ ትሰማላችሁ፤ ነገር ግን
አታስተውሉም፤
ማየትንም ታያላችሁ፤ ነገር ግን
ልብ አትሉም።
15የሕዝቡ ልብ ደንድኖአልና፤
ጆሮአቸውም አይሰማም፤
እንዳያዩም ዐይናቸውን ጨፍነዋል፤
ይህ ባይሆን ኖሮ፣ በዐይናቸው
አይተው፣
በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው፣
ወደ እኔ በተመለሱና በፈወስኋቸው
ነበር።'
16የእናንተ ዐይኖች ስለሚያዩ፣ ጆሮዎቻ
ችሁም ስለሚሰሙ ግን የተባረኩ ናቸው።
17እውነት እላችኋለሁ፤ ብዙ ነቢያትና ብዙ
ጻድቃን እናንተ የምታዩትን ለማየትና የም
ትሰሙትንም ለመስማት ተመኝተው ነበር፤
ግን አልሆነላቸውም።
18"እንግዲህ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ፤
19የእግዚአብሔርን መንግሥት ቃል ሰምቶ
ከማያስተውል ከማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ
ክፉው መጥቶ የተዘራውን ዘር ይነጥቃል።
ይህ እንግዲህ በመንገድ ዳር የተዘራው
ዘር ነው። 20በድንጋያማ መሬት ላይ
የተዘራው፣ ቃሉን ሰምቶ ወዲያውኑ በደስታ
የሚቀበለውን ሰው ይመስላል። 21ነገር ግን
ሥር መስደድ ባለመቻሉ ብዙ አይቈይም፤
በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣ
ወዲያውኑ ይሰናከላል። 22በእሾኽ መካከል
የተዘራው ዘር ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም
በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል
ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስላል። 23በጥሩ
መሬት ላይ የተዘራው ዘር ግን ቃሉን
ሰምቶ የሚያስተውለውን ሰው ይመስላል፤
በርግጥም ፍሬ ያፈራል፤ አንዱ መቶ፣
አንዱ ሥልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።"

## የእንክርዳዱ ምሳሌ

24ኢየሱስም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል
ነገራቸው፤ "መንግሥተ ሰማይ በዕርሻው
ቦታ ጥሩ ዘር የዘራን ሰው ትመስላለች።
25ነገር ግን ሰው ሁሉ ተኝቶ ሳለ፣ ጠላቱ

13፥8 ዘፍ26፥12
13፥9 ማቴ11፥15
13፥11 ማቴ3፥2፤ 11፥25፤ 16፥17፤ 19፥11፤ ዮሐ6፥65፤ 1ቆሮ2፥10፡14፤ ቈላ1፥27፤ 1ዮሐ2፥20፡27
13፥12 ማቴ25፥29
13፥13 ዘዳ29፥4፤ ኤር5፥21፤ ሕዝ12፥2
13፥14 ቍ35፤ ማቴ1፥22
13፥15 ኢሳ6፥9፡10፤ ዮሐ12፥40፤ ሐሥ28፥26፡27፤ ሮሜ11፥8
13፥16 ማቴ16፥17
13፥17 ዮሐ8፥56፤ ዕብ11፥13፤ 1ጴጥ10-12
13፥19 ማቴ4፥23፤ 5፥37
13፥21 ማቴ11፥6፤ 26፥31
13፥22 ማቴ19፥23፤ 1ጢሞ6፥9፡10፡17
13፥23 ቍ8
13፥24 ቍ31፡33፡45፡47፤ ማቴ18፥23፤ 20፥1፤ 22፥2፤ 25፥1፤ ማር4፥26፡30

---

**13፥3 በምሳሌ፤** በምዕራፍ 13 ላይ የሰማዩ መንግሥት ምሳሌዎች በተለያየ መልክ ቀርበዋል፤ ምሳሌዎቹ የሚገልጹትም የወንጌል ስብከትን ውጤት እንዲሁም እስከ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ የእግዚአብሔር መንግሥት በጕልሕ በምድር ላይ ሲገለጥ (ይኸውም አብያተ ክርስቲያናት) የሚፈጸሙትን መንፈሳዊ ሁኔታዎች ነው።

(1) ከእነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ በብዙዎቹ በዚህ ዘመን ሁሉ በተገለጠው መንግሥቱ ውስጥ ክፉና ደግ እንደሚኖሩ ክርስቶስ አስተምሮአል። ስሙን በሚጠሩት መካከል ወደ ክሕደት የሚመራ ዓለማዊነትና ተመሳስሎ መኖር እንዳለ ሁሉ፣ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራ ታማኝነትና ፈሪሀ እግዚአብሔርም አለ። በዘመኑ መጨረሻ ክፉዎች ይወገዳሉ፤ «በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ ያበራሉ።» (ቍ 43)

(2) ክርስቶስ እነዚህን ምሳሌዎች የተናገረው፣ እውነተኛ ደቀ መዛሙርቱ በመንግሥቱ ውስጥ ክፉው መኖሩን በውቀው እንዲጠነቀቁ፤ የሰይጣንንና የተከታዮቹን ተቃውሞና እንቅስቃሴ ማሸነፍ እንዲችሉ ለማስተማር ነው። ማሸነፍ የሚያስችለው ብቸኛ መንገድ ለክርስቶስ በሙሉ ልብ መስጠትና (ቍ 44፡46) የጽድቅ ሕይወትን መኖር ነው (ቍ 43፤ በራእ 2—3 የተጠቀሱትን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ያሉትን የመልካምና የክፉ አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ የሆኑትንም ይመልከቱ)።

(3) ምሳሌዎች ከዕለት ተዕለት ሕይወት የተገኙ ታሪኮችንና ከተወሰኑ መንፈሳዊ እውነቶች ጋር የሚዛመዱና እነዚህኑ መንፈሳዊ እውነቶች የሚያስረዱ ናቸው። እነዚህን ምሳሌዎች ልዩ የሚያደርጋቸው መንፈሳዊ ለሆኑ ሰዎች እውነትን የሚገልጡ፣ ለማያምኑ ሰዎች ደግሞ የተሰወሩ መሆናቸው ነው (ቍ 11)። ምሳሌዎች አንዳንድ ጊዜ ውሳኔን ይጠይቃሉ (ለምሳሌ ሉቃ 10፥30-37)።

**13፥3 አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ፤** ማር 4፥3 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥12 ላለው ይጨመርለታል፤** 25፥29 እና ማብራሪያውን፣ ማር 4፥25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥19 ክፉው ... ይነጥቃል፤** ማር 4፥15 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥24-25 ጥሩ ዘር ... እንክርዳድ፤** የስንዴውና የእንክርዳዱ ምሳሌ፣ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ከሚዘሩ ሰዎች ጐን ለጐን ክፉትን እንደሚዘራ በአጽንዖት ያስገነዝባል። «ዕርሻው» ዓለምን ሲወክል፣ «ጥሩው ዘር» ደግሞ የመንግሥቱን ታማኞች ይወክላል (ቍ 38)። (1) ወንጌልና እውነተኛ አማኞች በዓለም ሁሉ ይዘራሉ (ቍ 38)። ሰይጣንም እንደዚሁ ተከታዮቹ

መጥቶ በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ
ሄደ። [26]ስንዴው በቅሎ ማፍራት ሲጀምር
እንክርዳዱም አብሮ ብቅ አለ።
[27]"የዕርሻው ባለቤት አገልጋዮችም ወደ
እርሱ ቀርበው፣ 'ጌታ ሆይ፤ በዕርሻህ ቦታ
ጥሩ ዘር ዘርተህ አልነበረምን? እንክርዳዱ
ከየት መጣ?' አሉት።
[28]"እርሱም፣ 'የጠላት ሥራ ነው'
አላቸው።
አገልጋዮቹም፣ 'እንክርዳዱን ሄደን እንድ
ንነቅለው ትፈልጋለህ?' ብለው ጠየቁት።
[29]"እርሱ ግን፣ 'አይሆንም፤
ምክንያቱም እንክርዳዱን እንነቅላለን
ስትሉ ስንዴውንም አብራችሁ ልትነቅሉ
ትችላላችሁ፤ [30]ተዉ፣ አቸው፤ እስከ መከር
ጊዜ አብረው ይደጉ። በዚያን ጊዜ አጫጆቹን
እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ፤
በእሳትም እንዲቃጠል በየነዶው እሰሩት፤
ስንዴውን ግን ሰብስባችሁ በጐተራዬ ክተቱ
አላቸዋለሁ' " አላቸው።

## የሰናፍጭና የእርሾ ምሳሌ

*13፥31-32 ተጓ ምብ — ማር 4፥30-32፤*
*13፥31-33 ተጓ ምብ — ሉቃ 13፥18-21*

[31]ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው፤
"መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ በዕ
ርሻው ቦታ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር
ትመስላለች። [32]የሰናፍጭ ዘር ከሌሎች
ዘሮች ሁሉ ያነሰች ብትሆንም፣ ስታድግ ግን
ከቍ ጥቋጦዎች ሁሉ በልጣ፣ የሰማይ ወፎች
መጥተው በቅርንጫፎቿ ላይ እስኪያርፉ
ድረስ ዛፍ ትሆናለች።"

13፥30 ማቴ3፥12
13፥31 ቍ24፤ ማቴ17፥20፤ ሉቃ17፥6
13፥32 መዝ104፥12፤ ሕዝ17፥23፤ 31፥6፤ ዳን4፥12
13፥33 ቍ24፤ ዘፍ 18፥6፤ ገላ5፥9
13፥34 ዮሐ16፥25
13፥35 ቍ14፤ መዝ78፥2፤ ማቴ1፥22፤ ሮሜ16፥25፡26፤ 1ቆሮ2፥7፤ ኤፌ3፥9፤ ቆላ1፥26
13፥36 ማቴ15፥15
13፥37 ማቴ8፥20
13፥38 ዮሐ8፥44፡45፤ 1ዮሐ3፥10
13፥39 ኢዩ3፥13፤ ማቴ24፥3፤ 28፥20፤ ራእ14፥15
13፥41 ማቴ8፥20፤ 24፥31

[33]አሁንም ሌላ ምሳሌ እንዲህ ሲል
ነገራቸው፤ "መንግሥተ ሰማይ ሴት ወስዳ
ሊጡ በሙሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት
መስፈሪያ[a] ዱቄት ውስጥ በመደባለቅ
የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።"
[34]ኢየሱስ ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ
ተናገረ፤ ምሳሌም ሳይጠቀም የነገራቸው
አንድም ነገር አልነበረም። [35]በዚህም በነቢዩ
እንዲህ ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፤
"አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
የተሰወረውንም እናገራለሁ።"

## የእንክርዳዱ ምሳሌ ትርጒም

[36]ከዚያም ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ።
ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፣
"በዕርሻው ውስጥ ስላለው እንክርዳድ
የተናገርኸውን ምሳሌ ትርጒም ንገረን"
አሉት።
[37]እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ጥሩውን
ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ [38]ዕርሻውም
ይህ ዓለም ነው፤ ጥሩው ዘር የእግዚአብሔርን
መንግሥት ልጆች ያመለክታል፤ እንክር
ዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፤ [39]ዘርቶት
የሄደው ጠላትም ዲያብሎስ ነው፤ መከሩ
የዓለም መጨረሻ ሲሆን፣ አጫጆቹም
መላእክት ናቸው።
[40]"እንክርዳዱ ተነቅሎ በእሳት
እንደሚቃጠል ሁሉ በዓለም መጨረሻም
እንዲሁ ይሆናል። [41]የሰው ልጅ መላእክቱን
ይልካል፤ እነርሱም ለኀጢአት ምክንያት

[a]13፥33 ምናልባት 22 ሊትር ያህል

የሆኑትን፡ "የክፉው ልጆች"ን (ቍ 38) የእግዚአብሔርን እውነት ለመቃወም ሲል በእግዚአብሔር ልጆች መካከል ይዘራል (ቍ 25:38-39)።

(2) በሚታየው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ዋነኛው የሰይጣን መልእክተኞች ሥራ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን ማቃለል (ዘፍ 3፥4 ይመ)፣ ርኩሰትና ሐሰተኛ አስተምህሮ እንዲስፋፋ ማድረግ ነው (ከሐሥ 20፥29-30፤ ከ2ተሰ 2፥7፡12 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ በኋለኛው ዘመን ክርስቲያኖች ነን በሚሉ ነገር ግን የሐሰት አስተማሪዎች በሆኑ ሰዎች ምክንያት በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ አሳሳች ሁኔታ እንደሚከሠት ተናግሮአል (24፥11 እና ማብ ይመ፡ በገጽ 1471 ላይ፥ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሰይጣን ተከታዮች ሁኔታ የሚያበቃው፣ እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ ክፋትን ሁሉ በሚደመስስበት ጊዜ ነው (ቍ 38-43)። አማኞች ካላመኑት ጋር ያላቸውን የተደባለቀ ሁኔታ በአጽንዖት ስለሚናገሩ ሌሎች ምሳሌዎች ለማወቅ 22፥11-14ን፤ 25፥1-30ን፤ ሉቃ 18፥10-14ን፣ በገጽ 2058 ላይ፣ *"ለሰማቱ አብዮተ ክርስቲያናት የተላከ የክርስቶስ መልእክት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**13፥30 አብረው ይደጉ፤** የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮችና አማኞች በመምሰል የሚያታልሉ የሰይጣን ልጆች (ቍ 38፤ ከ2ቆሮ 11፥13-15 ጋር ያነጻጽሩ) አብረው ማደጋቸውን በተመለከተ ሦስት ነጥቦችን ልብ ማለት ይገባል፤ (1) በወንጌል ዘመን ሁሉ እንዲህ ዐይነቱ አብሮ መኖር ይከሠታል። እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ የክፉውን ልጆች ያጠፉ ዘንድ እግዚአብሔር መላእክቱን አያዝዝም (ቍ 30:38-41)።

(2) ከላይ የተገለጸው ምሳሌ ኀጢአት በሚሠሩ አባሎች ላይ ሊወሰድ ስለሚገባው የሥነ ሥርዐት እርምጃና ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ያልሆኑትን እንደዚሁም ሐሰተኛ አባሎችን ከኅብረት ማገድ እንደሚገባ በሌላ ስፍራ ከተጠቀሱት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች ጋር አይቃረንም (18፥15 እና ማብ፥ ሐሥ 20፥28 እና ማብ፥ 1ቆሮ 5፥1 እና ማብ ይመ)። ይሁን እንጂ በመንግሥቱ ባሉ ክፉ ግለሰቦች ላይ የሚወሰደው የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዐት ርምጃ ከፊል መፍትሔ ብቻ እንደ ሆነ ማስተዋል ተገቢ ነው። እግዚአብሔርና መላእክቱ የመጨረሻውን የመለየት ርምጃ ይወስዳሉ።

(3) ታማኝ የሆኑ ምእመናን ሰይጣን በእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ ላይ ከሚተክላቸው ተቃዋሚ ግለሰቦችና አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ዘወትር መጠንቀቅ ይገባቸዋል፤ በብዙ መንገድ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆችን በመምሰል ይመሳሰሉና (2ቆሮ 11፥13 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ *"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**13፥31 የሰናፍጭ ዘር፤** ሉቃ 13፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥33 እርሾ፤** ሉቃ 13፥21 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥41 ለኀጢአት ምክንያት የሆኑትንና ...**

የሆኑትንና ክፉ የሚያደርጉትን ሁሉ
ለቅመው ከመንግሥቱ ያወጣሉ። [42]ልቅሰና
ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን
እሳት ይጥሏቸዋል። [43]በዚያን ጊዜ ጻድቃን
በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ
ያበራሉ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ።

## የተደበቀ ሀብትና የዕንቍው ምሳሌ

[44]"መንግሥተ ሰማይ በዕርሻ ውስጥ
የተደበቀ ሀብት ትመስላለች፤ አንድ ሰው
ባገኘች ጊዜ መልሶ ሸሸጋት፤ ከመደሰቱም
የተነሣ ሂዶ፤ ያለውን ሁሉ በመሸጥ ያንን
የዕርሻ ቦታ ገዛ።
[45]"እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ውብ
ዕንቍ የሚፈልግ ነጋዴ ትመስላለች፤ [46]እ
ጅግ ውድ የሆነ ዕንቍ ባገኘም ጊዜ ሂዶ ያለ
ውን ሁሉ ሸጦ ገዛው።

## የመረቡ ምሳሌ

[47]"ደግሞም መንግሥተ ሰማይ ወደ
ባሕር ተጥሎ የዓሣ ዓይነቶችን የያዘ
መረብ ትመስላለች፤ [48]ዓሣ አጥማጆቹ
መረቡ ሲሞላባቸው ጎትተው ወደ ባሕሩ
ዳር አወጡት፤ ከዚያም ተቀምጠው ጥሩ
ጥሩውን እየለዩ በቅርጫት ውስጥ ሲመሩ፤
መጥፎ መጥፎውን ግን ጣሉት። [49]በዓለም
መጨረሻም ልክ እንደዚሁ ይሆናል፤
መላእክት መጥተው ኀጢአተኞችን
ከጻድቃን በመለየት፣ [50]ልቅሰና ጥርስ
ማፋጨት ወዳለበት ወደ እቶን እሳት
ይጥሏቸዋል።"
[51]ኢየሱስ፣ "ይህ ሁሉ ገብቷችኋል?"
አላቸው።
እነርሱም፣ "አዎን" አሉት።
[52]እርሱም፣ "ስለዚህም የመንግሥተ ሰማ
ይን ምስጢር የተረዳ ማንኛውም የኦሪት
ሕግ መምህር፣ ከክበረ ሀብቱ ክምችት አዲ
ሱንም አሮጌውንም የሚያወጣ ባለንብረት
ይመስላል" አላቸው።

## በገዛ አገሩ ያልተከበረው ነቢይ

*13፥54-58 ተጓ ምብ — ማር 6፥1-6*

[53]ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች እንደ
ጨረሰ፣ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ ሄደ፤ [54]ወደ
ገዛ አገሩ መጣ፤ በምኵራባቸውም ሕዝቡን
ያስተምር ጀመር። እነርሱም በመገረም
እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው ይህን ጥበብና
እነዚህን ታምራት የማድረግ ኀይል ከየት
አገኘ? [55]ይህ የአናጢው ልጅ አይደለምን?
የእናቱስ ስም ማርያም አይደለምን?
ወንድሞቹስ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ስምዖንና
ይሁዳ አይደሉምን? [56]እኅ ቶቹስ ከእኛው
ጋር አይደሉምን? ታዲያ ይህ ሰው ይህን
ሁሉ ከወዴት አገኘው?" [57]ስለዚህም
ሳይቀበሉት ቀሩ።
ኢየሱስ ግን፣ "ነቢይ የማይከበረው በራሱ
አገርና በራሱ ቤት ብቻ ነው" አላቸው።
[58]ባለማመናቸውም ምክንያት ብዙ ታምራ
ትን በዚያ አላደረገም።

13፥42 ማቴ8፥12
13፥43 ዳን12፥3፤ ማቴ11፥15
13፥44 ቍ 24፤ ኢሳ55፥1፤ ማቴ19፥21፤ ፊል3፥7፡8
13፥45 ቍ 24
13፥47 ቍ 24፤ ማቴ22፥10
13፥49 ማቴ25፥32
13፥50 ማቴ8፥12
13፥53 ማቴ7፥28
13፥54 ማቴ4፥23፤ 7፥28
13፥55 ማቴ12፥46፤ ሉቃ3፥23፤ ዮሐ6፥42
13፥57 ሉቃ4፥24፤ ዮሐ4፥44፤ 6፥61

**ያወጣሉ፤** ከታላቁ መከራ በኋላና በዘመን ፍጻሜ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ (ራእ 19፥11-21)፣ በምድር የሚኖሩ ክፉዎችና ደጎች ሁለቱም የሚሰበሰቡበት የመከር ጊዜ አለ (ቍ 30:40-42 ይመ፥ በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: (1) ክፉዎች በመጀመሪያ ተሰብስበው ከጻድቃን መካከል ይወሰዳሉ (ቍ 30:41:49):: (2) ቀጥሎ ጻድቃን ይሰበሰባሉ (ቍ30ለ:41-43:49)፡ ይህ መሰብሰብ የሚሆነው፥ "ከመንግሥቱ ውስጥ" ነው፤ (3) መከሩ ከተሰበሰበና ክፉዎች ከጠፉ በኋላ "ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሓይ ያበራሉ" (ቍ 43 ይመ፡ ከ25፥31-34 ጋር ያነጻጽሩ፤ ራእ 20፥4 እና ማብ ይመ)::

**13፥42 እቶን እሳት፤** ለኀጢአት ምክንያት በሚሆኑትና ክፉ በሚያደርጉት ላይ ምን እንደሚመጣ ኢየሱስ ይገልጻል (ቍ 41):: በእሳት ይቃጠላሉ፤ ታላቅ ሥቃይም ይደርስባቸዋል (ከራእ 14፥9-11፤ 20፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርጎ የሚቀበል ማንም ክርስቲያን ይህን አስተምህሮ አይክድም:: ክፉዎች ፈጽሞ አይጠፉም፥ ነገር ግን ለዘላለም ይቃጠሉ ዘንድ ወደ "እቶን እሳት" ይጣላሉ (10፥28 እና ማብ ይመ)::

**13፥44-46 *መንግሥተ ሰማይ ... ሀብት፤*** የተደበቀው ሀብትና የዕንቍው ምሳሌዎች ሁለት እውነቶችን ያስተምራሉ፤ (1) የእግዚአብሔር መንግሥት ከማንኛውም ነገር በላይ የሚፈለግ፣ ውድ የሆነ ዋጋ የማይተመንለት ሀብት ነው፤ (2) የእግዚአብሔር መንግሥት ሊገኝ የሚችለው ከመግባት የሚያግድን ማንኛውንም ነገር በመተው ነው:: "ያለውን ሁሉ በመሸጥ" ማለት ቃል ሙሉ ልባችንን ከሌሎች ጕዳዮች ላይ አንሥተን ከሙሉ ልቡ ወዳለው ወደ ክርስቶስ ማዞር አለብን ማለት ነው::

**13፥47 *መንግሥተ ሰማይ ... መረብ፤*** የመረቡ ምሳሌ እንደ ገና ክርስቶስ በከፍተኛ ደረጃ አጽንዖት ሰጥቶ የገለጠውን እውነት ያሳያል፥ ይህ ምሳሌ በሚታየው መንግሥት ውስጥ ያሉት ሁሉ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች እንዳልሆኑ ያመለክታል:: አብያተ ክርስቲያናትና የክርስቲያን ድርጅቶች፣ በእውነተኛ እምነትና በጽድቅ ሕይወት የሚኖሩ አማኞች ሁሉ ከሚገኙበት ከእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ኅብረት ጋር ተመሳሳይ አይደሉም (ከ24፥11:24፥ ከገላ 5፥19-21 ጋር ያነጻጽሩ፥ ሉቃ 13፥21 እና ማብ ይመ)::

**13፥49 ኀጢአተኞችን ከጻድቃን በመለየት፤** በመረቡ ምሳሌ በመጨረሻው ዘመን ኀጢአተኞችን ከጻድቃን የመለየት ቅደም ተከተል በስንዴውና በእንክርዳዱ ምሳሌ ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ 30:41:43)፤ክፉ ያደረጉ ሁሉ በመጀመሪያ ይሰበሰባሉ፤ ቀጥሎ ደግሞ ጻድቃን ይሰበሰባሉ (ከራእ 19፥11—20፥4 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ ቅደም ተከተል በግልጽ የሚያሳየው የመለየቱ ተግባር የሚከናወነው በታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ እንጂ (24፥29-31፥ ራእ 19፥11—20፥4) በመነጠቅ ጊዜ አለመሆኑን ነው፤ በዚህ ጊዜ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታማኞች የሆኑት ሁሉ ከክፉዎች መካከል ይሰበሰባሉ (1ተሰ 4፥13-18፥ ራእ 3፥10 ይመ):: እንደ ገናም በዚህ ምሳሌ ክርስቶስ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ለእርሱና ለቃሉ በእውነት ታማኞች ያልሆኑ እንደሚኖሩ በአጽንዖት ተናግሮአል::

### የመጥምቁ ዮሐንስ መሞት

*14፥1-12 ተጓ ምብ — ማር 6፥14-29*

**14** በዚያን ጊዜ የአራተኛው ክፍል
ገዥ የነበረው፣ ሄሮድስ ስለ ኢየሱስ
ዝና ሰማ፤ 2ባለሟሎቹንም፣ "እንዲህ ከሆነ
መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት ተነሥቶ መጥቶአል
ማለት ነው፤ ይህ ሁሉ ድንቅ ታምራት
በእርሱ የሚደረገውም ለዚህ ነው" አላቸው።
3ቀደም ሲል ሄሮድስ፣ በወንድሙ በፊልጶስ
ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ዮሐንስን
አስይዞ ወህኒ አስገብቶት ነበር። 4ምክ
ንያቱም ዮሐንስ፣ "እርሷን እንድታገባ ሕግ
አይፈቅድልህም" ይለው ነበር። 5ሄሮድስም
ዮሐንስን ሊገድለው ፈልጎ፣ ሕዝቡ
እንደ ነቢይ ይመለከተው ስለ ነበር ፈራ።
6ሄሮድስ የልደቱን ቀን ሲያከብር፣
የሄሮድያዳ ልጅ በዘፈን ደስ ስላሰኘችው፣
7የምትጠይቀውን ሁሉ ሊሰጣት በመሐላ
ቃል ገባ ላት። 8ልጅቷም በእናቷ ተመክራ፣
"የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በሳሕን ላይ
አድርገህ አሁኑኑ ስጠኝ" አለችው። 9በዚህ
ጊዜ ንጉሡ አዘነ፤ ይሁን እንጂ ስለ
መሐላውና ከእርሱ ጋር ስለነበሩ እንግዶች
ሲል ጥያቄዋ እንዲፈጸምላት አዘዘ።10ልኮም
በወህኒ ውስጥ እንዳለ የዮሐንስን ራስ
አስቈረጠ። 11የተቈረጠውንም ራስ በሳሕን
ላይ አድርገው ለልጅቱ ሰጧት፤ ልጅቱም
ወስዳ ለእናቷ ሰጠች። 12የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትም አስከሬኑን ወስደው ቀበሩት፤
ከዚያም ሄደው የሆነውን ለኢየሱስ ነገሩት።

### ኢየሱስም አምስት ሺህ ሰዎችን በታምር መገበ

*14፥13-21 ተጓ ምብ — ማር6፥32-44፤*
*ሉቃ 9፥10-17፤ ዮሐ6፥1-13*
*14፥13-21 ማመ — ማቴ 15፥32-38*

13ኢየሱስ የሆነውን ነገር በሰማ ጊዜ፣
ከነበረበት ተነሥቶ ወደ አንድ ገለልተኛ
ስፍራ በጀልባ ሄደ። ሕዝቡም ይህን
ሰምተው፣ ከየከተማው በእግር ተከተሉት።
14ኢየሱስም ከጀልባው ሲወርድ ብዙ ሕዝብ
አይቶ ራራላቸው፤ ሕመምተኞቻቸውንም
ፈወሳቸው።
15እየመሸ በመሄዱም ደቀ መዛሙርቱ
ወደ እርሱ ቀርበው፣ "ይህ ስፍራ ምንም
የማይገኝበት ምድረ በዳ ነው፤ ጊዜው
እየመሸ ስለሆነ፣ ወደ መንደሮች ሄደው
የሚበሉት ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን
አሰናብት" አሉት።
16ኢየሱስ ግን፣ "መሄድ
አያስፈልጋቸውም፤ የሚበሉትን እናንተ
ስጧቸው" አላቸው።
17እነርሱም፣ "በዚህ ያለን አምስት
እንጀራና ሁለት ዓሣ ብቻ ነው" አሉት።
18እርሱም፣ "እስቲ ያለውን ወደ እኔ
አምጡት" አላቸው። 19ከዚያም ሕዝቡ በሣሩ
ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤ አምስቱን እንጀ
ራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ዓይኑን ወደ ሰማይ
በማቅናት አመስግኖና ባርኮ እንጀራውን
ቈረሰ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ሰጠ፤ እነር
ሱም ለሕዝቡ ሰጡ። 20ሁሉም በልተው
ጠገቡ፤ ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ የተረፈውን
ቍርስራሽ ዐሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ
አነሡ። 21የበሉትም ከሴቶችና ከሕፃናት
ሌላ አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር።

### ኢየሱስ በባሕር ላይ በእግሩ ሄደ

*14፥22-33 ተጓ ምብ — ማር 6፥45-51፤*
*ዮሐ 6፥15-21፤*
*14፥34-36 ተጓ ምብ — ማር 6፥53-56*

22ወዲያውኑ ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ
ተሳፍረው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት
አዘዛቸውና እርሱ ሕዝቡን ለማሰናበት
ወደ ኋላ ቀረት አለ። 23ሕዝቡን ካሰናበተ

14፥1 ማር8፥15፤ ሉቃ3፥1፡19፤ 9፥7-7፤ 13፥31፤ 23፥7፡8፤ ሐሥ4፥27፤ 12፥1
14፥2 ማቴ3፥1
14፥3 ማቴ4፥12፤ 11፥2፤ ሉቃ3፥19፡20
14፥4 ዘሌ18፥16፤ 20፥21
14፥5 ማቴ11፥9
14፥10 ማቴ17፥12
14፥12 ሐሥ8፥2
14፥14 ማቴ4፥23፤ 9፥36
14፥17 ማቴ16፥9
14፥19 1ሳሙ9፥13፤ ማቴ26፥26፤ ማር8፥6፤ ሉቃ9፥16፤ 24፥30፤ ሐሥ2፥42፤ 20፥7፡11፤ 27፥35፤ 1ቆሮ10፥16፤ 1ጢሞ4፥4
14፥23 ሉቃ3፥21

**14፥6 በዘፈን፤** ይህች እግዚአብሔርን የማትፈራ ልጃገረድ ለሄሮድስና ለእንግዶቹ ያሳየችው ዘፈንና ጭፈራ ከሰዎች ሁሉ ቅዱስ የሆነው ሰው እንዲሞት አደረገ። (1) ዓለማዊ ግብዣዎች፣ ጭፈራና መንፈሳዊ ያልሆኑ ፊልሞች እግዚአብሔርን ወደ መርሳት፣ ሥጋዊ ስሜትን ወደ ማነሣሣት እንዲሁም ኀጢአትን፣ ጽድቅን ወይም ፍርድን ለመለየት የሚያስችለንን ችሎታ ወደ ማጣት ያደርሱናል። በእነዚህ ነገሮች ውስጥ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች አይሳተፉም (በገጽ 2022 ላይ፣ *«ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዕብራውያን ሴቶችና ልጃገረዶች ልዩ በሆነ የደስታ ወቅት (ከኤር 31፥4 ጋር ያነጻጽሩ) በስሜት ተነሣሥተው የጨፈሩበት ጊዜ አለ፤ ይልቁንም በጦርነት ድል ከተገኘ በኋላ ለእግዚአብሔር ዘምረዋል (ዘፀ 15፥19-21)። ይሁን እንጂ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የአይሁድ ወንዶች ከሴቶች ጋር የጨፈሩበትን ወይም የአይሁድ ሴቶች በአደባባይ ለሕዝብ የጨፈሩበትን የሚያመለክት ክፍል አናገኝም። የሄሮድያዳ ልጅ በሄሮድስ የልደት ቀን ግብዣ ላይ ያሳየችው ጭፈራ የጣዖት አምልኮ ልምድ ነው።

**14፥19 እንጀራና ... ዓሣ፤** አምስት ሺህ ሰዎች በታምር የተመገቡበት ታሪክ በአራቱም ወንጌሎች ተጽፎአል (ማር 6፥34-44፤ ሉቃ 9፥10-17፤ ዮሐ 6፥1-14)። የተፈጸመው ታምር ትምህርታዊነት የሚከተሉትን ያካትታል፤ (1) ለሥጋም ለነፍስም ምግብ የሚሰጠውን የሕይወት እንጀራ የሆነውን ኢየሱስን (ከዮሐ 6 ጋር ያነጻጽሩ) ማመልከቱን፤ (2) የእግዚአብሔር ኀይል ታምራት እንደሚያደርግ ማረጋገጫ መሆኑን፤ (3) ኢየሱስ ለተቸገሩ ሰዎች ያለውን ርኅራኄ የሚያሳይ ምሳሌ መሆኑን (ቊ 14፤ ከዘፀ 34፥6፤ ከሚክ 7፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (4) ያለን ጥቂቱ ነገር ለእግዚአብሔር እጅ ሲሰጥ ሊበዛና ሊባረክ እንደሚችል የሚያስተምር መሆኑን።

**14፥23 ለመጸለይ ብቻውን፤** ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻው ጊዜ እንዲኖረው ያደርግ ነበር (ከማር 1፥35፤ 6፥46፤ ከሉቃ 5፥16፤ 6፥12፤ 9፥18፤ 22፥41-42፤ ከዕብ 5፥7 ጋር ያነጻጽሩ)። እያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ ሕይወቱ በመልካም ሁኔታ ይገኝ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ለብቻው ጊዜ እንዲኖረው ያስፈልገዋል። የግል የጸሎት ጊዜ ፍላጎት አለመኖርና ከሰማያዊ አባታችን

በኋላም ለመጸለይ ብቻውን ወደ ተራራ
ወጣ፤ በምሽትም ጊዜ ብቻውን በዚያው
ነበር፤ [24]በዚያ ጊዜ ጀልባዋ ባሕሩን ዘልቃ[w]
እየተንገላታች ሳለች ነፋስ ተነሥቶ በማዕበል
ትንገላታ ጀመር።
[25]ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ደቀ መዛሙርቱ
ወዳሉበት መጣ። [26]ደቀ መዛሙርቱም
በባሕሩ ላይ እየተራመደ ሲመጣ ባዩት ጊዜ
ፈሩ፤ እነርሱም፣ "ምትሀት ነው!" በማለት
በፍርሃት ጮኹ።
[27]ኢየሱስም ወዲያውኑ፣ "አይዞአችሁ፤
እኔ ነኝ አትፍሩ" አላቸው።
[28]ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ
ከሆንህስ፣ በውሃው ላይ እየተራመድሁ ወደ
አንተ እንድመጣ እዘዘኝ" አለው።
[29]እርሱም፣ "ና" አለው።
ጴጥሮስም፣ ከጀልባው ወርዶ በውሃው
እየተራመደ ወደ ኢየሱስ አመራ። [30]ነገር ግን
የነፋሱን ኀይል ባየ ጊዜ ፈራ፤ መስጠምም
ሲጀምር፣ "ጌታ ሆይ፤ አድነኝ!" ብሎ
ጮኸ።
[31]ኢየሱስም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ
ያዘውና፣ "አንተ እምነት የጐደለህ፤ ለምን
ተጠራጠርህ?" አለው።
[32]ኢየሱስና ጴጥሮስ ጀልባው ላይ እንደ
ወጡ ነፋሱ ጸጥ አለ። [33]ከዚያም በጀልባው
ውስጥ የነበሩት፣ "በእውነት አንተ የእግዚአ
ብሔር ልጅ ነህ" ብለው ሰገዱለት።

## ፈውስ በጌንሴሬጥ

[34]ባሕሩን ከተሻገሩ በኋላ ጌንሴሬጥ ወደ
ተባለ ቦታ ደረሱ። [35]ነዋሪዎቹም ኢየሱስ
መሆኑን ባወቁ ጊዜ፣ በዙሪያው ወዳለ አካባቢ
ሁሉ መልእክት ላኩ፤ የታመሙትን ሁሉ ወደ
እርሱ በማስመጣት፣ [36]በሽተኞቹ የልብሱን
ጫፍ ብቻ ይነኩ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው
ለመኑት፤ የነኩትም ሁሉ ተፈወሱ።

14፥26 ሉቃ24፥37
14፥27 ዳን10፥12፤ ማቴ9፥2፤ 17፥7፤ 28፥10፤ ሉቃ1፥13:30፤ 2፥10፤ ሐሥ18፥9፤ 23፥11፤ ራእ1፥17
14፥31 ማቴ6፥30
14፥33 መዝ2፥7፤ ማቴ4፥3
14፥36 ማቴ9፥20
15፥2 ሉቃ11፥38
15፥4 ዘፀ20፥12፤ 21፥17፤ ዘሌ20፥9፤ ዘዳ5፥16፤ ኤፌ6፥2
15፥9 ኢሳ29፥13፤ ሚል2፥2፤ ቈላ2፥20-22
15፥11 ቍ18፤ ሐሥ10፥14:15
15፥13 ኢሳ60፥21፤ 61፥3
15፥14 ማቴ23፥16:24፤ ሉቃ6፥39፤ ሮሜ2፥19
15፥15 ማቴ13፥36

## የፈሪሳውያን ወግ

*15፥1-20 ተጓ ምብ — ማር 7፥1-23*

15 ከዚያም ከኢየሩሳሌም የመጡ
ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ [2]"ደቀ መዛሙርትህ
የአባቶችን ወግ የሚሽሩት ለምንድነው?
ምግብ ሲበሉ እጃቸውን አይታጠቡም"
አሉት።
[3]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እናንተስ ለወጋችሁ ስትሉ የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ ለምን ትሽራላችሁ? [4]እግዚአብሔር፣
'አባትህንና እናትህን አክብር፤ በአባቱ ወይም
በእናቱ ላይ ክፉ ቃል የሚናገር ይገደል' ብሎ
ሲያዝ፣ [5]እናንተ ግን፣ ማንም ሰው አባቱን ወይም
እናቱን፣ 'ላደርግላችሁ የሚገባውን
ማንኛውንም ነገር ለእግዚአብሔር መባ አድርጌ
አቅርቤአለሁ' ቢላቸው፣ [6]'አንድ ሰው
ይህን ካደረገ ዘንድ አባቱን ወይም እናቱን
አክብሮአል' ትላላችሁ። ስለዚህ ለወጋችሁ
ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ።
[7]እናንት ግብዞች፤ ኢሳይያስ ስለ እናንተ እንዲህ
ብሎ በትንቢት የተናገረው ትክክል ነው፤
[8]'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤
ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤
[9]በከንቱ ያመልኩኛል፣
ትምህርታቸውም የሰው ሥርዓት
ነው።' "
[10]ሕዝቡን ወደ እርሱ ቀረብ እንዲሉ
አድርጎ እንዲህ አላቸው፤ "ስሙ አስተውሉም፤
[11]ሰውን የሚያረክሰው ከአፉ የሚወጣው
እንጂ ወደ አፉ የሚገባው አይደለም።"
[12]ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፣
"ፈሪሳውያን ያልኸውን ሰምተው እንደ
ተቈጡ አወቅህ?" አሉት።
[13]እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ "የሰማዩ
አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል።
[14]ተዉአቸው፣ እነርሱ ዕውሮችን የሚመሩ
ዕውር መሪዎች ናቸው፤ ዕውር ዕውርን
ቢመራ ሁለቱም ተያይዘው ገደል ይገባሉ።"
[15]ጴጥሮስም፣ "ምሳሌውን አስረዳን"
አለው።

[w] *14፥24 ግሪኩ ብዙ ምዕራፍ ይላል*

ጋር ኅብረት ለማድረግ አለመሻት በውስጣችን ያለው መንፈሳዊ ሕይወት ለመውደቅ በማሽቈልቈል ሂደት ላይ እንዳለ የሚያሳይ የሚያጠራጥር ምልክት ነው:: ይህ እየሆነ ካለ፥ እግዚአብሔርን ከሚያሳዝነው ነገር ሁሉ በመመለስ፣ እግዚአብሔርንና የማዳን ጸጋውን ለመሻት ያለንን ጽኑ ውሳኔ ማደስ ይኖርብናል (ሉቃ 18፥1 እና ማብ ይመ)::

**14፥27 አትፍሩ፤** በዚህ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ እያሉ የሚያስፈሩ ነገሮች አሉ፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ወደ እርሱ እንድንመለከትና እንዳንፈራ ይፈልጋል:: የእርሱ የማጽናናት ቃሎች ወሰን በሌለው ኀይሉና በእውነት የእርሱ ለሆኑት ሁሉ ባለው ጥልቅ የግል ፍቅሩ ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: በቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን "አትፍሩ" በማለት ያጽናናል (ለምሳሌ ኢሱ 1፥9፤ 11፥6፤ 2ነገ 19፥6፤ 2ዜና 20፥15፤ 32፥7፤ ነህ 4፥14፤ መዝ49፥16፤ 91፥5፤ ኢሳ 10፥24፤ 37፥6፤ 44፥8፤ ማቴ 17፥7፤ 28፥10፤ ማር 5፥36፤ ሉቃ 12፥4፤ ዮሐ 14፥1:27፤ ሐሥ 18፥9፤ 1ጴጥ 3፥14 ይመ)::

**15፥6 ለወጋችሁ ብላችሁ፤** አንዳንድ ፈሪሳውያን ለትውፊቶቻቸውና ለሰዎች ሐሳብ ሲሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ይሽራሉ:: ዛሬ አማኞች በባህል፣ ተቀባይነት ባላቸው አስተያየቶች ወይም በዚህ ዘመን ባህላዊ ልማዶች፣ "የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይሽሩ" መጠንቀቅ ይገባቸዋል:: የእግዚአብሔርን ቃል መሻር ማለት በዚህ ዐይነቱ የፈሪሳውያንና የአይሁድ መሪዎች ኀጢአት ውስጥ መግባት ነው (ማር 7፥8 እና ማብ ይመ)::

**15፥8 ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤** ማር 7፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**15፥11 ሰውን የሚያረክሰው፤** ማር 7፥18 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

16እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "እናንተም
እስካሁን አላስተዋላችሁም ማለት ነውን?
17በአፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ ዘልቆ፣ ከዚያም
ወደ ውጪ እንደሚወጣ አታውቁምን?
18ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይመነጫል፤
ሰውንም የሚያረክሰው ይህ ነው፤ 19ክፉ
ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣
ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና
ስም ማጥፋት ከልብ ይመነጫሉና። 20ሰውን
የሚያረክሱ እነዚህ ናቸው እንጂ እጅን
ሳይታጠቡ መብላት ሰውን አያረክሰውም።"

## የከነዓናዊቷ ሴት እምነት

*15፥21-28 ተጓ ምብ — ማር 7፥24-30*

21ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና
ወደ ሲዶና አገር ሄደ። 22አንዲት ከነዓናዊት
ሴት ከዚያ አካባቢ በመውጣት ወደ ኢየሱስ
መጥታ፣ "ጌታ ሆይ፤ የዳዊት ልጅ፤
ራራልኝ፤ ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ በጣም
ትሠቃያለች" ብላ ጮኸች።
23እርሱ ግን አንድም ቃል አልመለሰላትም፤
በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው፣ "እየተከተለችን ትጮኻለችና
ብታሰናብታትስ?" ብለው ለመኑት።
24እርሱም፣ "የተላክሁት ከእስራኤል ቤት
ለጠፉት በጎች ብቻ ነው" አለ።
25ሴትዮዋም እግሩ ላይ ወድቃ፣ "ጌታ
ሆይ፤ ርዳኝ" አለች።
26እርሱም መልሶ፣ "የልጆችን እንጀራ
ወስዶ ለውሾች መወርወር አይገባም"
አላት።
27እርሷም፣ "አዎን ጌታ ሆይ፤ ውሾችም
እኮ ከጌታቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ
ይበላሉ" አለችው።
28በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ "አንቺ ሴት
እምነትሽ ታላቅ ነው እንደ ፈለግሽው
ይሁንልሽ" አላት። ልጇም ከዚያ ሰዓት
ጀምሮ ተፈወሰች።

## ኢየሱስ አራት ሺህ ሰዎች በታምር መገበ

*15፥29-31 ተጓ ምብ — ማር 7፥31-37*
*15፥32-39 ተጓ ምብ — ማር 8፥1-10*
*15፥32-39 ማመ — ማቴ 14፥13-21*

29ኢየሱስ ከዚያ ተነሥቶ በገሊላ ባሕር
አጠገብ ወዳለው ስፍራ በመሄድ ወደ ተራራ
ወጥቶ ተቀመጠ። 30ቍጥሩ ብዙ የሆነ
ሕዝብም አንካሶችን፣ ዐይነ ስውሮችን፣
ሽባዎችን፣ ዲዳዎችን እንዲሁም ሌሎች
ብዙዎችን ሕመምተኞች ይዘው ወደ እርሱ
በማምጣት በእግሩ ሥር አስቀመጧቸው፤
እርሱም ፈወሳቸው። 31ሕዝቡም ዲዳው
ሲናገር፣ ሽባው ደህና ሲሆን፣ አንካሳው
ቀጥ ብሎ ሲሄድ፣ ዐይነ ስውሩም ሲያይ
ተመልክተው ተደነቁ፤ የእስራኤልንም
አምላክ አመሰገኑ።
32ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፣
"ሕዝቡ ከእኔ ጋር ሦስት ቀን ስለሆናቸውና
የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤
በመንገድ ላይ በራብ ዝለው እንዳይወድቁ
ጦማቸውን ልሰዳቸው አልፈቅድም" አለ።
33ደቀ መዛሙርቱም፣ "በዚህ ምንም
በሌለበት ምድረ በዳ ይህንን ሁሉ ሕዝብ
ለማብላት በቂ እንጀራ ከየት እናገኛለን?"
በማለት መለሱለት።
34ኢየሱስም፣ "ስንት እንጀራ
አላችሁ?" ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ "ሰባት እንጀራና ጥቂት
ትናንሽ ዓሣ" አሉት።
35እርሱም ሕዝቡን መሬት ላይ
እንዲቀመጡ አዘዛቸው፤ 36ሰባቱን እንጀራና
ዓሣውን ይዞ ካመሰገነ በኋላ ቈርሶ ለደቀ
መዛ ሙርቱ ሰጣቸው፤ እነርሱም ለሕዝቡ
አከፋፈሉ። 37ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ ደቀ
መዛሙርቱም የተረፈውን ቍርስራሽ ሰባት
መሶብ ሙሉ አነሡ። 38የበሉትም ከሴቶችና
ከሕፃናት ሌላ አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።
39ኢየሱስ ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላ በጀልባ
ወደ መጌዶል ሄደ።

## ኢየሱስ ከሰማይ ምልክት እንዲያሳይ መጠየቁ

*16፥1-12 ተጓ ምብ — ማር 8፥11-21*

16 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው ሊፈትኑት በመሻት
ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት።
2እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤[a]
"ምሽት ላይ፣ 'ሰማዩ ስለ ቀላ ብራ ይሆናል'
ትላላችሁ፤ 3ንጋት ላይም፣ 'ሰማዩ ቀልቶአል፣
ከብዶአልም፤ ስለዚህ ዝናብ ይዘንባል'
ትላላችሁ። የሰማዩን ገጽታ ትለያላችሁ፤ ነገር
ግን የዘመኑን ምልክት መለየት አትችሉም።
4ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት
ይፈልጋል፤ ነገር ግን ከዮናስ ምልክት
በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም።"
ከዚያም ኢየሱስ ትቶአቸው ሄደ።

## የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን እርሾ

5ባሕሩን እንደ ተሻገሩም፣ ደቀ
መዛሙርቱ እንጀራ መያዝ ረስተው ነበር።
6ኢየሱስም፣ "ልብ በሉ፤ ከፈሪሳውያንና

15፥16 ማቴ16፥9
15፥18 ማቴ12፥34፤ ሉቃ6፥45፤ ያዕ3፥6
15፥19 ገላ5፥19-21
15፥20 ሮሜ14፥14
15፥21 ማቴ11፥21
15፥22 ማቴ4፥24፤ 9፥27
15፥24 ማቴ10፥6፡23፤ ሮሜ15፥8
15፥25 ማቴ8፥2
15፥28 ማቴ9፥22
15፥30 ማቴ4፥23
15፥31 ማቴ9፥8
15፥32 ማቴ9፥36
15፥36 ማቴ14፥19
15፥37 ማቴ16፥10
16፥1 ማቴ12፥38፤ ሐሥ4፥1
16፥3 ሉቃ12፥54-56
16፥4 ማቴ12፥39
16፥6 ሉቃ12፥1

[a]16፥2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የቍጥር 2 ከፊልና ቍጥር 3 በሙሉ የላቸውም

**15፥19 ከልብ ይመነጫልና፤** ማር 7፥21 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**15፥28 እምነትሽ ታላቅ ነው፤** በእውነተኛ እምነት መጽናት ማለት በትልቅ ችግር ውስጥ ብንገኝም፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን የማይመልስልንና የማይጠነቀቅልን በሚመስል ጊዜም እንኳ በእግዚአብሔር መታመንና ለእርሱ በእውነተኛነት መጽናት ማለት ነው። ይህ እምነት የሚፈተንበት ነው (ሉቃ 18፥1-7፤ 1ጴጥ 1፥7፤ ማር 7፥27 እና ማብ ይመ)።

**16፥6 ከ ... እርሾ ተጠበቁ፤** በዚህ ስፍራ፣ "እርሾ" የተባለው የክፋትና የመበከል ትእምርት ሲሆን፣ ይህም የፈሪሳውያንንና የሰዱቃውያንን ትምህርት ያመለክታል።

ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ" አላቸው።
7እነርሱ ግን እርስ በርሳቸው፣ "እንጀራ
ስላልያዝን ይሆናል" ተባባሉ።
8ኢየሱስም ሐሳባቸውን አውቆ እንዲህ
አላቸው፤ "እናንተ እምነት የጐደላችሁ፤
እርስ በርሳችሁ እንጀራ ስለ አለመያዛችሁ
ለምን ትነጋገራላችሁ? 9አምስቱ እንጀራ
ለአምስት ሺህ ሰው በቅቶ ስንት መሶብ ተርፎ
እንዳነሣችሁ አታስታውሱምን? 10እንዲሁም
ሰባቱ እንጀራ ለአራት ሺህ ሰው በቅቶ ስንት
መሶብ ተርፎ እንዳነሣችሁ ልብ አላላችሁም
ማለት ነውን? 11ታዲያ የነገርኋችሁ ስለ
እንጀራ እንዳልሆነ እንዴት አታስተውሉም?
አሁንም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ
ተጠንቀቁ።" 12በዚህ ጊዜ ያስጠነቀቃቸው
እንጀራ ውስጥ ስለሚጨመረው እርሾ
ሳይሆን፣ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን
ትምህርት መሆኑ ገባቸው።

## ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ማንነት መናገሩ

*16፥13-16 ተጓ ምብ — ማር 8፥27-29፤ ሉቃ 9፥18-20*

13ኢየሱስ ፊልጶስ ቂሣርያ ወደ ተባለው
አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፣
"ሰዎች፣ የሰውን ልጅ ማን ነው
ይላሉ?" ብሎ ጠየቃቸው።
14እነርሱም፣ "አንዳንዶቹ መጥምቁ
ዮሐንስ፣ ሌሎች ኤልያስ፣ ሌሎች ደግሞ
ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው
ይላሉ" አሉት።
15እርሱም፣ "እናንተስ እኔን ማን
ትሉኛላችሁ?" አላቸው።
16ስምዖን ጴጥሮስም፣ "አንተ ክርስቶስ[x]
የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" በማለት
መለሰ።

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ተናገረ

*16፥21-28 ተጓ ምብ — ማር 8፥31—9፥1፤ ሉቃ 9፥22-27*

17ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የዮና ልጅ
ስምዖን ሆይ፣ ብፁዕ ነህ፤ ይህን የገለጠልህ
በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም
አይደለም። 18አንተ ጴጥሮስ[y] ነህ፤ በዚህ ዐለት
ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም

16፥8 ማቴ6፥30
16፥9 ማቴ14፥17-21
16፥10 ማቴ15፥34-38
16፥12 ሐሥ4፥1
16፥14 ማቴ3፥1፤ ማር6፥15፤ ዮሐ21
16፥16 መዝ42፥2፤ ኤር10፥10፤ ማቴ4፥3፤ ሐሥ14፥15፤ 2ቆሮ6፥16፤ 1ተሰ1፥9፤ 1ጢሞ3፥15፤ ዕብ10፥31፤ 12፥22
16፥17 ማቴ13፥11፤ 1ቆሮ15፥50፤ ኤፌ6፥12፤ ዕብ2፥14
16፥18 ዮሐ1፥42፤ ኤፌ2፥20

[x]16፥16 ወይም መሲሕ፤ ቍ 20 ይመ
[y]16፥18 ጴጥሮስ ትርጉሙ ዐለት ማለት ነው

ክርስቶስ ትምህርታቸውን «እርሾ» አለው፤ ይህን ያለበት ምክንያትም ጥቂቱ በቀላሉ ዘልቆ ሊገባና አያሌ ሰዎች የተሳሳተን ነገር እንዲያምኑ ማድረግ ስለሚችል ነው (ማር 8፥15 እና ማብ ይመ)።

**16፥18 ጴጥሮስ … ዐለት … ቤተ ክርስቲያኔን፤** በእነዚህ ቃላት ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን (ቍ 16 ይመ፤ ከሐሥ 2፥14-26 ጋር ያነጻጽሩ) በመሰከሩት የምስክርነት እውነት ላይ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመሠረት ክርስቶስ የተስፋ ቃል ይሰጣል። ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ቃላትን በልዩ መንገድ ሲጠቀም እናያለን። ደቀ መዝሙሩን «ጴጥሮስ» (በግሪክ ቋንቋ «ፔትሮስ» ትርጕሙ ትንሽ ዐለት ማለት ነው) ብሎ ይጠራዋል፤ በመቀጠልም፣ «በዚህ ዐለት ላይ (በግሪክ ቋንቋ፤ ፔትራ ትርጕሙም ትልቅ ዐለት ወይም ድንጋያማ ገደል ማለት ነው) ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» ይላል፤ ይህም በጴጥሮስ ጠንካራ ምስክርነት ላይ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን የሚመሠ ርት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

(1) የመጀመሪያውና ትልቁ የቤተ ክርስቲያን መሠ ረት (1ቆሮ 3፥11)፣ ዐለት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጴጥሮስ በመጀመሪያው መልእክቱ ስለ ኢየሱስ፣ «… ሕያው ድንጋይ … የተመረጠና ክቡር የማእዘን ድንጋይ … ግንበኞች የናቁት ድንጋይ» (1ጴጥ 2፥4፡6-7) በማለት ይገልጻል። በሌላ በኩል ጴጥሮስና ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ለሚሠራው መንፈሳዊ ቤት ሕያዋን ድንጋዮች በመሆን የምንሠራ የሕንጻው አካል ነን (1ጴጥ 2፥5)።

(2) መጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ክፍል ጴጥሮስ ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ይልቅ ከፍተኛና ስሕተት አልባ ባለሥልጣን መሆኑን አያመለክትም (ከሐሥ 15፥ ከገላ 2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እንዲሁም ጴጥሮስ ክርስቶስን በመወከልና የቤተ ክርስቲያን ራስ በመሆን በደፋ የታወቁ ስሕተት አልባ ባለሥልጣን ተተኪዎች ይኖሩታል የሚልም አልተጠቀሰም።

በዚህ ስፍራ የታየውንና በመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ስፍራ የተጠቀሰውን ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በዝርዝር የተገለጸውን ሐሳብ ለመረዳት፣ በገጽ 1453 ላይ፣ *«ቤተ ክርስቲያን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**16፥18 የገሃነም ደጆች አያሸንፏትም፤** «የገሃነም ደጆች» የሚለው ሐረግ የሚወክለው የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ጥረት የሚያደርጉትን ሰይጣንንና የዓለምን ክፋት ሁሉ ነው። (1) ይህ ምንባብ አንድ አማኝ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ወይም ቤተ እምነት ወደ ኢግብረገባዊነት፣ አስተምህሮአዊ ስሕተት ወይም ክሕደት ውስጥ አይገቡም የሚል ትርጕም አይሰጥም። ኢየሱስ ራሱ ብዙዎች ከእምነት እንደሚወጡ ተናግሮአል፤ የአዲስ ኪዳን እምነትን የተዉትንም ከነጢአታቸው እንዲመለሱ፣ ባይመለሱ ግን ከመንግሥቱ ሊወገዱ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያን ሰጥቶአቸዋል (24፥10-11፤ ራእ 2፥5፡12-29፤ 3፥1-6፡14-16፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1962 ላይ፣ *«ክሕደት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በቍ 18 ላይ ያለው የተስፋ ቃል እምነትን የሚክዱትን ወይም የለብታ አቋም ያላቸውን አብያተ ክርስቲያናት አይመለከትም።

(2) ሰይጣን እጅግ የከፋ ነገርን ቢያደርግም፤ በአማኞች መካከል ክሕደት ቢከሠትም፣ አብያተ ክርስቲያናት የለብታ አቋም ቢኖራቸውም፤ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በእግዚአብሔር መንግሥት መንጋ መካከል ቢገቡም፣ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ እንደማትጠፋ ክርስቶስ በዚህ ስፍራ ተናግሮአል። እግዚአብሔር በሉዓላዊ ጸጋው፣ ጥበቡና ኀይሉ የሚጠብቃቸው፣ በቤዛነት ታሪክ ውስጥ ለእውነተኛው የክርስቶስና የሐዋርያት ወንጌል ታማኞች በመሆን የሚጸኑ፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ያለውን ኅብረት፣ የክርስቶስን ጌትነትና የመንፈስ ቅዱስን ኀይል የሚለማመዱ፣ የአማኞችና የአብያተ ክርስቲያናት ትሩፋን ምንጊዜም ይኖሩታል። የእግዚአብሔር እውነተኛ ሕዝብ

ደጆችም አያሸንፏትም።[ꭲ] 19የመንግሥተ
ሰማይን መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር
ያሰርኸው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤
በምድርም የፈታኸው ሁሉ በሰማይ
የተፈታ ይሆናል።" 20ቀጥሎም እርሱ
ክርስቶስ መሆኑን ለማንም እንዳይናገሩ
ደቀመዛሙርቱን አስጠነቀቃቸው።

21ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ
ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ፣ በዚያም
በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በኦሪት
ሕግ መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና
ይገደል ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት
ይነሣ ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ
ይገልጽላ ቸው ጀመር።

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ

22ጴጥሮስም ኢየሱስን ወደ ጐን ሳብ
አድርጎ፣ "ጌታ ሆይ፤ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ
አይድረስብህ" እያለ ይገሥጸው ጀመር።
23ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዞወር ብሎ፣
"አንተ ሰይጣን፣ ሂድ ከዚህ! የሰው እንጂ
የእግዚአብሔር ነገር በሐሳብህ ስለ ሌለ
መሰናክል ሆነህብኛል!" አለው።
24ከዚያም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን
እንዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ የሚወድ
ራሱን ይካድ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ
ይከተለኝ፤ 25ነፍሱንⁿ ሊያድን የሚፈልግ
ሁሉ ያጠፋ ታል፤ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ
የሚያጠፋት ያድናታል። 26ሰው ዓለምን
ሁሉ ቢያ ተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን
ይጠቀመዋል? ወይስ ሰው በነፍሱ ምትክ
ሊከፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድን ነው?
27የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክት
ጋር ይመጣል፤ ለእያንዳንዱም ሰው እንደ
ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል። 28እውነት
እላችኋለሁ፣ እዚህ ከቆሙት ሰዎች መካከል
የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስከሚያዩ
ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አሉ።"

ማቴ :15-51

16፥19 ኢሳ22፥22፤ ማቴ18፥18፤ ዮሐ20፥23፤ ራእ3፥7
16፥20 ማር8፥30
16፥21 መዝ22፥6፤ ኢሳ53፥3፤ ሆሴ6፥2፤ ማቴ12፥40፤ 17፥22፡23፤ 26፥67፡68፤ 27፥1፡2፡63፤ ማር9፥31፤ 10፥34፤ ሉቃ9፥22፡51፤ 17፥25፤ 18፥31-33፤ 24፥6፡7፡21፡46፤ ዮሐ2፥19፤ 18፥22፡23፤ 19፥3፤ ሐሥ2፥23፤ 3፥13፤ 1ቆሮ15፥3፡4
16፥23 ማቴ4፥10
16፥24 ማቴ10፥38፤ ሉቃ14፥27
16፥25 ዮሐ12፥25
16፥27 2ሳሙ6፥23፤ ኢዮ34፥11፤ መዝ62፥12፤ ኤር17፥10፤ ሕዝ18፥20፤ ማቴ8፥20፤ ሉቃ17፥30፤ ዮሐ14፥3፤ ሐሥ1፥11፤ 1ቆሮ1፥7፤ 3፥12-15፤ 2ቆሮ5፥10፤ 1ተሰ2፥19፤ 4፥16፤ ራእ1፥7፤ 22፥7፡12፡20
17፥1 ማቴ4፥21
17፥5 ማቴ3፥17፤ ሐሥ3፥22፡23
17፥7 ማቴ14፥27
17፥9 ማቴ8፥20፤ 16፥21፤ ማር8፥30
17፥11 ሚል4፥6፤

## የኢየሱስ መልክ በቅጽበት መቀየር

*17፥1-8 ተጓ ምብ — ሉቃ 9፥28-36*
*17፥1-13 ተጓ ምብ — ማር 9፥2-13*

**17** ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ፣
ጴጥሮስንና ያዕቆብን እንዲሁም
የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን ወደ አንድ
ከፍ ያለ ተራራ ብቻቸውን ይዞአቸው ወጣ።
2በዚያም በፊታቸው መልኩ ተቀየረ፤ ፊቱ
እንደ ፀሐይ አበራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን
አንጸባረቀ። 3ወዲያውም ሙሴና ኤልያስ
ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።
4ጴጥሮስም ኢየሱስን፣ "ጌታ ሆይ፤ በዚህ
ብንሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ፈቃድህ
ከሆነ፣ አንድ ለአንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ
ለኤልያስ ሦስት ዳሶች ልሥራ" አለው።
5እርሱ እየተናገረ ሳለ፣ ብሩህ ደመና
ሸፈናቸው፤ ከደመናውም ውስጥ፣ "በእርሱ
ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤
እርሱን ስሙት" የሚል ድምፅ ተሰማ።
6ደቀ መዛሙርቱም ይህን ሲሰሙ
ደንግጠው በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፉ።
7ኢየሱስም ቀርቦ ነካቸውና፣ "ተነሡ፤ አት
ፍሩ" አላቸው። 8ቀና ብለው ሲመለከቱም
ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ ማንንም አላዩም።
9ከተራራው በመውረድ ላይ ሳሉ ኢየሱስ፣
"የሰው ልጅ ከሞት እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን
ለማንም እንዳትናገሩ" ብሎ አዘዛቸው።
10ደቀ መዛሙርቱም፣ "ታዲያ የኦሪት
ሕግ መምህራን፣ ኤልያስ አስቀድሞ
መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድን ነው?"
ብለው ጠየቁት።
11እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ኤልያስ በርግጥ መጥቶ ሁሉንም ነገር
ያስተካክላል፤ 12ነገር ግን እላችኋለሁ፤
ኤልያስ መጥቶአል፤ ሆኖም የፈለጉትን
ነገር አደረጉበት እንጂ አላወቁትም።
እንዲሁም የሰው ልጅ በእጃቸው መከራን

17፥11 ሉቃ1፥16፡17 17፥12 ማቴ11፥14፤ 14፥3፡10፤ 16፥21

*ꭲ16፥18 ወይም ሊቋቋሟት አይችሉም*
*ⁿ16፥25 የግሪኩ ቃል ትርጉም ሕይወት ወይም ነፍስ ነው፤ ቍ 26 ይመ*

---

እንደመሆናቸው መጠን፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ኀይል የሆነውን መንፈስ ቅዱስን በሰይጣን፣ በኀጢአት፣ በበሽታ፣ በዓለምና በአጋንንት ሥራ ላይ ይገልጣሉ። እንግዲህ እንደዚህ ዐይነቷን ቤተ ክርስቲያን ሰይጣንና ሰራዊቱ ሁሉ ሊያጠፏት ወይም ሊቋቋሟት ከቶ አይችሉም።

16፥19 **የመንግሥተ ሰማይን መክፈቻዎች፤** "*መክፈቻዎች*" የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለጴጥሮስና ለቤተ ክርስቲያን በውክልና የሰጠውን ሥልጣን ያመለክታል። በእነዚህ መክፈቻዎች፣ (1) ኀጢአትን ይቃወማሉ፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዐት ያስከብራሉ (18፥15-18)፤ (2) በምድር ላይ የእግዚአብሔር ፀላማ ይፈጸም ዘንድ ውጤታማ ጸሎት ይጸልያሉ (18፥19-20)፤ (3) አጋንንትን ያስራሉ፤ በአጋንንት የታሰሩትንም ነጻ ያወጣሉ (በገጽ 1471 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (4) የኀጢአትን አስከፊነት፣ እግዚአብሔር ለጽድቅ ሕይወት ያስቀመጠውን መስፈርትና ሊመጣ ያለውን ፍርድ ያስታውቃሉ (ሐሥ 2፥23፤ 5፥3፡9)፤ (5) ንስሓ ለሚገቡና በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የኀጢአት ይቅርታንና ድነትን ያውጃሉ (ዮሐ 20፥23፤ ሐሥ 2፥37-40፤ 15፥7-9)።

16፥24 **መስቀሉንም ተሸክሞ፤** ማር 8፥34 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

16፥28 **በመንግሥቱ ሲመጣ፤** "የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ" የሚለው ሐረግ ክርስቶስ ተከታዮቹን በመንፈስ ቅዱስና በታላቅ ኀይል ባጠመቀበት በበዓለ ኀምሳ ቀን የሆነውን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ከማር 9፥1፤ ከሐሥ 1፥8፤ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥2 **መልኩ ተቀየረ፤** ሉቃስ 9፥29 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

# ቤት ክርስቲያን

*ማቴ 16፥18 "አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አያሸንፏትም።"*

"ኤቅሌሲያ" (ቤተ ክርስቲያን) የሚለው የግሪክ ቃል ታዝው የወጡና በአንድነት የተጠሩ ሰዎችን ስብሰባ ይወክላል። በአዲስ ኪዳን በመሠረቱ ይህ ቃል እግዚአብሔርን ለማምለክ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች በመሆን (ኤፌ 2፥19) በአንድነት የተሰበሰቡ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን ጉባኤ ያመለክታል። "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን (ማቴ 18፥17፤ ሐሥ 15፥4) ወይም ዓለም ዐቀፍ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን (ማቴ 16፥18፤ ሐሥ 20፥28፤ ኤፌ 2፥21-22) ያመለክታል።

(1) ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ (1ቆሮ 1፥2፤ 10፥32፤ 1ጴጥ 2፥4-10)፣ በክርስቶስ ሞት ቤዛነትን ያገኙ አማኞች ማኅበር በመሆን (1ጴጥ 1፥18-19) ተገልጻለች። በውስጧ ያሉት አማኞች የመጀመሪያ ተግባራቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሕያውና የግል ግንኙነት ያለው ኅብረት ሰብ ሆኖ በመቆም ነው (1ጴጥ 2፥5፤ ዕብ 11፥6 እና ማብ ይመ)፤ እነርሱም ከእንግዲህ የዚህ ምድር ዜጎች ሳይሆኑ ተጓዥ ሕዝቦች ናቸው (ዕብ 13፥12-14)።

(2) ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ተጠርተው የወጡና (በግሪክ ቋንቋ፣ "ኤካሊኦ") ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የገቡ ሕዝብ ናት። ከዓለም መለየት በቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ ጌታን አምላክና አባት አድርጎ በመቀበልም ሽልማትን ያስገኛል (2ቆሮ 6፥16-18 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር አብ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናት (1ቆሮ 3፥16 እና ማብ፤ 2ቆሮ 6፥14-7፥1፤ ኤፌ 2፥11-22፤ 1ጴጥ 2፥4-10 ይመ)። ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረው ይህ እውነት ጽድቅ ከሌለበት ነገርና ዓለማዊ ከሆነ ኢግብረገባዊነት መለየትን ይጠይቃል።

(4) ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት (1ቆሮ 6፥15-16፤ 10፥16-17፤ 12፥12-27)፤ አካልነቷ እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን አባሎቿን እጅግ አስፈላጊ ከሆነው ከክርስቶስ አንድነት በመለየት መቆም እንደማትችል ያመለክታል (ኤፌ 1፥22፤ 4፥15፤ 5፥23፤ ቈላ 1፥18)።

(5) ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ናት (2ቆሮ 11፥2፤ ኤፌ 5፥22-27፤ ራእ 19፥7-9)። ይህ የጋብቻ ምሳሌያዊ አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ያላትን መሰጠትና ታማኝነት ሲያመለክት፣ ክርስቶስም ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅርና ቅርርብ ያሳያል።

(6) ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊት ኅብረት (በግሪክ ቋንቋ፣ "ኮይኖንያ") ናት (2ቆሮ 13፥14፤ ፊል 2፥1)። ይህም ኅብረት የመንፈስ ቅዱስን በሰው ውስጥ ማደር (ሉቃ 11፥13፤ ዮሐ 7፥37-39፤ 20፥22)፣ የመንፈስን አንድነትና (ኤፌ 4፥4) በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅን (ሐሥ 1፥5፤ 2፥4፤ 8፥14-17፤ 10፥44፤ 19፥1-7) ያካትታል። ይህ ኅብረት በተግባር የሚገለጽ ፍቅርንና የርስ በርስ እንክብካቤን ማሳየት አለበት።

(7) ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት (በግሪክ ቋንቋ፣ "ዲያኮንያ") ናት። ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተሰጡት ስጦታዎች (በግሪክ ቋንቋ፣ "ካሪስማታ") ታገለግላለች (ሮሜ 12፥6፤ 1ቆሮ 1፥7፤ 12፥4-11፡28-31፤ ኤፌ 4፥11)።

(8) ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የገባች ሰራዊት ናት። በመንፈስ ሰይፍና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ትዋጋለች (ኤፌ 6፥17)። ቤተ ክርስቲያን ከሰይጣንና ከኀጢአት ጋር መንፈሳዊ ትግል ታካሂዳለች (በገጽ 1443 ላይ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ቤተ ክርስቲያን የተሞላችበት መንፈስ፣ ሰዎችን ከሰይጣን ግዛት ነጻ ለማውጣትና የጨለማውን ዓለም ኀይል ሁሉ ለማሸነፍ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ኀይሉ የሚጠቀም ተዋጊ ኀይል ነው (ሐሥ 26፥18፤ ኤፌ 6፥10-18፤ ዕብ 4፥12፤ ራእ 1፥16፤ 2፥16፤ 19፥15፡21)።

(9) መሠረት ሕንጻን ደግፎ እንደሚይዝ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም እውነትን ደግፋ የያዘች የእውነት ዐምድና መሠረት ናት (1ጢሞ 3፥15)። ቤተ ክርስቲያን እውነትን ከሚያጣምሙና የሐሰት ትምህርት ከሚያስተምሩ አስተማሪዎች ራሷን በመከላከል፣ እውነትን መንከባከብና መጠበቅ አለባት (ፊል 1፥16 እና ማብ፤ ይሁ 1፥3 እና ማብ ይመ)።

(10) ቤተ ክርስቲያን የወደፊት ብሩህ ተስፋ ያለው ሕዝብ ናት። ይህ ተስፋ የተመሠረተው

በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ 1ጢሞ 6፥14፤ 2ጢሞ 4፥8፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ 9፥28 ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(11) ቤተ ክርስቲያን የማትታይም የምትታይም ናት። (ሀ) የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ባላቸው ሕያው እምነት አንድ የሆኑ እውነተኛ አማኞች አካል ናት (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (ለ) የምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ታማኝ የሆኑ ድል አድራጊዎችን (ራእ 2፥11፡17፡26 ይመ፤ 2፥7 እና ማብ ይመ)፣ ክርስቲያን ተብለው የተጠሩ ሐሰተኞችን (ራእ 2፥2)፤ የወደቁትን (ራእ 2፥5)፣ በመንፈስ የሞቱትንና (ራእ 3፥1) የለብታ አቋም ያላቸውን (ራእ 3፥16፤ ማቴ 13፥24 እና ማብ፤ ሐሥ 12፥5 እና ስለ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ባሕርያት የተጠቀሰውን ማብ ይመ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ አካትታ ይዛለች።

ይቀበላል።" [13]በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ
ኢየሱስ የነገራቸው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ
መሆኑን ተረዱ።

## ኢየሱስ የሚጥል በሽታ ያለበትን ልጅ ፈወሰ

[14]ወደ ሕዝቡ እንደ ተመለሱ፣ አንድ
ሰው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ በፊቱ ተንበረከከና
እንዲህ አለ፤ [15]"ጌታ ሆይ፤ እባክህ ልጄን
ማርልኝ፤ በሚጥል በሽታ እጅግ እየተሠቃየ
ነው፤ ብዙ ጊዜ እሳት ውስጥ ይወድቃል፤
ውሃ ውስጥም ይገባል፤ [16]ወደ ደቀ መዛሙ
ርትህ አመጣሁት፤ ነገር ግን ሊፈውሱት
አልቻሉም።"

[17]ኢየሱስም፣ "አንት የማታምን ጠማማ
ትውልድ፤ እስከ መቼ እናንተ ጋር
እኖራለሁ፤ እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ።
ልጁን ወደዚህ አምጡት" አለ። [18]ከዚያም
ኢየሱስ ጋኔኑን ገሠጸውና ከልጁ ወጣ፤
ልጁም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነ።

[19]ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው ወደ
ኢየሱስ ቀርበው፣ "እኛ ጋኔኑን ማስወጣት
ያልቻልነው ለምንድን ነው?" ብለው
ጠየቁት።

[20]እርሱም እንዲህ አላቸው፤
"እምነታችሁ በማነሱ ምክንያት ነው፤
እላችኋለሁ፤ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል
እምነት ቢኖራ ችሁ፣ ይህንን ተራራ፣
'ከዚህ ተነሥተህ ወደዚያ ሂድ' ብትሉት
ይሄዳል፤ የሚሳናችሁም ነገር አይኖርም፤ ማቴ 21፥21-22
[21]የዚህ ዓይነቱ ግን በጸሎትና በጾም ካልሆነ
በስተቀር አይወጣም።"

[22]በገሊላ ተሰባስበው ሳሉ ኢየሱስ
እንዲህ አላቸው፤ "የሰውን ልጅ አሳልፈው
ለሰዎች ይሰጡታል፤ [23]ይገድሉታልም፤
እርሱም በሦስተኛው ቀን ይነሣል።" ደቀ
መዛሙርቱም እጅግ አዘኑ።

## ስለ ቤተ መቅደስ ግብር ክፍያ

[24]ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ
ቅፍርናሆም ከደረሱ በኋላ፣ የቤተ መቅደሱ
ግብር ተቀባዮች ወደ ጴጥሮስ ቀርበው
"መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር የቤተ መቅደስ
ግብር አይከፍልምን?" አሉት።

[25]እርሱም፣ "ይከፍላል እንጂ" አላቸው።

ጴጥሮስ ወደ ቤት እንደ ገባ ኢየሱስ
በቅድሚያ፣ "ስምዖን፤ የምድር ነገሥታት
ግብር ወይም ቀረጥ የሚቀበሉት ከራሳቸው
ልጆች ወይስ ከሌሎች ይመስልሃል?"
አለው።

[26]ጴጥሮስም፣ "ከሌሎች ነው የሚቀበሉት"
አለው።

ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "እንግዲያውስ
ልጆች ነጻ ናቸው፤ [27]ሆኖም
እንዳናስቀይማቸው ሂደህ መንጠቆህን ወደ
ባሕር ጣል፤ መጀመሪያ የምትይዘውን

17፥13 ማቴ3፥1
17፥15 ማቴ4፥24
17፥20 ማቴ13፥31፤ 21፥21፤ ሉቃ17፥6፤ 1ቆሮ13፥2
17፥22 ማቴ8፥20
17፥23 ማቴ16፥21፤ ሐሥ2፥23፤ 3፥13
17፥24 ዘፀ30፥13
17፥25 ማቴ22፥17-21፤ ሮሜ13፥7
17፥27 ዮሐ6፥61

17፥17 **የማታምን ጠማማ**፤ ይህ ክፍል በእውነተኛው የእግዚአብሔር መንግሥት ኀይል ሌሎችን ማገልገል ያቃታቸውን ደቀ መዛሙርትንና አብያተ ክርስቲያናትን ኢየሱስ እንዴት እንደገመገማቸው ያሳያል (በገጽ 1443 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር መንግሥት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: (1) በሰይጣን ወይም በአጋንንት የተጨቈኑትን ነጻ ለማውጣት አለመቻል (ቍ 15-21) የእምነት፣ የዕውቀትና የመንፈሳዊ ሥልጣን ማነስ ዕጦትን ይገልጣል (ቍ 17:20-21፤ ማር 9፥29)፤ (2) ከቍ 14-21 ያለው ትረካ እንዲጻፍ መንፈስ ቅዱስ የፈለገበት ዐላማ፣ አጋንንትን የሚያስወጣው ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን፣ ደቀ መዛሙርትም እንዲሁ በእምነት ተመሳሳይ የሆነ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ በአጽንዖት ይገለጽ ዘንድ ነው (ቍ 20-21፤ በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: የሰይጣንን ኀይል በመቃወም በሚካሄደው አገልግሎት ሕዝቡ መተባበር ሲያቅታቸው፣ ኢየሱስ በሕዝቡ ላይ በእጅጉ ቅር ይሰኛል፤ በጣሙም ያዝናል (10፥1 እና ማብ፤ 10፥8፤ ማር 9፥28-29፤ ሉቃ 9፥1፤ ዮሐ 14፥12 እና ማብ ይመ)::

17፥20 **እምነት ... የሚሳናችሁም ነገር አይኖርም**፤ ኢየሱስ በተደጋጋሚ በእውነተኛ እምነት ባሕርይ ላይ ማብራሪያ ሰጥቶአል:: ማብራሪያ የሰጠውም ተራራን ስለሚያንቀሳቅስ፣ ታምራትንና ፈውስን ስለሚያከናውን፤ ታላቅ ነገርን ለእግዚአብሔር ስለሚያደርግ እምነት ነው:: ኢየሱስ ማብራሪያ የሰጠበት ይህ እምነት ምንድን ነው? (1) እውነተኛ እምነት ውጤትን የሚያስገኝ ፍሬያማ እምነት ነው፤ ይኸውም "ተራራን የሚያስነሣ" ማለት ነው::

(2) እውነተኛ እምነት ማለት እምነትን እንደ ጉልበት ወይም እንደ ኀይል በመቍጠር በራሱ "በእምነት" ማመን ሳይሆን፣ "በእግዚአብሔር ማመን" ማለት ነው (ማር 11፥22)::

(3) እውነተኛ እምነት እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ልብ ውስጥ የሚሠራው ሥራ ነው (ማር 9፥24፤ ፊል 2፥13):: በልባችን ውስጥ የሚሠራውም ጸሎታችን እንደተመለሰልን እንድናምን የሚያደርገውን ማስተዋል መለኮታዊ በሆነ መንገድ ወደ ልባችን በማፍሰስ ነው (ማር 11፥23):: ይህ እምነት በውስጣችን የሚፈጠረው በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ በራሳችን አእምሮ ውስጥ እውን ልናደርገው አንችልም (ሮሜ 12፥3፤ 1ቆሮ 12፥9 ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(4) እውነተኛ እምነት ከክርስቶስ ወደ እኛ የሚተላለፍ ስጦታ ስለ ሆነ፣ ለእግዚአብሔር የገባነውን ቃል እንዲሁም በእርሱ ላይ ያለንን መተማመን (ሮሜ 10፥17፤ ፊል 3፥8-15) በጠለቀ መንገድ ለማሳደግ ወደ ክርስቶስና ወደ ቃሉ መቅረብ እጅግ አስፈላጊ ነው:: "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና" (ዮሐ 15፥5፤ በተጨማሪም ዮሐ 3፥27፤ ዕብ 4፥16፤ 7፥25 ይመ) ስለሚል፣ ለማንኛውም ነገር በእርሱ ላይ እንታመናለን:: በሌላ አነጋገር፣ የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን (ዕብ 12፥2) ክርስቶስን አጥብቀን መፈለግ አለብን:: የእርሱ ቅርብ ህልዎትና የእኛም ለቃሉ መታዘዝ የእምነት ምንጭና ምስጢር ናቸው (9፥21፤ ዮሐ 15፥7)::

(5) እውነተኛ እምነት በእግዚአብሔር ቍጥጥር ሥር ነው:: እምነት የሚሰጠው በፍቅሩ፣ በጥበቡ፣ በጸጋውና በመንግሥቱ ዐላማ መሠረት ነው:: የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸምና እርሱ ለእኛ ያለውንም ፍቅሩን ለመግለጽ ይሰጣል:: ለራሳችን የግል ፍላጎት ግን ጥቅም ላይ መዋል የለበትም (ያዕ 4፥3)::

ዓሣ አፉን ስትከፍት የምታገኘውን አንድ
እስታቴር በእኔና በአንተ ስም ክፈል።"

## በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?

*18፥1-5 ተጓ ምብ — ማር 9፥33-37፤ ሉቃ 9፥46-48*

**18** በዚያ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
ኢየሱስ ቀርበው፣ "በመንግሥተ
ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው?" ብለው
ጠየቁት። ²ኢየሱስ አንድ ሕፃን ጠርቶ
በመካከላቸው አቆመና እንዲህ አላቸው፤
³"እውነት እላችኋለሁ፣ ካልተለወጣችሁ
እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ፈጽሞ ወደ
መንግሥተ ሰማይ አትገቡም። ⁴ስለዚህ
በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ እንደዚህ
ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው።
⁵"እንደዚህ ያለውንም ሕፃን በስሜ
የሚቀበል እኔን ይቀበላል። ⁶ነገር ግን
በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ
አንዱን የሚያሰናክል ሰው፣ ከባድ የወፍጮ
ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር
ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል። ⁷ይህች ዓለም
የመሰናክል ምክንያት በመሆኗ ወዮላት!
መሰናክል መምጣቱ አይቀርምና፤ ነገር
ግን የመሰናክሉ ምክንያት ለሚሆነው ሰው
ወዮለት። ⁸እጅህ ወይም እግርህ ለመሰናክል
ምክንያት ቢሆንብህ፣ ቈርጠህ ጣለው፤ ሁለት
እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም
እሳት ከምትጣል፣ እንከን ወይም ሽባ ሆነህ
ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። ⁹እንዲሁም
ዐይንህ ለመሰናክል ምክንያት ቢሆንብህ፣
አውጥተህ ጣለው፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ
ገሃነመ እሳት ከምትጣል፣ አንድ ዐይን
ኖሮህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል።
¹⁰"ከእነዚህ ከታናናሾች መካከል አንዱን
እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ እላችኋለሁና፤
በሰማይ ያሉት መላእክታቸው በሰማይ ያለውን
የአባቴን ፊት ሁልጊዜ ያያሉ፤ ¹¹የሰው ልጅ
የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና።

18፥3 ማቴ3፥2፤ 19፥14፤ 1ጴጥ2፥2
18፥4 ማር9፥35
18፥5 ማቴ10፥40
18፥6 ማቴ5፥29፤ ማር9፥42፤ ሉቃ17፥2
18፥7 ሉቃ17፥1
18፥8 ማቴ5፥29
18፥9 ማቴ5፥22፡29
18፥10 ዘፍ48፥16፤ መዝ34፥7፤ ሐሥ12፥11፡15፤ ዕብ1፥14

**18፥1 ከሁሉ የሚበልጥ፤** ሉቃ 22፥24-30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**18፥3 ካልተለወጣችሁ፤** ለውጥን አስመልክቶ ኢየሱስ የሚፈልገው ለውጥ የሚጀምረው እንደ ሕፃናት በመሆን ነው፤ ይኸውም ትሑት በመሆን፣ አስመሳይ ባለመሆን፣ በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፉ በመሆን፣ የዋህና በሰማያዊ አባት ለመታረም ዝግጁ በመሆን ነው። በሥነ መለኮታዊ አመለካከት መሠረት፣ ከመጀመሪያው የሕፃን ልጅ ዐይነት የትሕትና ደረጃ በኋላ፣ ኢየሱስ የሚሻው ለውጥ ሁለት ክፍሎችን ይዞአል፤ የመጀመሪያው ከቅድስና ውጭ ከሆነ ነገር ሁሉ በፍጥነት መራቅ ማለት ሲሆን፡ ሁለተኛው ወደ እግዚአብሔር መመለስና የጽድቅን ሥራ መሥራት ነው፡ ይኸውም ለንስሐ የሚገባ ፍሬን ማፍራት ማለት ነው (3፥8 እና ማብ ይመ)።

(1) መለወጥ የአንድ ወቅት የሐዘን ወይም የንስሓ ድርጊት ብቻ መሆኑን አያመለክትም፡ ነገር ግን ሁሉን ዐቀፍ የሕይወት ዝንባሌ ለውጥ ነው (2ቆሮ 7፥10 እና ማብ ይመ)። ይህ የዝንባሌ ለውጥ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡ ምክንያቱም በተፈጥሮችን ከእግዚአብሔር ዘወር የሚያደርግና ወደ ዘላለማዊ ሞት የሚመራንን የሕይወት መንገድ እንከተላለንና (ሮሜ 1፥18-32፤ ኤፌ 2፥2-3)። መለወጥ እግዚአብሔር ለሚሰጠው ድነት ሰው የሚያደርገው አጸፋ ሲሆን፣ ይህም በእምነት በሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኀይል የሚከናወን ነው (ሐሥ 11፥18)።

(2) ከእግዚአብሔር ጋር ካለን አዲስ ግንኙነት የተነሣ መለወጥ በግንኙነቶቻችን ዙሪያ፡ በባሕርያችን፣ በውሳኔዎቻችን፣ ደስ በምንሰኝባቸው ጉዳዮችና በሕይወት ላይ ባለን አጠቃላይ አመለካከት አዲስ ሁኔታን እንዲከሠት ያደርጋል። መለወጥ ለድነት የሚያበቃ የእውነተኛ እምነት ክፍል ሲሆን፣ ለድነትና ለመቀደስ መሠረታዊ የሆነ አስፈላጊ ነገር ነው (ሐሥ 26፥18)።

**18፥6 የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ፤** የዚህ ጥቅስ ትርጉም ሕፃንን ወይም በእምነቱ ሕፃን የሆነን አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወት የሚያሰናክል ሁሉ የክርስቶስን ታላቅ ቍጣ በራሱ ላይ ያመጣል ማለት ነው። (1) መጋቢዎች፡ አስተማሪዎች በተለይም ወላጆች ለእነዚህ የክርስቶስ ቃሎች ልዩ ትኵረት ሊሰጡ ይገባል። የወላጆች ኀላፊነት ልጆቻቸውን በእግዚአብሔር መንገድ መምራትና (ዘዳ 6፥1-9፤ ሉቃ 1፥17 እና ማብ፡ ኤፌ 6፥4፤ 1ጢሞ 4፥16 ይመ፤ በገጽ 1894 ላይ፣ ***"ወላጆችና ልጆች"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) እንዲሁም ከዓለምና ከሰይጣን ተጽዕኖ መጠበቅ ነው (ቲቶ 1፥10-11፡ 2፥11-12፡ 1ዮሐ 2፥15-17)። (2) ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በማይፈሩ ጓደኞች ተጽዕኖ ሥር እንዲሆኑ መፍቀድ የለባቸውም። በተጨማሪም ከሕዝብ ትምህርት ወይም ከመገናኛ ብዙኃን የመዝናኛ መርሐ ግብሮች በሚሰማው አእምሯቸው እንዳይበከል የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው (ከመዝ 101፥3፤ ከኤፌ 6፥4፤ ከቈላ 3፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

**18፥7 ለሚሆነው ሰው ወዮለት፤** በሌሎች ሰዎች በተለይም በሕፃናት ፊት ኀጢአት የተሞላበትን ነገር በማስቀመጥ መሣሪያ የሚሆኑ የመጨረሻውን ፍርድ እንደሚቀበሉ ኢየሱስ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል (ቍ 2፥5-7)። (1) በሌሎች መንገድ ላይ ሰዎች ኀጢአትን እንዲሠሩ መነሻ ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ማስቀመጥ፣ ታላቅ ፈታኝ ከሆነው ከሰይጣን ጋር መተባበር ነው፤ እነዚህ መነሻ ምክንያቶችም ዓለማዊ መዝናኛ፣ ሰብአዊ ትምህርት፣ ኢግብረገባዊ ፊልሞች፡ ወሲባዊ ግንኙነትን የሚያሳዩ ሥነ ጽሑፎች፡ ሱስ የሚያሲዙ ዕፆች፡ የአልኮል መጠጦች፣ መጥፎ ምሳሌዎች፡ የሐሰት ትምህርቶችና ኀጠአተኛ ባልንጀሮች ናቸው (ከ4፥1፤ ከዘፍ 3፥1-6፡ ከዮሐ 8፥44፤ ከያዕ 1፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) በቤተሰብ፣ በቤት፣ በቤተ ክርስቲያንና በግል ሕይወት ሌሎችን ወደ ፈተና ወይም ወደ ኀጢአት ሊመሩ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ማስወገድ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው የሚጓዙበት የጽድቅ መንገድ ነው (ቍ 7-9)።

**18፥10 መላእክታቸው፤** ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር በመላእክት አማካይነት ለታማኞቹ እንክብካቤ እንደሚያደርግላቸው ያስተምራሉ፤ እነዚህ መላእክት በቅንነትና በፍቅር ለእግዚአብሔር ልጆች የሚገባውን ሁሉ ያደርጋሉ (ከመዝ 34፥7፤ 91፥11፡ ከሉቃ 15፥10፡ 16፥22፤ ከዕብ 1፥14፡ ከራእ 5፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 372 ላይ፣ ***"መላእክትና የእግዚአብሔር መልአክ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

### የጠፋው በግ ምሳሌ

12"እስቲ ንገሩኝ፤ አንድ ሰው መቶ በጎች
ቢኖሩትና ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋበት
ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ላይ ትቶ የጠፋውን
ለመፈለግ አይሄድምን? 13እውነት እላችኋ
ለሁ፤ የጠፋውን በግ ሲያገኝ፣ ካልጠፉት
ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በዚያ በተገኘው ደስ
ይለዋል። 14እንደዚሁም ከእነዚህ ከታናናሾቹ
መካከል አንዱ እንኳ እንዲጠፋ በሰማያት
ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።

### ስለ መቀያየም

15"ወንድምህ ቢበድልህ[a] ሄደህ አንተና
እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው። ቢሰማህ፣
ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ።
16ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም
በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ
ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው።
17እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን
ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ
አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው።
18"እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር
ያሰራችሁት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤
በምድርም የፈታችሁት ሁሉ በሰማይ
የተፈታ ይሆናል።
19"ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፤
በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ ስለ ምንም
ነገር በመስማማት ብትጠይቁ በሰማይ
ያለው አባቴ ያደርግላችኋል፤ 20ሁለት
ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት
መካከል በዚያ እገኛለሁና።"

18፥15 ዘሌ19፥17፤ ሉቃ17፥3፤ ገላ6፥1፤ ያዕ5፥19-20
18፥16 ዘኍ35፥30፤ ዘዳ17፥6፤ 19፥15፤ ዮሐ8፥17፤ 2ቆሮ13፥1፤ 1ጢሞ5፥19፤ ዕብ10፥28
18፥17 ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ6፥1-6
18፥18 ማቴ16፥19፤ ዮሐ20፥23
18፥19 ማቴ7፥7
18፥20 ማቴ28፥20

[a] 18፥15 አንዳንድ ቅጆች ቢበድል/ኀጢአት ቢሠራ ይላሉ።

**18፥15 ወንድምህ ቢበድልህ፤** ከቍ 15-17 ባለው ክፍል ላይ በግል ጒዳይ አንድ ክርስቲያን በሌላው የቤተ ክርስቲያን አባል ላይ በደል ቢፈጽም፣ ጒዳዩ የሚስተካከልበትን ወይም የሥነ ሥርዐት ርምጃ ሊወሰድ የሚቻልበትን መንገድ ኢየሱስ አሳይቶአል። በዚህ ስፍራ ላይ የተሰጠውን የክርስቶስን *መመሪያ* ችላ ማለት የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝብ ባለባት ቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈሳዊ ድንዛዜን፣ በመጨረሻም ጥፋትን ያስከትላል (ከ1ጴጥ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 5፥13 እና ማብ ይመ)።

(1) የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዐት ርምጃ ዐላማ ለእግዚአብሔር ክብር ተገቢ ቦታ ለመስጠት (6፥9፤ ሮሜ 2፥23-24)፣ የቤተ ክርስቲያንን ግብረ ገባዊ ንጽሕናና አስተምህሮአዊ እውነት ለመጠበቅ (1ቆሮ 5፥6-7፤ 2ዮሐ 1፥7-11) እንዲሁም ከሥነ ሥርዐት ውጭ የሆኑ አባሎችን ለማዳን ከስሕተታቸው ታርመው ክርስቶስን እንዲመስሉ ለማድረግ ነው (1ቆሮ 5፥5፤ ያዕ 5፥19-20)።

(2) በደል የፈጸመው ሰው በመጀመሪያ በግል ሊመከርና ሊገሠጽ ይገባል። ምክሩንና ግሣጼውን ከተቀበለ፣ ይቅርታን ሊያገኝ ይገባል (ቍ 15)። በደል የፈጸመው ሰው ለክርስቲያን ወንድሙ ከጥፋቱ መመለሱን ባያሳይ ግን (ቍ 15-16)፣ ከዚያም በአንድ ወይም በሁለት አባላት ፊት አምቢተኛ ቢሆን (ቍ 16)፣ በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማ፣ እንደ ጣዖት አምላኪ ሰው መቈጠር አለበት፤ ይህም ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ እንዳለ፣ ከክርስቶስ እንደ ተለየና ከጸጋ እንደ ወደቀ ሰው መታየት አለበት ማለት ነው (ቍ 17 ይመ፤ ከገላ 5፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ዐመፀኛ ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል የመሆን መብት የለውም፤ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረትም ሊወገድ ይገባል።

(3) ቤተ ክርስቲያንን የማንጻት ተግባር መከናወን ያለበት ኀጢአትና ኢግብረ ገባዊነት በተከሠተበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፤ አስተምህሮአዊ ክሕደት እንዲሁም ለእውነተኛው ለመሠረታዊው የአዲስ ኪዳን እምነት ታማኝ አለመሆን በሚታይበት ዘንድም መፈጸም አለበት (ገላ 1፥9 እና ማብ፤ ይሁ 1፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ ***"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"*** እና በገጽ 1716 ላይ፤ ***"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"*** በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)።

(4) የቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዐት ርምጃ *መፈጸም* ያለበት በትሕትና፣ በፍቅር፣ በፀፀትና ራስን *በመመርመር መንፈስ* ነው (22፥37 እና ማብ፤ 2ቆሮ 2፥6-7፤ ገላ 6፥1 ይመ)።

(5) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዝሙት ርኵሰት ተፈጽሞ ቢገኝ፣ በ1ቆሮ 5፥1-5 እና በ2ቆሮ 2፥6-11 ላይ በተጻፈው መሠረት ርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ስለ እንዲህ ዐይነቱ የከፋ በደል ጉባኤው መፀፀትና ማዘን ይኖርበታል (1ቆሮ 5፥2)፤ "እንደዚህ ያለው ሰው ብዙዎች የወሰኑበት ቅጣት በቂው ነው" (2ቆሮ 2፥6)፤ ከቤተ ክርስቲያንም መወገድ አለበት (1ቆሮ 5፥2፡13)። ግልጽ በሆነ መንገድ ንስሓ ከገባ በኋላ፣ አማኙ ይቅርታን ሊያገኝ ይገባል፤ በፍቅር መያዝ ይኖርበታል፤ ወደ ኅብረቱም እንዲመለስ መደረግ አለበት (2ቆሮ 2፥6-8)።

(6) የመሪ አገልጋዮች (ሽማግሌ፣ መጋቢ፣ ወንጌላዊ ወዘተ) በደል በግል ከታየ በኋላ ሌሎች ይማሩ ዘንድ በጉባኤ ፊት መገሰጥና የሥነ ሥርዐት ርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ይኸውም፣ "ሌሎች አይተው እንዲጠነቀቁ ኀጢአት የሚሠሩትን በጉባኤ ፊት ገሥጻቸው" በተባለው መሠረት ነው (ገላ 2፥11-18፤ 1ጢሞ 5፥19-20 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1925 ላይ፣ ***"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(7) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎችና የአጥቢያ ማኅበሩን ምእመናን መጋቢዎች ማስታወስ ያለባቸው፣ "ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ" (ሐሥ 20፥28) የሚለውን ትእዛዝ ነው (በገጽ 1716 ላይ፣ ***"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። መሪዎች ሰዎችን የመመለስ፣ ሥነ ሥርዐት የመጠቀም ወይም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ዐላማ ጥፋተኞችን የማስወገድ ርምጃ ባለመውሰዳቸው ከጠፉት ማለትም "ከሰው ሁሉ ደም" (ሐሥ 20፥26) ንጹሓን ለመሆናቸው በየግላቸው በኀላፊነት በጌታ ይጠየቃሉ (ከሕዝ 3፥20-21፤ ከሐሥ 20፥26-27 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሕዝ 3፥18 እና ማብ ይመ)።

**18፥19 ሁለት ሆናችሁ ... በመስማማት፤** በጸሎት ውስጥ ትብብርና ስምምነት ካለ ታላቅ ሥልጣን አለ። ምክንያቱም ሁለት ወይም ሦስት አማኞች በእምነትና ለክርስቶስ በመሰጠት ቢሰበሰቡ፣ እርሱ በመካከላቸው ስለሚገኝ ነው (ቍ 20)። የእርሱ ህልውና እምነትን፣ብርታትን፣ ምሪትን፤ ጸጋንና መጽናናትን ያስገኛል (ከመዝ 46፥5፤ ከኢሳ 12፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

### ይቅርታ ስለ ማድረግ

21በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ኢየሱስ ቀርቦ፣
"ጌታሆይ፤ወንድሜቢበድለኝስንትጊዜ ይቅር
ልበለው? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?" አለው።
22ኢየሱስም "እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ
እስከ ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም" አለው።
23"ስለዚህ መንግሥተ ሰማይ፣
በአገልጋዮቹ እጅ የነበረውን ሂሳብ
ለመተሳሰብ የፈለገን ንጉሥ ትመስላለች።
24ሂሳቡን ማጣራት እንደ ጀመረም በሥር
ሺህ ታላንት* ዕዳ ያለበትን አንድ አገልጋይ
አቀረቡለት። 25አገልጋዩም ያለበትን ዕዳ
መክፈል ስላቃተው እርሱ ራሱ፣ ሚስቱ፣
ልጆቹና ንብረቱ ሁሉ ተሸጠው ዕዳው
እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።
26"በዚህ ጊዜ አገልጋዩ እግሩ ላይ ወድቆ፣
'ታገሰኝ፣ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልሃለሁ'
ሲል ለመነው። 27ጌታውም አዘነለትና
ማረው፤ ዕዳውንም ትቶለት አሰናበተው።
28"ያ አገልጋይ ከጌታው ፊት እንደ ወጣ
አንድ መቶ ዲናር* የእርሱ ዕዳ ያለበትን
አገልጋይባልንጀራውንአግኝቶአንቅአድርጎ
በመያዝ 'ያለብህን ዕዳ ክፈለኝ!' አለው።
29"ባልንጀራው አገልጋይም ከፊቱ
ወድቆ፣ 'ታገሠኝ እከፍልሃለሁ' ብሎ
ለመነው።
30"ነገር ግን ሊታገሠው ፈቃደኛ ስላልነ
በረ፣ ያለበትን ዕዳ እስኪከፍለው ድረስ
ወህኒ ቤት አስገባው። 31የሆነውን ነገር ያዩ
ሌሎች አገልጋዮችም በጣም አዘኑ፤ ሄደውም
ሁኔታውን በሙሉ ለጌታቸው ነገሩት።
32"በዚህ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን አስጠርቶ
እንዲህ አለው፤ 'አንተ ክፉ አገልጋይ፤
ስለ ለመንኸኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውሁልህ፤
33እኔ እንደ ማርሁህ አንተም ባልንጀራህን
ልትምረው አይገባህም ነበርን?' 34በቍጣም
ያለበትን ዕዳ ከፍሎ እስኪጨርስ ድረስ
ለአሳሪዎች አሳልፎ ሰጠው።

18፥21 ማቴ6፥14፤ ሉቃ17፥4
18፥22 ዘፍ4፥24
18፥23 ማቴ13፥24፤ 25፥19
18፥25 ዘሌ.25፥39፤ 2ነገ4፥1፤ ነህ5፥5፥8፤ ሉቃ7፥42
18፥26 ማቴ8፥2
18፥35 ማቴ6፥14፤ ያዕ2፥13
19፥1 ማቴ7፥28
19፥2 ማቴ4፥23
19፥3 ማቴ5፥31
19፥4 ዘፍ1፥27፤ 5፥2
19፥5 ዘፍ2፥24፤ 1ቆሮ6፥16፤ ኤፌ5፥31
19፥7 ዘዳ24፥1-4፤ ማቴ5፥31
19፥9 ሉቃ16፥18

35"ስለዚህ እያንዳንዳችሁ
ወንድሞቻችሁን ከልባችሁ ይቅር
ካላላችሁ፣ የሰማዩ አባቴም እንደዚሁ
ያደርግባችኋል።"

### ስለ መፋታት የቀረበ ጥያቄ

*19፥1-9 ተጓ ምባ — ማር10፥1-12*

19 ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ፣ ገሊላን ትቶ ከዮርዳኖስ ማዶ
ወዳለው ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደ። 2ብዙ
ሕዝብም ተከተለው፤ በዚያም ፈወሳቸው።
3ፈሪሳውያንም ሊፈትኑት ቀርበው፣
"ለመሆኑ አንድ ሰው በማንኛውም ምክንያት
ሚስቱን መፍታት ተፈቅዶአልን?" ሲሉ
ጠየቁት።
4እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "ፈጣሪ
በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደ
ፈጠራቸው አላነበባችሁምን? 5እንዲህም
አለ፤ 'ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤
ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም አንድ
ሥጋ ይሆናሉ' የተባለው በዚህ ምክንያት
አይደለምን? 6ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው
እንጂ ሁለት አይደሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር
ያጣመረውን ሰው አይለየው።"
7እነርሱም፣ "ታዲያ፣ ሙሴ አንድ ወንድ
የፍቺውን የምስክር ወረቀት ሰጥቶ ሚስቱን
እንዲያሰናብት ለምን አዘዘ?" አሉት።
8ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ሙሴ
የልባችሁን ጥንካሬ አይቶ ሚስቶቻችሁን
እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ እንጂ ከመጀመሪያው
እንዲህ አልነበረም፤ 9እላችኋለሁ፤ በትዳር
ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ
ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ሴት የሚያገባ ሁሉ
አመንዝራ ይሆናል፤ እርሷንም አመንዝራ
ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም ሴት
የሚያገባ ያመነዝራል።"

*18፥24 በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የሚያህል ነው
*18፥28 ጥቂት ብር ያህል ነው

**18፥35 ይቅር ካላላችሁ፤** በዚህ ምሳሌ ኢየሱስ ያስተማረው፣ የእግዚአብሔር ይቅርታ ንስሓ ለሚገቡ ኀጢአተኞች ሁሉ በነጻ የሚሰጥ ቢሆንም፣ አንድ ሰው ሌሎችን ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ካልሆነ፥ እርሱም በበኩሉ ይቅርታን እንደማያገኝ ነው። በሌላ አነጋገር አንድ ሰው መራራና ይቅር የማይል ልብ ስላለው፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሊያጣ ይችላል ማለት ነው (6፥14-15፤ ዕብ 12፥15፤ ያዕ 3፥11፡14 እና ማብ ይመ፡ በተለይም በኤፌ 4፥31-32 ላይ መራርነት፣ ቅሬታና ጥላቻ ከክርስትና ሕይወት ጋር የማይጣጣሙ መሆናቸውን፣ ሊወገዱም እንደሚገባ ጳውሎስ ያስተማረውን ትምህርት ልብ ይበሉ)።

**19፥9 በትዳሯ ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ፤** በትዳር ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከአንድ የትዳር ጓደኛ ጋር እንዲኖር በሕይወት ዘመንም አንድ ጋብቻ እንዲፈጸም ነው (ቍ 5-6፡ ዘፍ 2፥24 እና ማብ፤ ሚክ 2፥7 እና ማብ፤ 4፥12 እና ማብ፤ ሚል 2፥14 እና ማብ ይመ)። በዚህም ጉዳይ ላይ ኢየሱስ፣ «በትዳር ላይ ዝሙት ፈጽማ እስካልተገኘች ድረስ» የሚለውን ልዩ ሐሳብ ሰጥቶአል። ለትዳር ታማኝ አለመሆን (በግሪክ ቋንቋ፣ ፖርኔያ) ምንዝርናን ወይም ማናቸውንም ዐይነት የዝሙት ርኵሰትን ያካትታል (ከ5፥32 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ መፋታት ሊፈቀድ የሚችለው ዝሙት ተፈጽሞ ሲገኝ ነው። መፋታትን በተመለከተ የሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው፤ (1) ከቍ 7-8 ኢየሱስ መፋታትን ሲያወግዝ በምንዝርና ምክንያት የሚከሠተውን መለያየት ማውገዙ አይደለም፡ ይሁን እንጂ የተናገረው የጋብቻ ሥነ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ባል ሙሽራዪቱ ድንግል አለመሆኗን ሲያውቅ በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት የተፈቀደውን ፍቺ የሚያመለክት ነው (ዘዳ 24፥1-4)። በእንዲህ ዐይነቱ ጉዳይ ሁለቱ በአንድነት መቈየታቸውን እግዚአብሔር ይሻል፤ ይሁን እንጂ ከሕገዘቡ የልብ ድንዳኔ የተነሣ (ቍ 7-8)፣ ከጋብቻ በፊት ለተፈጸመ የቅድስና ጕድለት መፋታትን ፈቅዶአል።

(2) ከጋብቻ በኋላ ለሚከሠት ኢግብረገባዊነት፣ የብሉይ ኪዳን ሕግ ኀጢአት የፈጸሙትን ሁለቱን በመግደል ትዳሩ መፍረስ እንዳለበት ያዛል (ዘሌ 20፥10፤ ዘዳ 22፥22)። ይህም በርግጥ በደል የተፈጸመበት ሰው እንደ ገና የማግባት ዕድል ሊኖረው እንደሚችል

¹⁰ደቀ መዛሙርቱም፣ "የባልና የሚስት
ጉዳይ እንዲህ ከሆነ አለማግባት ይሻላል"
አሉት።
¹¹ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፤
"ከተሰጣቸው በስተቀር ይህንን ትምህርት
ማንም ሊቀበል አይችልም፤ ¹²ምክንያቱም
አንዳንዶች ጃንደረባ ሆነው ይወለዳሉ፤
ሌሎች በሰው እጅ ተሰልበው ጃንደረባ
ይሆናሉ፤ ደግሞም ለመንግሥተ ሰማይ ሲሉ
ራሳቸውን ጃንደረባ የሚያደርጉ አሉ። ይህን
መቀበል የሚችል ይቀበል።"

## ኢየሱስ ሕፃናትን ባረካቸው

*19፥13-15 ተጓ ምብ — ማር 10፥13-16፤ ሉቃ 18፥15-17*

¹³ከዚያም እጆቹን በላያቸው ላይ ጭኖ
እንዲጸልይላቸው ሕፃናትን ወደ እርሱ
አቀረቧቸው። ደቀ መዛሙርቱ ግን ሕፃናቱን
የመጡትን ሰዎች ገሠጿቸው።
¹⁴ኢየሱስም፣ "ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤
አትከልክሏቸው፤ መንግሥተ ሰማይ እንደ
እነርሱ ላሉት ናትና" አላቸው። ¹⁵እጁንም
ከጫነባቸው በኋላ ከዚያ ስፍራ ተነሥቶ
ሄደ።

## የሀብታሙ ጥያቄ

*19፥16-29 ተጓ ምብ — ማር 10፥17-30፤ ሉቃ 18፥18-30*

¹⁶ከዚያም አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ
ቀርቦ፣ "መምህር ሆይ፤ የዘላለምን ሕይወት
አገኝ ዘንድ ምን መልካም ነገር ልሥራ"
ሲል ጠየቀው።
¹⁷ኢየሱስም፣ "ስለ መልካም ነገር ለምን
ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንዱ ብቻ
ነው፤ ወደ ሕይወት ለመግባት ከፈለግህ ግን
ትእዛዛቱን ጠብቅ" አለው።
¹⁸ሰውየውም፣ "የትኞቹን ትእዛዛት?"
ሲል ጠየቀ።
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "አትግደል፤
አታመንዝር፤ አትስረቅ፤ በሐሰት
አትመስክር፤ ¹⁹አባትህንና እናትህን
አክብር፤ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ።"
²⁰ጐልማሳውም ሰውየ፣ "እነዚህንማ
ጠብቄአለሁ፤ ከዚህ ሌላ የሚጐድለኝ ምን
አለ?" አለው።
²¹ኢየሱስም፣ "ፍጹም ለመሆን ከፈለግህ፣
ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፣ ገንዘቡን
ለድኾች ስጥ፤ በሰማይም ሀብት ታገኛለህ።
ከዚያም መጥተህ ተከተለኝ" አለው።
²²ጐልማሳው ሰውየም ይህን ሲሰማ ብዙ
ሀብት ስለ ነበረው እያዘነ ሄደ።
²³ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ
አለ፤ "እውነት እላችኋለሁ፣ ለሀብታም ወደ
መንግሥተ ሰማይ መግባት እጅግ አስቸጋሪ
ነው። ²⁴ደግሞ እላችኋለሁ፤ ሀብታም ወደ
እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል
በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።"
²⁵ይህን ሲሰሙ፣ ደቀ መዛሙርቱ
እጅግ በመገረም፣ "እንግዲያስ ማን ሊድን
ይችላል?" ሲሉ ጠየቁ።
²⁶ኢየሱስም እየተመለከታቸው፣ "ይህ ማር 9፥42-48
በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ
ግን ሁሉም ነገር ይቻላል" አላቸው።
²⁷ጴጥሮስም መልሶ፣ "እኛ ሁሉን ትተን
ተከትለንሃል፤ ታዲያ ምን እናገኝ ይሆን?"
አለው።
²⁸ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ በሚመጣው አዲስ ዓለም የሰው
ልጅ በክብሩ ዙፋን ላይ በሚቀመጥበት
ጊዜ፣ እናንተም የተከተላችሁኝ በዐሥራ
ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ በዐሥራ
ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ላይ ትፈርዳላችሁ።
²⁹ስለ ስሜ ብሎ ቤቶችን፣ ወንድሞችን፣
እኅቶችን፣ አባትን፣ እናትን*፣ ልጆችን
ወይም ዕርሻን የሚተው ሁሉ መቶ ዕጥፍ
ይቀበላል፤ የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።
³⁰ነገር ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች፣ ብዙ
ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።"

19፥11 ማቴ13፥11፤ 1ቆሮ7፥7-9፡17
19፥13 ማር5፥23
19፥14 ማቴ18፥3፤ 25፥34፤ 1ጴጥ2፥2
19፥16 ማቴ25፥46፤ ሉቃ10፥25
19፥17 ዘሌ18፥5
19፥18 ያዕ2፥11
19፥19 ዘፀ20፥12-16፤ ዘሌ19፥18፤ ዘዳ5፥16-20፤ ማቴ5፥43
19፥21 ማቴ5፥48፤ 6፥20፤ ሐሥ2፥45
19፥23 ማቴ13፥22፤ 1ጢሞ6፥9፡10
19፥26 ዘፍ18፥14፤ ኢዮ42፥2፤ ኤር32፥17፤ ሉቃ1፥37፤ 18፥27፤ ሮሜ4፥21
19፥27 ማቴ4፥19
19፥28 ማቴ20፥21፤ 25፥31፤ ሉቃ22፥28-30፤ ራእ3፥21፤ 4፥4፤ 20፥4
19፥29 ማቴ6፥33፤ 25፥46
19፥30 ማቴ20፥16፤ ማር10፥31፤ ሉቃ13፥30

*19፥29 አንዳንድ ቅጆች እናትን ወይም ሚስትን ይላሉ

የመለክታል (ሮሜ 7፥2፡ 1ቆሮ 7፥39 ይመ)።
(3) በአዲስ ኪዳን የአማኝ መብት ከዚህ ያነሰ አይደለም። መፋታት አሳዛኝ ጉዳይ ቢሆንም፥ ለጋብቻ ታማኝ አለመሆን ደግሞ በትዳር ጓደኛ ላይ የሚፈጸም አሠቃቂ ኀጢአት ነው፥ ስለዚህ ተበዳይ ወገን ጋብቻውን በፍቺ ለማቋረጥ የሚያስችል ተገቢ መብት እንዳለው ክርስቶስ አስተምሮአል። እርሱ ወይም እርሷ ሌላ አማኝ እንደ ገና የማግባት ነጻነት አላቸው (1ቆሮ 7፥27-28)።
(4) ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 7፥12-16 ላይ አብሮ ስለ መቆየት፥ ስለ መለያየትም ጉዳይ፣ መፋታት የሚፈቀደው የማያምነው ወገን መለያየትን ከመረጠ ብቻ እንደ ሆነ ገልጿል። በተጨማሪም እንዲህ ዐይነት መለያየት ያጋጠመው አማኝ፣ ሌላ አማኝ እንደ ገና ቢያገባ ኀጢአት እንዳልሆነ አስተምሮአል (1ቆሮ 7፥15 እና ማብ፡ 7፥27-28 ይመ)።
**19፥13 ሕፃናትን፤** ማር 10፥16 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
**19፥21 ሄደህ ንብረትህን ሁሉ ሸጠህ፤** ጌታ ኢየሱስ ወጣቱን ባለጠጋ ደካማ ጐኑ በሆነው ማለትም በሀብቱ ፈተነው። ክርስቶስን ከሁሉ በላይ አስበልጦ ለማክበር አልፈለገም። የክርስቶስ ሐሳብ አማኞች ሁሉ ያላቸውን ንብረት መሸጥ አለባቸው የሚል ትርጉም አለውን? ፈጽሞ እንዲህ ማለት አይደለም፥ ስለ ቤተ ሰቦቻችንና ስለ ሌሎች ፍላጎት መጠንቀቅ ይኖርብናልና። ይሁን እንጂ ክርስቶስ ከእኛ የሚፈልገውን ማናቸውንም ነገር ለመስጠት ፈቃደኞች መሆን ይገባናል። ለእርሱ ያለን መስጠት ከዚህ ያነሰ ሊሆን አይገባም።
**19፥23 ለሀብታም ወደ መንግሥተ ሰማይ፤** በገጽ 1577 ላይ፣ "*ብልጽግናና ድህነት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።
**19፥29 መቶ ዕጥፍ ይቀበላል፤** ማር 10፥30 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።
**19፥30 ፊተኞች ኋለኞች፤** "ፊተኞች" የተባሉት በሀብታቸው፣ በትምህርታቸው፣ በማዕረጋቸው ወይም በችሎታቸው ምክንያት በዓለም አንዳንድ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ልዩ ክብር የተሰጣቸው ናቸው። "ኋለኞች"

## የወይን ቦታው ሠራተኞች ምሳሌ

20 "መንግሥተ ሰማይ ለወይኑ ቦታ
ሠራተኞችን ለመቅጠር ማልዶ
የወጣን የአትክልት ስፍራ ባለቤት
ትመስላለች። [2]በቀን አንዳንድ ዲናር
ሊከፍላቸው ከተስማሙ በኋላ ሠራተኞቹን
በወይኑ ቦታ አሰማራቸው።
[3]"ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመውጣት
ሥራ ፈትተው በገበያ ቦታ የቆሙትን ሌሎች
ሰዎች አግኝቶ፣ [4]'እናንተም ሄዳችሁ በወይኔ
ቦታ ሥሩ፤ ተገቢውን ክፍያ እሰጣችኋለሁ'
አላቸው፤ [5]እነርሱም ሄዱ።
"ከቀኑ በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት
ላይ ወጥቶ ሌሎች የቀን ሠራተኞችን
ቀጠረ። [6]ከሰዓት በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት
ገደማ ወጥቶ ቆመው የነበሩ ሌሎች ሰዎች
አገኘና፣ 'ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ እዚህ ለምን
ትቆማላችሁ?' በማለት ጠየቃቸው።
[7]"እነርሱም፣ 'የሚቀጥረን ሰው ስለ
አጣን ነው' አሉት።
እርሱም፣ 'እናንተም ሄዳችሁ በወይኔ
ቦታ ሥሩ' አላቸው።
[8]"በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት
ባለቤት የሠራተኞቹን ተቈጣጣሪ፣ 'ኋላ
ከመጡት ጀምረህ መጀመሪያ እስከመጡት
ድረስ ያሉትን ሠራተኞች በሙሉ ጥራና
ደመወዛቸውን ክፈላቸው' አለው።
[9]"በዐሥራ አንደኛው ሰዓት ገደማ
የተቀጠሩት ሠራተኞች ቀርበው፣ እያንዳንዳ
ቸው አንዳንድ ዲናር ተቀበሉ። [10]በመጀ
መሪያ የተቀጠሩት ሲቀርቡ ብልጫ ያለው
ክፍያ የሚያገኙ መስሎአቸው ነበር፤ ነገር
ግን እነርሱም አንዳንድ ዲናር ተከፈላ
ቸው። [11]ክፍያውን ሲቀበሉ በባለቤቱ ላይ
በማጕረምረም፣ [12]'እነዚህ በመጨረሻ
የተቀጠሩት አንድ ሰዓት ብቻ ሲሠሩ፣
ቀኑን ሙሉ በሥራ ስንደክምና በፀሐይ
ስንንቃቃ ከዋልነው ጋር እንዴት እኩል
ትከፍለናለህ?' አሉት።
[13]"እርሱም አንደኛውን ሠራተኛ
እንዲህ አለው፤ 'ወዳጄ ሆይ፤ በደል
አላደረስሁብህም፤ በአንድ ዲናር ለመሥራት
ከእኔ ጋር ተስማምተህ አልነበረምን? [14]በል
ድርሻህን ይዘህ ሂድ፤ ለአንተ የሰጠሁትን
ያህል በመጨረሻ ለመጣውም ሰው መስጠት
እፈልጋለሁ። [15]ታዲያ በራሴ ገንዘብ
የፈለግሁትን ማድረግ አልችልምን? ወይስ
ቸር በመሆኔ ምቀኝነት ያዘህን?'
[16]"ስለዚህ ኋለኞች ፊተኞች፣ ፊተኞችም
ኋለኞች ይሆናሉ።"

20፥1 ማቴ13፥24፤ 21፥28:33
20፥8 ዘሌ19፥13፤ ዘዳ24፥15
20፥11 ዮና4፥1
20፥12 ዮና4፥8፤ ሉቃ12፥55፤ ያዕ1፥11
20፥13 ማቴ22፥12፤ 26፥50
20፥15 ዘዳ15፥9፤ ማር7፥22
20፥16 ማቴ19፥30
20፥18 ማቴ8፥20፤ 27፥1:2፤ ሉቃ9፥51
20፥19 ማቴ16፥21፤ ሐዋ2፥23
20፥20 ማቴ4፥21፤ 8፥2
20፥21 ማቴ19፥28
20፥22 ኢሳ51፥17:22፤ ኤር49፥12፤ ማቴ26፥39:42፤ ማር14፥36፤ ሉቃ22፥42፤ ዮሐ18፥11
20፥23 ሐዋ12፥2፤ ራእ1፥9
20፥24 ሉቃ22፥24:25

## ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረ

*20፥17-19 ተጓ ምብ — ማር 10፥32-34፤ ሉቃ 18፥31-33*

[17]ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ
ሳለ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለብ
ቻቸው ወስዶ እንዲህ አላቸው፤ [18]"እንግዲህ
ወደ ኢየሩሳሌም መሄዳችን ነው፤ የሰው ልጅ
ለካህናት አለቆችና ለኦሪት ሕግ መምህራን
አልፎ ይሰጣል፤ እነርሱም እንዲሞት ይፈር
ዱበታል፤ [19]እንዲያላግጡበት፣ እንዲገርፉ
ትና እንዲሰቅሉት ለአሕዛብ አሳልፈው
ይሰጡታል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሞት
ይነሣል።"

## በጌታ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የማግኘት ጥያቄ

*20፥20-28 ተጓ ምብ — ማር 10፥35-45*

[20]ከዚያም፣ የዘብዴዎስ ልጆች እናት
ከልጆቿ ጋር ወደ ኢየሱስ ቀርባ በፊቱ
ተንበርክካ እየሰገደች፣ አንድ ነገር
እንዲያደርግ ላት ለመነችው።
[21]እርሱም፣ "ምን ትፈልጊያለሽ?"
አላት።
እርሷም፣ "እነዚህ ሁለት ልጆቼ፣ በመንግ
ሥትህ አንዱ በቀኝህ፣ አንዱ በግራህ
እንዲቀመጡ ፍቀድ" አለችው።
[22]ኢየሱስም፣ "የምትለምኑትን
አታውቁም፤ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ
ትችላላችሁን?" አላቸው።
እነርሱም፣ "እንችላለን" አሉት።
[23]እርሱም፣ "ከጽዋዬ በርግጥ
ትጠጣላችሁ፤ ነገር ግን በቀኜና በግራዬ
መቀመጥ አባቴ ላዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ
የምፈቅደው ነገር አይደለም" አላቸው።
[24]ሀሥሩም ይህንን በሰሙ ጊዜ፣ ሁለቱን
ወንድማማቾች ተቈጧቸው። [25]ኢየሱስም
አንድ ላይ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤
"የአሕዛብ ገዢዎች በሕዝባቸው ላይ
ጌቶች እንደሚሆኑ፣ ባለ ሥልጣኖቻቸውም
በኀይል እንደሚገዟቸው ታውቃላችሁ፤

---

የተባሉት ደግሞ የማይታወቁትና ይህን ያህል ጠቃሚ አይደሉም የሚባሉት ናቸው:: በሚመጣው ዘመን ታላላቅ መሪዎች እንዲሆኑ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሚሰጣቸው «ብዙዎች» ከሌሎች ቀጥሎ ሥልጣን ይሰጣቸዋል፤ የማይታወቁ ብዙዎች ደግሞ ለከበረ ሥልጣን ሲሾሙ ከፍ ከፍ ይላሉ (ከ1ቆሮ 15፥41-42 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ የሚሆንበት ምክንያት እግዚአብሔር ለሰዎች ዋጋ የሚሰጠው በውጫዊ ገጽታ ሳይሆን፣ በልባቸው ውስጥ ባለ ቅንነት፣ ንጽሕናና ፍቅር በመሆኑ ነው (1ሳሙ 16፥7):: ክርስቶስ ለትሑታን የሚሰጠውን ዋጋ ለማስተዋል፣ የድኻዪቱን መበለትና (ማር 12፥42-44) የቢታንያዋን ማርያምን (26፥7-13) ታሪክ ያንብቡ::

**20፥1 ለወይኑ ቦታ ሠራተኞችን፤** የወይን ቦታው ሠራተኞች ምሳሌ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ጕዳይ የበጎ ሥራ ውጤት ሳይሆን፤ እንዲሁ የተገኘ ስጦታ እንደ ሆነ ያስተምራል:: ክርስቶስ በዚህ ስፍራ ስለሚከተሉት ሦስት የተሳሰሩ አመለካከቶች ማስጠንቀቂያ በመስጠት አስተምሯል፡ (1) በተመቻቸ ሥልጣን ወይም ኀላፊነት ምክንያት የበላይነት ስሜት ሊኖር እንደማይገባ፣ (2) እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ጸጋውን ለመስጠት ያለውን ሐሳብ ሳያከፍሉ መቅረት ተገቢ እንዳልሆነ፣ (3) በሌሎች መንፈሳዊ በረከት መቅናት እንደማያስፈልግ::

26በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን
የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ
አገልጋያችሁ ይሁን፤ 27የበላይ ለመሆን
የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ 28የሰው
ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና
ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት
መጥቶአልና።"

## የሁለት ዐይነ ስውሮች መፈወስ

*20፥29-34 ተጓ ምብ — ማር 10፥46-52፤ ሉቃ 18፥35-43*

29ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ከኢያሪኮ
ወጥተው ሲሄዱ ብዙ ሕዝብ ተከተለው።
30በዚያም ሁለት ዐይነ ስውሮች በመንገድ
ዳር ተቀምጠው ነበር፤ ኢየሱስም በዚያ
ማለፉን ሲሰሙ፣ "ጌታ ሆይ፤ የዳዊት ልጅ
ማረን!" በማለት ጮኹ።
31ሕዝቡም በግሣጼ ቃል ዝም እንዲሉ
ነገሯቸው፤ እነርሱ ግን አምርረው በመጮኽ፣
"ጌታ ሆይ፤ የዳዊት ልጅ ማረን!" አሉ።
32ኢየሱስም ቆም ብሎ ጠራቸውና፣ "ምን
እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ?" አላቸው።
33እነርሱም፣ "ዐይኖቻችን እንዲያዩ
እንፈልጋለን" አሉት።
34ኢየሱስም ራራላቸው፤ ዐይኖቻቸውንም
ዳሰሰ፣ ወዲያው አዩ፤ ተከተሉትም።

## ኢየሱስ በታላቅ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

*21፥1-9 ተጓ ምብ — ማር 11፥1-10፤ ሉቃ 19፥29-38*
*21፥4-9 ተጓ ምብ — ዮሐ 12፥12-15*

21 ኢየሩሳሌም መቃረቢያ ደብረ
ዘይት ተራራ ላይ ወደምትገኘው
ቤተ ፋጌ ወደ ተባለችው ስፍራ እንደ
ደረሱ፣ ኢየሱስ ሁለት ደቀ መዛሙርት ላከ፤
2እንዲህ አላቸው "ባቅራቢያችሁ ወዳለው
መንደር ሂዱ፤ እንደ ደረሳችሁም አንዲት
አህያ ከነውርንጫዋ ታስራ ታገኛላችሁ፤
ፈትታችሁም ወደ እኔ አምጧቸው። 3ማንም
ሰው ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ ቢላችሁ፣
'ጌታ ይፈልጋቸዋል' በሉት፤ ወዲያውኑ
ይሰዳቸዋል።"
4ይህ የሆነውም በነቢዩ እንዲህ በማለት
የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው።
5"ለጽዮን ልጅ እንዲህ በሏት፤
'እነሆ፤ ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ፣
በአህያዪቱና በግልገሏ፣
በውርንጫዪቱም ላይ ተቀምጦ ወደ
አንቺ ይመጣል።' "
6ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ
እንዳዘዛቸው አደረጉ። 7አህያዪቱንና
ውርንጫዋን አምጥተው ልብሶቻቸውን
በላያቸው ላይ አኖሩ፤ እርሱም
ተቀመጠባቸው። 8ከሕዝቡም አብዛኛው
ልብሶቻቸውን፣ በመንገድ ላይ አነጠፉ፤
ሌሎቹም ከዛፎች ቅርንጫፍ እየዘነጠፉ
በመንገዱ ላይ ጣል ጣል አደረጉ። 9ቀድሞት
ከፊቱ የሚሄደውና ከኋላው ይከተለው የነበረው
ሕዝብም እንዲህ እያለ ይጮኽ ነበር፣
"ሆሣዕና^ለዳዊት ልጅ፤"
"በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ
ነው፤"
"ሆሣዕና በአርያም!"
10ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜም ከተማዋ
በመላ፣ "ይህ ማነው?" በማለት ታወከች።
11ሕዝቡም፣ "ይህ በገሊላ ከምትገኘው
ከናዝሬት የመጣው ነቢዩ ኢየሱስ ነው"
አሉ።

## ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲነግዱ ያገኛቸውን አስወጣቸው

*21፥12-16 ተጓ ምብ — ማር 11፥15-18፤ ሉቃ 19፥45-47*

12ከዚያም ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ
ገብቶ በቤተ መቅደስ ውስጥ ይሸጡና ይገዙ
የነበሩትን አባረራቸው፤ የገንዘብ ለዋጮ

20፥26 ማር9፥35
20፥28 ዘፀ30፥12፤ ኢሳ42፥1፤ 44፥22፤ 53፥10፤ ማቴ8፥20፤ 26፥28፤ ሉቃ12፥37፤ 22፥27፤ ዮሐ13፥13-16፤ 2ቆሮ8፥9፤ ፊል2፥7፤ 1ጢሞ2፥6፤ ቲቶ2፥14፤ ዕብ9፥28፤ 1ጴጥ1፥18፡19
20፥30 ማቴ9፥27
21፥1 ማቴ24፥3፤ 26፥30፤ ማር14፥26፤ ሉቃ19፥37፤ 21፥37፤ 22፥39፤ ዮሐ8፥1፤ ሐሥ1፥12
21፥4 ማቴ1፥22
21፥5 ኢሳ62፥11፤ ዘካ9፥9
21፥8 2ነገ9፥13
21፥9 ቍ15፤ መዝ118፥26፤ ማቴ9፥27፤ 23፥39፤ ሉቃ2፥14
21፥11 ዘዳ18፥15፤ ሉቃ7፥16፡39፤ 24፥19፤ ዮሐ1፥21፡25፤ 6፥14፤ 7፥40
21፥12 ዘፀ30፥13፤ ዘሌ1፥14፤ ዘዳ14፥26

^21፥9 በዕብራይስጡ አገላለጽ አሁን አድን ማለት ሲሆን የምስጋና አገላለጽ ነው፤ ቍ 15 ይመ

**20፥26 በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም፤** በዚህ ዓለም በሌሎች ላይ፣ «ጌቶች» እና «ባለሥልጣኖች» የሆኑት ታላላቅ ወንዶችና ሴቶች እንደ ሆኑ ይቈጠራሉ። በእግዚአብሔር መንግሥት ትልቅነት የሚለካው፣ ሥልጣንን በሌሎች ላይ በማሳየት ሳይሆን፣ ራስን ለአገልግሎት አሳልፎ በመስጠት እንደ ሆነ ኢየሱስ አስተምሮአል። አማኞች ሥልጣናቸውን ወይም አገዛዛቸውን ለማስከበር ሲሉ ሌሎችን በመጨቈን ከፍተኛ የሥልጣን ዕርከን ላይ መድረስ የለባቸውም። ይልቁንም ሌሎችን በመርዳት ለሰዎች ሁሉ መንፈሳዊ እድገት እውን ይሆን ዘንድ ሕይወታቸውን መስጠት አለባቸው (ቍ 28 ይመ፤ ከዮሐ 13፥34፤ ከ1ቆሮ 13፤ ከቈላ 3፥14፤ ከ1ዮሐ 3፥14፤ 4፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።
**20፥28 ለብዙዎች ቤዛ፤** ቤዛ የሚለው ቃል ሌሎች ነጻነትን ያገኙ ዘንድ የተከፈለ ዋጋን ያመለክታል። በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ፣ የክርስቶስ ሞት ዋጋ በመሆን ወንዶችና ሴቶች ከኀጢአት ባርነት ነጻ ይወጡ ዘንድ ዋጋ ሆኖ ተከፍሎአል (በገጽ 1736 ላይ፣ «*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ነጻ የወጡት ከፍርድ (ሮሜ 3፥25-26)፤ ከኀጢአትና (ኤፌ 1፥7) ከሞት (ሮሜ 8፥2) ነው። «ለብዙዎች» የሚለው ሐረግ «ለሰዎች ሁሉ» ማለት ነው (1ጢሞ 2፥5-6 ይመ፤ ሮሜ 3፥25 እና ስለ ክርስቶስ መስቀል የተሰጠውን ማብ ይመ)።
**21፥12 ኢየሱስ ... ጠረጴዛና ... በመገልበበ፤** ይህ ጊዜ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ በመግባት፣ ቤተ መቅደሱን ከርኩሰት ያነጻበት ሁለተኛ ጊዜ ነው (በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ቤተ መቅደሱን ስለ ማንጻቱ ሉቃ 19፥45 እና ማብ፤ ዮሐ 2፥13-22 ይመ)። በእግዚአብሔር ቤት የሚታይ ግብዝነት፣ ስግብግብነት፣ ራስን የማገልገል ምኞት፣ ኢግብረገባዊነትና እግዚአብሔርን አለመፍራት የእግዚአብሔርን ፍርድና የጽድቅ ቍጣ እንደሚያመጣ የክርስቶስን ስም የተሸከሙ ሁሉ ሊያውቁ ይገባል። ክርስቶስ በደሙ ለዋጀት ቤተ ክርስቲያን ጌታ ነው፤ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን «የጸሎት ቤት» እንድትሆን ይፈልጋል (ቍ 13)።

ችን ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መቀመጫ
በመገለባበጥ፣ [13]"'ቤቴ የጸሎት ቤት
ይባላል' ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን፣
'የዘራፊዎች ዋሻ' አደረጋችሁት" አላቸው።
[14]በቤተ መቅደሱም ውስጥ ዐይነ
ስውሮችና ሽባዎች ወደ እርሱ ቀረቡ፤
እርሱም ፈወሳቸው። [15]ነገር ግን የካህናት
አለቆችና የኦሪት ሕግ መምህራን
ያደረጋቸውን ታምራትና፣ "ሆሣዕና፤
ለዳዊት ልጅ" እያሉ የሚጮኹትን ሕፃናት
ባዩ ጊዜ በቍጣ ተሞሉ።
[16]እነርሱም፣ "እነዚህ ሕፃናት የሚሉትን
ትሰማለህ" አሉት።
ኢየሱስም፣ "አዎን እሰማለሁ፤ እንዲህ
ሉቃ የሚለውን ከቶ አላነበባችሁምን?"
1፡42- "'ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ፣
47 ሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ፡' "
[17]ትቶአቸው ከከተማው ወጣ፤ ወደ
ቢታንያም ሄዶ በዚያው አደረ።

## ፍሬ አልባ የሆነችው በለስ

*21፡18-22 ተጓ ምብ — ማር 11፡12-14:20-24*

[18]ኢየሱስ በማግስቱ ማለዳ ወደ
ከተማዪቱ በመመለስ ላይ ሳለ ተራበ፤
[19]በመንገድ ዳርም አንድ የበለስ ዛፍ አይቶ
ወደ እርሷ ሲሄድ ከቅጠል በስተቀር ምንም
ስላላገኘባት፣ "ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ!"
አላት፤ የበለሷ ዛፍ ወዲያውኑ ደረቀች።
[20]ደቀ መዛሙርቱም የሆነውን አይተው
በመደነቅ፣ "የበለሷ ዛፍ እንዴት ባንዴ
ልትደርቅ ቻለች?" አሉ።
[21]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ እምነት ቢኖራችሁ
ባትጠራጠሩ፣ በበለሷ ዛፍ ላይ የሆነውን
ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ተራራ፣
'ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ' ብትሉት
ማር እንኳ ይሆናል፤ [22]እምነት ካላችሁ በጸሎት
4፡40 የም ትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ።"

## በኢየሱስ ሥልጣን ላይ የቀረበ ጥያቄ

*21፡23-27 ተጓ ምብ — ማር 11፡27-33፤ ሉቃ 20፡1-8*

[23]ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ
በማስተማር ላይ ሳለ፣ የካህናት አለቆችና
የሕዝብ ሽማግሌዎች ቀርበው፣ "ይህን ሁሉ
ነገር የምታደርገው በምን ሥልጣን ነው?
ሥልጣኑንስ የሰጠህ ማን ነው?" ብለው
ጠየቁት።

21፡13 ኢሳ56፡7፤ ኤር7፡11
21፡14 ማቴ4፡23
21፡15 ቍ9፤ ማቴ9፡27፤ ሉቃ19፡39
21፡16 መዝ8፡2
21፡17 ማቴ26፡6፤ ማር11፡1፤ ሉቃ24፡50፤ ዮሐ11፡1:18፤ 12፡1
21፡19 ኢሳ34፡4፤ ኤር8፡13
21፡21 ማቴ17፡20፤ ሉቃ17፡6፤ 1ቆሮ13፡2፤ ያዕ1፡6
21፡22 ማቴ7፡7
21፡23 ሐሥ4፡7፤ 7፡27
21፡26 ማቴ11፡9
21፡28 ቍ33፤ ማቴ20፡1
21፡31 ሉቃ7፡29:50
21፡32 ማቴ3፡1-12፤ ሉቃ3፡12:13፤ 7፡29:30:36-50
21፡33 መዝ80፡8፤ ኢሳ5፡1-7፤ ማቴ25፡14:15

[24]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እኔም አንድ ጥያቄ እጠይቃችኋለሁ፤
መልሱን ብትነግሩኝ፣ እኔም እነዚህን ነገሮች
በምን ሥልጣን እንደማደርግ እነግራችኋለሁ፤
[25]የዮሐንስ ጥምቀት የመጣው
ከየት ነበር? ከሰማይ ወይስ ከሰዎች?"
እነርሱም እርስ በርስ በመነጋገር እንዲህ
ተባባሉ፤ 'ከሰማይ ነው?' ካልን 'ታዲያ
ለምን አላመናችሁበትም?' ይለናል፤ [26]'ከሰ
ዎች ነው' ካልን ደግሞ፣ 'ሕዝቡ ዮሐንስን
ነቢይ ነው' ብሎ ስለሚያምን እንፈራለን።"
[27]ስለዚህ፣ "አናውቅም" ብለው ለኢየሱስ
መለሱለት።
እርሱም፣ "እኔም እነዚህን ነገሮች በምን
ሥልጣን እንደማደርግ አልነግራችሁም"
አላቸው።

## የመታዘዝ ትርጕም

[28]ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ምን
ይመስላችኋል? ሁለት ወንዶች ልጆች
ያሉት አንድ ሰው ነበረ፤ ወደ መጀመሪያው
ልጁ ሄዶ፣ 'ልጄ ሆይ፤ ዛሬ ወደ ወይኑ ቦታ
ሄደህ ሥራ' አለው።
[29]"ልጁም፣ 'አልሄድም' አለው፤ ኋላ ግን
ተጸጽቶ ሄደ።
[30]"ወደ ሁለተኛው ልጁ ሄዶ እንደዚያው
አለው፤ ልጁም 'እሺ ጌታዬ እሄዳለሁ'
አለው፤ ነገር ግን ሳይሄድ ቀረ።
[31]"ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው
የትኛው ነው?"
እነርሱም፣ "የመጀመሪያው ልጅ"
አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና
አመንዝራዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
በመግባት ይቀድሟችኋል፤ [32]መጥምቁ
ዮሐንስ የጽድቅን መንገድ ሊያሳያችሁ ወደ
እናንተ መጣ፤ እናንተ አላመናችሁትም፤
ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝራዎች ግን
አመኑት። የሆነውን ካያችሁ በኋላ እንኳ
ንስሓ ገብታችሁ አላመናችሁትም።

## የወይን ዕርሻ ገበሬዎች ምሳሌ

*21፡33-46 ተጓ ምብ — ማር 12፡1-12፤ ሉቃ 20፡9-19*

[33]"ሌላም ምሳሌ ስሙ፤ አንድ የወይን
ዕርሻ ባለቤት ነበረ፤ በዕርሻው ዙሪያ አጥር
አጠረ፤ ለወይኑ መጭመቂያ ጕድጓድ

**21፡13 የጸሎት ቤት፤** ማር 11፡17 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**21፡21 እምነት ቢኖራችሁ፤** ኢየሱስ በዚህ ስፍራ ስለ እምነትና ስለ ጸሎት ይናገራል (ቍ 22)፤ ይኸውም የምናገኘው የጸሎት መልስ ከእምነታችን ጋር የተያያዘ መሆኑን ያመለክታል። የማይጠራጠሩት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማውን ሁሉ ቢጠይቁ፣ የለመኑት ሊፈጸምላቸው ወይም ሊሰጣቸው ይችላል (17፡20 እና ማብ፤ ማር 11፡24 እና ማብ ይመ፤ ከ1ነገ 17፡1:7፤ 18፡42-45፤ ከሉቃ 17፡5-6 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 528 ላይ፣ "መልስ የሚያስገኝ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። በዚህ መንገድ የቀረበው የጸሎት መልስ ብቸኛው የጸሎት መልስ መንገድ ይህ ነው የሚል ሐሳብ አይሰጥም (ለምሳሌ ዳን 10፡12-14፤ ያዕ 4፡3 ይመ)።

**21፡33-44 ገበሬዎቹ፤** ከቍ 33-44 የተገለጸው ይህ ምሳሌ እስራኤል የእግዚአብሔርን አንድያ ልጅ ያልተቀበለች መሆኗን ያመለክታል (ከማር 12፡1 እና ማብ፤ ከሉቃ 20፡9 ጋር ያነጻጽሩ)።

ቈፈረ፤ ለጥበቃ የሚሆን ማማ ሠራ፤
ከዚያም ዕርሻውን ለገበሬዎች አከራይቶ
ወደ ሌላ አገር ሄደ። 34የመከር ወራት
ሲደርስ፣ ፍሬውን ለመቀበል አገልጋዮቹን
ወደ ገበሬዎቹ ላካቸው።
35"ገበሬዎቹም አገልጋዮቹን ይዘው
አንዱን ደበደቡት፤ ሌላውን ገደሉት፤
ሌላውን ደግሞ በድንጋይ ወገሩት።
36እርሱም ከፊተኞቹ የሚበልጡ ሌሎች
አገልጋዮቹን ላከ፤ ገበሬዎቹም ተመሳሳይ
ድርጊት ፈጸሙባቸው። 37በመጨረሻም፣
'ልጄን ያከብሩታል' በማለት ልጁን ላከ።
38"ነገር ግን ገበሬዎቹ ልጁን ባዩት
ጊዜ፣ 'ይህማ ወራሹ ነው፤ ኑ፣ እንግደለውና
ርስቱን እንውረስ' ተባባሉ። 39ይዘውም ከወ
ይኑ ዕርሻ ውጭ አውጥተው ገደሉት።
40"ታዲያ የወይኑ ዕርሻ ባለቤት ሲመጣ
እነዚያን ገበሬዎች ምን የሚያደርጋቸው
ይመስላችኋል?"
41እነርሱም፣ "እነዚያን ክፉዎች በአሰቃቂ
ሁኔታ ገድሎ ከወይኑ ዕርሻ ተገቢውን ፍሬ
በወቅቱ ለሚያስረክቡት ለሌሎች ገበሬዎች
ያከራያል" አሉት።
42ኢየሱስም እንዲህ ተብሎ
በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን
አላነበባችሁምን?አላቸው፤
" 'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
የማእዘን ራስ[ፐ] ሆነ፤
እግዚአብሔር ይህን አድርጎአል፤
ሥራውም ለዐይናችን ድንቅ ነው።'
43"ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬዋን
ለሚያፈራ ሕዝብ ትሰጣለች፤ 44በዚህ
ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይሰባበራል፤ ድንጋዩ
የሚወድቅበት ሰው ግን ይደቅቃል።"[ሀ]
45የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን
ምሳሌዎቹን በሰሙ ጊዜ፣ ስለ እነርሱ
የሚናገር መሆኑን ዐወቁ። 46ነገር ግን ይዘው
ሊያስሩት ቢፈልጉም ሕዝቡ ኢየሱስን እንደ
ነቢይ አድርጎ ይመለከት ስለ ነበር ፈሩ።

21፥34 ማቴ22፥3
21፥35
2ዜና24፥21፤
ማቴ23፥34፡37፤
ዕብ11፥36፡37
21፥36 ማቴ22፥4
21፥38 መዝ2፥8፤
ማቴ12፥14፤
ዕብ1፥2
21፥41
ማቴ8፥11፡12፤
ሐሥ13፥46
21፥42
መዝ118፥22፡23፤
ሐሥ4፥11
21፥43 ማቴ8፥12
21፥44 ሉቃ2፥34
21፥46 ቍ11፡26
22፥2 ማቴ13፥24
22፥3 ማቴ21፥34
22፥4 ማቴ21፥36
22፥7 ሉቃ19፥27
22፥9 ሕዝ21፥21
22፥10
ማቴ13፥4፤ 7፡48
22፥12
ማቴ20፥13፤
26፥50
22፥13 ማቴ8፥12
22፥14 ራእ17፥14

## በሰርግ ድግስ ላይ የተጠሩ ሰዎች ምሳሌ

*22፥2-14 ተጓ ምብ — ሉቃ 14፥16-24*

22 ኢየሱስም እንደ ገና እንዲህ የሚል
ምሳሌ ነገራቸው፤ 2"መንግሥተ
ሰማይ ለልጁ ሰርግ የደገሰ ንጉሥ
ትመስላለች፤ 3ንጉሡም የተጋበዙትን ሰዎች
እንዲጠሩ አገልጋዮቹን ላከ፤ እነርሱ ግን
አንመጣም አሉ።
4"እንደ ገናም ሌሎች አገልጋዮች ልኮ፣
'የተጋበዙትን፣ እነሆ፣ በሬዎችንና የሰቡ
ከብቶቼን አርጄ ድግሱን አዘጋጅቻለሁ፤
ሁሉም ነገር ዝግጁ ስለሆነ ወደ ሰርጉ ኑ
በሏቸው' አለ።
5"ተጋባዦቹ ግን ጥሪውን ችላ ብለው፣
አንዱ ወደ ዕርሻው ሌላው ወደ ንግዱ ሄደ፤
6የቀሩትም አገልጋዮቹን በመያዝ አንገላ
ተው ገደሏቸው። 7ንጉሡም በመቈጣት
ሠራዊቱን ልኮ ገዳዮቻቸውን አጠፋ፤
ከተማቸውንም አቃጠለ።
8"ከዚያም አገልጋዮቹን እንዲህ
አላቸው፤ 'የሰርጉ ድግስ ዝግጁ ነው፤
ነገር ግን የተ ጋበዙት የሚገባቸው ሆነው
ስላልተገኙ፣ 9ወደ መንገድ መተላለፊያ
ወጥታችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ
ድግስ ጥሩ።' 10አገልጋዮቹም ወደ መንገድ
ወጥተው ያገኙትን መልካሙንም ክፉውንም
ሁሉ ሰብስበው የሰርጉን አዳራሽ በእንግዶች
ሞሉት።
11"ንጉሡም የተጋበዙትን እንግዶች
ለማየት ሲገባ፣ አንድ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ
ሰው አየ፤ 12እንዲህም አለው፤ 'ወዳጄ ሆይ፤
የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት እዚህ
ልትገባ ቻልህ?' ሰውየው ግን የሚመልሰው
ቃል አልነበረውም።
13"ንጉሡም አገልጋዮቹን፣ 'እጅና
እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ
አውጥታችሁ ጣሉት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል' አላቸው፤ 14የተጠሩት

[ፐ]21፥42 ወይም የማእዘን ድንጋይ
[ሀ]21፥44 አንዳንድ ቅጆች ቍጥር 44 የላቸውም

21፥43 **የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ፤** እስራኤል መሲሑንና መንግሥቱን ተቃወመች። ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር መንግሥትና ኀይሉ፣ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ወንጌሉን ለተቀበሉ ለሌሎች ዐልፎ ተሰጠ (1ጴጥ 2፥9)። ይህ መርሕ አሁንም ይሠራል። የጽድቅ መንገዱን ባለመቀበል (ሮሜ 11፥19-22) ለክርስቶስ ታማኝ ሳይሆኑ ከቀሩት ላይ የእግዚአብሔር መንግሥትና ኀይሉ ተነጥቀው ይወሰዳሉ፤ በእነዚህ ፈንታ ግን ራሳቸውን ከዓለም በመለየት መንግሥቱንና ጽድቁን አስቀድመው ለሚሹ ሰዎች ይሰጣሉ (5፥6፤ 6፥33 ይመ)።

21፥44 **ይሰባበራል፤** ሉቃ 20፥18 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

22፥11 **የሰርግ ልብስ፤** በምድር የእግዚአብሔር መንግሥት አባላት ነን የሚሉ ብዙዎች የሰርግ ልብስ አይለብሱም፤ ስለዚህም ከተመረጡት መካከል አይደሉም (ቍ 14)። «የሰርግ ልብስ» የሚወክለው የዝግጁነትን ሁኔታ ነው፤ ይኸውም በክርስቶስ ላይ ያለው እውነተኛ እምነት አሁን የሚገኝበትን ደረጃ የሚያሳይ ሲሆን፤ በክርስቶስ ጋ በቀጣይነት ሊገለጥ የሚችለውን መታዘዝንም ይጨምራል (ከ24፥44፤ ከ25፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ራሳችንን እንድንመረምርና «ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆንን?» ብለን እንድንጠይቅ ለማድረግ፣ ክርስቶስ የሰርግ ልብስ ስላልለበሰው ሰው በዚህ ስፍራ ይናገራል።

22፥14 **የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸውና፤** የድነት ጥሪ ለብዙዎች ነው፤ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ በመስጠት፣ ኀጢአታቸውን በመናዘዝና ክርስቶስን በማመን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲወርሱ የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው። በራሳችን ፈቃድ በነጻነት ለእግዚአብሔር ጸጋ የምንሰጠው ምላሽ የተመረጠ ሕዝብ እንድንሆን ያደርገናል (በገጽ 1860 ላይ፣ *«ምርጫና አስቀድሞ መወሰን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ብዙዎች፣ የተመረጡት ግን ጥቂቶች
ናቸውና።"

## ግብር ስለ መክፈል

*22፥15-22 ተጓ ምብ — ማር 12፥13-17፤*
*ሉቃ 20፥20-26*

15ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ወጥተው በመሄድ
በአፍ እላፊ እንዴት እንደሚያጠምዱት
ተማከሩ። 16ደቀ መዛሙርታቸውን ከሄሮድስ
ወገኖች ጋር ወደ እርሱ ልከው እንዲህ
አሉት፤ "መምህር ሆይ፤ አንተ እውነተኛና
የእግዚአብሔርንም መንገድ በእውነት
የምታስተምር እንደ ሆንህ፣ ለማንም
ሳታዳላ ሁሉን በእኩልነት እንደምትመለከት
እናውቃለን፤ 17ንገረን፤ ምን ይመስልሃል?
ለመሆኑ ለቄሣር ግብር መክፈል ይገባል
ወይስ አይገባም?"
18ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን በመረዳት
እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ ግብዞች ለምን
በነገር ልታጠምዱኝ ትሻላችሁ? 19ለግብር
የሚከፈለውን ገንዘብ እስቲ አሳዩኝ።"
እነርሱም አንድ ዲናር አመጡለት።
20እርሱም፣ "በዚህ ገንዘብ ላይ የሚታየው
መልክ የማን ነው? ጽሕፈቱስ የማን ነው?"
አላቸው።
21እነርሱም፣ "የቄሣር ነው" አሉት።
እርሱም መልሶ፣ "እንግዲያውስ የቄሣርን
ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ"
አላቸው።
22ይህን ሲሰሙ ተደነቁ፤ ትተውትም
ሄዱ።

## ስለ ሙታን ትንሣኤ

*22፥23-33 ተጓ ምብ — ማር 12፥18-27፤*
*ሉቃ 20፥27-40*

23የሙታን ትንሣኤ የለም ብለው
የሚያምኑ ሰዱቃውያን በዚያኑ ቀን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ ብለው ጠየቁት፤
24"መምህር ሆይ፤ ሙሴ፣ 'አንድ ሰው
ከሚስቱ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ
የሚቱን ሚስት አግብቶ ለእርሱ ዘር ይተ
ካለት' ብሎአል። 25በእኛ ዘንድ ሰባት
ወንድማማቾች ነበሩ፤ የመጀመሪያው
ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ በመሞቱ፣
ሚስቱን ወንድሙ አገባት፤ 26ሁለተኛውም
ለመጀመሪያ ወንድሙ እንዲሁ ልጅ ሳይፈራ
ሞተ፤ በዚህ ሁኔታ ሴትዮዋ ለሰባተኛው
ወንድሙ ደረሰችው። 27በመጨረሻ ሴትዮዋ
ራሷ ሞተች። 28ስለዚህ ሁሉም ስላገቧት
በትንሣኤ ቀን ከሰባቱ ለየትኛው ሚስት
ትሆናለች?"
29ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፤ "ቅዱ
ሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል
ስለማታውቁ ትስታላችሁ፤ 30ከትንሣኤ
በኋላ ሰዎች እንደ ሰማይ መላእክት ይሆናሉ
እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡም። 31ስለ ሙታን
ትንሣኤ ግን እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ
የተናገራችሁን አላነበባችሁምን? 32'እኔ
የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣
የያዕቆብ አምላክ ነኝ።' እግዚአብሔር የሕያዋን
እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም።
33ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ በትምህርቱ
ተደነቁ።

## ታላቁ ትእዛዝ

*22፥34-40 ተጓ ምብ — ማር 12፥28-31*

34ኢየሱስ ሰዱቃውያንን ዝም
እንዳሰኛቸው ሰምተው፣ ፈሪሳውያን
በአንድነት ተሰበሰቡ፤ 35ከእነርሱም አንድ
የኦሪት ሕግ አዋቂ፣ ሊፈትነው ፈልጎ
እንዲህ አለው፤ 36"መምህር ሆይ፤ ከሕግ
ሁሉ የሚበልጠው የትኛው ትእዛዝ ነው?"
37እርሱም እንዲህ አለው፤ "'ጌታ
አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣
በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤' 38ይህ የመጀመሪያ
ውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤
39ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣
'ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ' የሚለው

22፥16 ማር3፥6
22፥17 ማቴ17፥25
22፥21 ሮሜ13፥7
22፥22 ማር12፥12
22፥23 ሐሥ4፥1፤ 23፥8፤ 1ቆሮ15፥12
22፥24 ዘዳ25፥5-6
22፥29 ማቴ24፥38
22፥32 ዘፀ3፥6፤ ሐሥ7፥32
22፥33 ማቴ7፥28
22፥34 ሐሥ4፥1
22፥35 ሉቃ7፥30፤ 10፥25፤ 11፥45፤ 14፥3
22፥37 ዘዳ6፥5
22፥39 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43

---

**22፥30 ሰዎች ... አያገቡም፤ አይጋቡም፤** ማር 12፥25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**22፥35 የኦሪት ሕግ ዐዋቂ፤** የኦሪት ሕግ ዐዋቂ (በግሪክ ቋንቋ፣ "ኖሚኮስ") የሙሴን ሕግ የሚተረጕምና የሚያስተምር ሰው ነው።

**22፥37 ጌታ አምላክህን ... ውደድ፤** በክርስቶስ ከሚያምኑትና በእርሱ በኩል የተገኘውን ድነት ከተቀበሉት ሁሉ እግዚአብሔር የሚጠይቀው እጅግ ታላቅ የሆነ ፍቅርን ነው (ከዘዳ 6፥5፣ ከሮሜ 13፥9-10፤ ከ1ቆሮ 13 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) እንዲህ ዐይነቱ ፍቅር እግዚአብሔር የሚከበርበትና ከፍ ከፍ የሚልበት የልብ ዝንባሌ ይኖረን ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግን የምንናፍቅበትን፣ እርሱን ለመታዘዝ የምንጥርበትን እንዲሁም በምድር ላይ የእርሱን ፈቃድና ክብር በቅንነት የምንጠብቅበትን ሁኔታ ይጠይቃል። እግዚአብሔርን በእውነት የሚወዱ በሥቃዩ ለመካፈል ይፈልጋሉ (ፊል 3፥10)፤ መንግሥቱን ያስፋፋሉ (1ቆሮ 9፥23)፤ እንዲሁም በምድር ላይ ለክብሩና ለጻድቅ መንግዱ ይኖራሉ (6፥9-10፥33)።

(2) ለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባ ፍቅር በሙሉ ልብ የሚገለጽና የላቀ ፍቅር መሆን አለበት፤ ይኸውም እግዚአብሔር ልጁን ለእኛ በሰጠበት ፍቅር የሚገዛ ፍቅር ነው (ዮሐ 3፥16 እና ማብ፤ ሮሜ 8፥32 ይመ)። ሊኖረን የሚገባ ፍቅርም በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ተገልጾአል፤ ሮሜ 12፥1-2፤ 1ቆሮ 6፥20፤ 10፥31፤ 2ቆሮ 9፥15፤ ኤፌ 4፥30፤ 5፥1-2፤ ቈላ 3፥12-17።

(3) ለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባ ፍቅር የሚከተሉትን ያካትታል፤ (ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር በታማኝነትና በመገዛት ላይ የተመሠረተ የግል ግንኙነት ሊኖረን የሚገባ መሆኑን፤ (ለ) የአባትና የልጅ ግንኙነቱ አንድነትን ባገኘንበት አምላክ በጽናትና በማይወላውል ታዛዥነት ማመን የሚያስፈልግ መሆኑን፤ (ሐ) ለእርሱ ላለን ታማኝነት በጽኑ መቆም ያለብን መሆኑን፤ (መ) እግዚአብሔርን በሚቃወም ዓለም መካከል ለክርስቶስ የጽድቅ መስፈርቶች ራስን አሳልፎ በመስጠት በተገለጸ ልባዊ ቍርጠኝነት መኖርን፤ (ሠ) ህልዎቱንና ኅብረቱን አጥብቆ መሻትን።

**22፥39 ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ፤**

ነው፤ 40ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት
ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።"

## ክርስቶስ የማን ልጅ ነው?

*22፥41-46 ተጓ ምብ — ማር 12፥35-37፤*
*ሉቃ 20፥41-44*

41ፈሪሳውያን ተሰብስበው ሳሉ ኢየሱስ፣
እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ 42"ስለ ክርስቶስ[a]
ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?"
እነርሱም፣ "የዳዊት ልጅ ነው" አሉት።
43እርሱም እንዲህ አላቸው፤ "ታዲያ፣
ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ለምን 'ጌታዬ'
ይለዋል? ለምንስ፣ እንዲህ ይለዋል?
44"'ጌታ ጌታዬን፤
ጠላቶችህን ከእግርህ በታች
እስካንበረክክልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ።" '
45ስለዚህ ዳዊት፣ 'ጌታዬ' ብሎ ከጠራው፣
እንዴት ልጁ ሊሆን ይችላል?" 46አንድ ቃል
ሊመልስለት የቻለ ወይም ከዚያን ቀን ጀምሮ
ሊጠይቀው የደፈረ ማንም አልነበረም።

## ኢየሱስ ፈሪሳውያንንና የኦሪት ሕግ መምህራንን ነቀፈ

*23፥1-7 ተጓ ምብ — ማር 12፥38፡39፤*
*ሉቃ 20፥45-46*
*23፥37-39 ተጓ ምብ — ሉቃ 13፥34፡35*

23 ከዚያም ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ
መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤
2"የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን
በሙሴ ወንበር ላይ ተቀምጠዋል። 3ስለዚህ
የሚነግሯችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ጠብቁትም፤
ነገር ግን እንደሚናገሩት አያደርጉምና
ተግባራቸውን አትከተሉ። 4እንዲሁም
ለመሸከም የማይቻል ከባድ ሸክም አስረው
በሰዎች ትከሻ ላይ ይጭናሉ፤ ራሳቸው ግን
በጣታቸው እንኳ አይነኩትም።
5"ለመታየት ሲሉ የሚያደርጉትን ሁሉ
በሰው ፊት ያደርጋሉ፤ አሸንክታባቸውን[b]
ያሰፋሉ፤ የቀሚሳቸውን ዘርፍ ያስረዝማሉ።
6በግብዣ ቦታ የከበሬታ ስፍራ፣ በምኵራብም
የመጀመሪያውን መቀመጫ መያዝ ይወዳሉ።
7እንዲሁም በገበያ መካከል ሰላምታ
መቀበልንና በሰዎች አንደበት 'መምህር'
ተብለው መጠራትን ይሻሉ።
8"እናንተ ግን 'መምህር' ተብላችሁ
አትጠሩ፤ አስተማሪያችሁ አንድ ብቻ
ሲሆን፣ እናንተ ሁላችሁም ወንድማማቾች
ናችሁና። 9በሰማይ ያለ አንድ አባት
ስላላችሁ፣ በምድር ማንንም 'አባት' ብላችሁ
አትጥሩ። 10መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ
ስለሆነ፣ 'መምህር' ተብላችሁ አትጠሩ።
11ከመካከላችሁ ከሁላችሁ የሚበልጠው
አገልጋያችሁ ይሆናል፤ 12ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ይዋረዳል፤ ራሱን የሚያዋርድ
ግን ይከበራል።
13"እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ

22፥40 ማቴ7፥12፤ ሉቃ10፥25-28
22፥42 ማቴ9፥27
22፥44 ነገ15፥3፤ መዝ110፥1፤ ሐሥ2፥34፡35፤ 1ቆሮ15፥25፤ ዕብ1፥13፤ 10፥13
22፥46 ማር12፥34፤ ሉቃ20፥40
23፥2 ዕዝ7፥6፡25
23፥4 ሉቃ11፥46፤ ሐሥ15፥10፤ ገላ6፥13
23፥5 ዘፀ13፥9፤ ዘኍ15፥38፤ ዘዳ6፥8፤ 22፥12፤ ማቴ6፥1፡2፡5፡16
23፥6 ሉቃ11፥43፤ 14፥7፤ 20፥46
23፥7 ቍ 8፤ ማቴ26፥25፡49፤ ማር9፥5፤ 10፥51፤ ዮሐ1፥38፡49፤ 3፥2፡26፤ 20፥16
23፥9 ሚል1፥6፤ ማቴ6፥9፤ 7፥11
23፥11 ማር9፥35
23፥12 1ሳሙ2፥8፤ መዝ18፥27፤ ምሳ3፥34፤ ኢሳ57፥15፤ ሕዝ21፥26፤ ሉቃ1፥52፤ 14፥11
23፥13 ቍ 15፡23፡25፡27፡29፤ ሉቃ11፥52

[a] 22፥42 ወይም መሲሑ
[b] 23፥5 ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ጥቅሶች የተጻፉበት በግንባርና በክንድ ላይ የሚታሰር ትንሽ ጥቅልል ነው

የእግዚአብሔር ልጆች ሰውን ሁሉ (ከገላ 6፥10፤ ከ1ተሰ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ) ጠላቶቻቸውንም ጭምር (5፥44) የመውደድ ግዴታ አለባቸው። እንዲሁም በእውነት ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖችን ሁሉ ልዩ በሆነ መንገድ እንዲወዱ ታዘዋል (ዮሐ 13፥34 እና ማብ፡ ገላ 6፥10 ይመ፤ ከ1ተሰ 3፥12፤ ከ1ዮሐ 3፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) አማኞች ለክርስቲያን ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው፣ ለጎረቤቶቻቸውና ለጠላቶቻቸው ያላቸው ፍቅር ለእግዚአብሔር ሊኖራቸው በሚገባ ፍቅርና መስጠት ሊገዛ፤ በዚህም ፍቅር ቍጥጥር ሥር ሊሆንና ሊመራ ይገባል። (2) ለእግዚአብሔር ሊኖረን የሚገባ ፍቅር "የመጀመሪያውና ታላቁ ትእዛዝ" (ቍ 37-38) ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቅድስና፣ እርሱም ለንጽሕና ያለው መሻት፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተገለጠው ፈቃዱና መስፈርቱ ለሰው ሁሉ በምናሳየው ፍቅር ፈጽሞ ሊመቻመቹ አይገባም።

**23፥13 ፈሪሳውያን ... ወዮላችሁ፤** በምዕራፍ 23 ላይ የተገለጹት የኢየሱስ ቃላት እጅግ ከባድ የሆነ ውግዘትን ያዘሉ ናቸው። በዚህ ስፍራ የተገለጹት ቃላት የተገለጠውን ከፊል የእግዚአብሔር ቃል በመቃወም የራሳቸውን ሐሳብና ትርጓሜ ተክተው ሲያስተምሩ በነበሩ የሃይማኖት መሪዎችና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ላይ የተሰነዘሩ ነበሩ (ቍ 23፡28፤ 15፥3፡6–9፤ ማር 7፥6-9)። (1) የኢየሱስን መንፈስ ማስተዋል ይገባል። ይህ መንፈስ ሁሉን በዝምታ የሚያልፍ፣ ሁሉን እንዲሁ የሚቀበልና እንደዚሁም ለእግዚአብሔርና ለቃሉ መኖር ስለሚገባ ታማኝነት ግድየለሽና ልል የሆነ ሰው መንፈስ ዐይነት አይደለም፤ ኢየሱስ ኀጢአትን ታግሦ የሚያልፍ ደካማ ሰባኪ አልነበረም። ለጥሪው ታማኝ በመሆኑ በክፋት ላይ ቍጣውን ገለጸ (ከ21፥12-17፤ ከዮሐ 2፥13-16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ዘንድ የሚታየውን ኀጢአትና ርኩሰትም አወገዘ (ቍ 23፡25)።

(2) ኢየሱስ ከአባቱ እስትንፋስ የተገኙትን ቅዱሳት መጻሕፍት ከመውደዱና የአባቱ ቃል ከመጣመሙ የተነሣ ስለ ተጐዱት ሰዎች በማዘኑ የሚከተሉትን ብርቱ ሐሳብ ያለባቸውን ቃሎችና ሐረጐች ለመናገር ተገድዶአል (15፥2-3፤ 18፥6-7፤ 23፥13፡15) "ግብዞች" (ቍ 15)፤ "የገሃነም ልጅ" (ቍ 15)፣ "ዕውር መሪዎች" (ቍ 16)፣ "ተላላዎች" (ቍ 17)፣ "ቅሚያና ስስት ሞልቶባችኋል" (ቍ 25)፤ "በኖራ ተለስነው የሚያምሩ ... ርኩሰት የተሞላ መቃብሮችን ..." (ቍ 27)፣ "ውስጣችሁ ... በክፋት የተሞላ" (ቍ 28)፣ "እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች" (ቍ 33)፤ "ትገድላላችሁ" (ቍ 34)። እነዚህ ቃላት ከበድ ያሉና የውግዘት ቃላት ቢሆኑም፣ ለእነርሱ ከሞተላቸው (ከዮሐ 3፥16፤ ከሮሜ 5፥6፡8 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ከጌታ ኢየሱስ አንደበት በሐዘን፣ ከተሰበረ ልብ ስለሚያምቁ የተነገሩ ናቸው (ቍ 37)።

(3) ኢየሱስ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችንና ሰባኪዎችን ባሕርይ ሲገልጽ ዝነኛና ዋና ለመሆን፣ በሌሎች ዘንድም ክብርን ለማግኘት እንደሚሹ አመልክቶአል (ቍ 5)፤ የከበሬታ ስፍራን ይወዳሉ (ቍ 6)፤ ሹመትን ይሻሉ (ቍ 7)፤ ባጣመሙት ወንጌላቸውም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይገቡ ያደርጋሉ (ቍ 13፤ በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት*

መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ሰዎች ወደ
መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ በሰዎች
ላይ በሩን ስለ ምትዘጉባቸው ወዮላችሁ!
እናንተ ራሳችሁ አትገቡም፤ መግባት
የሚፈልጉትንም አታስገቡም። [14]እናንተ
ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና
ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ የመበለቶችን ቤት
እያራቈታችሁ፣ ለሰው ይምሰል ረዥም ጸሎት
ስለምታደርጉ የከፋ ፍርድ ትቀበላላችሁ።*
[15]"እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ አንድን ሰው ወደ
አይሁድ ሃይማኖት ለማስገባት በባሕርና
በየብስ ስለምትዞሩ፣ ባመነም ጊዜ ከእናንተ
በእጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት
ወዮላችሁ።
[16]"እናንተ ዕውር መሪዎች፤ ወዮላችሁ!
'ማንም በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም
አይደለም፤ ነገር ግን በቤተ መቅደሱ ውስጥ
ባለው ወርቅ ቢምል መሐላው ይደርስበታል'
ትላላችሁ። [17]እናንተ የታወራችሁ ተላላዎች!
ከወርቁና ወርቁን ከቀደሰው ቤተ መቅደስ
የቱ ይበልጣል? [18]እንዲሁም፣ 'ማንም
በመሠዊያው ቢምል ምንም አይደለም፤ ነገር
ግን በላዩ ላይ ባለው መባ ቢምል መሐላው
ይደርስበታል' ትላላችሁ፤ [19]እናንተ
ዕውሮች፤ ከመባውና መባውን ከቀደሰው
መሠዊያ የቱ ይበልጣል? [20]ስለዚህ፣
በመሠዊያው የማለ፣ በመሠዊያውና በላዩ
ላይ ባለው ሁሉ ይምላል። [21]እንዲሁም
በቤተ መቅደሱ የማለ፣ በቤተ መቅደሱና
በውስጡ በሚያድረው ይምላል። [22]በሰማይ
የማለም በእግዚአብሔር ዙፋንና በዙፋኑ ላይ
በተቀመጠው ይምላል።
[23]"እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ!
ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት
እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን
ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን
ግን ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን
ማድረግ በተገባችሁ ነበር፤ [24]እናንተ
የታወራችሁ መሪዎች፤ ትንኝን እጥርታችሁ
ትጥላላችሁ፤ ግመልን ግን ትውጣላችሁ።

23፥15 ማቴ5፥22፤ ሐሥ2፥11፤ 6፥5፤ 13፥43
23፥16 ቍ24፤ ኢሳ9፥16፤ ማቴ5፥33-35፤ 15፥14
23፥17 ዘፀ30፥29
23፥19 ዘፀ29፥37
23፥21 1ነገ8፥13፤ መዝ26፥8
23፥22 መዝ11፥4፤ ማቴ5፥34
23፥23 ዘሌ27፥30፤ ሚክ6፥8፤ ሉቃ11፥42
23፥24 ቍ16
23፥25 ማር7፥4፤ ሉቃ11፥39
23፥27 ሉቃ11፥44፤ ሐሥ23፥3
23፥29 ሉቃ11፥47፡48
23፥31 ማቴ5፥12
23፥32 ሕዝ20፥4፤ 1ተሰ2፥16
23፥33 ማቴ3፥7፤ 5፥22፤ 12፥34
23፥34 2ዜና36፥15፡16፤ ማቴ10፥17፡23፤ ሉቃ11፥49
23፥35 ዘፍ4፥8፤ 2ዜና24፥21፤ ዘካ1፥1፤ ዕብ11፥4
23፥36 ማቴ10፥23፤ 24፥34፤ ሉቃ11፥50፡51
23፥37 2ዜና24፥21፤ መዝ57፥1፤ 61፥4፤ ኢሳ31፥5፤ ማቴ5፥12

[25]"እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ!
የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ
ትወለውላላችሁ፤ በውስጣቸው ግን ቅሚያና
ስስት ሞልቶባቸዋል። [26]አንተ ዕውር ፈሪሳዊ
አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጥ
አጽዳ፤ ከዚያም ውጭው የጸዳ ይሆናል።
[27]"እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ውጫቸው በኖራ
ተለስነው የሚያምሩ፣ ውስጣቸው ግን
በሙታን ዐፅምና በብዙ ርኵሰት የተሞላ
መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ!
[28]እናንተም በውጭ ለሰዎች ጻድቃን
ትመስላላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በግብዝነትና
በክፋት የተሞላ ነው።
[29]"እናንተ ግብዞች የኦሪት ሕግ
መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ!
የነቢያትን መቃብር እየገነባችሁ፣
የጻድቃንንም ሐውልት እያስጌጣችሁ፣
[30]'በአባቶቻችን ዘመን ብንኖር ኖሮ፣
የነቢያትን ደም በማፍሰስ አንተባበራቸውም
ነበር' ትላላችሁና። [31]በዚህም የነቢያት ገዳዮች
ለነበሩት አባቶቻችሁ ልጆች መሆናችሁን
በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ። [32]እንግዲህ
የአባቶቻችሁን ጅምር ተግባር ከፍጻሜ
አድርሱ!
[33]"እናንተ እባቦች፤ የእፉኝት ልጆች!
ከገሃነም ፍርድ እንዴት ልታመልጡ
ትችላላችሁ? [34]ስለዚህ ነቢያትን፣
ጠቢባንንና መምህራንን እልክላችኋለሁ፤
ከነዚህም አንዳንዶቹን ትገድላላችሁ፤
አንዳንዶቹን ትሰቅላላችሁ፤ ሌሎቹንም
በምኵራቦቻችሁ ትገርፉቸዋላችሁ፤
ከከተማ ወደ ከተማ ታሳድዷቸዋላችሁ።
[35]ስለዚህ፣ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ
በመቅደሱና በመሠዊያው መካከል እስከ
ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ
ደም ድረስ በምድር ላይ ለፈሰሰው ንጹሕ
ደም ሁሉ እናንተ ተጠያቂዎች ናችሁ።
[36]እውነት እላችኋለሁ፤ ላለፈው ነገር ሁሉ
ይህ ትውልድ ይጠየቅበታል።
[37]"አንቺ ነቢያትን የምትገድዪ፣ ወደ

*አስተማሪዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። መንፈሳዊና የእግዚአብሔር ሰዎች መስለው የሚታዩ ሞያተኛ ሃይማኖተኞች ናቸው፡ ሆኖም በርግጥ ጻድቃን አይደሉም (ቍ 14፡25-27)። ስለ ቀድሞዎቹ መንፈሳዊያን የእግዚአብሔር ሰዎች ጽድቅ ይናገራሉ፤ ነገር ግን የእነርሱን ሕይወት ተመክሮ ወይም ለእግዚአብሔር፣ ለቃሉና ለጽድቁ የነበራቸውን ታማኝነት አይከተሉም (ቍ 29-30)።

(4) መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ከእንደነዚህ ዐይነቶቹ የሐሰት ሃይማኖት መሪዎች እንዲጠነቀቁ (7፥15፤ 24፥11)፣ አማኞች እንዳልሆኑም እንዲቈጥሯቸው (ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ)፣ የእነርሱን አገልግሎት እንዳይደግፉ ወይም ከእነርሱ ጋር ኅብረት እንዳያደርጉ ያዛል (2ዮሐ 1፥9-11)።

(5) ዛሬ በቤተ ክርስቲያን በፍቅር፣ በመቻቻል ወይም በአንድነት ስም፣ እውነተኛውን የክርስቶስንና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት ለሚያጣምሙ (7፥15፤ ገላ 1፥6-7፤ 2ዮሐ 1፥9) ኢየሱስ በሐሰት ትምህርት ላይ ያለውን አመለካከት ለሌሎች ማካፈል እንደሚገባቸው የማያምኑ ሰዎች፣ ከሐሰተኛ ነቢያትና አስተማሪዎች ክፉ ድርጊት ጋር የሚተባበሩ ናቸው (2ዮሐ 1፥10-11)።

**23፥28 በውጭ ... ጻድቃን፤** ኢየሱስ በሕዝብ ፊት ባላቸው አገልግሎት ጻድቃን እየመሰሉ ነገር ግን በግብዝነት፣ በትዕቢት፣ በዝሙትና በክፋት የተሞላ ልብ ስለ ነበራቸው በእርሱ ዘመን ስላሉ የሃይማኖት መሪዎችና አገልጋዮች መናገሩን ይቀጥላል። እነርሱ ውጭው ያማረና የሚማርክን በኖራ የተለሰነን መቃብር ይመስላሉ፣ ይሁን እንጂ በውስጣቸው መጥፎ ሽታና የተበከለ ነገር ተሸሽጎ ይገኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐሰት ትምህርት የሚናገረውን የበለጠ ለመረዳት በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**23፥37 ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም፣**

አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ የምትወግሪ
ኢየሩሳሌም ሆይ፤ አንቺ ኢየሩሳሌም!
ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር
እንደምትሰበ ስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ
ስንት ጊዜ ፈለግሁ! እናንተ ግን ፈቃደኛ
አልሆናችሁም፤ [38]እነሆ፤ ቤታችሁ ወና
ሆኖ ይቀርላችኋል! [39]እላችኋለሁና፤ 'በጌታ
ስም የሚመጣ የተባረከ ነው' እስክምትሉ
ድረስ ዳግመኛ አታዩኝም።"

## የዓለም መጨረሻ ምልክቶች

*24፥1-51 ተጓ ምብ — ማር13፥1-37፤ ሉቃ 21፥5-36*

24 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሲሄድ፣
ደቀ መዛሙርቱ የቤተ መቅደሱን
ሕንጻ ሊያሳዩት ወደ እርሱ ቀረቡ። [2]እርሱ
ግን፣ "ይህን ሁሉ ታያላ ችሁ? እውነት
እላችኋለሁ፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተከቦ
የምታዩት፣ ሳይፈርስ እንዲህ እንዳለ የሚቀር
አንድ ድንጋይ እንኳ አይኖርም" አላቸው።
[3]በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ
ሳለ፣ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ
ቀርበው "እስቲ ንገረን፤ የምትለው ሁሉ መቼ
ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ
ምልክትስ ምንድን ነው?" አሉት።
[4]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤

23፥38 1ነገ9፥7-8፤ ኤር22፥5
23፥39 መዝ118፥26፤ ማቴ21፥9
24፥2 ሉቃ19፥44
24፥3 ማቴ13፥39፤ 21፥1፤ 28፥20፤ ሉቃ17፥30
24፥4 ማር13፥5

---

ሉቃ 13፥34 እና ማብራሪያውን፤ እንዲሁም ሉቃ 19፥41 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**23፥39 … እስክምትሉ ድረስ ዳግመኛ አታዩኝም፤** የኢየሩሳሌም ከተማ በተደጋጋሚ የኢየሱስን መልእክት ተቃውማ ነበር። ስለዚህ እስራኤላውያን በእርሱ ላይ የፈጸሙትን በደል እስኪያውቁና ታዳጊያቸው ሆኖ እንዲመጣ መሲሑን እስኪጠሩ ድረስ ክርስቶስ እያዘነ (ቍ 37-38) ይሄዳል፤ ዳግመኛም አያዩትም፤ (1) ይህ ሊሆን የሚችለው እስራኤል (ማለትም ትሩፋኑ፣ ኢሳ 6፥13 እና ማብ፣ 10፥20 እና ማብ፣ 17፥7 እና ማብ ይመ) በታላቁ መከራ አስከፊ ቀናት ውስጥ ሲያልፉና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ ብቻ ነው (ሆሴ 5፥15—6፥3 ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በዘመኑ መጨረሻ ላይ እስራኤል ከባድ መከራ ውስጥ ስትገባ (አሞ 9፥9)፣ የዓለም መንግሥታት ሁሉ በእስራኤል ላይ ይነሣሉ (ዘካ 12፥1-4)፤ ከእስራኤል ሕዝብም ሁለት ሦስተኛው እጅ ይገደላል (ዘካ 13፥8-9)። እስራኤል ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ስትቃረብ፣ ትሩፋኑ በንስሓና በልቅሶ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ (ኢሳ 26፥16-17፤ 64፥1፡6፤ ሆሴ 5፥15፤ ዘካ 12፥4-5፡10፤ ሮሜ 11፥26፤ ራእ 11፥2 እና ማብ፡ 12፥6 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1758 ላይ፣ *"እስራኤል በእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**24፥3—25፥46 በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተዘረዘረው ሐሳብ፣** "የደብረዘይቱ ንግግር" ይባላል። የኢየሱስ ትንቢት በዚህ ስፍራ በመሠረቱ፣ "የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክት ምንድን ነው?" ለሚለው ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ የተሰጠ መልስ ነበር፤ የሰጣቸው መልሶችም የሚከተሉት ናቸው፤ (1) እስከ መጨረሻው ዘመን የሚዘልቁ አጠቃላይ ምልክቶች (24፥4-14)፤ (2) የዘመኑን የመጨረሻ ቀናት የሚያመለክቱ ልዩ ምልክቶች፣ ይኸውም ታላቁ መከራን (24፥15-28)፤ (3) ጌታ ኢየሱስ በኀይልና በታላቅ ክብር በድል አድራጊነት ሲመጣ የሚከሠቱ እጅግ አስደናቂ ምልክቶች (24፥29-31)፤ (4) በታላቁ መከራ ለነበሩ ቅዱሳን፣ ከመከራው በኋላ ወዲያውኑ ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ የሚያመለክቱ ምልክቶች ሲከሠቱ ነቅተው መጠባበቅ እንዳለባቸው የተሰጠ ማሳሰቢያ (24፥32-35)፤ (5) ከታላቁ መከራ በፊት የሚኖሩ አማኞች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለታማኞቹ ባልተጠበቀና ባልታወቀ ጊዜ ስለሚመጣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ዝግጁ በመሆን እንዲጠባበቁ የተሰጠ ማሳሰቢያ (24፥36-51፤ 25፥1-30፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንጥቀት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (6) እርሱ ወደ ምድር ከተመለሰ በኋላ በሕዝቦች ሁሉ ላይ ስለሚፈጸመው ፍርድ ገለጻ (25፥31-46)።

በማቴዎስ ምዕራፍ 24 ላይ ስለ ክርስቶስ ምጽአት አያሌ ዝርዝር ጕዳዮች እንዳልተገለጹ ልብ ይበሉ። ከዚህም በላይ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ በመሆን ስለ መጨረሻው ዘመን የተነገሩትን የትንቢቶች ምስጢር ለመረዳት የቻለ ማንም የለም። ስለዚህ በኢየሱስ ንግግር ውስጥ የተጠቀሰው ምስጢር ትሕትናን ማሳየትና በራሱ በጌታ ኢየሱስ ላይ ልብን ማሳረፍ ተገቢ መሆኑን አስገንዝቦ ያልፎአል። በመጨረሻው ዘመን የእስተርእዮታዊ ግንዛቤ ተጨማሪ መገለጥ እንደሚኖረን ተስፋ ማድረግ እንችላለን (ከዳን 12፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

**24፥4-51 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤** ኢየሱስ የሰጠው መልስ እስከ ቍ 51 ይዘልቃል። ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ያደረገው ንግግር ለደቀ መዛሙርቱና እስከ ዘመኑ መጨረሻ ማለትም እርሱ ይህን ምድር ለመግዛት በድል አድራጊነት ተመልሶ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ላሉት ለእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች ነው። (1) ከታላቁ መከራ ጊዜ በፊት የሚኖሩትን አማኞች በተመለከተ፣ እርሱ የሚመጣበትን ዘመን ማስላት ወይም መገመት እንደማይችሉ ክርስቶስ ይነግራቸዋል (ቍ 42-44)። ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ መሆን አለባቸው፤ ይመጣል ብለው በማይጠብቁት ጊዜ (ቍ 44 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንጥቀት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊወስዳቸው ይመጣልና (ማለትም "ወደ አባቴ ቤት" ዮሐ 14፥2-3 እና ማብ ይመ)።

(2) በታላቁ መከራ ጊዜ በክርስቶስ ያመኑት በርግጠኝነት እርሱ ለእነርሱ ሲል የሚመጣበትን ጊዜ ማወቅ ይችላሉ፤ በቅርቡ እንደሚመለስ የሚያውቁባቸውንና የሚጠባበቁባቸውን ምልክቶች ክርስቶስ ይሰጣቸዋልና (ቍ 15-29)። እነዚህን ምልክቶች ሲያዩ፣ "እርሱ በደጅ እንደ ቀረበ" ያውቃሉ (ቍ 33 እና ማብ ይመ)።

**24፥4፤** ከቍ 4-14 ባሉት ጥቅሶች ኢየሱስ የመጨረሻውን ዘመን ባሕርይ በአጠቃላይ የሚገልጹ ምልክቶችን ይሰጣል (ከቍ 3 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ምልክቶችም የመጨረሻው ዘመን እየቀረበ ሲመጣ እየጐሉ ይሄዳሉ። (1) በምትታየው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኛ

5ብዙዎች፣ 'እኔ ክርስቶስ ነኝ' በማለት
በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።
6ስለ ጦርነትና ጦርነትን የሚያናፍስ ወሬ
ትሰማላችሁ፤ እነዚህ ነገሮች የግድ መፈጸም
አለባቸው፤ ሆኖም መጨረሻው ገና ስለ ሆነ
በዚህ እንዳትደናገጡ ተጠንቀቁ። 7ሕዝብ
በሕዝብ ላይ፣ መንግሥትም በመንግሥት
ላይ ይነሣል፤ በተለያየ ስፍራም ራብና
የመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናል፤ 8ይህ ሁሉ
ግን የምጡ መጀመሪያ ነው።
9"በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው
ይሰጧችኋል፣ ይገድሏችኋል፣ በስሜ
ምክንያት በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ
ትሆናላችሁ። 10በዚያን ጊዜ ብዙዎች
ይሰናከላሉ፤ እርስ በርስ አሳልፈው
ይሰጣጣሉ፤ ይጠላላሉም። 11ብዙዎች
ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችን
ያስታሉ። 12ክፋት ስለሚገን የብዙ ሰዎች
ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ 13እስከ መጨረሻ
የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። 14ለሕዝብ
ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግሥት
ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም
መጨረሻው ይመጣል።

24፥5 ቍ 11:23:24፤ 1ዮሐ2፥18
24፥7 ኢሳ19፥2፤ ሐሥ11፥28
24፥9 ማቴ10፥17፤ ዮሐ15፥21፤ 16፥2
24፥11 ማቴ7፥15፤ ማር13፥5
24፥13 ማቴ10፥22
24፥14 ማቴ4፥23፤ ሉቃ2፥1፤ 4፥5፤

24፥14 ሐሥ11፥28፤ 17፥6፤ ሮሜ10፥18፤ ራእ3፥10፤ 16፥14

"24፥5 ወይም መሲሕ፤ ቍ 23 ይመ ሁ34 ወይም ዘር

ነቢያትና የሃይማኖት መልክ ያላቸው ሰዎች ይበዛሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ (ቍ 4-5:11)፡ (2) የጦርነት፣ የራብና የመሬት መንቀጥቀጥ መብዛት (ቍ 6-7) የአዲሱ መሲሓዊ ዘመን «የምጡ መጀመሪያ» (ቍ 8) ይሆናል፡ (3) የመጨረሻው ዘመን እየተቃረበ ሲመጣ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ስደት እጅግ ከባድ ይሆናል (ቍ 9)፤ ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ለክርስቶስ የነበራቸውን ታማኝነት ይተዋሉ (ቍ 9-10)፡ (4) በመፅ፣ ወንጀልና የእግዚአብሔርን ሕግ መጣስ በፍጥነት እየጨመረ ይሄዳል፡ የብዙ ሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል፡ የቤተ ሰብ ፍቅርም ይቀንሳል (ቍ 12 ይመ፤ ከማር 13፥12፤ ከ2ጢሞ 3፥3 ጋር ያጻጽሩ)፡ (5) ችግሩ እየባሰ ቢሄድም እንኳ፣ ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል (ቍ 14)። (6) የሚድኑት በመጨረሻው ዘመን በሚከሠት መከራ ሁሉ በእምነታቸው ጸንተው የሚቆሙት ይሆናሉ (ቍ 13)፡ (7) ታማኝ የሆኑት የእነዚህን ምልክቶች በብዛት መምጣት ሲመለከቱ የክርስቶስ ምጽአት ቀን ለእነርሱ «እየተቃረበ መምጣቱን» ያውቃሉ (ዕብ 10፥25፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)።

**24፥5 ብዙዎች ... ብዙዎችንም ያስታሉ፤** ይህ የመጀመሪያ የሆነው ዋና ምልክት የተለየ አስፈላጊነት ወይም ጠቃሚነት አለው። በዚህ ዘመን ማብቂያ ላይ በምድር ላይ ሃይማኖታዊ አጭበርባሪነት እየተስፋፋ ይሄዳል። ክርስቶስ እጅግ ከማሰቡ የተነሣ የእርሱ ተከታዮች ከዘመኑ መጨረሻ በፊት ከዚህ ዓለም አቀፍ ሃይማኖታዊ አጭበርባሪነት ይጠንቀቁ ዘንድ በደብረ ዘይት ንግግሩ ሁለት ጊዜ በመደጋገም ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል (ቊ 11 እና ማብ፤ ቊ 24 ይመ፤ በገጽ 1913 ላይ፥ *«የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**24፥9 የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤** በክርስቶስ ያሉ አማኞች ሁሉ በምድር ላይ ባለ ጕዟቸው ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ለእርሱና ለቃሉ ካለን ታማኝነት አንጻር ለክርስቶስ ስንል መሠቃየታችን የክርስትና እምነት ዋነኛ አካል ነው (ከዮሐ 15፥20፤ 16፥33፤ ከሐሥ 14፥22፤ ከሮሜ 5፥3 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 5፥10 እና ማብ፤ 2ጢሞ 3፥12 እና ማብ ይመ)።

**24፥11 ብዙዎች ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ፤** የመጨረሻዎቹ ቀናት ሲቃረቡ፣ የሐሰት ትምህርት አስተማሪችና ሰባኪዎች በይበልጥ እየበረከቱ ይሄዳሉ (በገጽ 1519 ላይ፥ *«የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። አብዛኛው ምእመን በክሕደት ውስጥ ይገባል። ለእግዚአብሔር ቃልና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጽድቅ ራሳቸውን የሰጡ ጥቂቶች ይሆናሉ።

(1) አማኞች ነን የሚሉ ክርስቲያኖች ከተገለጠው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ቢሆንም እንኳ «አዲስ መገለጥን» ይቀበላሉ። ይህም በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ወደ መቃረን የሚያመራ ነው (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 2ጢሞ 3፥8፤ 4፥3 እና ማብ ይመ)። የተጣመመ ወንጌልን የሚሰብኩ በአብያተ እምነቶችና በሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች ወሳኝ የሆነ የመሪነት ሥልጣንን ሊይዙ ይችላሉ (7፥22 እና ማብ ይመ)፤ ይህም ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ያሉትን ብዙዎችን ለማሳትና ለማጣመም ያስችላቸዋል (ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 2ጢሞ 4፥3 እና ማብ፤ 2ጴጥ 3፥3-4 ይመ)።

(2) በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች በመተት፣ በኮከብ ቈጠራ፣ በጥንቈላ፣ በሟርትና በሰይጣናዊ እምነት ውስጥ ይዘፈቃሉ። የኢጋንንትና የክፉ መናፍስት ተጽዕኖ ይበዛል (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)።

(3) ከስሕተት የመጠበቅ ሁኔታ በጽኑ እምነትና በክርስቶስ ፍቅር ውስጥ፤ ፍጹም በሆነው በቃሉ ሥልጣን ሥር በመገዛትና (ቍ 4:11:13:25) ቃሉን በጥልቀት በማወቅ ውስጥ ይገኛል (1ጢሞ 4፥16 እና ማብ ይመ)።

**24፥12 ክፋት ስለሚገን፤** የመጨረሻው ዘመን በማይታመን ሁኔታ የኢግብረገባዊነት መብዛት፣ የስፍረተቢስነት፣ በእግዚአብሔር ላይ የማመፅና ግብረገባዊ ግዴታዎችን የመጣስ ሁኔታ የሚታይበት ዘመን ነው። በዚህ ዘመን ከተፈጥሮ ባሕርይ ውጭ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት፣ ኢግብረገባዊነት፥ ምንዝርና፥ ወሲባዊ ግንኙነትን በሥዕል ወይም በጽሑፍ መከታተል፣ በዕፅ ሱስ መጠመድ፣ መንፈሳዊ ያልሆነ ሙዚቃና፣ ፍትወትን የሚያነሣሣ ተዝናኖት በብዛት ይስፋፋሉ። የሰው ልብ ሐሳብ ባለማቋረጥ በክፋት ሲሞላ (ዘፍ 6፥5)፣ «በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው» (ቍ 37) ይሆናል። ግብረሰዶማዊነት፣ ግብረሰዶማዊትነትና፥ ማንኛውም ዐይነት ከተፈጥሮ ባሕርይ ውጭ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ኀብረተሰቡን ሲያጥለቀልቀው «እንደ ሎጥ ዘመን» (ሉቃ 17፥28:30) ይሆናል (ዘፍ 19፥5 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 2ጢሞ 3፥1-8 እና ማብ ይመ)። በመቀጠልም ኢየሱስ እውነተኛ ፍቅር እየቀዘቀዘ እንደሚሄድ ተናግሮአል።

**24፥14 የመንግሥት ወንጌል ... መጨረሻው፤** የመጨረሻው ዘመን የሚመጣው፣ «የመንግሥት ወንጌል» በዓለም ሁሉ በበቂ ሁኔታ ተሰብኮ ሲያበቃ ነው። (1) «የመንግሥት ወንጌል» የሚያመለክተው በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና ጽድቅ የሚሰበከውን የሐዋርያትን ወንጌል እንዲሁም በወንጌል ዋና ዋና ምልክቶች የጸናውን ትምህርት ነው (በገጽ 1443 ላይ፣ *«የእግዚአብሔር መንግሥት»*

15"እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል
የተነገረው፣ 'የጥፋት ርኵሰት' በተቀደሰው
ስፍራ ቆሞ ስታዩ፣ አንባቢው ያስተውል።
16በዚያን ጊዜ በይሁዳ የሚገኙ ወደ
ተራራዎች ይሽሹ፤ 17በቤቱ ጣራ ላይ
የሚገኝ ማንም ሰው ዕቃ ውን ከቤቱ
ለማውጣት አይውረድ፤ 18በዕርሻ ቦታው
የሚገኝ ማንም ሰው ልብሱን ለመውሰድ
አይመለስ። 19በእነዚያ ቀናት ለነፍሰ
ጡሮችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 20እንግዲህ
ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት ቀን
እንዳይሆን ጸልዩ፤ 21በዚያን ጊዜ፣ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሆኖ
የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የሚስተካከለው
የሌለ፣ ታላቅ መከራ ይሆናል። 22ቀኖቹ
ባይጥሩ ኖሮ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልተረፈ
ነበረ፤ ስለተመረጡት ሲባል ግን እነዚያ
ቀኖች ያጥራሉ። 23በዚያን ጊዜ ማንም፣
'ይኸውላችሁ ክርስቶስ እዚህ አለ' ወይም
'እዚያ አለ' ቢላችሁ አትመኑ፤ 24ሐሰተኛ
ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤
ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ
ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ።
25እነሆ፤ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።
26"ስለዚህ፣ 'ያውላችሁ እበረሐው ውስጥ
አለላችሁ' ቢሏችሁ ወደዚያ አትውጡ፤
'ይኸውላችሁ እልፍኝ ውስጥ አለላችሁ'
ቢሏችሁ አትመኑ፤ 27መብረቅ ከምሥራቅ
ወጥቶ ምዕራብ ድረስ እንደሚያበራ፣ የሰው
ልጅ አመጣጥም እንደዚሁ ይሆናል። 28በድን
ባለበት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ።
29"ወዲያውኑ ከእነዚያ ከመከራው ቀናት
በኋላ፣ 'ፀሓይ ትጨልማለች፤
ጨረቃ ብርሃኗን ትከለክላለች፤
ከዋክብት ከሰማይ ይረግፋሉ፤
የሰማይ ኀይላትም ይናጋሉ።'
30"በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት
በሰማይ ላይ ይታያል፤ የምድር ወገኖች
ሁሉ ያለቅሳሉ፤ የሰው ልጅም በሰማይ
ደመና ሆኖ በኀይልና በታላቅ ክብር
ሲመጣ ያዩታል፤ 31መላእክቱንም ከታላቅ
የመለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤
እነርሱም ምርጦቹን ከአራቱም ነፋሳት፣

24፥15 ዳን9፥27፤ 11፥31፤ 12፥11፤ ሐሥ6፥13
24፥17 1ሳሙ9፥25፤ ማቴ10፥27፤ ሉቃ12፥3፤ ሐሥ10፥9
24፥19 ሉቃ23፥29
24፥21 ሕዝ5፥9፤ ዳን12፥1፤ ኢል2፥2
24፥22 ቍ 24፥31
24፥23 ሉቃ17፥23፤ 21፥8
24፥24 ዘዳ7፥11፡22፤ 2ተሰ2፥9-11፤ ራእ13፥13፤ 16፥14፤ 19፥20
24፥27 ሉቃ17፥24፡30፤ ማቴ8፥20
24፥28 ሉቃ17፥37
24፥29 ኢሳ13፥10፤ 34፥4፤ ሕዝ32፥7፤ ኢል2፥10፡31፤
24፥29 ሶፎ1፥15፤
24፥29ራእ6፥12፡13፤ 8፥12 24፥30 ራእ1፥7
24፥31 ኢሳ27፥13፤ ዘካ9፥14፤ ማቴ13፥41፤ 1ቆሮ15፥52፤ 1ተሰ4፥16፤ ራእ8፥2፤ 10፥7፤ 11፥15

በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ይህ ተግባር በበላሚው መሠረት የተፈጸመ መሆኑን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የአንድ አማኝ ኀላፊነት ጌታ ተመልሶ የእርሱን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ እስከሚወስድበት ጊዜ ድረስ በታማኝነትና በጽናት "ሕዝቦች ሁሉ" ወንጌል እንዲሰሙ ጥረት ማድረግ ነው (28፥19-20 እና ማብ፡ ዮሐ 14፥3 እና ማብ፡ 1ተሰ 4፥13 እና ማብ ይመ)።

(3) ብዙ ተርጓሚዎች "የመጨረሻው" የሚለው ሐረግ፡ "በክርስቶስ የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ" የሚለውንና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታማኞች "ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን" ያሉትን እንደሚያመለክት ያምናሉ (1ተሰ 4፥16-17 ይመ፡ በገጽ 1907 ላይ፣ "**ንጥቀት**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ክርስቶስ ታማኝ ለሆኑትው ቤተ ክርስቲያን ባልተጠበቀ ጊዜ የሚገለጥበትን ሁኔታ የሚያመለክቱ ኢየሱ ዝርዝር ሐሳቦችን ከቍጥር 37-44 ባለው ክፍል ገልጾአል።

**24፥14 መጨረሻው ይመጣል፤** ክርስቶስ ስለ መጨረሻው ዘመን ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው፡ ትንቢቱ ሁሉ በእነርሱ ትውልድ ዘመን እንደሚፈጸም አድርጎ ነው። ስለዚህ ይህ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ተስፋ ነበር። ይህም በየዘመኑ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የሚጠባበቁት ተስፋ መሆን አለበት። እኛም ጌታ እንደሚመለስ፣ የዘመኑ ፍጻሜም በእኛ ትውልድ እንደሚሆን ተስፋ ማድረግ አለብን (1ቆሮ 15፥51 እና ማብ ይመ)። የክርስቶስ ምጽአት በቅርቡ እንደሚሆን በማሰላሰልና ወንጌልን እንድናሠራጭ ክርስቶስ ያዘዘን መሆኑን በማጤን መካከል ባለ ሽክም መሠረት መኖር አለብን።

**24፥15-28 እነዚህ ጥቅሶች ስለ ታላቁ መከራ የሚያወሱ ናቸው።** ይህን ርእስ ጕዳይ በጥንቃቄ ለማጥናት በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**24፥29 ፀሓይ ትጨልማለች፤** ከታላቁ መከራ በኋላ ወዲያውኑ የክርስቶስን ምጽአት የሚቀድሙና ተመልሶ ስለ መምጣቱ ግልጽ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ አስደናቂ ምልክቶች በሰማይ ላይ ይታያሉ (ቍ 30)። በኀይልና በታላቅ ክብር የክርስቶስ ወደ ምድር መመለስ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ለሚጠብቅና ከፀሐይ፣ ከጨረቃ፣ ከከዋክብትና ከሰማይ ኀይላት መናወጥ ጋር የሚዛመዱትን የሰማይ ላይ ምልክቶች ልብ ብሎ ለሚመለከት በታላቁ መከራ ለሚገኝ ለማንኛውም አማኝ ድንገተኛ ክሥተት አይሆንም (ኢሳ 13፥6-13 እና ማብ ይመ)።

**24፥30 የሰው ልጅም ... ሲመጣ፤** ይህ ጥቅስ የክርስቶስ መገለጥ በሰማይ ላይ የሚከሠተው፣ ከታላቁ መከራና በሰማይ ላይ ከሚታዩ ምልክቶች በኋላ እንደሚሆን ያመለክታል። ክርስቶስ በክፉዎች ላይ ለመፍረድ (ራእ 19፥11—20፥3)፣ ታማኝ ሕዝቡን ለመታደግና በምድር ላይ ጽድቅን ለመመሥረት ይመጣል (ራእ 20፥4)። ሕያዋንም ሆኑ ሙታን ከምድር ተነጥቀው የተወሰዱት ክርስቲያኖች ሁሉ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፡ በገጽ 1907 ላይ፣ "**ንጥቀት**" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ክርስቶስ በኀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ አብረውት ይመለሳሉ (ራእ 19፥14 እና ማብ ይመ)። ምልክቱ ክርስቶስ ራሱ በሚያብረቀርቅ ብርሃን ታጅቦ በክብር ደመና የሚመለስበት ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

**24፥31 እነርሱም ምርጦቹን ... ይሰበስባሉ፤** ከታላቁ መከራ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ የሚከተሉት ክሥተቶች ይፈጸማሉ፤ (1) የእግዚአብሔር ፍርድ በክፉዎች (ቍ 30፤ ራእ 19፥11-12)፣ በሐሰተኛው ክርስቶስ (ራእ 19፥20) እና በሰይጣን (ራእ 20፥1-3) ላይ ይገለጣል፤ (2) ክርስቶስ ሲመጣ በምድር በሚኖሩት ላይ ፍርድና መለየት ይሆናል (13፥41 እና ማብ፡ 25፥32 እና ማብ ይመ)፤ (3) ክርስቶስ ሲመጣ በምድር ላይ የነበሩ ቅዱሳን (13፥40 ይመ)፣ በመንግሥተ ሰማይ ያሉ ቅዱሳንም ጭምር (ከማር 13፥27 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ፡ ራእ 19፥14 እና ማብ፡ 20፥4፡6 ይመ) በሁሉም ዕድሜ ያሉ ቅዱሳን በሙሉ በአንድነት ይሰበሰባሉ፤ (4) የሺህ ዓመቱ የክርስቶስ መንግሥት በምድር ላይ ይመሠረታል (ራእ 20፥4 እና ማብ ይመ)።

ከሰማያት ከአንዱ ዳርቻ ወደ ሌላው ዳርቻ
ይሰበስባሉ።
32 "ከበለስ ዛፍ ይህን ትምህርት ተማሩ፤
ቅርንጫፉ ሲለመልም፣ ቅጠሏ ሲያቈጠቍጥ፣
ያን ጊዜ በጋ እንደ ተቃረበ ታውቃላችሁ።
33 እንደዚሁም እነዚህን ሁሉ ስታዩ፣ እርሱ
በደጅ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ። 34 እውነት
እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ይህ
ትውልድ" አያልፍም። 35 ሰማይና ምድር
ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ፈጽሞ አያልፍም።

## የሚመጣበት ቀንና ሰዓት አለመታወቁ

*24፡37-39 ተጓ ምብ — ሉቃ 17፡26፡27*
*24፡45-51 ተጓ ምብ — ሉቃ 12፡42-46*

36 "ያን ቀንና ሰዓት ግን ከአብ በስተቀር
የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም
ቢሆን‹ ማንም አያውቅም። 37 ልክ በኖኅ
ዘመን እንደ ሆነው የሰው ልጅ መምጣትም
እንደዚሁ ይሆናል፤ 38 ከጥፋት ውሃ በፊት
ኖኅ ወደ መርከቡ እስከገባበት ቀን ድረስ
ሰዎች ሲበሉና ሲጠጡ፣ ሲያገቡና ሲጋቡ
እንደ ነበሩ፣ 39 እስከዚያ ጊዜ ድረስም ምን
እንደሚመጣ ሳያውቁ ድንገት የጥፋት
ውሃ እንዳጥለቀለቃቸው፣ የሰው ልጅ
ሲመጣም እንደዚሁ ይሆናል። 40 በዚያን ጊዜ
ሁለት ሰዎች በዕርሻ ላይ ይሠላሉ፤ አንዱ

24፡33 ያዕ5፡9
24፡34 ማቴ16፡28፤ 23፡36
24፡35 ማቴ5፡18
24፡36 ሐሥ1፡7
24፡37 ዘፍ6፡5፤ 7፡6-23
24፡38 ማቴ22፡30
24፡39 ሉቃ17፡30
24፡40 ሉቃ17፡34

‹24፡36 አንዳንድ ቅጆች ወልድም ቢሆን የሚለው የላቸውም

**24፡32 ከበለስ ዛፍ፤** የበለስ ዛፍ ማቈጥቈጥ (ከሉቃ 21፡29-31 ጋር ያነጻጽሩ) በታላቁ መከራ ጊዜ የሚከሠቱትን ሁኔታዎች የሚያመለክት ነው (ቍ 15-29)። አንዳንዶች የበለስን ዛፍ ከእስራኤል መንግሥት መመሥረት ጋር ያያይዙታል (ከሆሴ 9፡10፤ ከሉቃ 13፡6-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

**24፡33 እነዚህን ሁሉ፤** ይህ በታላቁ መከራ ጊዜ የሚከሠቱትን ምልክቶች ሁሉ የሚያመለክት ነው (ቍ 15-29)፤ ዋናው ምልክት፣ "የጥፋት ርኵሰት" የተባለው ነው በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በትንቢት የተነገሩት ነገሮች ሲገለጡ የታላቁ መከራ ታማኞች፣ "እነዚህን ሁሉ ያያሉ"፤ የጌታ ምጽአት "በደጅ እንደ ቀረበ"ም ያውቃሉ።

**24፡34 ይህ ትውልድ፤** "ይህ ትውልድ" የሚለው ሐረግ በታላቁ መከራ ዘመን የሚፈጸሙትንና (ቍ 5 እና ማብ ይመ) እየጐሉ የሚሄዱትን የዘመኑን አጠቃላይ ምልክቶች ማየት የሚጀምረውን ትውልድ ሊመለከት ይችላል (ቍ 4-14)፤ ወይም ደግሞ የአይሁድን ሕዝብ እንደ አንድ ዘር አድርጎ ሊያሳይ ይችላል።

**24፡36 ከአብ በስተቀር፤** ይህ ጥቅስ የሚገልጸው ክርስቶስ የሚመለስበትን ጊዜ የሚያውቀው አብ ብቻ መሆኑን ነው። ይህም ክርስቶስ በምድር ላይ የነበረበትን ጊዜ የሚያመለክት መሆኑን መረዳት እንዳለብን ያሳያል። ጸሎት ባቀረበበት ጊዜ በርግጥ ወደ ቀድሞው ክብሩ የተመለሰው ኢየሱስ (ዮሐ 17፡5)፣ ወደፊት ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ ያውቅ ነበር። በታላቁ መከራ ጊዜ ያሉ ቅዱሳንም ክርስቶስ በዝርዝር የተናገራቸውን የመከራውን ምልክቶች በመመልከት፣ ጌታ በመጨረሻ የሚመለስበትን ጊዜ ማወቅ ይችላሉ (በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**24፡37 የሰው ልጅ መምጣትም፤** ስለ፣ "የሰው ልጅ መምጣት" ክርስቶስ የተናገረው ቃል የሚከተሉት ጥምር ሐሳቦች አሉት፤ የመጀመሪያው ደረጃ እርሱ ተመልሶ የሚመጣው ባልታወቀና ባልተጠበቀ ወቅት መሆኑ ነው (ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን የሚነጠቁበት ጊዜ ነው፤ ቍ 42 እና ማብ፤ ዮሐ 14፡3 እና ማብ፤ ራእ 3፡10 እና ማብ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ከታላቁ መከራ በኋላ እርሱ የሚመለስበት ጊዜ ክፉዎችን የሚያጠፋበትና ጻድቃንን ወደ መንግሥቱ የሚሰበስብበት ጊዜ ነው (ራእ 19፡11-20፡4)። ይህን ጥምር አመላካች ሐሳብ ክርስቶስ፣ "በኖኅ ዘመን" (ቍ 37-44) የነበሩትን የሕዝብ ወገኖች ማንነት ሲገልጽ ቀደም ሲል ተገንዝበናል። እነዚህ ሦስት የሕዝብ ወገኖችና ከክርስቶስ ምጽአት ጋር ያላቸው ግንኙነት እንደሚከተለው ተገልጿዋል፤

(1) የታላቁ መከራ ኢአማንያን በኖኅ ዘመን በጥፋት ውሃ ባለቁት ሰዎች ተመስለዋል። ክርስቶስ የሚመለስበትን ጊዜ አያውቁም፤ ዝግጁዎች አይደሉም፤ ስለዚህ በመጨረሻው ዘመን ይጠፋሉ (ቍ 38-39 ይመ፤ ከሉቃ 17፡26-28 ያነጻጽሩ)። ይህ ከታላቁ መከራ በኋላ የሚፈጸመው፣ ክርስቶስ የሚመለስበት ጊዜ ሁለተኛው ደረጃ ነው።

(2) የታላቁ መከራ አማኞች በኖኅ ተመስለዋል። ከመጨረሻው ዘመን ምልክቶች የተነሣ፣ የታላቁ መከራ ቅዱሳን ክርስቶስ የሚመለስበትን ትክክለኛውን ጊዜ ወደ ማወቅ ይደርሳሉ፤ ዝግጁዎችም ስለ ሆኑ ከጥፋት ይድናሉ። በተጠበቀው ጊዜ ክርስቶስ ለእነርሱ ይመለስላቸዋል (ቍ 27 ይመ፤ ከዘፍ 7፡4 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይኸኛውም ክርስቶስ የሚመለስበትን ሁለተኛውን ደረጃ ያመለክታል።

(3) ከታላቁ መከራ በፊት የሚኖሩ የአሁኑ ዘመን አማኞች ወይም የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ተመስለዋል። ወደ መንግሥተ ሰማይ ይወስዳቸው ዘንድ ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ አያውቁም (ቍ 42፡44፤ ዮሐ 14፡3 እና ማብ ይመ፤ ከ1ተሰ 4፡14 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ ለእነርሱ የሚመለስበትን ጊዜ የሚያመለክት ግልጽ የሆነ ምልክት የለም፤ ተመልሶ የሚመጣው ድንገት እንደ ሆነ ክርስቶስ ራሱ ተናግሮአልና (ቍ 42፡44)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን (ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን) ያመሳሰለው ከኖኅ (ይኸውም የመከራው ቅዱሳን) ጋር ሳይሆን በጥፋት ውሃ ካለቁት ሰዎች ጋር መሆኑን ልብ ይበሉ ("ሳያውቁ" ቍ 39 የሚለውን ቃል "ስለማታውቁ" ቍ 42 ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)። ይኸውም በአንድ በኩል ሲታይ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በጥፋት ውሃ ካለቁት ሰዎች ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ ማለት ነው፤ ክርስቶስ ለእነርሱ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ አያውቁም፤ ሲመጣም ይደነቃሉ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ በጥፋት ውሃ ያለቁት ሰዎች የጥፋቱ ውሃ የሚመጣበትን ጊዜ እንዳላወቁና ድንገት ሲመጣም እጅግ እንደ ተደነቁ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በማንኛውም ጊዜ ዝግጁ መሆን አለባቸው (ቍ 44)።

**24፡40 አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል፤** ክርስቶስ ይህን ዐረፍተ ነገር የተናገረው ለቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ከሰጠው ምክር በፊት ነው (ቍ 42-44)። ስለዚህ እነዚህ ቃላት ክርስቶስ በመነጠቅ ጊዜ ታማኞቹን

# ታላቁ መከራ

*ማቴ 24፥21 "በዚያን ጊዜ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ሆኖ የማያውቅ፣ ከዚያም በኋላ የማይስተካከለው የሌለ፤ ታላቅ መከራ ይሆናል።"*

---

ከማቴዎስ 24፥15 ጀምሮ ኢየሱስ በታላቁ መከራ ጊዜ ስለሚከሠቱ ልዩ ምልክቶች ተናግሮአል (ራእ 7፥14ን ከማቴ 24፥21 ጋር ያነጻጽሩ፤ በሁለቱም ጥቅሶች ያሉት ሐረጎች በግሪክ ቋንቋ ተመሳሳዮች ናቸው)፡ እነዚህ ምልክቶች ከታላቁ መከራ በኋላ ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምሪትን ይሰጣሉ፣ ተመልሶ የሚመጣ መሆኑንም አመላካች ናቸው (ማቴ 24፥30-31 ይመ፤ ከራእ 19፥11—20፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

ዋናው ምልክት፣ "የጥፋት ርኵሰት" (ማቴ 24፥15) ነው፥ ይህም በታላቁ መከራ ጊዜ ያሉ ታማኞች በዘመኑ መጨረሻ የክርስቶስ ምጽአት መቃረቡን የሚረዱበት ልዩ የሆነ በግልጽ የሚታይ ሁነት ነው። ይህ ግልጽ የሆነ የሚታይ ሁነት በኢየሩሳሌም ያለው የአይሁድ ቤተ መቅደስ በሐሰተኛው ክርስቶስ ወደፊት የሚረክስበትን ሁኔታ በቅድሚያ የሚያመለክት ነው (ዳን 9፥27 እና ማብ ይመ፤ 1ዮሐ 2፥18፤ በገጽ 1913 ላይ፣ "የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ሐሰተኛው ክርስቶስ ወይም የዐመፅ ሰው የተባለው በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ የራሱን ምስል በማቆም አምላክነቱን ያውጃል (2ተሰ 2፥3-4 ራእ 13፥14-15)። የሚከተሉት ሐሳቦች ይህንን ዋና ሁነት በተመለከተ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እውነቶች ናቸው፤

(1) "የጥፋት ርኵሰት" የታላቁን መከራ የመጨረሻ ደረጃ ጅማሬን ያመለክታል፤ ይህም ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ በመምጣቱና በአርማጌዶን በክፉዎች ላይ እውን በሚያደርገው ፍርድ ፍጻሜ ያገኛል (ማቴ 24፥21፡29-30፤ ዳን 9፥27 ይመ፤ ራእ 19፥11-21)።

(2) ይህ ሁነት የሚፈጸምበትን ጊዜ ልብ በማለት ("ስታዩ" ማቴ 24፥15) የታላቁ መከራ ቅዱሳን የመከራው ዘመን የሚያበቃበትንና ክርስቶስ በምድር ላይ ለመግዛት ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ርግጠኛ በመሆን ማወቅ ይችላሉ (ማቴ 24፥33 እና ማብ ይመ)። በዚህ ሁነትና በመጨረሻው ዘመን መካከል ያለው የጊዜ ልክ ሦስት ዓመት ተኩል ወይም አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሥልሳ ቀን እንደ ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ጊዜ ተጠቅሶአል (ዳን 9፥25-27፤ ራእ 11፥1-2፤ 12፥6፤ 13፥5-7፤ ዳን 9፥25-27 እና ማብ ይመ)።

(3) የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በጕጕት ከመጠባበቅ የተነሣ (ማቴ 24፥33)፣ ዳግም ምጽአቱን በተመለከተ የሚነገር ማንኛውም ወሬ አታላይ ስለሆነ፣ ቅዱሳን መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል (ማቴ 24፥23-27)። ከታላቁ መከራ በኋላ "የሰው ልጅ መምጣት" በዓለም ውስጥ ባሉት ሁሉ ዘንድ የሚታወቅና የሚታይ ነው (ማቴ 24፥27-30)።

ሌላው ምልክት ሐሰተኛ ነቢያት የሰይጣን አገልጋዮች በመሆን መገለጣቸውና "ታላላቅ ምልክቶችንና ታምራትን" ማድረጋቸው ነው (ማቴ 24፥24)።

(1) በርግጥ ሐሰተኞች ሆነው ሳለ፥ ክርስቲያኖች ነን ከሚሉ ፈውስን፣ ምልክቶችንና ድንቆችን እያደረጉ፣ አገልግሎታቸው በታላቅ ሁኔታ እንደ ተሳካላቸው ከሚናገሩ ከእነዚህ ነቢያት፣ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ኢየሱስ ምክር ይሰጣል። በተመሳሳይ ጊዜ እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለውን እውነት ያጣምማሉ፤ ይቃወማሉም (ማቴ 7፥22 እና ማብ፡ ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1913 ላይ፣ "የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በሌላ ሰፍራ መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችን፥ መሪዎችንና ሰባኪዎችን ሁሉ የሚመራውን መንፈስ ባለማቋረጥ ክርስቲያኖች መፈተን እንደሚገባቸው ያሳስባል (1ዮሐ 4፥1 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔር አማኞች ለእርሱ ያላቸውን ፍቅርና ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያላቸውን ታማኝነት ይፈትን ዘንድ በታምራት የታጀበ አታላይ መንፈስ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሠራ ይፈቅዳል (ዘዳ 13፥3)። ይህ የመታለል ወቅት ቀላል አይሆንም፤ በማቴ 24፥24 ላይ በመጨረሻው ዘመን ሃይማታዊ ማታለል በስፋት የሚገለጥበት ጊዜ ስለ ሆነ፣ የተመረጡት እንኳ (ማለትም ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች) እውነተኛውን ከሐሰተኛው ለመለየት እንደሚቸገሩ ኢየሱስ ገልጾአልና (1ጢሞ 4፥16 እና ማብ፡ ያዕ 1፥21 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1860 ላይ፥ "ምርጫና አስቀድሞ መወሰን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤

(3) በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚገኙ ያሉ እውነትን የማይወዱ ሁሉ ይታለላሉ።

ሐሰተኛው ክርስቶስ ከመጣ በኋላ (2ተሰ 2፥11 እና ማብ ይመ)፣ የወንጌልን እውነት አምነው እንዲቀበሉ ተጨማሪ ዕድል አይሰጣቸውም።

በመጨረሻ ታላቁ መከራ በዓለም ላሉ ሰዎች ሁሉ የባሰ ሥቃይና መከራ ወቅት ይሆናል፤ በዚህም መሠረት የሚከተሉትን ልብ ይበሉ፡-

(1) መከራው ዓለም ዐቀፋዊ ነው (ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ)። (2) በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እስካሁን ድረስ እጅግ አስከፊ ከተባለው ሥቃይና መከራ ሁሉ የከፋ ይሆናል (ዳን 12፥1፤ ማቴ 24፥21)። (3) ለአይሁድ የከፋ የሥቃይ ዘመን ይሆናል (ኤር 30፥5-7)። (4) ዘመኑ ሁሉ "በዐመፅ ሰው" ተጽዕኖ ሥር ይሆናል (ይህም ሐሰተኛው ክርስቶስ ነው፤ ከዳን 9፥27፤ ከራእ 13፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1913 ላይ፤ "የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን" በሚል ርእስ የቀረበው የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (5) በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ታማኞች ከመከራው ዘመን ትድግና እንደሚያገኙና እንደሚያመልጡ ቃል ተገብቶላቸዋል (ሉቃ 21፥36 እና ማብ፤ 1ተሰ 5፥8-10፤ ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ)። (6) በዚህ ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑና የሚድኑ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ይኖራሉ (ዘዳ 4፥30-31፤ ሆሴ 5፥15፤ ራእ 7፥9-17፤ 14፥6-7)። (7) በእግዚአብሔር በመታመን ለሚጸኑ ሁሉ የታላቅ ሥቃይና የአስፈሪ ስደት ዘመን ይሆናል (ራእ 12፥17፤ 13፥15)። (8) በኀጢአተኞች ላይ የእግዚአብሔር ቍጣና ፍርድ የሚወርድበት ጊዜ ይሆናል (1ተሰ 5፥1-11፤ ራእ 6፥16-17)። (9) ኢየሱስ፣ "ቀኖቹ ያጥራሉ" (ማቴ 24፥22) ብሎ ሲናገር ለመከራው ከተወሰነው ሦስት ዓመት ተኩል ወይም አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሥልሳ ቀን የሚቀነስ ጊዜ ይኖራል ማለት አይደለም። ይልቁንም የመከራው ጊዜ ባይወሰን ኖሮ፣ የሰው ዘር ሁሉ ይጠፋ እንደ ነበር የሚያመለክት ይመስላል። (10) ታላቁ መከራ የሚያበቃው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሽራዪቱ ጋር በክብር ለታማኞቹ ነጻነትን ለመስጠት፣ በክፉዎች ላይ ደግሞ ፍርድንና ጥፋትን ለመፈጸም ሲመጣ ነው (ሕዝ 20፥34-38፤ ማቴ 24፥29-31፤ ሉቃ 19፥11-27፤ ራእ 19፥11-21)። (11) ታላቁ መከራ ሲያበቃ ጌታ ኢየሱስ ዳግም የሚመጣበትን ይህን ጊዜ በማቴ 24፥42፡44 ላይ ባልተጠበቀ ጊዜ ከሰማይ እንደሚወርድ ከተናገረው ጋር አሳክረን መመልከት የለብንም (ይህ ምጽአት በታላቁ መከራ ማብቂያ ላይ ከሚሆነው የክርስቶስ የመጨረሻ ምጽአት በተለየ ጊዜ እውን የሚሆነውን የአማኞችን መነጠቅ የሚመለከት እንደ ሆነ ከሚያሳዩት በእነዚህ ጥቅሶች ላይ የተጻፉ ማስታወሻዎችን ይመልከቱ)። (12) የሰባቱ ዓመት የመከራ ዘመን አጠቃላይ ማብራሪያ የተገለጸበት ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የሚገኘው በራእይ 6—18 ላይ ነው።

ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል። [41]ሁለት ሴቶች
በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች፣
ሌላዋ ትቀራለች።
[42]"እንግዲህ ጌታችሁ የሚመጣበትን
ቀን ስለማታውቁ ነቅታችሁ ጠብቁ።
[43]ይህን ልብ በሉ፤ ባለቤት ሌሊት ሌባ
በየትኛው ሰዓት እንደሚመጣ ቢያውቅ
ኖሮ፣ በንቃት ቤቱም እንዳይደፈር
በተጠባበቀ ነበር።
[44]የሰው ልጅም ባላሰባችሁት ሰዓት
ይመጣልና እናንተም እንደዚሁ ዝግጁ ሁኑ።
[45]"በተገቢው ጊዜ ምግባቸውን
እንዲሰጣቸው ባለቤቱ በቤቱ ሰዎቹ ላይ
የሾመው ታማኝና ብልኅ አገልጋይ እንግዲህ
ማነው? [46]ባለቤቱ ተመልሶ በሚመጣበት
ጊዜ የተጣለበትን ሀደራ እየፈጸመ
የሚያገኘው ያ አገልጋይ የተባረከ ነው፤
[47]እውነት እላችኋለሁ፤ በንብረቱ ሁሉ ላይ
ይሾመዋል። [48]ነገር ግን ያ አገልጋይ ክፉ
ቢሆንና ለራሱ፣ 'ጌታዬ ይዘገያል' በማለት፣

24፥41 ሉቃ17፥35
24፥42 ማቴ25፥13፤ ሉቃ12፥40
24፥43 ሉቃ12፥39
24፥44 1ተሰ5፥6
24፥45 ማቴ25፥21:23
24፥46 ራእ16፥15
24፥47 ማቴ25፥21:23

ወደ ራሱ ሲጠራ፣ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ከክፉዎች መካከል የሚለዩበትን ሁኔታ ያመለክታሉ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፡ በገጽ 1907 ላይ፥ *"ንቀቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ጌታ ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን አማኞች ሳያስቡት ስለሚያጋጥማቸው ሁኔታ በአጽንዖት ተናግሮአል (ቍ 37 እና ማብ ይመ)።

**24፥42 እንግዲህ ... ነቅታችሁ ጠብቁ፤** "ንቅታችሁ ጠብቁ" (በግሪክ ቋንቋ፣ ግሬጎሬኦ) የሚለው ሐረግ በአሁን ጊዜያት የተመለከተ ትእዛዝ አንቀጽ ነው፤ ይህም በአሁን ጊዜያት ሊፈጸም የሚገባን የማያቋርጥን ንቃት ያመለክታል። ስለ ወደፊቱ ብቻ ሳይሆን ዛሬ መንቃት ያስፈለገበት ምክንያቱ፣ የአሁኑ ዘመን አማኞች ጌታ ለእነርሱ የሚመጣበትን ጊዜ ባለማወቃቸው ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)። ለዚህ ዘመን አማኞች ምንም ዐይነት ማስጠንቀቂያ ምልክቶች አይሰጡም፤ ዛሬ ጌታ አይመጣም የሚል ግምትም ሊኖራቸው አይችልም። በሌላ አነጋገር ክርስቶስ በማንኛውም ጊዜ ሊመለስ ይችላል ለሚለው ታሪካዊ እውነታ ራሳቸውን መስጠት አለባቸው (ቍ 44 እና ማብ ይመ፡ ከማር 13፥33-37 ጋር ያነጻጽሩ)። ለቤተ ክርስቲያን የእርሱ ተመልሶ መምጣት በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል ነው።

**24፥42 የሚመጣበትን ጊዜ ስለማታውቁ፤** ደቀ መዛሙርቱ ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ክርስቶስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ፣ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ከዓለም ውስጥ ለመውሰድ ከመንግሥተ ሰማይ ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን (ይኸውም መነጠቅ ነው) እንደሚያመለክት መረዳት ይገባል (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንቀቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (1) ከታላቁ መከራ በፊት ለሚኖሩት ቅዱሳን ዳግም ምጽአቱ ባልተጠበቀ ጊዜና ያለ ማስጠንቀቂያ እንደሚሆን ኢየሱስ በግልጽ ይናገራል። እርሱ የተናገረው የሚመጣበትን ቀን አለማወቃቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ባላሰቡት ሰዓት (ቍ 44) የሚመጣ መሆኑን ጭምር ነው። ይህም ለታማኞቹ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድንገተኛ፣ አስደናቂና ባልተጠበቀ ጊዜ እንደሚሆን በግልጽ ያመለክታል። ይህ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጀመሪያው ደረጃ እንደ ሆነ ይጠቀሳል።

(2) ከታላቁ መከራ በኋላ ክርስቶስ በዓለም ላይ ለመፍረድ በኀይልና በክብር የሚመለስበትን ጊዜ በተመለከተ (ቍ 30፤ ራእ 19፥11-21)፣ ዳግም ምጽአቱ ይሆናል ተብሎ የታሰበ፣ የተጠበቀ፣ አስቀድሞ የታወቀ ይሆናል (ሉቃ 21፥28፤ ቍ 33 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በታላቁ መከራ ጊዜ የሚከሠቱት ሁኔቶችና ምልክቶች ለመከራው ዘመን ቅዱሳን የርግጠኝነትንና የመጠባበቅን ስሜት ያሳድራሉ እንጂ፣ የአሁን ዘመን የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን በመነጠቅ ጊዜ የሚሰማቸውን የመደነቅ ስሜት ዐይነት አያሳድሩባቸውም (ቍ 44 እና ማብ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)። ከታላቁ መከራ በኋላ እውን የሚሆነው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት አንዳንድ ጊዜ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሁለተኛ ደረጃ በመባል ይታወቃል።

**24፥43 ሌባ፤** በማይታወቅ ሰዓት እውን የሚሆነው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሌባ ድንገት ቤት ሰብሮ እንደሚገባ ዐይነት ነው። ስለዚህ ጌታ በማንኛውም ሰዓት ሊመጣ ስለሚችል፣ ትጉሕ ደቀ መዝሙር ተዘጋጅቶ መጠበቅ አለበት (ቍ 44)።

**24፥44 ባላሰባችሁት ሰዓት፤** ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ ታማኞች ባልተጠበቀና ባልታወቀ ሰዓት ተመልሶ ስለ መምጣቱ እንደ ገና ይናገራል፤ (1) ይህ ማስጠንቀቂያ ለታላቁ መከራ ቅዱሳን የተሰጠ አይደለም (በገጽ 1471 ላይ፥ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ በተመለከተ ባልተጠበቀ ጊዜ እንደሚመጣና (ቍ 42:44) "በተጠበቀ ጊዜ እንደሚመጣ" (ቍ 33) የተናገረውን ለማስማማት ያለው ብቸኛ መንገድ ዳግም ምጽአቱ ሁለት ደረጃዎች እንዳሉት ማሰብ ብቻ ነው። የመጀመሪያው ደረጃ ክርስቶስ አማኞችን ከምድር ለመውሰድ ባልተጠበቀ ጊዜ የሚመጣበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው (ከ1ተሰ 4፥17 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ *"ንቀቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ የዳግም ምጽአቱ ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዘመኑ መጨረሻ በተጠበቀ ጊዜ (ይኸውም ከታላቁ መከራና የሰማይ ላይ ምልክቶች ከታዩ በኋላ ነው፤ ቍ 29-30) ክፉዎችን ለማጥፋትና በምድር ላይ መንግሥቱን ለመጀመር የሚመጣበት ጊዜ ነው (ቍ 42 እና ማብ ይመ፤ ራእ 19፥11-21፤ 20፥4)።

(2) ይሁ የክርስቶስ ዳግሞ ምጽአት እንደ አንድ ሁነት ሁለት ደረጃዎችን የያዘ ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳን ስለ መሲሑ መምጣት የተነገረውን አስቀድሞ ያመለክታል። ብሉይ ኪዳን መሲሑ አንድ ጊዜ እንደሚመጣ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ ተፈጻሚነቱን በሁለት ደረጃዎች ያሳያል፥ ይኸውም ለኀጢአት ይሞት ዘንድ የመጣበትና ለመንገሥ የሚመጣበት ጊዜ ነው (ኢሳ 9፥2-7፤ 40፥3-5 ይመ፤ ኢሳይያስ 61፥1-3ን ከሉቃስ 4፥18-19 ጋር ያወዳድሩ፤ ኢሳ 9፥7 እና ማብ ይመ)።

(3) የሚመጣበት ጊዜ ስለማይታወቅ (ማለትም መነጠቅ)፣ በመንፈሳዊ ረገድ ምንጊዜም ዝግጁ መሆን እንደሚገባ ክርስቶስ የሰጠው አጣዳፊ ማስጠንቀቂያ፣ ከታላቁ መከራ በፊት ያለውን ማንኛውንም ክርስቲያን የሚመለከት ነው (ቍ 15-29)። ይህም በእምነት ለመጽናት የሚያስችል አነሣሽ መነሻ ምክንያት ነው።

**24፥48 ጌታዬ ይዘገያል፤** በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለጌታ ታማኞች ያልሆኑት ክርስቲያኖች፣ ክርስቶስ አሁን ሊመጣ አይችልም ብለው ካመኑ፣ ባልተጠበቀ ጊዜ የክርስቶስ መምጣት አሁን ነቅተው ለመጠበቅ

[49]ተነሥቶ ሌሎች አገልጋይ ባልንጀሮቹን
መምታት ቢጀምር፣ ከሰካራሞችም ጋር
ቢበላና ቢጠጣ፣ [50]እርሱ ባልጠበቀው
ቀንና ባላሰበው ሰዓት ጌታው መጥቶ፣
[51]ይቈራርጠዋል፤ ዕድል ፈንታውንም
ማቴ 25፥31-46 ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያም
ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

## የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ

25 "በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማይ
መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን
ሊቀበሉ የወጡ ዐሥር ልጃገረዶችን
ትመስላለች። [2]ከእነርሱም አምስቱ
ልጃገረዶች ዝንጉዎች፣ አምስቱ ደግሞ
አስተዋዮች ነበሩ፤ [3]ዝንጉዎቹ መብራት
ይዘው መጠባበቂያ ዘይት አልያዙም ነበር።
[4]አስተዋዮቹ ግን ከመብራታቸው ጋር
መጠባበቂያ ዘይት በማ ሰሮ ይዘው ነበር።
[5]ሙሽራው በዘገየ ጊዜ፣ ሁሉም እንቅልፍ
ተጫጫናቸውና ተኙ።
[6]"እኩለ ሌሊት ላይ፣ 'ሙሽራው እየመጣ
ነው፤ወጥታችሁ ተቀበሉት!' የሚል ጥሪ
ተሰማ።
[7]"በዚህ ጊዜ ልጃገረዶቹ ሁሉ ተነሥተው
መብራቶቻቸውን እየተረኰሱ መዘጋጀት
ያዙ። [8]ዝንጉዎቹ አስተዋዮቹን፣ 'መብራታ
ችን ሊጠፉብን ስለሆነ፣ ከዘይታችሁ
ስጡን' አሏቸው።
[9]"አስተዋዮቹ ልጃገረዶች ግን መልሰው፣
'ያለን ዘይት ለእኛም ለእናንተም ላይበቃ
ስለሚችል፣ ሂዳችሁ ከሻጮች ለራሳችሁ
ግዙ' አሏቸው።
[10]"ዘይት ሊገዙ እንደ ሄዱ፣ ሙሽራው
መጣ፤ ተዘጋጅተው የነበሩት ልጃገረዶችም
ወደ ሰርጉ ግብዣ አብረውት ገቡ፤ በሩም
ተዘጋ።
[11]"ዘግየት ብለው ሌሎቹ ልጃገረዶች
መጥ ተው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በሩን
ክፈት ልን' አሉ።
[12]"እርሱ ግን መልሶ፣ 'እውነት
እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም' አላቸው።
[13]"እንግዲህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ስለማ
ታውቁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ።

24፥49 ሉቃ21፥34
24፥51 ማቴ8፥12
25፥1 ማቴ13፥24፤ ሉቃ12፥35-38፤ ሐሥ20፥8፤ ራእ4፥5፤ 19፥7፤ 21፥2
25፥2 ማቴ24፥45
25፥5 1ተሰ5፥6
25፥8 ሉቃ12፥35
25፥10 ራእ19፥9
25፥12 ቍ41፤ ማቴ7፥23
25፥13 ማቴ24፥42፡44፤ ማር13፥35፤ ሉቃ12፥40
25፥14 ማቴ21፥33፤ ሉቃ19፥12
25፥15 ማቴ18፥24፡25

## የሰነፉ አገልጋይ ምሳሌ

*25፥14-30 ማጣ — ሉቃ 19፥12-27*

[14]"የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮቹን
ጠርቶ ያለውን ንብረት በዐደራ በመስጠት
ወደ ሌላ አገር ሊሄድ የተነሣ አንድ
ሰውን ትመስላለች፤ [15]ለእያንዳንዱ እንደ
ችሎታው በመደልደል ለአንዱ አምስት

[a]25፥15 አንድ ታላንት በሺህ የሚቈጠር ብር የሚያህል ነው

አንሣሽ ምክንያት ሊሆን አይችልም። (1) አንድ አማኝ ነኝ የሚል ሰው ክርስቶስ ምጽአቱን ለጥቂት ዓመታት ያዘገያል በማለት ሀነቢአት የሚመላለስ ከሆነ፥ እንደ ክፉው አገልጋይ ይቈጠራል። እንዲህ ዐይነቱ ሰው ክርስቶስ ድንገት ሲመጣበት ቅጣት የማይቀር መሆኑ አይሰማውም (ቍ 44 እና ማብ፣ ሉቃ 12፥45-46 እና ማብ ይመ)። (2) ኢየሱስ ታማኝ አለመሆንና ግብዝነትን፣ የክርስቶስ ምጽአት ይዘገያል ከሚለው እምነትና ምኞት ጋር እንደሚያያይዘው መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።
**25፥1-13 ይህ ክፍል የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ ይባላል።** ምሳሌው በአጽንዖት የሚያስገነዝበው ክርስቶስ ባልታወቀና ባልተጠበቀ ጊዜ ስለሚመጣ፣ አማኞች ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ከዚህ አንጻር ሳያቋርጡ መመርመር እንዳለባቸው ነው። ቀኑና ሰዓቱ ሲደርስ ተመልሶ የሚመጣው ጌታ ይቀበላቸው ዘንድ (ቍ 10) በእምነት መጽናት አለባቸው። እርሱ በሚመለስበት ጊዜ ከጌታ ጋር ሊኖር የሚገባን የግል ኅብረት ማድረግ አለመቻል፣ ከእርሱ ሀልዎትና ከመንግሥቱ መለየት ማለት ነው።

(1) ዝንጉዎቹን ከአስተዋዮቹ የሚለያቸው፣ ዝንጉዎቹ የሚመጣው ጌታ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ) ባልተጠበቀ ጊዜ ማለትም የማያጠራጥሩና የተለዩ ምልክቶች አስቀድመው ሳይከሡቱ እንደሚመጣ አለመረዳታቸው ነው (ቍ 13፤ 24፥36፡44 እና ማብ ይመ)።

(2) ክርስቶስ በዚህም ሆነ በሌላ ስፍራ ላይ (ሉቃ 18፥8)፥ እርሱ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አብዛኞዎቹ ዝግጁ ሆነው እንደማይጠብቁ አመልክቶአል (ቍ 8-13)። ለዳግም ምጽአቱ በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሁሉ ራሳቸውን ዝግጁ እስከሚያደርጉ ድረስ እንደማይጠብቅ ክርስቶስ በግልጽ ተናግሮአል።

(3) ልጃገረዶቹ በሙሉ (ታማኞቹም ሆኑ ታማኝ ያልሆኑት) ሙሽራው ድንገት ሳይታሰብ እንደመጣባቸው ልብ ማለት አስፈላጊ ነው (ቍ 5-7)። የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ የሚያመለክተው፣ ከመከራው በኋላ ከክርስቶስ ምጽአት በፊት በቂ ምልክቶችን የሚያዩትን በመከራው ዘመን የነበሩትን ሳይሆን፣ ከመከራው በፊት ያሉትን አማኞች ነው (በገጽ 147፤ ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።
**25፥4 ዘይት፤** ተከታታይነት ባላቸው መግለጫዎችና ምሳሌዎች ኢየሱስ (ምዕ 25) ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ታማኝነትና ንቁ መጠበቅ እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነ በአጽንዖት ተናግሮአል። የዐሥሩ ልጃገረዶች ምሳሌ የተሰጠው፣ አስቀድሞ ባልታወቀበት ቀን (ሉቃ 21፥19 እና ማብ) እውን የሚሆነው የክርስቶስ ምጽአት ከሚያስከትለው አሳሳቢ ሁኔታ የተነሣ፣ በእምነት የመጽናትንና የመንፈሳዊ ዝግጁነትን አስፈላጊነት በአጽንዖት ለማመልከት ነው። በምሳሌው ውስጥ የተጠቀሰው ዘይት እውነተኛ እምነትን፣ ጽድቅንና የመንፈስ ቅዱስን ሕያው ሀልዎት ይወክላል። ስለ ጽናት የሚያስተምሩ ሌሎች አምስት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፦ የዘሪው ምሳሌ (ሉቃ 8፥4-15)፣ የቤቱ ጌታ ምሳሌ (ሉቃ 12፥35-40)፣ የታማኙና የብልኁ መጋቢ ምሳሌ (ሉቃ 12፥42-48)፥ የሕንጻ ሠራተኛው ምሳሌ (ሉቃ 14፥28-30)፣ ጣዕም የሌለው ጨው ምሳሌ (ሉቃ 14፥34-35)።
**25፥15 ታላንት፤** የታላንቱ ምሳሌ በመንግሥተ ሰማይ ሊኖረን የሚገባ ስፍራና አገልግሎት በምድር ላይ ባለን የሕይወት ታማኝነትና አገልግሎት እንደሚወሰን ያመለክታል (ከቍ 29 ጋር ያነጻጽሩ)። ታላንት በምድር ሳለን እግዚአብሔርን ለማገልገል ያለንን ችሎታ፣ ጊዜ፣ የዕውቀት ምንጭ ሀብትና ምቹ ሁኔታዎች ይወክላል። እነዚህ ነገሮች የተሰጠ ንን ሁሉ ጥበብ በሞላበት መንገድና በአግባቡ መጠቀም የምንችልበትን ኀላፊነት የሚያመለክቱ ከእግዚአብሔር የተሰጡ ዐደራዎች ናቸው።

ታላንት፣[15] ለሌላው ሁለት፣ ለሌላው ደግሞ
አንድ ታላንት ሰጥቶ ጕዞውን ቀጠለ።
[16]አምስት ታላንት የተቀበለው ሰውዬ
ወዲያው በገንዘቡ ንግድ ጀምሮ አምስት
ታላንት አተረፈ፤ [17]እንዲሁም ሁለት
ታላንት የተቀበለው ሁለት አተረፈ፤
[18]አንድ ታላንት የተቀበለው ግን መሬት
ቈፍሮ የጌታውን ገንዘብ ደበቀ።
[19]"የአገልጋዮቹም ጌታ ከብዙ ጊዜ በኋላ
ከሄደበት ተመልሶ የሰጣቸውን ገንዘብ ተሳሰበ፤
[20]አምስት ታላንት የተቀበለውም፣ ሌላ
አምስት ተጨማሪ ታላንት ይዞ በመቅረብ፣
'ጌታ ሆይ! አምስት ታላንት ዐደራ ሰጥተኸኝ
ነበር፤ ይኸውልህ አምስት ተጨማሪ ታላንት
አትርፌአለሁ' አለው።
[21]"ጌታውም፣ 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለሆንህ በብዙ ነገር ላይ
እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' አለው።
[22]"እንዲሁም ሁለት ታላንት የተቀበለው
አገልጋይ ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ ሁለት ታላንት
ሰጥተኸኝ ነበር፤ ይኸው ሁለት ተጨማሪ
ታላንት አትርፌአለሁ' አለው።
[23]"ጌታውም፣ 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ
መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር
ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ
እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' አለው።
[24]"አንድ ታላንት የተቀበለው አገልጋይ
ቀርቦ፣ 'ጌታ ሆይ፤ አንተ ካልዘራህበት
የምታጭድ፣ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ
ጨካኝ ሰው መሆንህን ዐውቃለሁ፤ [25]ስለዚህ
ፈራሁ፤ ሄጄም መሬት ቈፍሬ ታላንትህን
ጕድጓድ ውስጥ ደበቅሁት፤ ገንዘብህ
ይኸውልህ' አለው።
[26]"ጌታውም መልሶ፣ 'አንተ ክፉ፣
ሰነፍ አገልጋይ፤ ካልዘራሁበት የማጭድ፤
ካልበተንሁበትም የምሰበስብ መሆኔን ታውቅ
ኖሮአል? [27]ታዲያ፣ በምመለስበት ጊዜ
ገንዘቤን ከነወለዱ እንዳገኘው ለለዋጮች
መስጠት ይገባህ ነበር።
[28]"'በሉ እንግዲህ ታላንቱን ወስዳችሁ
ዐሥር ታላንት ላለው ስጡ፤ [29]ላለው
ይጨመርለታል፤ የተትረፈረፈም
ይኖረዋል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ
ይወሰድበታል። [30]ይህን የማይረባ አገልጋይ
ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት
በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጥታችሁ
ጣሉት' አለ።

## የመጨረሻው ፍርድ

[31]"የሰው ልጅ ከመላእክቱ ሁሉ ጋር በክ
ብሩ ሲመጣ፣ በክብሩ ዙፋን ላይ ይቀመጣል፤
[32]ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እርሱም፣
እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ፣
ሕዝቡን አንዱን ከሌላው ይለያል፤
[33]በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎቹን ግን በግራው
ያቆማቸዋል።
[34]"በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል
ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንት አባቴ
የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ
የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፤
[35]ምክንያቱም ተርቤ አብልታችሁኛል፤
ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ
ተቀብላችሁኛል፤ [36]ታርዤ አልብሳችሁኛል፤
ታምሜ አስታምማችሁኛል፤ ታስሬ
ጠይቃችሁኛል።'
[37]"ጻድቃንም መልሰው እንዲህ
ይሉታል፤ 'ጌታ ሆይ፤ ተርበህ አይተን
መቼ አበላንህ? ወይም ተጠምተህ አይተን
መቼ አጠጣንህ? [38]እንግዳ ሆነህ አይተን
መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን
መቼ አለበስንህ? [39]እንዲሁም ታመህ
ወይም ታስረህ አይተን መቼ ጠየቅንህ?'
[40]"ንጉሡም መልሶ፣ 'እውነት
እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት
ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁትን፣ ለእኔ
እንዳደረጋችሁት ነው' ይላቸዋል።
[41]"ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ
እንዲህ ይላቸዋል፤ 'እናንተ የተረገማችሁ፤
ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው

25፥19 ማቴ18፥23
25፥21 ቍ 23፤ ማቴ24፥45፡47፤ ሉቃ16፥10
25፥23 ቍ 21
25፥29 ማቴ13፥12፤ ማር4፥25፤ ሉቃ8፥18፤ 19፥26
25፥30 ማቴ8፥12
25፥31 ማቴ19፥28፤ ሉቃ17፥30
25፥32 ሚል3፥18፤ ሕዝ34፥17፡20
25፥34 ማቴ3፥2፤ 5፥3፡10፡9፤ 19፥14፤ ሐሥ20፥32፤ 1ቆሮ15፥50፤ ገላ5፥21፤ ዕብ4፥3፤ 9፥26፤ ያዕ2፥5፤ ራእ13፥8፤ 17፥8
25፥35 ኢዮ31፥32፤ ዕብ13፥2
25፥36 ኢሳ58፥7፤ ሕዝ18፥7፤ 2ጢሞ1፥16፤ ያዕ1፥27፤ 2፥15፡16
25፥40 ማቴ10፥40፡42፤ ዕብ13፥2
25፥41 ኢሳ66፥24፤ ማቴ3፥12፤ 5፥22፤ 7፥23፤ ማር9፥43፡48፤ ሉቃ3፥17፤ 2ጴጥ2፥4፤ ይሁ7

**25፥29 ላለው፤** አማኝ በመንግሥተ ሰማይ የሚኖረውን ሽልማትና ስፍራ በተመለከተ ኢየሱስ አስፈላጊ የሆነ መርሕ ሰጥቶአል። አማኞች ወደፊት ከእግዚአብሔር መንግሥት የሚቀበሉት አሁን በእጃቸው በያዙት ነገር ይወሰናል። በመንግሥተ ሰማይ የሚኖራቸው ማዕረግና ርስት አሁን ለእግዚአብሔር መንገድና መንግሥት ካላቸው መሰጠት ጋር የሚመጣጠን ይሆናል (ሉቃ 22፥24-30 እና ማብ ይመ)።

**25፥32 በጎችን ከፍየሎች፤** በበጎችና በፍየሎች ላይ የሚሰጠው ፍርድ ከታላቁ መከራ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት የሚፈጸም ሲሆን፤ ክርስቶስ በምድር ንግሥ አገዛዙን ከመጀመሩ በፊት ይከናወናል (ከዳን 7፥9-14፤ ከራእ 5፥10፤ 19፥11-20፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ የመከራውን ጊዜ ያለፉና በምድር ላይ የሚኖሩት የዳኑትና የጠፉት በአንድነት ይቀላቀላሉ፤ (2) ፍርዱ ክፉዎችን ከጻድቃን መለየትን የሚያካትት ነው (ቍ 32-33፤ 13፥41 እና ማብ ይመ)፤ (3) ፍርዱ በክርስቶስ ላሉትና ሥቃይን ለሚያዩት በማድረግ ተጨባጭ የፍቅርና የቸርነት ሥራ ላይ ይመሠረታል። ፍቅርንና ርኅራኄን መግለጽ የእውነተኛ እምነትና ድነት ተፈጥሮአዊ ክፍል እንደ ሆነ ይቈጠራል (ቍ 35-46)፤ (4) ክፉዎች ወደ ክርስቶስ መንግሥት እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፤ ነገር ግን ወደ ዘላለማዊ ጥፋት ውስጥ ይገባሉ (ቍ 41፡46፤ ራእ 14፥11)፤ (5) ጻድቃን የዘላለምን ሕይወትና (ቍ 46) የእግዚአብሔርን መንግሥት ይወርሳሉ (ቍ 34፤ ራእ 20፥4 እና ማብ ይመ)።

**25፥41 ለዲያብሎስና ለመላእክቱ፤** ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያካሄደው የመጀመሪያው ዐመፅ (4፥10 እና ማብ ይመ) ከሰማይ መላእክት ሦስት እጅን ያህል ወደ እርሱ ሳበ (ራእ 12፥4)፤ ከእነዚህ የተወሰኑት በገሃነም ሲታሰሩ (2ጴጥ 2፥4፤ ይሁ 1፥6)፣ ሌሎቹ ተለቀው በሰይጣን ግዛትና ቍጥጥር ሥር ሆነው ይገኛሉ (12፥24፤ 25፥41፤ ኤፌ 2፥2፤ ራእ 12፥7)። እነዚህ የተለቀቁት መላእክት በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁ መልእክተኞቹ ሲሆኑ (ኤፌ 6፥11-12)፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት አጋንንት ጋር ተመሳሳይ ሳይሆኑ አይቀሩም (በገጽ 1499 ላይ፣ «በሰይጣንና

የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ፤ 42ምክንያቱም ተርቤ አላበላችሁኝምና፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፤ 43እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፤ ታምሜና ታስሬ አልጠየቃችሁኝም።'

44"እነርሱም መልሰው፣ 'ጌታ ሆይ፤ ተርበህ ወይም ተጠምተህ፣ እንግዳ ሆነህ ወይም ታርዘህ፣ ታመህ ወይም ታስረህ ዐይተን መቼ አልደረስንልህም' ይሉታል።

45"በዚያን ጊዜ እርሱም መልሶ፣ 'እውነት እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ላላማድረጋችሁ፣ ለእኔ እን ዳላደረጋችሁት ነው' ይላቸዋል።

46"እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን
ማቴ 26፡64 ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።"

## አይሁድ በኢየሱስ ላይ መዶለታቸው

*26፡2-5 ተጓ ምብ — ማር 14፡1፡2፤ ሉቃ 22፡1፡2*

**26** ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱን፣ 2"ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንደሚሆን ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል" አላቸው።

3ከዚህ በኋላ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ቀያፋ በተባለ ሊቀ ካህን ግቢ ውስጥ ተሰብስበው፤ 4በረቀቀ መንገድ ኢየሱስን ለማስያዝና ለማስገደል ተማከሩ። 5ነገር ግን፣ "በሕዝቡ መካከል ረብሻ እንዳ ይነሣ በበዓል ቀን አይሁን" በማለት ተስማሙ።

## ኢየሱስን ሽቶ የቀባችው ሴት

*26፡6-13 ተጓ ምብ — ማር 14፡3-9*
*26፡6-13 ማመ — ሉቃ 7፡37፡38፤ ዮሐ 12፡1-8*

6ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ፣ 7አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ አንድ ብልቃጥ የአልባስጥሮስ ሽቶ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች፤ በማእድ ላይ ተቀምጦ ሳለም በራሱ ላይ አፈሰሰችው።

8ደቀ መዛሙርቱ ይህንን በተመለከቱ ጊዜ ተቈጥተው እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሁሉ ብክነት ለምንድነው? 9ሽቶው በብዙ ዋጋ ተሽጦ ገንዘቡን ለድኾች መስጠት ሲቻል!"

25፡45 ምሳ14፡31፤ 17፡5
25፡46 ዳን12፡2፤ ማቴ19፡29፤ ዮሐ3፡15፡16፡36፤ 5፡29፤ 17፡2፡3፤ ሐሥ24፡15፤ ሮሜ2፡7፤ ገላ6፡8፤ 1ዮሐ1፡2፤ 5፡11፡13፡20
26፡1 ማቴ7፡28
26፡2 ዮሐ11፡55
26፡3 ቍ57፤ መዝ2፡2፤ ሉቃ3፡2፤ ዮሐ11፡47-53፤ 18፡13፡14፡24፡28፤ ሐሥ4፡6
26፡4 ማቴ12፡14
26፡5 ማቴ27፡24
26፡6 ማቴ21፡17
26፡11 ዘዳ15፡11
26፡12 ዮሐ19፡40
26፡14 ቍ25፡47፤ ማቴ10፡4
26፡15 ዘፀ21፡32፤ ዘካ11፡12
26፡17 ዘፀ12፡18-20፤ ዘዳ16፡5-8
26፡18 ማር14፡35፡41፤ ዮሐ7፡6፡8፡30፤ ዮሐ8፡20፤ 12፡23፤ 13፡1፤ 17፡1
26፡21 ሉቃ22፡21-23፤ ዮሐ13፡21

10ኢየሱስ ይህን ዐውቆ እንዲህ አላቸው፤ "ይህችን ሴት ለምን ታስቸግሯታላችሁ? መልካም ነገር አድርጋልኛለች፤ 11ድኾች ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ናቸው፤ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልሆንም። 12ሽቶውን በሰውነቴ ላይ በማፍሰሷ፣ እኔን ለቀብር ለማዘጋጀት ነው፤ 13እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም ዙሪያ ሁሉ፣ በየትኛውም ስፍራ እርሷ ያደረገችው በመታሰቢያነት ይነገርላታል።"

## ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ተስማማ

*26፡14-16 ተጓ ምብ — ማር 14፡10፡11፤ ሉቃ 22፡3-6*

14ከዚህ በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የነበረውና የአስቆሮቱ ይሁዳ የተባለው ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ፣ 15"እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ እናንተስ ምን ትሰጡኛላችሁ?" አላቸው። እነርሱም ሠላሳ ጥሬ ብር ቈጥረው ሰጡት። 16ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይሁዳ፣ ኢየሱስን አሳልፎ የሚሰጥበትን አመቺ ጊዜ ይፈልግ ነበር።

## የጌታ ራት

*26፡17-19 ተጓ ምብ — ማር 14፡12-16፤ ሉቃ 27፡7-13*
*26፡20-24 ተጓ ምብ — ማር 14፡17-21*
*26፡26-29 ተጓ ምብ — ማር 14፡22-25፤ ሉቃ 22፡17-20፤ 1ቆሮ 11፡23-25*

17በቂጣ በዓል የመጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ "ፋሲካን እንድትበላ የት እንድናዘጋጅልህ ትፈልጋለህ?" አሉት።

18እርሱም፣ "ወደ ከተማ ሂዳችሁ እገሌ የተባለውን ሰው፣ 'መምህር ጊዜዬ ተቃርቦአልና ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን በቤትህ አከብራለሁ ብሏል' በሉት" አላቸው። 19ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ ባዘዛቸው መሠረት የፋሲካን ራት አዘጋጁ።

20በመሸም ጊዜ ኢየሱስ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር በማእድ ተቀመጠ፤ 21በመብላት ላይ ሳሉም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል" አላቸው።

22እነርሱም እጅግ አዝነው፣ ተራ በተራ፣ "ጌታ ሆይ፤ እኔ እሆን ይሆን?" አሉት።

---

*በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

26፡2 ፋሲካ፤ ፋሲካ (በግሪክ ቋንቋ፣ "ፓስካ") በታሪክ ሂደት ውስጥ እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡበት ሁኔታ ጋር የተያያዘ የፀደይ ወራት በዓል ነው። በዓሉ የሚከበረው እግዚአብሔር ግብፅን ሲቀጣ መቃኖቻቸውና ጉበኖቻቸው በበግ ደም በመቀባታቸው፣ የዕብራውያንን ቤቶች የሞት መልአክ "ያለፈበትን" ሁኔታ የሚያስታውስ ነው (ዘፀ 12፡7 እንዲሁም በገጽ 129 ላይ፣ *"የፋሲካ በዓል"* ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው፣ "የፋሲካ በዓል መዘጋጃ" በሆነበት ዕለት ነበር (ዮሐ 19፡14)፤ እርሱ የተሠዋልን "የፋሲካ በጋችን" ነውና (1ቆሮ 5፡7)።

26፡13 **በመታሰቢያነት፤** ይህ የማርያም ታሪክ (ቍ 6-13) ምንጊዜም ወንጌል ሲሰበክ አብሮ መነገር እንዳለበት ጌታ አዞአል። እንዲህ የተደረገውም የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ ከማንም ይልቅ የእርሷን የመስጠት ምሳሌ እንዲከተሉ ነው። የእርሷ ድርጊት ለጌታ ያላትን እውነተኛ መስጠትና ጥልቅ ፍቅር የሚገልጥ ነው። የክርስትና እምነት ሲባል በመሠረቱ በመጀመሪያ በግል ጌታን ማገልገል ነው። ለኢየሱስ ያለን ልባዊ ቅርበትና ፍቅር ከእርሱ ጋር ላለን ግንኙነት ከፍተኛ ዋጋ ያለው መሆኑን ከዚህ እንማራለን (ዮሐ 21፡15 እና ማብ ይመ)።

[23]እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እሳልፎ የሚሰጠኝ ከወጭቱ ውስጥ አብሮኝ
ያጠቀሰው ነው፤ [24]የሰው ልጅ ስለ እርሱ
እንደ ተጻፈው ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰውን
ልጅ አሳልፎ ለሚሰጠው ሰው ወዮለት፤ ለዚያ
ሰው ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው ነበር።"
[25]አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም፣ "መምህር
ሆይ፣ እኔ እሆንን?" አለው።
እርሱም፣ "አንተ አልህ"[a] አለው።
[26]እየበሉ ሳሉ፣ ኢየሱስ እንጀራን
አንሥቶ ባረከ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ
በመስጠት፣ "እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ
ነው" አላቸው።
[27]ከዚያም ጽዋውን አንሥቶ አመሰገነ፤
ለደቀ መዛሙርቱም በመስጠት እንዲህ አላ
ቸው፤ "ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ፤ [28]ስለ ብዙ
ዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የእዲስ
ኪዳን ደሜ ይህ ነው። [29]እላችኋለሁ፤ በአ ባቴ
መንግሥት ከእናንተ ጋር በአዲስ መልክ
እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ፣ ከእ
ንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም።"
[30]መዝሙር ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ
ዘይት ተራራ ወጡ።

## የጴጥሮስ ክህደት አስቀድሞ መነገሩ

*26፥31-35 ተጓ ምብ — ማር 14፥27-31፤ ሉቃ 23፥31-34*

[31]ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤
"ሁላችሁም በዚህች ሌሊት በእኔ ተሰናከላችሁ
ትሄዳላችሁ፤ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
"'እረኛውን እመታለሁ፤
የመንጋውም በጎች ይበተናሉ።'
[32]ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ቀድሜአችሁ
ወደ ገሊላ እሄዳለሁ።"
[33]ጴጥሮስም መልሶ፣ "ሌሎች በሙሉ
ባንተ ምክንያት ቢሰናከሉ እንኳ እኔ በፍ
ጹም አልሰናከልም!" አለው።
[34]ኢየሱስም፣ "እውነት እልሃለሁ፤
በዛሬዋ ሌሊት ዶሮ ከመጮኹ በፊት ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ" አለው።
[35]ጴጥሮስ ግን "ከአንተ ጋር መሞት
ቢያስፈልግ እንኳ ከቶ አልክድህም!"
አለው። ሌሎቹም ደቀ መዛሙርት በሙሉ
እንደዚሁ አሉ።

## የኢየሱስ ጸሎት በጌቴሴማኒ

*26፥36-46 ተጓ ምብ — ማር 14፥32-42፤ ሉቃ 22፥40-46*

[36]ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ስፍራ ሄደ፤
እነርሱንም፣ "ወደዚያ ሄጄ በምጸልይበት
ጊዜ እና ንተ እዚህ ተቀመጡ" አላቸው።
[37]ከእር ሱም ጋር ጴጥሮስንና ሁለቱን
የዘብደዎስ ልጆች ይዞ በመሄድ ይተከዝና
ይጨነቅ ጀመር፤ [38]ከዚያም፣ "ነፍሴ እስከ
ሞት ድረስ እጅግ አዘነለች፤ ከእኔ ጋር
በመትጋት እዚሁ ቈዩ" አላቸው።
[39]ጥቂት ዕልፍ ብሎ በግንባሩ በመደፋት፣

26፥23 መዝ41፥9፤ ዮሐ13፥18
26፥24 ቍ31፡54፡56፤ ኢሳ53፤ ዳን9፥26፤ ማር9፥12፤ ሉቃ24፥25-27፡46፤ ሐሥ17፥2፡3፤ 26፥22፡23፤ 1ጴጥ1፥10፡11
26፥25 ማቴ10፥4፤ 23፥7
26፥26 ማቴ14፥19
26፥27 1ቆሮ10፥16
26፥28 ዘፀ24፥6-8፤ ዘካ9፥11፤ ሚል2፥5፤ ማቴ20፥28፤ ማር1፥4፤ ዕብ9፥20፤ 10፥29፤ 13፥20
26፥29 ሐሥ10፥41
26፥30 ማቴ21፥1
26፥31 ዘካ13፥7፤ ማቴ11፥6፤ ዮሐ16፥32
26፥32 ማቴ28፥7፡10፡16
26፥34 ቍ75፤ ዮሐ13፥38
26፥35 ዮሐ13፥37
26፥37 ማቴ4፥21
26፥38 ቍ40፡41፤ ዮሐ12፡27
26፥39 ቍ42፤ መዝ40፥6-8፤ ኢሳ50፥5፤ ማቴ6፥10፤ 20፥22፤ ዮሐ4፥34፤ 5፥30፤ 6፥38

[a]26፥25 *«ወይም አንተ ራስህ ተናገርህ»*

**26፥26 እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ሥጋዬ ነው፤** በ1ቆሮ 11፥24-25 በጌታ እራት ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**26፥28 የአዲስ ኪዳን፤** በገጽ 1970 ላይ፥ *«የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**26፥28 የኀጢአት ይቅርታ፤** ኀጢአትን ስለ ሠራን፣ ከእግዚብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ስላበላሸንና ለፍርድ የተዳረግን ስለ ሆንን፣ ይቅርታ አስፈላጊ ነው (ሮሜ 1፥18-32)። ይህ ግንኙነት ሊስተካከል የሚችልበት መንገድ ይቅርታ ነው (ኤፌ 1፥7፤ ቈላ 2፥13)።

(1) ለይቅርታ የተሰጡት የዕብራይስጥና የግሪክ ቃላት፣ «መሸፈን»፣ «ምሕረት ማድረግ»፣ «መተው»፣ «ማስወገድ» የሚሉትን ሐሳቦች ያመለክታሉ። የእግዚአብሔር ይቅርታ የተፈጸመውን ኀጢአት አለማሰብን (ማር 2፥5፤ ዮሐ 8፥11)፣ ኀጢአተኞችን ከዘላለም ቅጣት ማዳንን (ሮሜ 5፥9፤ 1ተሰ 1፥10)፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንዲቀላቀሉ በምሕረት መቀበልን (ሉቃ 15፥20 …)፣ ከኀጢአት ግዛት ነጻ እንዲወጡ መታደግንና ወደ ክርስቶስ መንግሥት እንዲገቡ ማሻገርን (ቈላ 1፥13) እንዲሁም ሁለንተናቸው እንዲታደስ ማድረግንና የዘላለም ሕይወት ተስፋ እንዳላቸው ማሳወቅን ያካትታል (ሉቃ 23፥43፤ ዮሐ 14፥19ለ)።

(2) ይቅርታን ለመቀበል ንስሓ መግባት፥ ማመንና ኀጢአትን መናዘዝ ያስፈልጋል (ሉቃ 17፥3-4፤ ሐሥ 2፥38፤ 5፥31፤ 20፥21፤ 1ዮሐ 1፥9)። እግዚአብሔር ይቅርታን ይሰጥ ዘንድ፣ ደም መፍሰስ ነበረበት (ዕብ 9፥22)። ስለዚህ ይቅርታን ማግኘት በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት ተመሥርቶአል (ቍ 28፤ ዮሐ 1፥29፤ 3፥16፤ ሮሜ 8፥32)። መለኮታዊ ይቅርታ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የድነት ግንኙነት የምንጠብቅበትና የማያቋርጥ አስፈላጊ ሂደት ነው (6፥12፡14-15፤ 1ዮሐ 1፥9)።

**26፥37 ይተክዝና ይጨነቅ ጀመር፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ የመጀመሪያው ደረጃ ነው። የክርስቶስ አካላዊና መንፈሳዊ ሥቃይ የጀመረው በጌቴሴማኒ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በጌቴሴማኒ የነበረውን ሥቃይ እንዲህ ይገልጸዋል፥ «ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር» (ሉቃ 22፥44)። በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ላብ በሚያመነጭ ዕጢ ውስጥ ያሉ ትንንሽ የደም ቧምቧዎች ተቀደው ደምና ላብ እንዲቀላቀል ሊያደርጉ ይችላሉ (ክርስቶስ የተሠቃየበትን የዚህን ደረጃ ሁኔታ የበለጠ ለመረዳት የሚቀጥለውን ማብ ይመ፤ የክርስቶስን ሥቃይ ሁለተኛ ደረጃ ለመረዳት ደግሞ ቍ 67 እና ማብ ይመ)።

**26፥39 ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤** ክርስቶስ፣ «ይህ ጽዋ» ያለው የብዙ ውይይት ርእስ ጕዳይ ነበር፤ (1) ክርስቶስ ከአካላዊ ሞት ለመዳን የጸለየ መሆኑ አጠራጣሪ ነው፤ ለሰው ልጅ ኀጢአት ለመሞት ራሱን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ ሰጥቶአልና (ከማር 10፥33-34፤ ከሉቃ 9፥51፤ ከዮሐ 12፥24፡27፤ ከዕብ 10፥5-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ለኀጢአት የመጨረሻ ቅጣት ከሆነው ሞት ማለትም ከአባቱ ከመለየት ቅጣት ይድን ዘንድ መጸለዩ ይበልጥ እውነት ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ አካላዊ ሞቱ ለበደለኞች ኀጢአት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ተቀባይነትን ያገኘ

"አባቴ ሆይ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ፤
ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ
እንደምትፈልገው ይሁን" ብሎ ጸለየ።
[40]ከዚያም ተመልሶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ
ሲመጣ፣ ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም
እንዲህ አለው፤ "እናንት ሰዎች፤ ከእኔ ጋር
ለአንድ ሰዓት እንኳ መትጋት አቃታችሁን?
[41]ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስ
ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው።"
[42]እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ሄዶ፣ "አባት
ሆይ፤ ይህ ሳልጠጣው የማያልፍ ጽዋ ከሆነ፣
ፈቃድህ ይፈጸም" ብሎ ጸለየ።
[43]እንደገናም በመጣ ጊዜ ዐይኖቻቸው
በእንቅልፍ ከብደው ስለ ነበር ተኝተው አገ
ኛቸው። [44]ትቶአቸውም እንደገና በመሄድ
ለሦስተኛ ጊዜ ቀደም ብሎ የጸለየውን ጸሎት
ደገመ።
[45]ከዚያም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ
እንዲህ አላቸው፤ "አሁንም ዐርፋችሁ
ተኝታችኋል? እነሆ፣ ሰዓቱ ቀርቦአል፤ የሰው
ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ይሰጣል፤
[46]ተነሡ እንሂድ፤ አሳልፎ የሚሰጠ ኝም
እየመጣ ነው።"

## የኢየሱስ መያዝ

*26፥47-56 ተጓ ምብ — ማር 14፥43-50፤ ሉቃ 27፥47-53*

[47]በመናገር ላይ እያለ፣ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከካህናት አለቆችና
ከሕዝቡ ሽማግሌዎች ዘንድ የተላኩ ሰይፍና
ዱላ የያዙ ብዙ ሰዎችም አብረውት ነበሩ።
[48]ይሁዳም፣ "እኔ የምስመው እርሱ ነው፤
ያዙት" ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ስለ ነበር፣
[49]በቀጥታ ወደ ኢየሱስ ሄዶ፣ "መምህር ሆይ፤
ሰላም ለአንተ ይሁን" በማለት ሳመው።
[50]ኢየሱስም፣ "ወዳጄ ሆይ፤ የመጣህበትን
ፈጽም"* አለው።
በዚህ ጊዜ ሰዎቹ ቀርበው ኢየሱስን
ያዙት፤ አሰሩትም። [51]ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት
አንዱ፣ ሰይፉን መዝዞ በመሰንዘር የሊቀ ካህ
ናቱን አገልጋይ ጆሮውን ቈረጠው።
[52]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "በል
ሰይፍህን ወደ ሰገባው መልስ፤ ሰይፍን
የሚመዝዙ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ።
[53]ከሰፈለግ አባ ቴን ብጠይቀው ከዐሥራ
ሁለት ክፍለ ሰራዊት የሚበልጡ መላእክት
የማይሰድልኝ ይመስልሃል? [54]ይህ ቢሆን
ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ይሆናል ያሉት
ነገር እንዴት ይፈጸማል?"
[55]በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ሕዝቡን እንዲህ
አላቸው፤ "ወንበዴ እንደሚይዝ ሰው
ሰይፍና ዱላ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁ?
በየዕለቱ በቤተ መቅደስ ተቀምጬ ሳስተምር
አልያዛችሁኝም ነበር፤ [56]ነገር ግን ይህ
ሁሉ የሆነው ነቢያት በቅዱሳት መጻሕፍት
የተናገሩት ይፈጸም ዘንድ ነው።" በዚያን
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጥለውት ሸሹ።

## ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት

*26፥57-68 ተጓ ምብ — ማር 14፥53-65፤ ዮሐ 18፥12-13፡19-24*

[57]በዚህ ጊዜ ኢየሱስን የያዙት ሰዎች፣
የኦሪት የሕግ መምህራንና የሕዝብ
ሽማግሌዎች ተሰብስበው ወደ ነበሩበት፣
ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት።
[58]ነገር ግን ጴጥሮስ ክርቀት ሆኖ እስከ
ሊቀ ካህናቱ ቅጥር ግቢ ይከተለው ነበር፤
ወደ ውስጥ ገብቶም የሁኔታውን መጨረሻ
ለማየት ከጠባቂዎች ጋር ተቀመጠ።
[59]በዚህ ጊዜ የካህናት አለቆችና የአይሁድ
ሸንጎ በሙሉ ኢየሱስን ለማስገደል የሐሰት
ማስረጃ ይፈልጉ ነበር፤ [60]ብዙ የሐሰት ምስ
ክሮች ቢቀርቡም በቂ ማስረጃ አላገኙም፤
በኋላ ግን ሁለት ሰዎች ቀርበው፣ [61]"ይህ
ሰው፣ 'የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ፣
በሦስት ቀን ውስጥ መልሼ ልሠራው እች
ላለሁ' ብሎአል" በማለት ተናገሩ። [62]በዚህ
ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ተነሥቶ በመቆም፣
"እነዚህ ሰዎች ለሚመሰክሩብህ ሁሉ ምንም
መልስ አትሰጥምን?" አለው። [63]ኢየሱስ ግን
ዝም አለ።
ሊቀ ካህናቱም፣ "በሕያው እግዚአብሔር ስም
አምልሃለሁ፤ አንተ ክርስቶስ" የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆንህ ንገረን" አለው።
[64]ኢየሱስም፣ "አንተው ራስህ ብለኸዋል፤
ነገር ግን ለሁላችሁም ልንገራችሁ፤ ወደ ፊት

26፥40 ቍ38
26፥41 ማቴ6፥13
26፥42 ቍ39
26፥45 ቍ18
26፥47 ማቴ10፥4
26፥49 ቍ25፤ ማቴ23፥7
26፥50 ማቴ20፥13፤ 22፥12
26፥51 ሉቃ22፥36፤ ዮሐ18፥10
26፥52 ዘፍ9፥6፤ ዘፀ21፥12፤ ራእ13፥10
26፥53 2ነገ6፥17፤ ዳን7፥10፤ ማቴ4፥11
26፥54 ቍ24፤ ማቴ1፥22
26፥55 ማር12፥35፤ ሉቃ21፥37፤ ዮሐ7፥14፡28፤ 18፥20
26፥56 ቍ24፤ ማቴ1፥22
26፥57 ቍ3
26፥58 ቍ69፤ ማር14፥66፤ 15፥16፤ ሉቃ11፥21፤ 22፥55፤ ዮሐ7፥32፡45፡46፤ 18፥15
26፥59 ማቴ5፥22
26፥60 ዘዳ19፥15፤ መዝ27፥12፤ 35፥11፤ ሐሥ6፥13
26፥61 ዮሐ2፥19
26፥63 ዘሌ5፥1፤ ማቴ4፥3፤ 16፥16፤ ማር14፥61፤ ሉቃ22፥67
26፥64 ማቴ27፥11፤ ማር16፥19፤ ሉቃ22፥70፤ ራእ1፥7

*26፥50 ወይም «ወዳጄ ሆይ፤ ለምን መጣህ?»
"26፥63 ወይም «መሲሑ»፤ ቍ68 ይመ

ዘንድ ጸልዮአል። ሲጸልይ ግን፣ «እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን፣ አንተ እንደምትፈልገው ይሁን» ብሎአል። ከዚያም ለእኛ ድነትን ያስገኝልን ዘንድ አካላዊ ሞትን ሊሞትና ከሰማያዊ አባቱ በመንፈስ ሊለይ ራሱን አሳልፎ ሰጠ (ከ27፥46 ጋር ያነጻጽሩ)። ጸሎቱ ተሰማለት፤ የተወሰነበትን ጽዋ ይጠጣ ዘንድ በአባቱ ብርታትን አግኝቶአልና (ዕብ 5፥7 ይመ)።

**26፥57 ኢየሱስን የያዙት፤** ክርስቶስ ከተያዘበት ጀምሮ በመስቀል እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ ማጥናት መንፈሳዊ በረከትን የሚያስገኝ ሊሆን ይችላል። ቅደም ተከተሉ እንደሚከተለው ነው፤ (1) መያዙ (26፥47-56፤ ማር 14፥43-52፤ ሉቃ 22፥47-53፤ ዮሐ 18፥2-12)፤ (2) በሐና (ዮሐ 18፥12-14፡19-24) እና በቀያፋ (26፥57፡59-68፤ ማር 14፥53፡55-65፤ ሉቃ 22፥54፡63-65፤ ዮሐ 18፥24) ፊት በሃይማኖት መከሰሱ፤ (3) በጴጥሮስ መካዱ (26፥58፡69-75፤ ማር 14፥54፡66-72፤ ሉቃ 22፥54-62፤ ዮሐ 18፥15-18፡25-27)፤ (4) በአይሁድ ሸንጎ መወገዙ (27፥1፤ ማር 15፥1፤ ሉቃ 22፥66-71)፤ (5) የይሁዳ መሞት (27፥3-10)፤ (6) በጲላጦስ ፊት በሕዝብ መከሰሱ (27፥2፡11-14፤ ማር 15፥2-5፤ ሉቃ 23፥1-5፤ ዮሐ 18፥28-38)፤ (7) ወደ ጲላጦስ መልሶ በሰደደው (27፥11-26፤ ማር 15፥6-15፤ ሉቃ 23፥11-25፤ ዮሐ 18፥28—19፥1፡4-16) በሄሮድስ ፊት መከሰሱ (ሉቃ 23፥6-12)፤ (8) የደረሰበት ፌዝ (27፥27-30፤ ማር 15፥16-19፤ ዮሐ 19፥2-3)፤ ከዚህም በኋላ መደብደቡና እንዲሰቀል መደረጉ (27፥31)፤ (9) ወደ ጎልጎታ መሄዱ (27፥32-34፤ ማር 15፥20-23፤ ሉቃ 23፥26-33)፤ (10) ስቅለቱ (27፥35 እና ማብ ይመ)።

የሰው ልጅ በኀያሉ ቀኝ ተቀምጦ በሰማይ
ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ" አለው።
65በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀዶ፣
"በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል ተናግሮአል፤
ከዚህ ሌላ ምን ምስክርነት ያስፈልገ ናል?
በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል መናገሩን
እናንተው ራሳችሁ ሰምታችኋል፤ 66ምን
ይመስላችኋል?" አላቸው።
እነርሱም፣ "ሞት ይገባዋል!" ብለው
መለሱ።
67በዚህ ጊዜ ፊቱ ላይ እየተፉ በጡጫ
መቱት፤ ሌሎቹም በጥፊ እየመቱት፣
68"ክርስቶስ ሆይ፤ ማነው የመታህ? እስቲ
ትንቢት ንገረን!" አሉት።

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

*26፥69-75 ተጓ ምብ — ማር 14፥66-72፤ ሉቃ 22፥55-62፤ ዮሐ 18፥16-18:25-27*

69ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ ግቢ
ውስጥ ተቀምጦ ሳለ አንዲት የቤት ሠራተኛ
ወደ እርሱ ቀርባ፣ "አንተም ከገሊላው
ኢየሱስ ጋር ነበርህ" አለችው።
70እርሱ ግን፣ "ምን እንደምትናገሪ
አላውቅም" በማለት በሁላቸውም ፊት ካደ።
71ከግቢው መውጫ ወደ ሆነው በር
ሲያመራ ሌላዋ ሠራተኛ ተመልክታው፣
በዚያ ለነበሩት ሰዎች፣ "ይህ ሰው ከናዝሬቱ
ኢየሱስ ጋር ነበር" አለች።
72እርሱም በመሐላ ቃል፣ "ሰውየውን አላ
ውቀውም!" ሲል ዳግመኛ ካደ።
73ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በዚያ ቆመው
የነበሩት ሰዎች ቀርበው ጴጥሮስን፣
"አነጋገርህ ስለሚያጋልጥህ፣ በርግጥ
አንተም ከእነርሱ አንዱ ነህ!" አሉት።
74እርሱም እየማለና እየተገዘተ፣ "እኔ
ሰው የሆነ አላውቀውም!" አላቸው።
ወዲያውም ዶሮ ጮኸ። 75በዚህ ጊዜ
ጴጥሮስ፣ "ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ" ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ቃል
ትዝ አለው፤ ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ
መራራ ልቅሶ አለቀሰ።

## ይሁዳ ራሱን ሰቀለ

27 ጠዋት በማለዳ ላይ፣ የካህናት
አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ሁሉ
ኢየሱስ ስለሚገደልበት ሁኔታ ተመካከሩ፤
2ካሰሩትም በኋላ ወስደው ለገዥው ለጲላጦስ
አሳልፈው ሰጡት።
3አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ኢየሱስ እንደ
ተፈረደበት ባየ ጊዜ ተጸጸተ፤ የወሰደውን
ሠላሳ ጥሬ ብር ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ
ሽማግሌዎች መልሶ በመስጠት፣ 4"ንጹሕ
ሰው አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ" አለ።
እነርሱም፣ "ታዲያ እኛ ምን አገባን፤
የራስህ ጉዳይ ነው!" አሉት።
5ስለዚህ ይሁዳ ብሩን በቤተ መቅደስ ውስጥ
ወርውሮ ወጣ፤ ሄዶም ራሱን ሰቅሎ ሞተ።
6የካህናት አለቆች ብሩን እንሥተው፣
"የደም ዋጋ ስለሆነ ወደ መባ ልንጨምረው
አይፈቀድም" አሉ፤ 7ተመካክረውም
ለእንግዶች የመቃብር ስፍራ እንዲሆን
በገንዘቡ የሸክላ ሠሪውን ቦታ ገዙበት።
8ስለዚህም ያ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ "የደም
መሬት" ተብሎ ይጠራል። 9በዚህም በነቢዩ
ኤርምያስ እንዲህ ተብሎ የተነገረው
ተፈጸመ፤ "ለእርሱ ዋጋ ይሆን ዘንድ
የእስራኤል ልጆች የገመቱትን ሠላሳ
ጥሬ ብር ተቀበሉ፤ 10እግዚአብሔርም ባዘዘኝ
መሠረት ለሸክላ ሠሪው ቦታ ከፈሉ።"

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

*27፥11-26 ተጓ ምብ — ማር 15፥2-15፤ ሉቃ 23፥2:3:18-25፤ ዮሐ 18፥29—19፥16*

11በዚህ ጊዜ ኢየሱስ አገረ ገዥው ፊት
ቀረበ፤ አገረ ገዥውም፣ "አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?" በማለት ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ "አንተው እንዳልኸው ነው"
ሲል መለሰለት።
12የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች
ሲከሱት ግን ምንም መልስ አልሰጠም።

26፥65 ማር14፥63
26፥66
ዘሌ24፥16፤
ዮሐ19፥7
26፥67
ማቴ16፥21
26፥68
ሉቃ22፥63-65
26፥75 ቍ34፤
ዮሐ13፥38
27፥1
ማቴ12፥14፤
ማር15፥1፤
ሉቃ22፥66
27፥2
ማቴ20፥19፤
ማር15፥1፤
ሉቃ13፥1፤
ሐሥ3፥13፤
1ጢሞ6፥13
27፥3 ማቴ10፥4፤
26፥14:15
27፥4 ቍ24
27፥5
ሉቃ1፥9:21፤
ሐሥ1፥18
27፥8 ሐሥ1፥19
27፥9 ማቴ1፥22
27፥10 ኤር32፥6-
9፤ ዘካ11፥12:13
27፥11 ማቴ2፥2
27፥12 ማር14፥61

**26፥67 እየተፉ በጡጫ መቱት፤ ... በጥፊ እየመቱት፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ሁለተኛው ደረጃ ነው። በምሽት ከተያዘና ደቀ መዛሙርቱም ትተውት ከሄዱ በኋላ (ቍ 55-57) ኢየሱስ በቀያፋና በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀረበ። ፊቱን ሸፍነው በተደጋጋሚ አፌዙበት፤ ተፉበት፤ ፊቱንም በጥፊ መቱት (የክርስቶስን ሥቃይ ሦስተኛ ደረጃ በተመለከተ 27፥2 እና ማብ ይመ)።

**27፥2 ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ሦስተኛው ደረጃ ነው። በማለዳ ኢየሱስ ከተገረፈና ከደከመ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ጲላጦስ ፊት ለጥያቄ እንዲቀርብ ተደረገ። በርባን ተፈታ (ቍ 21)፤ ኢየሱስ ግን ተገርፎ ይሰቀል ዘንድ ዐልፎ ተሰጠ (ቍ 26፤ የክርስቶስን ሥቃይ አራተኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 26 እና ማብ ይመ)።

**27፥3 ይሁዳም ... ተጸጸተ፤** ይሁዳ የሠራው ኀጢአት ኢየሱስን ለሞት እንደሚያበቃው ተረዳ። በተመሳሳይ ሁኔታ የእኛ ድርጊት በመልካምም ሆነ በክፉ ሌሎችን መንካቱ የማይቀር ነው። እንዲንቀሳቀሱ የምናደርጋቸውን አያሌ ነገሮች ልናቆማቸው አንችልም፤ የእነዚህም ድርጊቶች ክፉና አፍራሽ ውጤት በእኛና በሌሎች ሕይወት ይደርሳል። ጎጂ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጊቶችንና ዕቅዶችን ሁሉ ማስወገድ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

**27፥5 ይሁዳ ... ሞተ፤** ማቴዎስ ይሁዳ፣ «ራሱን ሰቅሎ» እንደ ሞተ ጽፎአል፤ ሐሥ 1፥8 ላይ ደግሞ ወድቆ እንደ ሞተ ተጠቅሶአል። ይሁዳ የሞተው ራሱን ሹል ዕንጨት ላይ በመስቀል ወይም ራሱን በዕንጨት በመውጋት ሳይሆን አይቀርም።

**27፥9 በነቢዩ ኤርምያስ፤** ማቴዎስ በዚህ ስፍራ ትንቢታዊ ትእምርቶችን አንዱን ከኤርምያስ (ኤር 32፥6-9) ሌላውን ከዘካርያስ (ዘካ 11፥12-13) በመውሰድ አያይዞና ዕጥርጥር አድርጎ አቅርቦአል። ከዚያም ቀዳሚውንና ታዋቂውን ነቢይ በምንጭነት ጠቀሰ። ይህም ምንባቦች ከነቢያት መጻሕፍት ሲጠቀሱ ተደጋግሞ የሚፈጸም ልማድ ነው።

13በዚህ ጊዜ ጲላጦስ፣ "ስንት ነገር አቅርበው
እንደ ሚከሱህ አትሰማምን?" አለው።
14እርሱ ግን አገረ ገዥው እስኪገረም
ድረስ ለቀረበበት ክስ አንዲት ቃል እንኳ
አልመለሰም።
15አገረ ገዥው ሕዝቡ በበዓሉ
እንዲፈታላቸው የሚጠይቁትን አንድ
እስረኛ የመፍታት ልማድ ነበረው። 16በዚያን
ጊዜ በዐመፅ የታወቀ በርባን የሚባል እስረኛ
ነበር። 17ሕዝቡ እንደተሰበሰቡ ጲላጦስ፣
"ከበርባንና ክርስቶስ ከሚባለው ከኢየሱስ፣
ማንን እን ድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?"
አላቸው፤ 18ጲላጦስም በቅናት አሳልፈው
እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።
19በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ ሳለ
ሚስቱ፣ "በእርሱ ምክንያት ዛሬ በሕልም
ብዙ ስለተሠቃየሁ፣ በዚያ ንጹሕ ሰው
ላይ ምንም ነገር እንዳታደርግ" የሚል
መልእክት ላከችበት።
20ነገር ግን የካህናት አለቆችና
ሽማግሌዎች በርባን እንዲፈታላቸው
ኢየሱስ ግን እንዲገደል ይለምኑ ዘንድ
ሕዝቡን ያግባቡ ነበር።
21አገረ ገዥውም፣ "ከሁለቱ ማንን
እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?" በማለት
ጠየቀ።
እነርሱም፤ "በርባንን!" በማለት መለሱ።
22ጲላጦስም፣ "ታዲያ ክርስቶስ
የተባለውን ኢየሱስንስ ምን ላድርገው?"
አላቸው።
ሁሉም፣ "ይሰቀል!" አሉ።
23ጲላጦስም፣ "ለምን? ምን ክፉ ነገር
አድርጎአል?" በማለት ጠየቃቸው።
እነርሱ ግን አብዝተው እየጮኹ፣
"ይሰቀል!" አሉ።
24ጲላጦስ ሁኔታው ሽብር ከማስነሣት
በስተቀር ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን
ተመልክቶ፣ "እኔ ከዚህ ሰው ደም ንጹሕ
ነኝ፤ ከእንግዲህ ኀላፊነቱ የራሳችሁ ነው"
በማለት ውሃ አስመጥቶ በሕዝቡ ፊት
እጆቹን ታጠበ።
25ሕዝቡም በሙሉ፣ "ደሙ በእኛና
በልጆቻችን ላይ ይሁን!" ብለው መለሱ።
26በዚህ ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፤
ኢየሱስን ግን ካስገረፈው በኋላ እንዲሰቀል
አሳልፎ ሰጠው።

27፥13 ማቴ26፥62
27፥14 ማር14፥61
27፥15 ዮሐ18፥39
27፥17 ቍ22፤ ማቴ1፥16
27፥19 ቍ24፤ ዘፍ20፥6፤ ዘኍ12፥6፤ 1ነገ3፥5፤ ኢዮ33፥14-16፤ ማቴ1፥20፤ 2፥12፡13፡19፡22፤ ዮሐ19፥13
27፥20 ሐሥ3፥14
27፥22 ማቴ1፥16
27፥24 ቍ4፤ ዘዳ21፡ 6-8፤ መዝ26፥6፤ ማቴ26፥5
27፥25 ኢያ2፥19፤ ሐሥ5፥28
27፥26 ኢሳ53፥5፤ ዮሐ19፥1
27፥27 ዮሐ18፥28፡33፤ 19፥9
27፥28 ዮሐ19፥2
27፥29 ኢሳ53፥3፤ ዮሐ19፥2፡3
27፥30 ማቴ16፥21
27፥31 ኢሳ53፥7
27፥32 ማር15፥21፤ ሉቃ23፥26፤ ሐሥ2፥10፤ 6፥9፤ 11፥20፤ 13፥1፤ ሰብ13፥12

## ኢየሱስ በሮማውያን ወታደሮች እጅ

*27፥27-31 ተጓ ምብ — ማር 15፥16-20*

27ከዚያም የአገረ ገዥው ወታደሮች ኢየ
ሱስን ወደ ገዥው ግቢ ወሰዱት፤ ሰራዊቱንም
ሁሉ በዙሪያው አሰባሰቡ። 28ልብሱን ገፈው
ቀይ ልብስ አጠለቁለት፤ 29እሾኽ ጐንጕነው
አክሊል በመሥራት ራሱ ላይ ደፉበት፤
የሸምበቆ በትር በቀኝ እጁ በማስያዝ በፊቱ
ተንበርክከው፣ "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤
ሰላም ለአንተ ይሁን" በማለት አሾፉበት፤
30ተፉበትም፤ የሸምበቆ በትሩን ከእጁ
ወስደው ራሱ ላይ በሸምበቆው ደጋግመው
ደጋግመው መቱት፤ 31ካሾፉበት በኋላም
ቀዩን ልብስ ገፈው የራሱን መጐናጸፊያ
አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ይዘውት ሄዱ።

## የኢየሱስ መሞት

*27፥45-56 ተጓ ምብ — ማር 15፥33-41፤ ሉቃ 23፥44-49*

32ይዘውትም ሲሄዱ ስምዖን ተብሎ

---

27፥24 **ጲላጦስ፤** የጲላጦስ ትልቁ ነቢአት እውነተኛና ትክክለኛ የሆነውን ነገር እያወቀ ለሥልጣኑ፣ ለማዕረጉና ለግል ጥቅሙ ሲል እንዳላወቀ ሆኖ፣ መገኘቱ ነው። ጲላጦስ ክርስቶስ ምንም ዐይነት በደል እንደሌለበት ያውቃል፡ ይህንንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ተናግሮአል (ቍ 18፤ ዮሐ 19፥4፡6)።

27፥26 **ኢየሱስን ግን ካስገረፈው፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ አራተኛው ደረጃ ነው። (1) በሮማውያን የግርፋት ደንብ መሠረት የሚቀጣው ሰው ልብሱ ተገፎ በምሰሶ ላይ ተዘርግቶ እንዲቆም ወይም ዝቅ ባለ ምሰሶ ላይ እንዲጐነበስ ይደረጋል፤ እጆቹም ይታሰራሉ። መግረፊያው ዐጠር ያለ የዕንጨት እጀታ ባላቸው ጠፍሮች ላይ የታሰሩ ቍርጥራጭ ብረቶች ያሉት ወይም ዐጥንት የተሰካባቸው አያሌ የቆዳ ጠፍሮችን የያዘ ጅራፍ ነው። በዚህ ጅራፍ ግራና ቀኝ የቆሙ ወታደሮች በየቆሙበት አቅጣጫ ሆነው የሚቀጣውን ሰው ጀርባ ይገርፋሉ። ይህም ርምጃ የሚገረፈው ሰው አካል እንዲቈራረጥ፣ የደም ሥሮቹ እንዲበጣጠሱና አንዳንዴም የሰውየው የውስጥ አካል ለከፍተኛ ጉዳት እንዲጋለጥ ያደርጋል። ብዙውን ጊዜ በዚህ ሁኔታ የሚቀጣው ሰው እየተገረፈ ሳለ ይሞታል።

(2) ግርፋት አስከፊ የሥቃይ ቅጣት ነው። ኢየሱስ የራሱን መስቀል ለመሸከም አለመቻሉ ከዚህ አስከፊ ሥቃይ የተነሣ መሆኑ አያጠራጥርም (ቍ 32፤ ሉቃ 23፥26)። እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤ "ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ፡ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን" (ኢሳ 53፥5፤ 1ጴጥ 2፥24)። (የክርስቶስን ሥቃይ አምስተኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 28 እና ማብ ይመ)።

27፥28-29 **ቀይ ልብስ ... እሾኽ ጐንጕነው አክሊል፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ አምስተኛው ደረጃ ነው። ኢየሱስን ፊትተው በሮም ወታደሮች መካከል እንዲቆም አደረጉት (ቍ 27)። ወታደሮቹ ቀይ ልብስ በትከሻው ላይ በማድረግ፣ የሸምበቆ በትር በእጆቹ አስይዘው ከረጃጅም የእሾኽ ቅርንጫፎች አክሊል በማበጀት በራሱ ላይ ደፉበት (ቍ 29)። ወታደሮቹ የእሾኽ አክሊሉን ራስ ቅሉ ላይ በመጫን አሾፉበት፣ ፊቱንም መቱት (ቍ 30-31)። (የክርስቶስን ሥቃይ ስድስተኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 31 እና ማብ ይመ)።

27፥31 **ሊሰቅሉትም ይዘውት ሄዱ፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ስድስተኛው ደረጃ ነው። የመስቀሉ ከባድ ግንድ በክርስቶስ ትከሻ ላይ ታስሮ ነበር። ወደ ጎልጎታ የሚደረገውን አድካሚና አሰልቺ ጕዞ ጀመረ። የመስቀሉ ግንድ ክብደትና የደረሰበት አካላዊ ድካም ኢየሱስን እንዲወድቅ አደረገው። ለመነሣት ሞከረ፤ ይሁን እንጂ አልቻለም። ከዚያም ስምዖን የክርስቶስን መስቀል ይሸከም ዘንድ አስገደዱት። (የክርስቶስን ሥቃይ ሰባተኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 35 እና ማብ ይመ)።

የሚጠራ የቀሬና ሰው አገኙ፤ መስቀሉንም
እንዲሸከም አስገደዱት። [33]ትርጓሜው፣ "የራስ
ቅል ስፍራ" ከሆነው ጎልጎታ ከተባለው ቦታ
ሲደርሱ፣ [34]ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን
ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን ቀምሶ
ሊጠጣው አልፈቀደም። [35]ከሰቀሉትም በኋላ
ዕጣ ጥለው ልብሱን ተካፈሉ፤* [36]በዚያም
ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር። ከራስጌውም፣
[37]"ይህ የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው" የሚል
የክስ ጽሑፍ አኖሩ። [38]ሁለት ወንበዴዎች
አንዱ በቀኙ፣ አንዱ በግራው አብረውት
ተሰቅለው ነበር። [39]መንገድ በላፊዎችም
በንደል እየተሳደቡና ራሳቸውን እየነቀነቁ፣
[40]"ቤተ መቅደስን አፍርሰህ በሦስት ቀን
ውስጥ የምትሠራው፤ እስቲ ራስህን አድን!
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ በል ከመስቀል
ውረድ!" ይሉት ነበር።
[41]የካህናት አለቆችም ከኦሪት ሕግ
መምህራንና ከሽማግሌዎች ጋር ሆነው
እያሾፉበት እንዲህ ይሉ ነበር፤ [42]"ሌሎችን
አዳነ፤ ራሱን ግን ማዳን አይችልም! የእስራኤል
ንጉሥ ከሆነ አሁን ከመስቀል ይውረድ፤
እኛም እናምንበታለን። [43]በእግዚአብሔር ታምኖአል፤ 'የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ' ይል ስለ ነበር
እስቲ ከወደደው አሁን ያድነው!" [44]ከእርሱ
ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎችም እንደዚሁ

27፥33 ዮሐ19፥17
27፥34 ቍ48፤ መዝ69፥21
27፥35 መዝ22፥18
27፥36 ቍ54
27፥38 ኢሳ53፥12
27፥39 መዝ22፥7፤ 109፥25፤ ሰቆ2፥15
27፥40 ቍ42፤ ማቴ4፥3፡6፤ ዮሐ2፥19
27፥42 ዮሐ1፥49፤ 3፥15፤ 12፥13
27፥43 መዝ22፥8
27፥45 አሞ8፥9
27፥46 መዝ22፥1
27፥48 ቍ34፤ መዝ69፥21
27፥50 ዮሐ19፥30
27፥51 ቍ54፤ ዘፀ26፥31-33፤ ዕብ9፥3፡8፤ 10፥19፡20

የሰድብ ናዳ ያወርዱበት ነበር።

## የኢየሱስ መሞት

*27፥45-56 ተጓ ምብ — ማር 15፥33-41፤ ሉቃ 23፥44-49*

[45]ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
[46]በዘጠኝ ሰዓት ገደማ፣ ኢየሱስ ድምፁን ከፍ
አድርጎ፣ "ኤሎሄ! ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ?"
እያለ ጮኸ፤ ትርጓሜውም "አምላኬ፤
አምላኬ፤ ለምን ተውኸኝ?" ማለት ነው።
[47]በዚያ ቆመው ከነበሩት አንዳንዶቹ ጩኸቱን
ሲሰሙ፣ "ኤልያስን እየተጣራ ነው!" አሉ።
[48]ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጦ ሰፍነግ
በመውሰድ የከመጠጠ ወይን ጠጅ ውስጥ
ነከረው፤ ሰፍነጉንም በሸምበቆ ዘንግ ጫፍ
ላይ በማድረግ እንዲጠጣው ለኢየሱስ አቀረ
በለት። [49]የቀሩት ግን፣ "ተዉት፤ እስቲ
ኤልያስ መጥቶ ሲያድነው እናያለን!" አሉ።
[50]ኢየሱስ እንደ ገና ከፍ ባለ ድምፅ
ጮኸ፤ መንፈሱንም አሳልፎ ሰጠ።
[51]በዚያን ጊዜ የቤተ መቅደስ መጋረጃ

*27፥35 ጥቂት የጥንት ቅጆች "በነቢዩ ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ የተባለው ይፈጸም ዘንድ" የሚል አላቸው

**27፥35 ከሰቀሉትም፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ሰባተኛው ደረጃ ነው። በጎልጎታ የመስቀሉ ግንድ በምድር ላይ እንዲጋደም ተደረገ፤ ኢየሱስንም በግንዱ ላይ አስተኙት። እጆቹ ግራና ቀኝ በግንዱ ላይ ተዘረጉ፤ ከዚያም ከባድና ጠፍጣፋ የብረት ምስማር በእጆቹ ወይም በእጆቹ አንጓ ላይ መጀመሪያ በቀኝ እጁ፣ ቀጥሎም በግራ እጁ ላይ መትተው ከግንዱ ጋር ቸነከሩት። ከዚያም ክርስቶስ በግንዱ ላይ እንደ ተቸነከረ በገመድ ወይም በመስላል እንዲነሣ ተደረገ፤ የመስቀሉ ግንድ ከቋሚው ግንድ ጋር ተያይዞ ወይም በምስማር ተመትቶ ነበር፤ የክርስቶስን አካል ደግፎ የያዘው ዕንጨትም በላዩ ላይ ተጣብቆአል። በመጨረሻም እግሮቹ ወደ ታች እንዲዘረጉ ተደረገ፤ በትልቅ ምስማርም ተቸነከሩ (የክርስቶስን ሥቃይ ስምንተኛ ደረጃ በመተለከተ ቍ 39 እና ማብ ይመ)።

**27፥39 በንደል እየተሳደቡና፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ስምንተኛው ደረጃ ነው። ኢየሱስ አሁን በደም የተነከረ፣ ቍስል በቍስል የሆነና ለሕዝብ እይታ የተጋለጠ አሳዛኝ ሰው ሆኖአል። በመላ አካሉ ላይ የሥቃይ ጣር፣ በእጆቹ ላይ ጕዳትና ዝለት፣ ከፍተኛ የሰውነት መሸማቀቅና በጀርባው ላይ ከደረሰው ግርፋት የተነሣ የቈዳ መላላጥ ደርሶበት ነበር። ከዚያም የባሰ ሌላ ሥቃይ ይሰማው ጀመር፤ ይኸውም ልቡን ፈሳሽ ደም ዐፍኖ ባስጨነቀበት ጊዜ ደረቱን እየወጋ ያስቸገረው ከፍተኛ ሥቃይ ነበር። በእጅጉ ተጠማ (ዮሐ 19፥28)፤ በመስቀሉ አጠገብ የሚያልፉ መንገደኞች የሚሳደቡት ስድብና የሚያወርዱት ርግማን ይታወቀው ነበር (ቍ 39-44)። (የክርስቶስን ሥቃይ ዘጠነኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 46 እና ማብ ይመ)።

**27፥46 ለምን ተውኸኝ?** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ዘጠነኛው ደረጃ ነው። እነዚህ ቃላት ክርስቶስ ለጠፋው ዓለም የተሠቃየውን ሥቃይ ከፍተኛ ደረጃ ያሳያሉ። በአረማይክ ቋንቋ፣ «አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ» ብሎ ኢየሱስ ክርስቶስ መጮኹ፣ የኀጢአተኛ ሰው ተተኪ ሆኖ ከእግዚአብሔር የተለየበትን ሁኔታ ያረጋግጣል። በዚህ ጊዜ ይህ ጩኸት ሐዘን፣ ጭንቀትና ጣር ከከፋ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ያመለክታል። እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ (ኢሳ 53፥5)፤ «ለብዙዎች ቤዛ» ሊሆንም ራሱን ሰጠ (20፥28፤ 1ጢሞ 2፥6)። «ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው» (2ቆሮ 5፥21)፤ እኛ ተትተን እንዳንቀር እርሱ ተትቶ ሞተ (ከመዝ 22 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ እኛ በክርስቶስ ሥቃይ ቤዛነትን አግኝተናል (1ጴጥ 1፥19 ይመ)። (የክርስቶስን ሥቃይ ዐሥረኛ ደረጃ በተመለከተ ቍ 50 እና ማብ ይመ)።

**27፥50 ኢየሱስ እንደ ገና ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ፤** ይህ የክርስቶስ ሥቃይ ዐሥረኛው ደረጃ ነው። ክርስቶስ የመጨረሻ ቃሉን፣ «ተፈጸመ» (ዮሐ 19፥30) በማለት ከፍ ባለ ድምፅ አሰማ። ይህ ጩኸት የሥቃዩን መጨረሻና የቤዛነት ሥራው መፈጸሙን ያመለክታል። የኀጢአታችን ዕዳ ሙሉ በሙሉ ተከፈለ፤ የድነት ዕቅድም ጽኑ መሠረት አገኘ። ከዚህም በኋላ፣ «አባት ሆይ፤ መንፈሴን በእጅህ እሰጣለሁ» (ሉቃ 23፥46) በማለት ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻ ጸሎቱን አቀረበ። (የክርስቶስን ሥቃይ የመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተ 26፥37 እና ማብ ይመ)።

**27፥51 የቤተ መቅደስ መጋረጃ ... ተቀደደ፤** የቤተ መቅደሱ መጋረጃ መቀደድ (ዘፀ 26፥33 እና ማብ ይመ) አሁን ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት ለመግባት መንገድ መከፈቱን ያመለክታል። ቅድስቱንና ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚለየው መጋረጃ ወደ እግዚአብሔር ሀልዎት የሚያስገባውን መንገድ ዘግቶት ነበር። በክርስቶስ ሞት አማካይነት፣ መጋረጃው ተወገደ፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን (ይኸውም የእግዚአብሔር ሀልዎት) የሚያስገባው መንገድም በክርስቶስና በሚያድነው ቃሉ ለሚያምኑ ሁሉ ተከፈተ (ከዕብ 9፥1-14፤ 10፥19-22 ጋር ያነጻጽሩ)።

ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተቀደደ፤ ምድር
ተናወጠች፤ ሀለቶችም ተሰነጣጠቁ፤
52መቃብሮች ተከፈቱ፤ አንቀላፍተው
የነበሩትም ብዙዎች ቅዱሳን ተነሡ፤
53ከመቃብርም በመውጣት ከኢየሱስ
ትንሣኤ በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው
ለብዙዎች ታዩ።
54የመቶ አለቃውና አብረውት ኢየሱስን
ይጠብቁት የነበሩት የመሬት መናወጡንና
የሆነውን ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ እጅግ ፈርተው፤
ይህስ "በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ
ነበር!" አሉ። 55ከገሊላ የመጡና ኢየ ሱስን
በሚያስፈልገው ነገር ለማገልገል የተከተሉት
ብዙ ሴቶች ሁኔታውን ከርቀት እየተመለከቱ
በአካባቢው ነበሩ። 56ከእነርሱም መካከል
ማርያም መግደላዊት፣ ማርያም የያዕቆብና
የዮሴፍ እናት እንዲሁም የዘብዴዎስ ልጆች
እናት ነበሩ።

### የኢየሱስ መቀበር

*27፥57-61 ተጓ ምብ — ማር15፥42-47፤ ሉቃ 23፥50-56፤ ዮሐ 19፥38-42*

57ምሽት ላይ ዮሴፍ የሚባል ሀብታም ሰው
ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱ ራሱም የኢየሱስ
ደቀ መዝሙር ነበረ። 58ጲላጦስ ፊት ቀርቦ
የኢየሱስን በድን ለመነው፤ ጲላጦስም እንዲ
ሰጠው አዘዘ። 59ዮሴፍም በድኑን ወስዶ
በንጹሕ የበፍታ ጨርቅ ከፈነው፤ 60ለራሱ
ከዐለት አስፈልፍሎ ባዘጋጀው መቃብር
ውስጥ አኖረው፤ ከዚያም ትልቅ ድንጋይ
አንከባሎ የመቃብሩን በር ዘግቶ ሄደ። 61በዚህ
ጊዜ ማርያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም
ከመቃብሩ ትይዩ ተቀምጠው ነበር።

### የመቃብሩ ጥበቃ

62በማግሥቱ፣ ከሰንበት ዝግጅት በኋላ
ባለው ቀን፣ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን
ጲላጦስ ፊት ቀርበው እንዲህ አሉት፤
63"ክቡር ሆይ፤ ያ አሳች በሕይወት ሳለ፣
'ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ' ያለው ትዝ
ብሎናል፤ 64ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ እስ
ከሬኑን ሰርቀው ለሕዝቡ፣ 'ከሙታን
ተነሥቶአል' ብለው እንዳያስወሩ መቃብሩ
እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ እንዲጠበቅ
ትእዛዝ ስጥልን፤ አለዚያ የኋለኛው ስሕተት
ከፊተኛው የባሰ ይሆናል!"
65ጲላጦስም፣ "ጠባቂዎች አሏችሁ፤
ሂዱና በምታውቁት መንገድ አስጠብቁ"
አላቸው። 66እነርሱም ሄደው መቃብሩን
በማኅተም አሽገው ጠባቂ አቆሙበት።

27፥53 ማቴ4፥5
27፥54 ቍ36፤ማቴ4፥3፥ 17፥5
27፥55 ሉቃ8፥2፡3
27፥56 ማር15፥47፥ ሉቃ24፥10፤ ዮሐ19፥25
27፥60 ማቴ27፥66፤ 28፥2፤ ማር16፥4፤ ሐሥ13፥29
27፥63 ማቴ16፥21
27፥64 ማቴ28፥13
27፥65 ቍ66፤ ማቴ28፥11
27፥66 ቍ60፤ ዳን6፥17፤ ማቴ28፥2፡11
28፥1 ማቴ27፥56፤ ሉቃ8፥2
28፥2 ማቴ27፥51፡60፤ ዮሐ20፥12፤ ሐሥ5፥19
28፥3 ዳን7፥9፥ 10፥6፤ ማር9፥3፤ ዮሐ20፥12
28፥5 ቍ10፤ ማቴ14፥27
28፥6 ማቴ16፥21
28፥7 ቍ10፡16፥ ማቴ26፥32
28፥9 ዮሐ20፥14-18

### የኢየሱስ ከሙታን መነሣት

*28፥1-8 ተጓ ምብ — ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10*

28 ሰንበት ካለፈ በኋላ፣ በሳምንቱ
መጀመሪያ ቀን ጎሕ ሲቀድ፣ ማርያም
መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም መቃብሩን
ሊያዩ ሄዱ።
2በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ
ሆነ፤ የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ ወደ
መቃብሩ በመሄድ ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ
ላይ ተቀመጠበት፤ 3መልኩ እንደ መብረቅ
ብሩህ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር።
4ጠባቂዎቹ መልአኩን ከመፍራት የተነሣ
ተንቀ ጠቀጡ፤ እንደ በድንም ሆኑ።
5መልአኩም ሴቶቹን እንዲህ አላቸው፤
"አትፍሩ፤ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደም
ትፈልጉ አውቃለሁና፤ 6እርሱ በዚህ የለም፤
እንደ ተናገረው ተነሥቶአል፤ ኑና ተኝቶ
በት የነበረውን ቦታ እዩ። 7አሁንም ፈጥና
ችሁ ሂዱና ለደቀ መዛሙርቱ፣ 'ከሙታን
ተነሥቶአል፤ ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ
ይሄዳል፤ በዚያ ታዩታላችሁ' ብላችሁ
ንገሯቸው። እንግዲህ ነግሬአችኋለሁ!"
8ሴቶቹም በፍርሀትና በደስታ ተሞልተው
ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር በፍጥነት
እየሮጡ የመቃብሩን ስፍራ ትተው ሄዱ።
9ወዲያው ኢየሱስ አገኛቸውና፣ "ሰላም

**27፥52 ብዙዎች ቅዱሳን ተነሡ፤** የዚህ ሁነት አስፈላጊነት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በዳግም ምጽአቱ የክብር ትንሣኤን እንደምናገኝ የሚያመለክት ትንቢታዊ ማረጋገጫ መሆኑ ነው:: የእርሱ ትንሣኤ የሞትን ድል መሆን ያረጋግጣል (1ቆሮ 15፥50-58፤ 1ተሰ 4፥14 ይመ)::

**28፥6 እርሱ ... ተነሥቶአል፤** የኢየሱስ ትንሣኤ ከወንጌል ዋና ዋና እውነቶች አንዱ ክፍል ነው (1ቆሮ 15፥1-8):: የክርስቶስ ትንሣኤ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው? (1) ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ማረጋገጫ ነው (ዮሐ 10፥17-18፤ ሮሜ 1፥4)፤ (2) የቤዛነት ሞቱ በቂ መሆኑን ያረጋግጣል (ሮሜ 6፥4፤ 1ቆሮ 15፥17)፤ (3) የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነተኛነት ያረጋግጣል (መዝ 16፥10፥ ሉቃ 24፥44-47፤ ሐሥ 2፥31)፤ (4) ክፉዎች ወደ ፊት እንደሚፈረድባቸው ያረጋግጣል (ሐሥ 17፥30-31)፤ (5) የክርስቶስ ስጦታ ለሆነው ለመንፈስ ቅዱስ፥ ለሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወትና (ዮሐ 20፥22፤ ሮሜ 5፥10፥ 1ቆሮ 15፥45) ለአማኙ ሲል ለሚፈጽመው ሰማያዊ የምልጃ አገልግሎቱ (ዕብ 7፥23-28) መሠረት ነው፤ (6) አማኞች ወደ ፊት የሚኖሩቸውን ሰማያዊ ርስት (1ጴጥ 1፥3-4) እንዲሁም ጌታ ተመልሶ ሲመጣ ከሞት መነሣታቸውንና መለወጣቸውን ያረጋግጣል (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፥ 1ተሰ 4፥14 ... ይመ)፤ (7) በየዕለቱ ባለን ተመክሮ የክርስቶስ ህልዎትና ኀይል በኃጢአት ላይ ድል እንዲኖረን ያበቁናል (ገላ 2፥20፥ ኤፌ 1፥18-20)።

**28፥9 ኢየሱስ አገኛቸውና፤** ትንሣኤ ታሪካዊነቱ በሚገባ ተረጋግጦአል:: ከትንሣኤው በኋላ ክርስቶስ ለሐዋርያትና ለብዙዎች ተከታዮቹ በመታየትና እነርሱንም በማነጋገር አርባ ቀን በምድር ላይ ቈይቶአል። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ የታየው ለሚከተሉት ነው:- (1) ለመግደላዊት ማርያም (ዮሐ 20፥11-18)፤ (2) ከመቃብሩ ደርሰው ለተመለሱት ሴቶች (ቍ 9-10)፤ (3) ለጴጥሮስ (ሉቃ 24፥34)፤ (4) ለሁለቱ የኤማሁስ መንገደኞች (ሉቃ 24፥13-32)፥ (5) ከቶማስ በስተቀር ለሁሉም ደቀ መዛሙርትና አብረዋቸው ለነበሩት ለሌሎች (ሉቃ 24፥36-43)፥ (6) ከአንድ ሳምንት በኋላ እሑድ ምሽት ላይ ለደቀ መዛሙርቱ በሙሉ (ዮሐ 20፥26-31)፤

ለእናንተ ይሁን!" አላቸው። እነርሱም ወደ
ኢየሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።
10ኢየሱስም፣ "አትፍሩ፤ ሂዱና ወደ ገሊላ
እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሯቸው፤ በዚያ
ያዩኛል" አላቸው።

## የጠባቂዎች ምስክርነት

11ሴቶቹ በመንገድ ላይ ሳሉ፣ ከጠባቂዎቹ
ጥቂቶቹ ወደ ከተማ በመሄድ የሆነውን ሁሉ
ለካህናት አለቆች አወሩላቸው። 12የካህናት
አለቆችም ከሽማግሌዎች ጋር ተሰብስበው
ተማከሩ፤ ለወታደሮቹ በቂ ገንዘብ በመስ
ጠት 13እንዲህ አሏቸው፤ " 'ተኝተን ሳለን
ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት'
በሉ፤ 14ይህ ወሬ በገዥው ዘንድ ቢሰማ እንኳ፣
እኛ እናስረዳዋለን፤ ምንም ክፉ ነገር እንዳ
ይደርስባችሁ እናደርጋለን።" 15ወታደሮቹም
ገንዘቡን ተቀብለው እንደ ታዘዙት አደረጉ።
ይህም ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁዶች
ዘንድ በሰፊው እንደተሰራጨ ነው።

## ታላቁ ተልእኮ

16ከዚያም በኋላ አንዱ ደቀ መዛሙርት
በገሊላ ወዳለው ኢየሱስ ወዳመለከታቸው
ተራራ ሄዱ። 17ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ ጥቂቶች
ግን ተጠራጠሩ። 18ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ
ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ "ሥልጣን
ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ 19ስለዚህ
ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና
በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ
መዛሙርት አድርጓቸው፤ 20የዘዝኋችሁንም

28፥10 ማቴ12፥50፤ 25፥40፤ ማር3፥34፤ ዮሐ20፥17፤ ሮሜ8፥29፤ ዕብ2፥11-13፥17
28፥11 ማቴ27፥65፥66
28፥13 ማቴ27፥64
28፥14 ማቴ27፥2
28፥16 ቍ7፥10፤ ማቴ26፥32
28፥18 ዳን7፥13፥14፤ ሉቃ10፥22፤ ዮሐ3፥35፤ 13፥13፤ 17፥2፤ 1ቆሮ15፥27፤ ኤፌ1፥20-22፤ ፊል2፥9፥10
28፥19 ኢሳ49፥6፤ ማር16፥15፥16፤ ሉቃ24፥47፤ ሐሥ1፥8፤ 2፥38፤ 8፥16፤ 14፥21፤ ሮሜ6፥3፥4፤ ገላ3፥27፤ ቈላ2፥12
28፥20 ዘዳ31፥6፤ 1ነገ8፥57፤ ሐጌ1፥13፤ ማቴ13፥39፤ 18፥20፤ 24፥3፤ ዮሐ14፥26፤ ሐሥ2፥42፤ 18፥10

(7) በገሊላ ባሕር አጠገብ ለሰባት ደቀ መዛሙርት (ዮሐ 21፥1-25)፤ (8) በገሊላ ለአምስት መቶ ሰዎች (ቍ 16-20ን ከ1ቆሮ 15፥6 ጋር ያወዳድሩ)፡ (9) ለያዕቆብ (1ቆሮ 15፥7)፤ (10) ታላቁን ተልእኮ ለተቀበሉት ደቀ መዛሙርት (ቍ 16-20)፤ (11) በዕርገቱ ጊዜ ለነበሩት ሐዋርያት (ሐሥ 1፥3-11) እና (12) ለሐዋርያው ጳውሎስ (1ቆሮ 15፥8)።

**28፥10 አትፍሩ፤** እነዚህ ሴቶች መፍራት የሌላባቸው ለምንድን ነው? የሚከተለው የመልአኩ መልስ ለጥያቄው መልስ ይሆናል፤ «ኢየሱስን እንደምትፈልጉ በውቃለሁና» (ቍ 5)። ዓለም ጌታ ኢየሱስን በጠላውና በሰቀለው ጊዜ ሴቶቹ የኢየሱስ ታማኝ ወዳጆች በመሆን ጸኑ። ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ፍቅሩን፥ ድንቱንና ቅዱስ ቃሉን በሚቃወመው ዓለም ውስጥ ያሉ አማኞች ለእርሱ በታማኝነት ከጸኑ፣ የሚፈሩበት ምክንያት አይኖራቸውም። ዮሐንስ ይህንን እውነት በ1ዮሐ 2፥28 ላይ እንዲህ በማለት ገልጾታል፤ «እንግዲህ ልጆች ሆይ፥ እርሱ ሲገለጥ ድፍረት እንዲኖረን፣ በሚመጣበትም ጊዜ በፊቱ እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።»

**28፥18 ሥልጣን ሁሉ፤** የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓለም ሁሉ ወንጌልን ለማወጅ ሥልጣንና ኀይል እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸዋል (ቍ 19-20)። ነገር ግን የአብን ተስፋ ማለትም በጰንጠቈስጤ ዕለት የሚወርደውን የመንፈስ ቅዱስን ኀይል እንዲጠብቁ የተሰጣቸውን የኢየሱስን ትእዛዝ መፈጸም ነበረባቸው። ወደ አሕዛብ ስንሄድ አብሮን የሚሆነውን የሐዋርያት ሥራ 1፥8 ተስፋን ማግኘት የምንችለው በመጀመሪያ በሐዋርያት ሥራ 1፥4 ላይ የተሰጠውን መመሪያ ከጠበቅን ብቻ ነው (ሉቃ 24፥47-49፥ ሐሥ 1፥8፤ 2፥4 ይመ)።

**28፥19 ሂዱና ... እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤** እነዚህ ቃላት የትኛውም ትውልድ ውስጥ ለሚገኙ የኢየሱስ ተከታዮች ሁሉ ከክርስቶስ የተሰጡ ታላቅ ተልእኮ ናቸው። ቃላቱ የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ሥራ ዐላማ፣ ኀላፊነትና ተልእኮ የሚመለከቱ ናቸው፡ (1) ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስና ሐዋርያት የገለጡትን አዲስ ኪዳን መሠረት በማድረግ ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ወንጌልን መስበክ አለባት (ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)። ይህ ተግባር ሚሲዮናውያንን ወደ እያንዳንዱ አገር የመላክን ተቀዳሚ ኀላፊነት ያካትታል (ሐሥ 13፥1-4)።

(2) የወንጌል ስብከት የሚከተሉትን ማእከል ያደረገ መሆን አለበት፤ ንስሓንና የኀጢአት ስርየትን (ሉቃ 24፥47)፥ «የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ» የመቀበል ተስፋን (ሐሥ 2፥38)፣ የኢየሱስን ከሰማይ መምጣት እየተጠባበቁ ሳለ (ሐሥ 3፥19-20፤ 1ተሰ 1፥10) ከዚህ ጠማማ ትውልድ መለየት እንደሚገባ ምክር መስጠትን (ሐሥ 2፥40)።

(3) ዋናው ዐላማ የክርስቶስን ትእዛዞች የሚጠብቁ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው። በዚህ ምንባብ ውስጥ ቀጥተኛ የሆነ ትእዛዝ ሰጪ ክፍል ይህ ብቻ ነው። ክርስቶስ የወንጌል ሥርጭትና ሐዋርያዊ ምስክርነት ሰዎችን ወደ እምነት ውሳኔ የሚያደርሱ ብቻ ናቸው የሚል ሐሳብ አልሰጠም። መንፈሳዊ ተግባራት የቤተ ክርስቲያን አባላትን ቍጥር በማብዛት ላይ ማተኮር የለባቸውም፥ ማተኮር ያለባቸው ግን ከዓለም ራሳቸውን የለዩ፣ የክርስቶስን ትእዛዝ የሚጠብቁ እንዲሁም እርሱን በፍጹም ልባቸው፥ ሐሳባቸውና ፈቃዳቸው (ከዮሐ 8፥31 ጋር ያነጻጽሩ) የሚከተሉትን ደቀ መዛሙርት በማፍራት ላይ ነው።

(4) ከዚህም በላይ ልብ መባል ያለበት፣ ኅብረተሰቡን ክርስቲያናዊ ባህልን እንዲከተል ማድረግ ወይም ዓለምን መውረስ ሳይሆን፣ በጠፉ ወንዶችና ሴቶች ላይ እንድናተኩር ክርስቶስ ያዘዘን መሆኑ ነው። ያመኑ ሁሉ የዓለምን ክፋት በማጋለጥ (ኤፌ 5፥11)፣ ክፉ ከሆነው ከአሁኑ የዓለም ሥርዐትና ከኢግብረገባዊነቱ ተለይተው መውጣት አለባቸው (ሮሜ 13፥12፤ 2ቆሮ 6፥14 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ «የአማኞች መለየት» በሚል ርእስ የቀረበውን የትከሩረት ጽሑፍ ይመ)።

(5) በክርስቶስና በወንጌሉ የሚያምኑ ሁሉ በውሃ «መጠመቅ» አለባቸው። ይህም ኢግብረገባዊነትን፣ ዓለምንና የራሳቸውን የኀጢአታዊ ተፈጥሮ ለማውገዝና ለመተው የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲሁም ለክርስቶስና ለመንግሥቱ ዐላማ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ የሰጡበትን ሁኔታ ይወክላል (ሐሥ 22፥16 እና ማብ ይመ)።

(6) በመንፈስ ቅዱስ ሀልዎትና ኀይል አማካይነት ክርስቶስ ከታማኝ ተከታዮቹ ጋር አብሮ ይሆናል (ከቍ 20፤ 1፥23፥ 18፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። ለሕዝብ ሁሉ ለመመስከር መሄድ ያለባቸው ከላይ ኀይልን ከለበሱ በኋላ ብቻ ነው (ሉቃ 24፥49፤ ሐሥ 1፥8 እና ማብ ይመ)።

**28፥20 ከእናንተ ጋር ነኝ፤** ይህ ሐረግ ያዘለው ሐሳብ የጠፉትን ለመመለስና ለጽድቅ መንገዱ እንዲገዙ ለማስተማር ለቆሙት ክርስቶስ ያረጋገጠው ተስፋ ነው። ኢየሱስ ተነሥቶአል፤ አሁንም ሕያው በመሆን

ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እነም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"

ለእያንዳንዳቸው ለልጆቹ ያስባል። በመንፈስ ቅዱስና (ዮሐ 14፥16፡26) በቃሉ (ዮሐ 14፥23) አማካይነት እርሱ ከእናንተ ጋር ነው። ያላችሁት በድካም፣ በድኽነት፣ በውርደትና በዝቅተኝነት ሁኔታ ቢሆንም፣ እርሱ ለእናንተ ይጠነቀቃል፤ በየዕለቱ በሕይወታችሁ በሚገጥማችሁ ማንኛውም ዐይነት መከራና ትግል ውስጥ በጥንቃቄ ይጠብቃችኋል፤ የሚያስፈልጋችሁን በቂ ጸጋና (2ቆሮ 12፥9) ወደ ቤቱ እንድትገቡ የሚረዳችሁን ሀልዎቱን ይሰጣችኋል (18፥20፤ ሐሥ 18፥10)። ይህ ለማንኛውም ፍርሀት፣ ጥርጥር፣ ችግር፣ የልብ ሕመምና ተስፋ መቍረጥ ክርስቲያን የሚሰጠው መልስ ነው።